# ሽማግሌውና ባህሩ

ትርጉም- መስፍን አለማየሁ



© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት 1991

ስልክ ቁ. 11 18 25
11 31 90
ፖ.ሣ.ቁ 12684
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የውስጥ ሥዕል ጥበበ ተረፈ
የሽፋን ሥዕል መስፍን ሃብተማርያም

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


መግቢያ ........................................ i

ደምሴ ፅጌ

ንፁህ ብርሃናማ ሥፍራ ........................................ 1

ኧርነስት ሄሚንግዌይ

የጕራዶው ቅርፅ ........................................ 11

ሆርዌ ሉዊ ቦርሄስ

እናት ........................................ 22

ጌ.ደ. ሞፖሣ

አባወራው ........................................ 37

ሚኻኤል ሾሎኾቭ

አንድ በርሜል አሞንቴያዶ ........................................ 54

ኤድጋር አለን ፖ

ሣሙና ብቻ ........................................ 65

ሄርናንዶ ቴሌዝ

ሽማግሌውና ባህሩ ........................................ 76

ኧርነስት ሄሚንግዌይ

መውጫ ........................................ 189

# መግቢያ

213

የስነ-ፅሑፍ ትርጉም በሌላ ቋንቋ፤ በሌላ ባህል ውስጥ የተፃፈን ሀሳብ፣ ስሜትና ውበት በራስ ቋንቋ ወደራስ ባህል ለመመለስ የሚደረግ ጥረት አይደል? . . . የስነ-ፅሑፍን ትርጉም ከሌላው ዓይነት ትርጉም የተለየና አስቸጋሪ የሚያ ደርገውም ይሄው ባህሪው ይመስለኛል::

ባገራችን የተለያዩ ድርሰቶች እየተተረጐሙ ገበያ ላይ መዋል ከጀመሩ ሰንበት ብለዋል:: ይሄ ደግሞ የሚያኮራ እንጂ የሚያሳፍር አይደለም፣ እነሰ የሚባል እንጂ በዛ ተብሎ የሚጮህበትም አይደል:: ለመሆኑ መቼ ነው ጥበብ ለሰው ዘር በዝቶ የምታውቀው?

እርግጥ የትርጉም ጉዳይ ሲወሳ ምን ዓይነት ድርሰት? ምን ዓይነት ትርጉም? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ:: ለኔ መልሱ ሁሉም ዓይነት ድርሰት፣ ሁሉም ዓይነት ትርጉም የሚል ነው:: /ይሄ እኮ የተርጓሚውም የአንባቢውም መብት ይመስለኛል/

ምንም ይሁን ምን ተጨንቆና ተጠቦ የተረጐመውን መጽሐፍ ይበልን ወደ ገበያ ብቅ የሚለውስ ተርጓሚ ለጥያቄዎቹ የአቅሙን መልስ መስጠቱ አይደል?...

ምን ዓይነት ትርጉም ተብሎ ሲጠየቅ ምን ዓይነት ትርጓሚስ መባሉ ይቀራል? . . . ሁለቱንም ቋንቋዎች ጠንቅቆ ሳያውቅ የሚተረጉም አለ፤ ሁለቱንም ቋንቋዎች ጠንቅቆ በማወቁ ብቻ የስነ-ፅሑፍን ባህርያት ሳይገነዘብ የሚተረጉምም አለ፤ የመጥለፊያ ቋንቋውን ብቻ በማወቁ የሚተረጉምም አለ:: እነዚህ ሁሉ ተርጓሚዎች በወቅቱ የትርጉም ደቦ ውስጥ እንደልብ ታይተዋል::

ሁለቱን ቋንቋዎችና የበቀሉበትን ባህል ከስነ - ፅሑፍ ባህርያት ጋር በውል የሚያውቁ ተርጓሚዎች እንደነዚያ ባይበዙም በጥቂቱ ታይተዋል::

መስፍን አለማየሁ እንግዳ ተርጓሚ አይደለም፡፡ ከዚህ በፊት ቢተረጉመው የጥበብ ጥማታችንን ያረካሉ ብሎ ያመነባቸውን ክላሲክና ዘመናዊ አጫጭር ታሪኮችንና በዘላለማዊ ነት መድረክ ላይ ጠጥቶ የማያልቅለትን የሼክስፒርን «የቬኒሱ ነጋዴ»ን በውብ አማርኛ ተርጉሞ በፍቅር አቀብሎናል፡፡[*]

ዝቅተኛ የጥበብ ዋጋ ያላቸው ወይም ጥበብ የሚለው ቃል ጨርሶ የማይጠጋቸው ግልብ ድርሰቶች በብዛት የመተርጎማቸውን ያህል በውበታቸው፣ በጥልቀታቸውና በወጥነታቸው በዘላለማዊነትን የተቀዳጁ የሥነ- ፅሑፍ ሥራዎችም በብዛትና በጥራት ይተረጎሙ ባይ ነው መስፍን፡፡ የህይወትን ላዩን ሳይሆን ውስጡን፣ መምሰሉን ሳይሆን እቅጩን፣ አጡጥተው የሚያሳዩ፣ ለዕለት ሳይሆን ዘላለሙን ከኛ ጋር የሚኖሩ መፃሕፍት መተርጎም አለባቸው ባይ ነው . . . ለዚህም ይመስለኛል ፅናትና ድክመት፣ ጥላቻና ፍቅር፣ መሆንና ምንነት፣ ክህደትና እምነት፣ ቂምና በቀልን የመሳሰሉ የሰው ልጅ ፈተናዎች በጥልቀት የተገለፀባቸውን አጫጭር ታሪኮችና አንድ ረጅም አጭር ልቦለድ /NOVELLA/ ለመተርጎም ቆርጦ የተነሳው፡፡

በስድስት የተለያዩ ደራሲያን የተፃፉ ድርሰቶችን መርጦ በአንድ ቅፅ አዳብሎ ለአንባቢ ማቅረብ፣ ቀርቦ ሲታይ የማይሰማውን ያህል ቀላል አይደለም፡፡ የመድብል ሥራ ልክ እንደወጥ ስራ ህብር እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ጥራዝ መጠቃለል፣ በአንድ ጣሪያ ስር እንደማደር ነውና በጥራዙ ውስጥ የሚጠቃለሉት ስራዎች ስምም ሊሆኑ ይገባል፡፡ የሚለያዩ ቢሆኑ ድርሰቶችን መርጦ ያዳበላቸው ሰው በልዩነታቸው አንድነት መፍጠሩን ማሳየት አለበት፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ከምንተዋወቃቸው ታላላቅ ደራሲያን መካከል ኧርነስት ሄሚንግዌይ እና ሚካኤል ሾሎኾቭ ለዓለም የስነ- ፅሑፍ ዕድገት ባበረከቱት አስተዋፅኦ በቀላሉ የማይገኘውን የኖቤልን ሽልማት ተቀብለዋል፡፡

---

[*] መስፍን አለማየሁ ከዚህ መግቢያ በኋላ ከሼክስፒር ስራዎች መካከል «ንጉስ ሊር»ን ተርጉሟል፡፡

አሜሪካዊው ኤድጋር አለን ፖ አጭር ታሪክ በስነ-ፅሑፍ ዕድገት ውስጥ ሲኖረው የሚገባውን ቦታና ባህርዩን በድርሰቶቹና በንድፈ ሀሳቦቹ ተንትኖ ከማሳወቁም በላይ የመጀመሪያው የወንጀል ነክ ታሪክ /Crime Story/ ፈጣሪም እንደሆነ ይነገርለታል:: ፈረንሳዊው ጊ.ደ.ሞፓሳም የተለያዩ የአጭር ልቦለድ ታሪክ አፃፃፍ ዘዴዎችን በእውቅ ድርሰቶቹ አማካይነት አስተዋውቋል::

ቦርሄስና ቱሊዝ እውቅ የላቲን አሜሪካ ደራሲያን ሲሆኑ በዚህ የስነ-ፅሑፍ ዘርፍ፣ ሦስተኛው ዓለም ከደረጁት አገሮች እኩል ሊሰለፍ መቻሉን አረጋግጠዋል::

የእነዚህኑ ታላላቅ ደራሲያን ስም ሳይ ካሉን ጥቂት ድንቅ ተርጓሚዎች አንዱ ማዕበል የሚያናውጠውን ባህር ብቻውን ሊያቋርጥ ሞክሮ እማህሉ ላይ ሰምጦ ሲቀር የማይ መስሎኝ ለመስፍን በጣም ሰግቼለት ነበር:: ከመጀመሪያው አጭር ታሪክ ውስጥ በፍርሀት ገብቼ ጥቂት ከተጓዝኩ በኋላ ግን ስጋቴ ሁሉ ወደ ድፍረትና እምነት ተለወጠ:: የሚሆነውን ሳላውቀው አጫጭር ታሪኮቹ ፋታ በማይሰጥ ደስታ እየተቀባበሉየመፅሐፉ ፊርጥ ለሆነው «ሽማግሌውና ባህሩ» ለተሰኘው አጭር ልቦለድ አስረከቡኝ::

«ሽማግሌውና ባህሩን» በጥቁር ቀለምና በነጭ ወረቀት ላይ ሳይሆን ከአስደናቂው ዓሣ አጥማጅ ሽማግሌ ጋር የረጋውንና ቀዝቀዝ ያለ አየር የሚነፍስበትን ባህር እየቀዘፍኩ ነው የተንሳፈፍኩበት:: ጉዞዬን እንደጨረስኩም ጮክ ብዬ መስፍን ተሳካለት! አማርኛም እልል ይበል አልኩ:: እና በሁለቱ ስኬት ሰከርኩ...

ደምሴ ፅጌ
አ.አ. 1982

# ንፁህ ብርሃናማ ሥፍራ

ኧርነስት ሄሚንግዌይ[1]

ሌሊቱ በጣም ስለገፋ ቡና ቤቱ ጭር ብሏል:: ከአንድ ሽማግሌ በስተቀር ሌላ ደንበኛ የለም:: በጉዳናው ዳር የተተከለው ዛፍ ከመንገድ መብራቶች በሚፈነጥቀው ብርሃን በፈጠረው ጥላ ውስጥ በፀጥታ ተቀምጠዋል - ሽማግሌው::

ቀን ቀን ከጉዳናው የሚነሳው አቧራ አይጣል ነው:: ሲመሽ ግን ጤዛ ይወርድና በያለበት እንዲረጋ ያደርገዋል:: ሽማግሌው ጆሮዋቸው በመደንቆሩ እስከ ወድቅትም ቢሆን በረንዳው ላይ ቁጭ ብለው ማምሸት ይወዳሉ:: ሌሊቱ ፀጥታ ስለሰፈነበት ልዩነቱን መለየት ጀምረዋል:: ሁለቱ አሣላፊዎች ሽማግሌው ሞቅ እያላቸው መሆኑን አላጡትም:: ስካሩ ጠና ያለ ቀን ሂሳባቸውን ሳይከፍሉ ውልቅ የማለት ጠባይ ያላቸው መሆኑን ስለሚያውቁ ዛሬም በዓይነቁራኛ እየጠበቋቸው ነው::

«ባለፈው ሣምንት ራሳቸውን ለመግደል ሞክረው ነበር» አለ አንደኛው አሣላፊ::

«ለምን?»

---

[1] ኧርነስት ሄሚንግዌይ በ1899 ተወልዶ 1961 ራሱን የገደለ ታላቅ አሜሪካዊ ደራሲ ነው::ይህ ሰው በርከት ያሉ ረጅምና አጫጭር ልቦለዶችን የጻፈ ሲሆን በ1954 በሥነ ፅሑፍ የኖቤል ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል:: ይህንን ሽልማት እንዲያገኝ ካደረጉት ሥራዎቹ ዋነኛው በዚህ መድብል መጨረሻ ላይ የሚገኘው «ሽማግሌውና ባህሩ» የተሰኘው ኖቬላ ነው:: ሄሚንግዌይ ብዙ ዕድሜውን በኩባ ኖሯል::

«ተስፋ ቆርጠው ነዋ»
«በምን ምክንያት»
«እንዲሁ»
«ያለምክንያት መሆኑን እንዴት አወቅህ?»
«ይገርምሃል መዓት ገንዘብ አላቸው»

ወደ ቡና ቤቱ በሚያስገባው በር አጠገብ ግድግዳ ውን ተጠግቶ በቆመ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጡና ወደ በረንዳው ይመለከቱ ጀመር:: ንፋሱ በለዘብታ የሚያወ ዛውዛቸው ዛፎች በፈጠሩት ጥላ ውስጥ ከተጉለቱት ሽማግሌ በስተቀር ከላይ እንደተገለፀው /አሁንም/ ሌላ ደንበኛ የለም::

በረንዳውን የሞሉት ጠረጴዛዎች በሙሉ ቦዝነ ዋል::አንድ ወታደርና እንዲት ኮረዳ ተቃቅፈው አለፉ:: ወታደሩ ኰሌታ ላይ የተለጠፉት ከነሐስ የተሰሩ የመ ለያ ቁጥሮች ከጉዳናው መብራት የሚፈሰው ብርሃን ሲያርፍባቸው ለቅጽበት እንደ ጉድ አንፀባረቁ:: ፀጉሯን ያልሸፈነችው ኮረዳ ርምጃዋን ለማስተካከል ከሰውየው ጎን ውን ውን ትላለች::

«የወታደር ፖሊሶች ካገኙት አይለቁትም» አለ አን ደኛው አሣላፊ::

«የሚፈልገውን እስካገኘ ቢያዝስ ምናለበት?»

«ይልቅ ከዋናው መንገድ ዞር ቢል ይሻለዋል:: አለያ እንጠልጥለው ነው የሚወስዱት:: በዚህ ካለፉ አምስት ደቂቃ ቢሆን ነው::»

ዛፎቹ በጣሉት ጥላ ውስጥ የተቀመጡት ሽማ ግሌ ብርጭቆዋቸውን ከስኒ ማስቀመጫ ጋር በማጋ

ሌሊት እንኳን። ሊጅግሩ አሣላፊ ተልጠፍ ብሎ ቀረባቸው።

«ምን ልታዘዝ?»

ሽማግሌው ቀና ብለው ተመለከቱት። «ሊላ ብራንዲ» አሉ።

«እረ ይበቃል፤ ይሆንልሉ» አለ አሣላፊው። ሽማግሌው እንደገና ተመለከቱት። ተመልሶ ሄደ።

«ዛሬስ እንደኛውን ተጉልተው ሊያድሩ ነው መሰለኝ» አለው ለሥራ ባልደረባው።

«እኔ ለራሴ እንቅልፍ ክፉኛ እያንገላጀጀኝ ነው። በቃ እኔ ከዘጠኝ ሰዓት በፊት ተኝቼ አላውቅም። ባለፈው ሣምንት ራሳቸውን ገድለው ቢሆን ለኛም ትልቅ ግልግል ነበር።»

አሣላፊው የብራንዲውን ጠርሙስና አንድ የስኒ ማስቀመጫ ከቡና ቤቱ መደርደሪያ ላይ አንስቶ ወደ ሽማግሌው አመራ። የስኒ ማስቀመጫውን ጠረጴዛው ላይ አኖረና ብራንዲውን ቀዳላቸው።

«ባለፈው ሣምንት ራስዎን እንደጀመሩ መጨረስ ነበረብዎት» አለ ጆሮዋቸው ለማይሰማው ሽማግሌ። እሳቸው ግን በጣት ምልክት «ትንሽ ጨምር» አሉት። አሣላፊው በትዕዛዙ መሠረት ብርጭቆውን ሞላው። ብራንዲው በጣም በመሙላቱ በብርጭቆው ወገብ እያቋረጠ ቁልቁል በመፍሰስ ስኒ ማስቀመጫው ላይ ተንጣለለ። «አመሰግናለሁ» አሉ አዛውንቱ። አሣላፊው ጠርሙሱን ወደ ቦታው መለሰና እንደገና ጓደኛው አጠገብ ተቀመጠ።

«አሁን በደንብ ሰክረዋል» አለው።
«በወትሮ ጀንበር ስታዘቀዝቅ እንደሰከሩ ነው»
«ለመሆኑ ለምን ነበር ራሳቸውን መግደል የፈለጉት?»
«እንዴት ማወቅ ይቻለኛል?»
«ለመሆኑ ምን ነበር ያደረጉት?»
«በገመድ ራሳቸውን አንጠለጠሉ»
«ታዲያ ማን ቆረጠላቸው?»
«የእህታቸው ልጅ»
«ለምን?»
«ለነፍሳቸው ፈርታ»
«ምን ያህል ገንዘብ ይኖራቸው ይሆን?»
«ልክ የለውም»
«ዕድሜያቸው ሰማንያ ሳይደርስ ይቀራል?»
«ምንም ይሁን ምን እኔ እንደሆንኩ ብጠየቅ ሰማንያ ደርሰው ነበር ነው የምለው»

«ምናለ አሁን ወደቤታቸው ቢሄዱልን። መቼም ዛሬ ከዘጠኝ ሰዓት በፊት ቤቴ እገባለሁ ማለት ዘበት ነው። ከዚያ በኋላ ምን መተኛት ይባላል?»

«ሌሊቱን ያለእንቅልፍ ማሳለፍ ደስ ይላቸዋል»

«እሳቸውማ ብቸኛ ስለሆኑ ነው። እኔ ግን ብቸኛ አይደለሁም። አልጋችን ውስጥ እየተገላበጠች የምትጠባበቀኝ ሚስት አለችኝ።»

«በአንድ ወቅት እሳቸውም ባለሚስት ነበሩ።»
«ከእንግዲህ በኋላ ግን ሚስት ብሎ ነገር ለምንም አይበጃቸውም»

«ይህንን እንኳን ማለት አትችልም። እንዲያውም ሚስት ቢያገቡ ሳይሻላቸው ይቀራል?»

«አሁን የሚኖሩት ከእህታቸው ልጅ ጋር ነው»

«እስትንማ መች አጣሁት። ገመዱን የቆረጠችው እሷ ናት ብለሽኝ የለ።»

«እኔ ግን ይህን ያህል እስከማረጅ ለመኖር አልሻም። እንደ ሽማግሌ የሚያስጠላ ምን አለ?»

«ግን ሁሉም አይደሉም። ለምሳሌ እኒህ ሽማግሌ ንፁህ ናቸው። መጠጡ እንኳን ጠብ አይልባቸውም። እንዲህ ሰክረው እንኳን ቆፍጣናነታቸውና ጥንቁቅነታቸው አልተናጋም። እስቲ ልብ ብለህ እያቸው።»

«ላያቸው አልፈልግም። የኔ ፍላጎት ወደቤታቸው እንዲሄዱልኝ ብቻ ነው። ለሠራተኞቼ ምንም አያስቡም።»

ሽማግሌው ዓይኖቻቸውን ከብርጭቆው ላይ አንስተው ቀና በማለት አሻግረው አተኮሩ- ወደ አደባባዩ። ቆየት አሉና አሳላፊዎቹን መመልከት ጀመሩ።

«ሌላ ብራንዲ» አሉ ወደብርጭቆዋቸው እየጠቆሙ። ወደ ቤቱ ለመሄድ የሚቁነጠነጠው አሳላፊ ተጠጋቸው።

«በቃ» አለ አሳላፊው። አነጋገሩ ቃላት እያጉደለ ነበር፤ አንዳንድ ደደብ ሰዎች ከስካራሞች ወይም ከውጭ አገር ዜጎች ጋር ሲነጋገሩ እንደሚያደርጉት።

«ዛሬ በቃ። አሁን ዝግ» አላቸው።

«ሌላ» ሽማግሌው ደግመው ጠየቁ።

«የለም። አልቋል» አሳላፊው የጠረጴዛውን ጠርዝ በፎጣ እራፊ እየጠራረገ ራሱን በአሉታ ነቀነቀ።

ሽማግሌው ከመቀመጫቸው ተነሱና የስኒ ማስቀ መጫዎቹን በዝግታ ቆጠሯቸው። የስኒ ማስቀመጫ ዎቹ ቁጥር የተቀዳላቸውን መጠጥ ብዛት የሚያመለ ክት ነው። ከቆዳ የተሠራች የማንቲም መያዣ አወ ጡና ሂሣባቸውን ከስኒ ማስቀመጫዎቹ በአንደኛው ላይ አኖሩ - ጉርሻውንም ጨምረው።


ጐዳናውን ያዘው ቁልቁል ሲጓዙ አሳላፊው ባለ ቤት ቆሞ ተመለከታቸው። አልፎ አልፎ ቢንገዳገዱም በኩራት ጅንን ብለው የሚራመዱ አዛውንት።

«አሁን ትንሽ ቆይተው ያሻቸውን ያህል ቢጠጡ ምን ነበረበት?»አለ ለመሄድ ያልተቻኮለው አሳላፊ ቡና ቤቱን ሲዘጋ። «ገና ስምንት ሰዓት ተኩል እንኳ አልሆነ»

«እኔ ደግሞ በጊዜ ገብቼ መተኛት እፈልጋለሁ»
«አንድ ሰዓት ታዲያ ምንድናት?»
«ከሳቸው ይበልጥ ለኔ ብዙ ናት»
«አንድ ሰዓት ምንም ለውጥ አልነበራትም»
«አንተም ያው ነህ። አነጋገርህ ሁሉ ልክ እንደ ሽማግሌ ነው። ከፈለጉ ከነጠርሙሱ ገዝተው ቤታ ቸው ውስጥ ሊጠጡ ይችላሉ።»

«እንደዚህኛው አይሆንማ»
«እሱስ አዎ»ባለትዳሩ አሳላፊ ስምምነቱን ገለፀ። ምንም እንኳን ለመሄድ ቢቻኮል ሐቁን ለመካድ ግን ፍላጎት አልነበረውም።

«አንተስ ካስለመድከው ሰዓት ቀደም ብለህ ወደ ቤት መግባት አያስፈራህም?»



«ለምን ልትሰድበኝ ትፈልጋለህ?»

«ኧረ ምን ቁርጦኝ እንዲያው ለቀልድ ያህል ነው»

«እኔ ግን አልፈራም» አለ ወደቤቱ ለመሄድ የሚጣደፈው አሳላፊ የመስኮቶቹን ተንሸራታች የብረት መዝጊያዎች ገጥሞ ቀና እያለ «በራሴ ሙሉ ዕምነት አለኝ»

«ወጣትነት፣ ዕምነት፣ሥራ» አለ ጠና ያለው አሳላፊ «ሁሉም ነገር አለህ»

«አንተስ ምን ይጐድልሃል?»

«ከሥራ በስተቀር ሌላ ምን አለኝ ብለህ?»

«እኔ ያለኝ ሁሉ አንተም አለህ»

«በጭራሽ:: በዕድሜዬ ዕምነት የሚሉ ነገር አላውቅም:: ደግሞም ወጣት አይደለሁም»

«በል እስቲ አሁን የማይረባ ነገር ማተቱን ትተህ የሚቆላለፈውን ቆላልፈው»

«ቡና ቤት ብዙ ማምሸት ከሚወዱት አንዱ እኔ ነኝ» አለ ጠና ያለው አሳላፊ::

ወደ አልጋቸው መሄድ ከሚቀፋቸው መሀል ነው መደቡ:: ለሌሊቱ ብርሃን ከሚያስፈልጋቸው ጋር::

«ወደ ቤቴ ሄጄ መጋደም እንዴት መሰለህ የናፈቀኝ»

«እኔና አንተ ሁለት የተለያየን ሰዎች ነን» አለ ጠና ያለው አሳላፊ:: አሁን ልብሱን ቀያይሮ ወደቤቱ ለመሄድ ተዘጋጅቷል:: «አየህ ጥያቄው የወጣትነትና

የዕምነት ብቻ አይደለም- ምንም እንኳን እነዚህ ሁለት ነገሮች ድንቅ መሆናቸው ባይካድም። ግን ዘወትር ማታ ማታ ቡና ቤቱን መዝጋት ይጨንቀኛል። በጭራሽ አልፈልግም። ምክንያቱም ምናልባት ጉራ ብሎ እየተዝናና ሊያመሽ የሚፈልግ ሰው ሊኖር ይችላል የሚል ግምት ስላለኝ»

«ሰውየ ሌሊቱን ሙሉ ሲሠሩ የሚያድሩ የቢና መሸታ ቤቶች አሉ»

«አልገባህም።ይሄኮ ንፁህና የደስደስ ያለው ቡና ቤት ነው። ያውም ከበቂ ብርሃን ጋር። ብርሃኑ ደግሞ ማለፊያ ነው። በዚያ ላይ የቅጠሎቹ ጥላ አለ። ይህ ሁሉ ደስታን ይሰጣል»

«በል ደህና እደር» አለ ወጣቱ አሳላፊ።

«ደህና እደር» አለ ሌላውም። መብራቱን አጠፋና ውይይቱን ከራሱ ጋር ቀጠለ። በርግጥ ዋናው ጉዳይ የብርሃን መኖር ነው። ግን ቦታውም ንፁህና የደስደስ ያለው ሊሆን ይገባል። ሙዚቃ አያስፈልግህም። ምንም ሙዚቃ አያስፈልግህም።ምንድነው የፈራው? በእርግጥ ፍርሐትም ሥጋትም አይደለም። ግን አንድ በደንብ የሚያውቀው ምንም ነው። ሁሉም ምንም ነበር። አዎ ሰውም ራሱ ምንም ነበር።ያ ብቻ ነበር፣ብርሃኑን ብቻ ነበር የፈለገው። እና በዚያ ላይ ጥቂት ንፅህናና ሥነ ሥርዓት። አንዳንዶች በውስጡ እየኖሩ እንኳን አይሰማቸውም።አያውቁትም። እሱ ግን ሁሉም ነገር ምንም መሆኑንና እንደገና፣መልሶ መላልሶ ምንም መሆኑን ያውቅ ነበር። ምንማችን ሆይ በምንም የምትኖር፣ ምንምህ ይቀደስ፣ ምንምህ ትምጣ፣ፈቃድህ በምንም እንደሆነች እንዲሁም በምንም ትሁን። የዕለት ምንማችንን ሁሉ ዛሬ ስጠን፣ምንማችንን ሁሉ ምንም በለን፣

እኛም ምንም ያሉንን ሁሉ ምንም እንድንል። ወደ ምንም አታግባን - ከምንም አድነን እንጂ። ምንም። ሰላም በምንም ለተመላ ምንም ይሁን! ምንም ካንቺ ጋር ነውና። ፈገግ ብሎ በመብራቱ ብርሃን ከሚያብረቀርቀው የቡና መኪና ፊት ለፊት ተገተረ።

«የንተ ምን ይሁንልህ?» ባሬስታው ጠየቀው።

«ምንም»

«ሊላ ቀውስ» አለና ፊቱን አዞረ-ባሬስታው።

«በትንሿ ስኒ» አለ አሳላፊው።

ቀድቶ ሰጠው።

«ጥሩ ብርሃን አለ። አስደሳችም ነው። ግን ባንኮኒው አልተወለወለም» አለ አሳላፊው።

ባሬስታው ቀና ብሎ ተመለከተው። መልስ ግን አልሰጠውም። ጊዜው የውይይት አይደለም። በጣም መሽቷል።

«ልድገምህ?» ባሬስታው ጠየቀ።

«የለም በቃኝ። አመሰግናለሁ» አለና አሳላፊው ወጥቶ ሄደ። መሸታ ቤቶችን በተለይ የቢና መሸጫ ሱቆችን በጭራሽ አይወድም። ንፁህና በብርሃን የተጥለቀለቀ ቡና ቤት ግን ለየት ያለ ነገር ነው። አሁን ራሱን በሌላ ተጨማሪ ሀሳብ ማንገላታት አያስፈልገውም። ቀጥ ብሎ ወደቤት መሄድ ብቻ። እንደ ደረሰ አልጋው ላይ በቁሙ ይገነደሳል፣ ሲነጋጋ እንቅልፍ ይወስደዋል። ለብቻው መነጋገር ጀመረ። ምናልባት፣ አለ ለራሱ ሲያወራ፣ ኢንሶምኒያ[1] ሊሆንም ይችላል። ብዙ ሰዎች ሳይኖርባቸው አይቀርም።

---

[1]ኢንሶምንያ እንቅልፍ የማጣት ችግር /በሽታ/ ነው።

# የጉራዴው ቅርፅ

ሆርሄ ሉዊ ቦርሄስ

የሚያስፈራ ጠባሳ ፊቱ ላይ ተጋድሟል:: ታዲያ ሁልጊዜ የተቆጣ ያስመስለዋል:: ዓመድማ ቀለም ያለ ውና እንደ ደጋን የተቆለመመው ጠባሳ የግንባሩን አንድ ጉንና በዚያው በኩል ያለውን የጉንጩን አጥ ንት ቅርፅ አበላሽቶዋቸዋል:: ዕውነተኛ ስሙን የሚያ ውቅ የለም::የታኪዋሬምቦ ነዋሪዎች በሙሉ የሚጠሩት በርስቱ ስም ነው:: «የላ ኬሎራዳው እንግሊዛዊ» ይሉ ታል:: ቀድሞ የመሬቱ ጌታ የነበረው ካርዶስ በመጀ መሪያ መሬቱን ሊሸጥለት ፍላጐት አልነበረውም:: ስለ ዚህ መሬቱን በእጁ ለማስገባት በልዩ ዘዴ መጠቀሙ ተነግሮኛል::ፊቱ ላይ ስለተጋደመው ጠባሳ ምሥጢሩን አጫውቶታል ይባላል:: የእንግሊዛዊው አመጣጥ ከወደ ጠረፍ አካባቢ ነው፤ ከሪዮግራንዲ ደ ሱል:: ብራዚል ውስጥ በኰንትሮባንድ ንግድ ላይ ተሰማርቶ መኖሩን ሁሉም ያወራሉ:: ርስቱን በገዛበት ጊዜ አረሙ ካለማላ ወሱ ሌላ ለብዙ ጊዜ ሳይጠረጉ የቆዩት የውኃ ጉድ ጓዶች ክርፋት አይጣል የሚያሰኝ ነበር:: እንግሊዛዊው ግን ከሠራተኞቹ እኩል ሌሊትና ቀን በመሥራት የተበ ላሸውን ለማቃናት ብዙም ጊዜ አልወሰደበት:: በተፈ ጥሮው ቁጡና ኃይለኛ በመሆኑ አንዳንዴ የሚወስደው ርምጃ እስከ ጭካኔ ይደርሳል:: ቢሆንም በአስተዳደር

---

ሆርሄ ሉዊ ቦርሄስ በ1889 ተወልዶ በ1986 ያረፈ ደራሲ ነው:: ቦርሄስ የአርጀንቲና ተወላጅ ሲሆን ባለቅኔ፣ የአጫ ጭር ልቦለዶች ደራሲና ሃያሲ ነበር:: ይህ ከዘመናችን ታላ ላቅ ደራሲያን አንዱ የሆነውና ብዙዎች ከፍራንዝ ከፍካ ጋር የሚያመሳስሉት ብዕረኛ በሥነፅሑፍ ሥራዎቹ በርካታ ሽልማቶችን ለማግኘት በቅቷል::

ችሎታው አድናቆትን አትርፏል፡፡ መጠጥ ይወዳል እየ
ተባለም ይታማል፡፡ በዓመት ሁለት ጊዜ በበጋ የማረ
ፊያ ቤቱ ውስጥ ከማንም ሳይገናኝ ለሁለትና ሦስት
ቀናት ቆይቶ የመውጣት ልዩ ዓመል አለው፡፡ ከዚህ
ሱባኢው ሲወጣ ታዲያ ጦር ሜዳ እንደከረመ ወይም
አንዳች አስደንጋጭ መዓት እንደወረደበት ሁሉ ግር
ጥት ብሎ አካሉ ተብረክርኮና ሁለመናው በሽብር
ተውጦ ነው፡፡ ሆኖም ምንም ይሁን ምን ወትሮ የሚ
ያሳየው የአለቃነት ስሜቱ ይናጋል ማለት ዘበት ነው፡፡
እኔም ትዝ ይለኛል፡፡ ቀዝቃዛ ዓይኖቹ፣ ጥንካሬ ያለው
ቅጥነቱና ግራጫው ሪዙ አሁንም ወለል ብለው ይታዩ
ኛል፡፡ ከማንም ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ ብቸኛ ነው፡፡
የስፓኝ ቋንቋ ችሎታው ይህን ያህል የሚያወላዳ አይ
ደለም፡፡ ለዚያውም የብራዚል ቅላፄ ያጠቃዋል፡፡ አልፎ
አልፎ ከሚመጡለት የሥራ መልዕክቶች በስተቀር ሌላ
ምንም ዓይነት ደብዳቤ አይደርሰውም፡፡

በሰሜን አውራጃዎች ውስጥ የመጨረሻ ጉብ
ኝቱን ባደረግሁ ጊዜ የካራጉታ ወንዝ ሞልቶ አላሻግር
በማለቱ አንድ ሌሊት ባኮ ኬሌራዳ ርስት ማሳለፍ ተገ
ድጄ ነበር፡፡ምንም እንኳን የሄድኩበት ወቅት ተስማሚ
አለመሆኑ ጥቂት ቆይቶ ቢሰማኝም በተቻለ መጠን አስ
ተናጋጁን ለማግባባት ጥረት ማድረግ ጀመርኩ፡፡ ከስሜ
ቶቻችን ሁሉ በቀላሉ ሊቀሰቀስና ሊነሳሳ በሚችለው
በአገር ፍቅር ስሜት ላይ አነጣጠርኩ፡፡ የእንግሊዝን
መንፈስና ወኔ የታደለ የትኛውም አገር አይበገሬ እንደ
ሚሆን ገለፅኩለት፡፡ ሰውየው በአነጋገሬ መስማማቱን
ከአረጋገጠልኝ በኋላ እንግሊዛዊ አለመሆኑን ከፈገግታ
ጋር ነገረኝ፡፡ የአየርላንድ ተወላጅ ነው፡፡ ይህንን ከተነ
ፈሰ በኋላ ግን ድንገት ፀጥ አለ፤ሳያስበው አንዳች ምስ
ጢር እንዳወጣ ሁሉ፡፡

ራት እንዳበቃ ለመናፈስ ወደ ውጭ ወጣን:: ዝናቡ አባርቷል:: ባሻገር ወደ ደቡብ ሲል ካሉት ተራሮች ጀርባ ግን አሁንም ይፈልቃል::

ራት ላይ ያስተናገደን ሠራተኛ አንድ ጠርሙስ ራም[1] አቀረበ::ዕቃውም ምንም እንደነገሩ ወደሆነው የምግብ ክፍል ተመልሰን መጠጡን በፀጥታ መሳብ ጀመርን:: በዚያ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ቆየን::

ሞቅታ እንደጀማመረኝ የተረዳሁት በስንት ሰዓት ግድም እንደሆነ አላስታውስም:: ስለጠባሳው እንዳነሳ የገፋፋኝም ስሜት ምን እንደነበረ አሁን በቅጡ ትዝ አይለኝም:: ጠየቅሁት:: ወዲያው የ«እንግሊዛዊው»ፊት ልውጥውጥ አለ:: ማንቁርቱን አንቆ ከቤቱ ያሽቀነጥረኛል የሚል ሥጋት ለጥቂት ጊዜ ወረረኝ::በመጨረሻ «የዚህን ጠባሳ ታሪክ የምነግርህ በአንድ ውለታ ብቻ ነው:: በምንም ዓይነት ለሐፍረትና ለውርደት እንደማታጋልጠኝ ቃል ከገባህልኝ ብቻ::» አለ በተለመደው ድምፁ::

ተስማማሁ:: የነገረኝ ታሪክ የሚከተለው ነው - እንግሊዝኛውን ከስፓኝ እና ከፖርቱጋል ቋንቋዎች እየቀየጠ::

ጊዜው በ1922 ወይም ወደዚያው ግድም ነበር:: ለአየርላንድ ነፃነት በንቁዕ ከሚታገሉት መሐል አንዱ

---

[1] ራም ከሸንኰራ አገዳ ጭማቂ ወይም አሰር /ሞላሰስ/ የሚዘጋጅ የአልኰል ይዘቱ ከፍተኛ የሆነና በተለይ በመርከበኞች ዘንድ ተወዳጅነት ያለው የመጠጥ ዓይነት::


RUM

መሆኔን አልደብቅም፡፡ ከዚያ ዘመን ጓዶቼ መካከል ጥቂቶቹ አሁንም በሕይወት አሉ፡፡ ሠላማዊ ሥራዎቻ ቸውን እያከናወኑ በአማን ይኖራሉ፡፡ሌሎቹ በእንግሊዝ ባንዲራ ስር ተሰልፈው በየበረሃውና በየባህሩ ይዋጋሉ፡፡ የሚገርም ነው፡፡ የተቀሩት፣ ምርጥ የሚባሉት፣ ግን በዓላማቸው እንደፀኑ ለዓላማቸው ወደቁ፡፡ በየጦር ሠፈሩ ግቢ ጉህ ሲቀድ በሰልፍ እየተኰለኰሉ እንቅል ፋቸውን ባልጨረሱ ወታደሮች ጥይት እየተደበደቡ አለቁ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ /ለያውም የታደሉት/ በስም የለ ሹና በአብዛኛው በምሥጢር በተካሄደው የርስ በርስ ውጊያ ውስጥ ከመጨረሻ ዕጣቸው ጋር ተፋጠጡ፡፡ ሁላችንም ሪፐብሊካውያን ነበርን፤የካቶሊክ ዕምነት ተከ ታዮች፡፡ በዚያን ወቅት ታዲያ ስሜታዊነት በጥቂቱም ቢሆን ያጠቃን የነበረ ይመስለኛል፡፡

አንድ ቀን ማታ ሙንስተር ከሚባል ከተማ አንድ የፓርቲያችን አባል የሆነ ሰው ይመጣል፡፡ጆን ቪንሰንት ሙን ይባላል ስሙ፡፡ ያቺ ምሽት በሕይወት እስካለሁ አትረሳኝም፡፡

ሙን ሃያ ዓመት እንኳን የሞላው አይመስልም፡፡ ገና ጮርቃ ነው፡፡ ቀጭን ለግላጋ፡፡ ሲያዩት ቆራጥነትና ወኔ ያለው መሆኑ ያጠራጥራል፡፡ ስለኮምዩኒዝም ግን በደንብ ያነበበ ይመስላል፡፡ በየውይይቱ ላይ የነገር መቋጫው ዲያሌክቲካዊ ቁስአካላዊነት ብቻ ነው፡፡አንድ ሰው ሌላውን ሰብዓዊ ፍጡር የሚወድባቸውም ሆነ የሚጠላባቸው ምክንያቶች በርከት ያሉ ሊሆኑ ይች ላሉ፡፡ የዓለምን ታሪክ «መጥፎ ኢኮኖሚያዊ ግጭት ነው»በማለት ያጠቃልለዋል፡፡የጀመርነውን ትግል በድል እንደምንወጣ አፉን ሞልቶ ይናገራል፡፡በኔ በኩል ግን የቆምንለት ዓላማ እየከሸፈ መሆኑን ከመግለፅ አልተቆ ጠብሁም፡፡

. . . ከነበርንበት ቦታ ስንወጣ ሌሊቱ መግፋቱን ተገነዘብሁ፡፡ ክርክራችን ግን አልተቋረጠም፡፡ከኛው ጋር ወደ ውጭ ዘለቀ፡፡ በኮሪደሩ እየተጓዝን፣ በደረጃዎቹ እየተንደረደርንና በጠመዝማዛው ጉዳና እያዘገምን ውይይታችንን ቀጠልን፡፡ ነገር ግን ሙን የሚወረውራቸው ሃሳቦች አንዳችም ስሜት ሊያሳድሩብኝ አልቻሉም፡፡ አዲሱ ጓድ በነፃ ውይይትና ክርክር ዕምነት እንደሌለው ለመረዳት ጊዜ አልወሰደብኝም፡፡ በትዕቢትና በንቀት መንፈስ፣ አንዳንዴም ከቁጣ ጋር፣ ህጉ እንዳለ ተግባራዊ እንዲሆን ትዕዛዝ የሚሰጥ ግትር ሰው ነበር፡፡

በመንገዳችን ላይ ከነበሩት መደዳውን የተቀጣጠሉ ቤቶች የመጨረሻውን አለፍ እንዳልን የተኩስ ድምፅ ድንገት ዙሪያችንን መላው፡፡ ከው ብለን በቆምንበት ቀረን፡፡ ድንጋጤው እየበረደልን ሲሄድ አጠገባችን የነበረውን ፋብሪካ ይሁን የወታደሮች ካምፕ፣ ምንነቱ ያልታወቀ ዕውር ህንፃ አለፍ ብለን ወደ ኮረኮንች መንገድ ታጠፍን፡፡ ከፊት ለፊታችን በእሣት ከምትንቀለቀል አነስተኛ ጎጆ ውስጥ አንድ ወታደር እመር ብሎ ወጣ፡፡ ዓይን በሚጣረረው በዚያ ብርሃን ውስጥ ሲያዩት በጣም ግዙፍ ነው፡፡ ገና ሲያየን ባለንበት እንድንቆም ትዕዛዙን አንባረቀ፡፡ በኔ በኩል ትዕዛዝ የማክበር ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ ዝም ብዬ መንገዴን ቀጠልኩ፡፡ ጓዴ ግን አልተከተለኝም፡፡ ገልመጥ ስል ጆን ሺንስንት ሙን ወደ ድንጋይነት የተለወጠ ይመስል ባለበት ተቸንክሮ ቆሟል—በፍርሃት ደንዝዞ፡፡ ወደኋላ ተመልሼ ወታደሩን በአንድ ቡጢ ከዘረርኩት በኋላ ሙንን ነቀነቅሁት፡፡ የማውቀውን ሁሉ ስድብ አከናንብኩትና ፈጥኖ እንዲከተለኝ በቁጣ አዘዝኩት፡፡ ያዳመጠኝ መሆኑን ስለተጠራጠርኩ ክንዱን ይዤ እየጎተትኩት እዚህም እዚያም በእሳት የተቦጫጨቀውን

ጨለማ ገባንበት:: ብዙም ሳይቆይ የጠመንጃ እሩምታ አጀበን::አንዲት ጥይት የሙንን የቀኝ ትከሻ ገሽልጣው አለፈች:: ሩጫችንን ቀጥለን በጥድ ዛፎች መሃል ስንሽ ለከለከ ጓደኛየ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁና ሲተነፍስ ሰማ ሁት:: አፎይታ::

በዚያ የመፀው ምሽት መደበቂያችንን በጄኔራል በርክሊ ቪላ አደረግን:: ጄኔራሉ/በበኩሌ አላውቃቸውም/ በወቅቱ ባገር አልነበሩም:: ለሥራ ጉዳይ ታዘው ወደ ቤንጋል ሄደው ነበር:: የቤቱ ዕድሜ ከአንድ ምዕት ዓመት ቢያንስም መጉሳቆልና እርጅና ይታይበታል:: በዚያ ላይ በጨለማ የተዋጠ ነው:: ግራ የሚያጋቡ ኰሪደሮችና ለምንም አገልግሎት የማይውሉ አዳራሾች ይበዙበታል:: ምድር ቤቱ ሙሉ በሙሉ የተያዘው በማይዩዚየሙና በትልቁ ቤተመፅሐፍት ነው:: መደርደሪ ያዎቹ ላይ ልዩ ልዩ መፅሐፍት ታጭቀዋል:: አለፍ አለፍ እያሉ በሥርዓት በተሰቀሉት በርካታ የህንድ ጥንታዊ አሽሟጣጭ ጉራዴዎች ዙሪያ አሁንም የጦር ነት ንፋስና የአመፅ አየር የሚያንዣብብ ይመስላል:: ሁነቶች በሙሉ አስገራሚ ሆነው እንዳገኛቸው በሹክ ሹክታ ገለፀልኝ:: የሚንቀጠቀጡት ከናፍሬ ደርቀዋል:: የመጀመሪያ የህክምና ርዳታ ከአደረግሁለት በኋላ ሻይ አፍልቼ ሰጠሁት:: ጥይቷ ጨርፋው ያለፈች በመሆኑ ቁስሉ ለከፋ የሚሰጥ አልነበረም:: ድንገት ግራ በተጋ ባና በተርበተበተ አነጋገር፣ «ግን 'ኮ ድፍረትህ ለአደጋ የሚያጋልጥ ነበር» አለኝ:: እንዳይጨነቅና ነገሩን እን ዲረሳው ነገርኩት:: የርስ በርስ ጦርነቱ ያንን መሣይ ተግባር መፈፀም አስለምዶኛል::የዘወትር ሥራየ ነበር:: በዚያ ላይ አንድም ቢሆን እንኳን የፓርቲያችን አባል የሆነ ሰው ተይዞ መታሰር ዓላማችንን አደጋ ላይ እን ደሚጥለው ግልፅ ነው::

በማግስቱ የሙን ፍርሃትና ድንጋጤ ሁሉ ጠፋና መንፈሱ ፍፁም ተረጋጋ። የጋበዝኩትን ሲጋራ ተቀ ብሎ ከለኮሰ በኋላ «ስለፓርቲያችን የገንዘብ ምንጮች» ኃይለኛ ጥያቄዎችን እየሰነዘረ ያፋጥጠኝ ጀመር። ጥያ ቄዎቹ ግልፅ ነበሩ። ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ የሚ ገኝ መሆኑን አስረዳሁት። /ደግሞም ዕውነት ነበር።/

በስተደቡብ በኩል የጠመንጃ ተኩስ አልፎ አልፎ ፀጥታውን ያደፈርሰዋል። ጓዶቻችን እየጠበቁን ስለሆነ ለጉዞ እንዲዘጋጅ አሳስቤው ካፖርትና ኮልት ሽጉጤን ለማምጣት ወደ መኝታ ክፍሌ አመራሁ። ስመለስ በቁ ሙቱ ሙሉ ሶፋው ላይ ተዘርግቷል። ዓይኖቹ ተከድ ነዋል። ትከሻው አካባቢ ከፉኛ ጨምድዶ እንደያዘውና ትኩሳትም የጀመረው መሆኑን ነገረኝ።

የሙን ፍርሀት የማይድን በሽታ ዓይነት መሆኑ ገባኝ።እኔ መሄድ ስለነበረብኝ ራሱን እንዲጠብቅና ጥን ቃቄ እንዲያደርግ መክሬው ወጣሁ። ስለ ጓደኛዬ ፍር ሃት እኔን ሐፍረት ገደለኝ። እኔ ራሴ ፈሪ የሆንኩ መሰለኝ። የአንድ ሰው *ሥራዎች* የመላው የሰው ዘር *ሥራዎች* እንደሆኑ ሊቆጠር ይችላል። በዚህም ምክን ያት ነው በአንድ የአትክልት *ሥፍራ* የተፈፀመ ጥፋት መላውን የሰው ልጅ መበከሉ ትክክል የሚሆነው።ለዚ ህም ነው የአንድ አይሁዳዊ መሰቀል ለመላው የሰው ዘር ቤዛነት ሊኖረው የበቃው። ምንአልባት ሾፐ ናወር «እኔ ሌሎች ነኝ፣ አንድ ሰው ደግሞ ሰዎችን በሙሉ ነው» ሲል አልተሳሳተ ይሆናል። ሼክስፒር በአንዳንድ መንገዶች ምስኪኑን ጆን ቪንሰንት ሙንን ነው።

በጄኔራሉ ትልቅ ቪላ ውስጥ ዘጠኝ ቀናት አሣለ ፍን። የአሁኑ ዓላማዬ በነጋ ጠባ በሐፍረት የሚጠዘጥ ዘኝን የዚህን ጠባሳ ታሪክ ማውጋት ስለሆነ ስለጦርነት

መዘዝ፣ ስለሚያስከትለው ሥቃይና ክብር ለማተት አልሻም። እና ይኸውልህ እነዚያ ዘጠኝ ቀናት አንዳችም ቁም ነገር ያልተፈፀመባቸው ባዶ በመሆናቸው እንደ ዘጠኝ ሳይሆን እንደ አንድ ቀን የሚቆጠሩ ነበሩ፤ ከመጨረሻይቱ ቀን ዋዜማ በስተቀር። በዚያች ዕለት የኛ ሰዎች በአንድ የወታደር ሠፈር ላይ አደጋ ጥለው በሥፍራው ያገኟቸውን በሙሉ ፈጅዋቸው። መሰንበቻውን ኤልፊን በሚባል ቦታ በመትረየስ ታጭደው የተሰውትን አሥራ ስድስት ጓዶቻችንን ተበቀሉልን። በዚያች ዕለት ታዲያ ማልጄ የወጣሁ ለዓይን መያዝ ሲጀምር እመለሳለሁ። ሙን ፎቅ ላይ በሚገኘው የመኝታ ክፍል ሆኖ እየጠበቀኝ ነበር። ህመሙ ስለጠናበት ወደምድር ቤት መውረድ ተስኖታል። ስለስትራቴጂ የሚያወራ አንድ መፅሐፍ በእጁ ይዞ እንደነበር ትዝ ይለኛል።«ከመሣሪያ ሁሉ ደስ የሚለኝ መድፍ ነው፣» በማለት አንድ ምሽት በጨዋታ መሃል ጠቀም አድርጐልኝ ነበር። ስለዕቅዶቻችን ይጠይቅና ስነግረው ትችት መሰንዘር ወይም ያለበቂ ምክንያት እቅዱ እንዲለወጥ ማሳሰብ ይወዳል። «በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ የሚገኘውን የገንዘብ ምንጫችንን» አዘውትሮ ማውገዝና ወደ አስከፊው መጨረሻችን እያመራን ስለመሆኑ መተንበይ ያስደስተዋል። ፈሪነቱ እንዳይታወቅበት ለመደበቅ ሲል እጅግ ግዙፍ የመንፈስ ኩራት ለማሳየት ጥረት ያደር ጋል።በዚህ ዓይነት አሥር ቀናት በአንድነት አሳለፍን።

በአሥረኛው ቀን ከተማይቱ በተቃዋሚዎቻችን እጅ ወደቀች። ድል ተመታን። ቁመተ ረጃጅምና ፀጥ ያሉ ፈረሰኞች ሠዋራ መንገዶችን ይቆጣጠራሉ። አየሩ በአመድና በጢስ ጢቅ ብሏል። ዓይኖቼ በአንድ ጉዳና ጥግ በተዘረረ ሬሣ ላይ አረፉ። ቀደም ሲል ወታደሮቹ በሕዝብ አደባባይ መሃል የተኩስ ዒላማ ሲለማመዱበት ያየሁት ሰው መሣይ ትልቅ አሻንጉሊት ፈጥሮብኝ ከነ

በረው የተለየ ስሜት ግን አላሳደረብኝም፡፡ ጎህ ሲቀድ ወጥቼ ከቀትር በኋላ ተመለስሁ፡፡ ሙን ቤተመፅሐፍቱ ውስጥ ሆኖ ከሰው ጋር ይነጋገራል፡፡ የሚያወራው በስልክ መሆኑን ከድምፁ ለመረዳት አላዳገተኝም፡፡ ትንሽ ቆይቶ ስሜ ሲጠራ ጆሮዬ ጥልቅ አለ፡፡ በማከታተልም ከሄድኩበት የምመለሰው በአንድ ሰዓት እንደሆንና የአትክልቱን ሥፍራ በማቋርጥበት ወቅት እንድያዝ መመሪያ ሲሰጥ ሰማሁ፡፡መልካሙ ወዳጄ በጥሩ ሁኔታ እየሸጠኝ ነበር፡፡ በመጨረሻ ለደህንነቱ በቂ ዋስትና እንዲሰጠው ጠየቀና ውይይቱ አበቃ፡፡

እዚህ ላይ ታሪኩ ይደበላለቅብኝና ውሉ ይጠፋኛል፡፡ ሆኖም ያንን ከሃዲ በነዚያ አስፈሪ ጨለማ ኮሪደሮችና በረጅሞቹ ደረጃዎች እንዳሳደድኩት ግን ትዝ ይለኛል፡፡ ሙን ከኔ ይበልጥ ቤቱን ደህና አድርጎ አጥንቶት ስለነበር አንድ ሁለቴ ዱካውን አጥፍቶብኝ ነበር፡፡ ሆኖም ወታደሮቹ ሳይደርሱብኝ በፊት እንደ ምንም ብዬ ያዝኩት፡፡ ሊያመልጥ በማይችልበት ቦታና ሁኔታ ውስጥ ነበር፡፡ ጊዜ ሳላባክን ከጄኔራሉ ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያዎች መካከል አንዱን ጉራዴ መዥረጥኩና በኃይል ሰነዘርኩ፡፡ ግማሽ ጨረቃ በሚመስለው በዚያ ብረት የገመስኩት ፊቱ የግማሽ ጨረቃ ቅርፅ ባለው ደም ለዘላለሙ ተበከለ፡፡ አየህ፣ አንተ ስለነገሩ ምንም የማታውቅ እንግዳ ሰው ስለሆንክ ድብቁው የኖርኩትን ምሥጢር ተናዝዤልሃለሁ፡፡ ንቀትህ እምብዛም አያቆስለኝም፡፡

እዚህ ላይ ተራኪው ንግግሩን ገታ፡፡ እጆቹ መንቀጥቀጣቸውን ማስተዋል አልተሳነኝም፡፡

«የሙንስ መጨረሻ ምን ሆነ?» በማለት ጠየቅሁት፡፡

«እስማ በይሁዳዊነት ለተጫወተው ሚና የሚገባውን ገንዘብ ተቀብሎ» ወደ ብራዚል ፈረጠጠ:: እንዲያውም ዛሬ ከቀትር በኋላ የስካራም መንጋ በዋናው አደባባይ መሃል ተሰብስቦ ሰው በሚመስል ትልቅ አሻንጉሊት ላይ ሲተኩሱ ቆሞ ያስተውል ነበር::»

ታሪኩ ይቀጥላል ብዬ መጠበቅ ጀመርኩ:: ግን ምንም:: እንደተቋረጠ ቀረ:: በመጨረሻ ሲታክተኝ እንዲቀጥልልኝ አፍ አውጥቼ ጠየቅሁት::

እንደማቃሰት ያለ ድምፅ አሰማ:: ቀጥሎም በጣም በሚማርክ ጨዋነትና ትህትና እንደቀስተደመና የተቆለመመ ነጭ ጠባሳውን በጣቱ ጠቆመልኝ::

«አታምነኝም?» አለ በሚርበተበት ዓይነት አነጋገር::«አይታይህም፣ የውርደት ምልክት የሆነ ፅሑፍ ፊቴ ላይ መሸከሜ አይታይህም?! ታሪኩን በዚህ መልክ የነገርኩህ እስከመጨረሻው በትዕግስት እንድትሰማኝ ብዬ ነው::

«የረዳኝን፣ መሸሸጊያና መደበቂያ የሰጠኝን ሰው አጋለጥሁት፣ አሣልፌም ሰጠሁት! አየህ ቪንሰንት ሙን ማለት እኔ ነኝ::አሁን ከመሰለህ ልትንቀኝ ትችላለህ::»

# እናት

ጊ.ደ. ሞፓሳ*

ወደ ቤርሌን ብቅ ካልኩ አሥራ አምስት ዓመት ገደማ ይሆነኛል። ትንሽ ዕረፍት ለማድረግና የተውኩትን አደን እንደገና መሞከር ስላማረኝ በመሀው አካባቢ ወደዚያ ብቅ አልኩ። የልብ ወዳጄ የሆነው ሴርቫል ጀርመኖች በጦርነቱ ወቅት ያቃጠሉትን ትልቅ ህንፃ አሳድሶ ስለነበር እርሱ ዘንድ በእንግድነት አረፍኩ።

መቼም አካባቢውን ስወደው ለጉድ ነው። በዚህ ዓለም ላይ ልዩ የማራኪነት ኃይል ያላቸው አንዳንድ አስደሳች ሥፍራዎች አሉ። ወደገጠር ወጣ ማለት የምንመርጥ ሰዎች ደግሞ የተወሰኑ ምንጮችን፣ ጫካ ዎችን ኩሬዎችንና ኮረብቶችን፣ በአንድ ወቅት ልባችንን ነክተው እንዳለፉ የሚያስደስቱ የሕይወት ገጠመኞች ዘወትር ስናስታውሳቸው እንኖራለን።

የቤርሌን ግን የተለየ ነው። በበኩሌ የምወደው መላውን ክፍለ ሀገር እንጂ ነጥዬ የማደላለት የለም። ብትንትን ብለው በየቦታው በሚታዩት ጫካዎች መሐል ለመሬት ደም እንደሚያስተላልፉ የደም ሥሮች እየ ተሹ ለክለኩ ከሚጠማዘዙት ኸረቶች በየቀኑ ልዩ ልዩ ዓይነት ዓሣዎችን እናጠምዳለን። አንዳንዶቹን እንዲ ያውም ለመታጠብና ለዋና እንጠቀምባቸውም ነበር።

---

* ጊ.ዶ. ሞፓሳ በ1805 ተወልዶ በ1893 የሞተ ፈረንሳዊ ደራሲ ሲሆን ዋናዎቹ ሥራዎቹ አጫጭር ልቦለዶች ነበሩ። ሞፓሳ ለዚህ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ማደግ፣ መበልፀግና በሕዝብ ዘንድ መወደድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቶ ያለፈ ታላቅና ሕያው ደራሲ ነው።

ይህም ብቻ አይደለም:: አነስ ያሉትን ዥረቶች ዳርቻ ተከትሎ በሚበቅለው ሠንበሌጥ ውስጥ ዘወትር የምና ድናቸው ቆቆች መቼም መች አይረሱኝም::

ታዲያ በእንግድነት ቆይታየ ወቅት አንድ ቀን ከወዳጄ ሴርቫል ጋር ለአደን እንወጣለን:: ከፊት ለፊት እያነፈነፉ ኩስ ኩስ የሚሉትን ሁለት ውሾቹን እየተ መለከትሁ መሬቱን በኃይል ላለመርገጥ እንደ ፍየል ጢብ ጢብ እያልኩ እራመዳለሁ::ሴርቫል መቶ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ከኔ በስተቀኝ ያለውን አልፋ አልፋ የሚባል ዕፅዋት የበቀለበትን መስክ ያስሣል:: ከፊቴ የተገሸረውን ቁጥቋጦ አለፍ እንዳልኩ አንድ የፈራረሰ የገጠር ቤት አየሁ::

ምናቤ በድንገት ባለፉት ጊዜያት ላይ አተኰረ:: ያንን ቤት በ1869 ባየሁበት ጊዜ የነበረበት ሁኔታ ትዝ አለኝ:: ንፁህ፣ በወይን ተክል የተሸፈነ፣ በግቢው ዶሮ ዎች የሚርመሰመሱበት ነበር:: አሁን ግን አፅሙ ብቻ ቀርቷል:: አዘንኩ:: ከሞተ ቤት ይበልጥ የሚያሳዝን ምን ነገር አለ?

አዕምሮየ በሣሣብ የኋሊት ከማፈግፈግ አልገታም በማለቱ ብዙ ያለፉ ሁኔታዎች በሰልፍ መግተልተል ጀመሩ::አንድ ቀን በጣም ደክሞኝ በዚያ አካባቢ ሣልፍ ወደቤቱ ጉራ ብዬ ያደረግሁት ዕረፍትና እንዲት ሴት የወይን ጠጅ በብርጭቆ ሞልተው የጋበዙኝ ሁሉ ትዝ አለኝ::አባወራው ያለ ፈቃድ የሚያድን ሽማግሌ ነበር::

በዚሁ ጦስ ከፖሊሶች ጋር በተፈጠረው ፍልሚያ ተገደለ:: ልጅየውም ረጅምና ቀጭን ሲሆን እንዳባቱ ኃይለኛ አዳኝ እንደሚወጣው ያስታውቅ ነበር:: እኔም በዚያን ጊዜ እንዳየሁት ትውስ ይለኛል:: ያካባቢው

ነዋሪዎች «ያልሰለጠን» እያሉ ነበር ቤተሰቡን የሚጠሩት።

ይህ ግን ስማቸው ይሁን የቅፅል ስማቸው በውል አላውቅም።

ከኔ ማዶ በጥንቃቄ ጉብጥ ጉብጥ የሚለውን ሲርቫልን ጠራሁት። በረጅም ርምጃው ቀልጠም ቀልጠም እያለ መጣ። «እዚህ ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ምን አጋጠማቸው?» ስል ጠየቅሁት።

የሚከተለውን ታሪክ ነገረኝ።

«ጦርነቱ እንደተጀመረ የሠላሣ ሦስት ዓመት ዕድሜ የነበረው ልጃቸው በፈቃደኝነት ተመዝግቦ ከሠራዊቱ ጋር ወደጦር ግንባር ዘመተ። በርግጥ እናቱ ብዙ ገንዘብ ስለነበራቸው በልጁ መሄድ እምብዛም ያዘነላቸው አልነበረም።

«አሮጊቷ ከመንደሩ ርቆ በሚገኘውና ጫካው ጠርዝ ላይ በተሠራው በዚህ ገለልተኛ ቤት ውስጥ ለብቻቸው መኖር ጀመሩ። መቼም ፍርሃት የሚባል ያውቃቸዋል ማለት ዘበት ነው። እርሳቸውም ልክ የባላቸውና የልጃቸው ዓይነት ነበሩ- ጠንካራ፣ ረጅም፣ ቀጭን አሮጊት። ሲስቁ አይቻቸዋለሁ የሚል ሰው ለአሣር ነው። ቀልድ ይሉ ነገር በጭራሽ አያውቁም። ሁልጊዜ ኩስታራ። በርግጥ የገጠር ሴቶች ሣቅ እንደ ማያበዙ የታወቀ ነው። ባይሆን ወንዶቹ ናቸው እንጂ ሴቶቹ ሣቃቸው የተቆጠበ ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያት አለው። የገጠር ሴቶች ህይወት ለውጥ የሌለውና አሰልቺ ስለሆነ ነፍሳቸው ዘወትር በሐዘን ቀጭማ የምትኖር ናት። ገበሬው ግን ለየት ይላል። አልፎ

አልፎም ቢሆን ወደ መንደርና ከተማ ወጣ ስለሚል በጥቂቱም ቢሆን ከየመሸታ ቤቱ ፈንጠዝያና ውካታ ተምሮ ይመለሣል። ሚስቱ ግን ዘላለሚን እንደጨፈገ ጋት ከመኖር ሌላ ፈገግታ ብዙም አይታይባትም። የፊቷ ጡንቻዎች የሣቅን እንቅስቃሴ ሳያውቁ በመጨረሻም በዚያው ክርረው ደርቀው ይቀራሉ።

«ታዲያ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩልህ እኒያ ብርቱ ሴት የተለመደ ኑሮዋቸውን በብቸኝነት መግፋት ቀጠሉ። ወዲያው ክረምቱ ገባና ቤቱም በበረዶ ተሸፈነ። በማምንት አንድ ቀን ዳቦና ሥጋ ለመግዛት ወደ መንደሯ ብቅ ይላሉ። ሸመታቸውን ሲጨርሱ ወደ ሌላ ወለም ዘለም የለም። በቀጥታ ወደቤታቸው ነው። በአካባቢው ጫካ ውስጥ የሚኖሩ ተኩላዎች በሰው ላይ አደጋ እንደማያደርሱ ስለሚታወቅ ምንም ቢሆን ባዶ እጃቸውን አይወጡም። እጅ ስለበዛበት የሰደፉ እን ጨቴት ማለቅ የጀመረውን የልጃቸውን ዝነት የከጀለው አሮጌ ጠመንጃ በትከሻቸው ያንግታሉ። ማንም ዓይኑን አሣርፎበት የማያውቀው ነጭ ፀጉራቸው ከተጠፈረ በት ጥቁር ሻሽ በላይ የጠመንጃቸው አፈሙዝ ተቀ ስሮ እየታየ በጥቂቱ ጉብጥ ብለው እርምጃቸውን በረ ጅሙ ጣል ጣል እያደረጉ በበረዶው ላይ በርጋታ ሲጓዙ ለሚያያቸው የሚያስገርሙ ትርዒት ነበሩ።

«አንድ ቀን የጀርመን ወታደሮች ወደ አካባቢው ደረሱ። ሀብትና የኑሮ ሁኔታ እየታየ በየነዋሪው ቤት እንዲቀመጡ ተደላደሉ። አሮጊቷ ደህና ገንዘብ ስለነበ ራቸው አራት ወታደሮች ተሰጧቸው።

«አራቱም ግዙፍና ልጅግር ነበሩ። ቆዳቸው በጣም ነጭ ሲሆን ሁሉም ሪዛቸውን በጣም አሳድገውት ነበር። የዓይኖቻቸው ቀለም ሰማያዊ ነው። የሰውነታ

ቸው ደልዳላነት ሲታይ በጠርንትና በአገልግሎት ላይ የከረሙ አይመስሉም። ጠባያቸውም ቢሆን የድል አድራጊ ወታደር አልነበረም። አራቱ ወጣቶች ከአርጊቷ ጋር መኖር ከጀመሩበት ቀን አንስቶ ከልብ ይጨነቁላቸውና ያስቡላቸው ጀመር። ድካምና ወጨ እንዳይበዛባቸው የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ሚት ሚት አራቱም ይነሱና ሲጥ በሚመስለው የሰሚንኛ ነጭ ገላቸው ላይ ውኃ እያፈናጠቁ የተለያዩ ልብሶችን ያጥባሉ። ሲትየዋ ምግባቸውን ለማበሳሰል ወዲያ ወዲህ ይላሉ። ከቁርስ በኋላ ወጣቶቹ ማዕድቤቱን የማዕዳት፣ የቤቱን ወለል የመወልወልና ሌሎችን ሥራዎች ተከፋፍለው ያከናውናሉ። ሁኔታቸው ሁሉ እናታቸውን በሥራ ማገዝ ከሚያስደስታቸው አራት ጥሩ ልጆች ጋር የሚመሳሰል ነበር።

«አርጊቷ ግን ዘወትር የሚያስቡት ስለራሳቸው ልጅ ብቻ ነው። ቀጭን፣ ቀውላላ ልጃቸው። እንደ ሚንጠ የተቀለመመ አፍንጫው፣ ቡናማ ዓይኖቹ፣ በላይኛው ከንፈሩ ዙሪያ የተቸመቸመው ፂሙ ሁልጊዜ ፊታቸው ድቅን ይልባቸዋል። በየዕለቱ አራቱ ወታደሮች እሣት ለመሞቅ ምድጃውን ከበው ሲቀመጡ «ሃያ ሦስተኛው የፈረንሣይ እግረኛ ጦር ወዴት እንዳመራ የሰማችሁት ነገር ይኖራል? የኔ ልጅ ምድቡ እዚያ ውስጥ ነው» በማለት ይጠይቃሉ።

«ኧረ የለም። ምንም የሰማነው ነገር የለም» በማለት ይመልሱላቸዋል።

«እናም የአርጊቷን ሐዘንና ጭንቀት ከልብ በማጤን እናቶቻቸውን አገራቸው ትተው የመጡት አራቱ ወታደሮች የተቻላቸውን ያህል ሊንከባከቧቸው ይሞክ

ራሱ።ሲትየዋም ለወጣቶቹ ያላቸው የመውደድ ስሜት ከቀን ወደቀን እየጨመረ ሄደ።

«ያካባቢውም ነዋሪ ስለአራቱ ጀርመናውያን አስተያየት ሲሰነዝሩ 'እነዚያ አራቱ ያስጥርጥር በደንብ ተመችቷቸዋል' ይሉ ነበር።

«አንድ ቀን አሮጊቷ ብቻቸውን ተቀምጠው ሣለ አንድ ሰው በበረዶ የተሸፈነውን መስክ እያቋረጠ ወደ ቤታቸው ሲያመራ ከሩቅ ይመለከቱታል።ማንነቱን ለመለየት ብዙም ጊዜ አልወሰደባቸውም። የመንደሩ ፖስተኛ መሆኑን አወቁ። አጠገባቸው እንደደረሰ አንድ የታጠፈ ወረቀት አቀበላቸው። ልብስ በሚሰፉ ጊዜ የሚጠቀሙበትን መነፅር ከማህደሩ አወጡና በጥሞና ማንበብ ጀመሩ። ደብዳቤው እንዲህ የሚል ነበር፤

*እሜቴ፣ ይህ ወረቀት ይዞልዎት የመጣው ዜና እጅግ እንደሚያሳዝንዎት አውቃለሁ። ልጅዎ ቮልተር በትናንትናው ዕለት በመድፍ ጥይት ተመትቶ ሞቷል። አካሉ ለሁለት ተቆርጦ ነበር። በወቅቱ አጠገቡ ስለ ነበርኩ ማናቸውንም ሁኔታ በሚገባ ለመመልከትና መሞቱንም ለማረጋገጥ ችያለሁ። የልጅዎና የኔ ምድብ ከመጀመሪያው አንስቶ በአንድ ጓድ ውስጥ በመሆኑ የሚደርስበትን ነገር ሁሉ ለርስዎ እንዳሳውቅለት አደራ ብሎኝ ስለነበር እነሆ ይህንን ደብዳቤ ለድጄል ዎታለሁ።*

*ሰዓቱን ከኪሱ አውጥቼ እኔ ዘንድ ያስቀመጥኩት ስለሆነ ጦርነቱ ሲያበቃ አምጥቼ አስረክብዎታለሁ።*

*ከሠላምታ ጋር*
*ሲዛር ሪቮ*
*በ23ኛው እግረኛ ጦር ተራ ወታደር*



ደብዳቤው ከሦስት ሣምንታት በፊት የተፃፈ ነበር።

«እናትየዋ አላለቀሱም።ብቻ በቆሙበት እንደ ምሰሶ ደርቀው ቀሩ፤ሀጥ እንዳሉ። ድንጋጤያቸው በማየሉና መላ አካላቸው በመደንዘዙ ሃዘን ሊሰማቸው አልቻለም። 'ቪክቶር የተገደለው በፈቃዱ ሄዶ ነው፣' አሉ በሃሳባቸው። ከዚያ ቀስ በቀስ ዕንባ በዓይኖቻቸው

ግኖም አሉ። ልባቸው በሐዘን ጉርና ተንቀሳቀሰ። የተለያዩ ሃሳቦች በየተራ ብቅ እያሉ ይጎነታትሏቸው ጀመር። ልብን የሚያሸብሩና መንፈስን የሚያስቃዩ ሃሳቦች። ልጃቸውን፣ ትልቁን ልጃቸውን ከዚያ ቀን በኋላ እንደ ወትሮው ሊሰሙት አይችሉም። በቃ! ፖሊሶች አባትየውን ገደሏቸው። ጀርመኖች ደግሞ ልጅየውን ቀጠፉት። በመድፍ ጥይት እንደዳቦ ቆረሱት።አስፈሪው ድርጊት ሲፈፀም የታያቸው መስላቸው። የልጃቸው ጭንቅላት ተቀንጥሶ ሲወድቅ፣ የተበለጠጡ ዓይኖቹ አንድ ነጥብ ላይ አፍጥጠው፣ ዘወትር ሲናደድና ሲቆጣ እንደሚያደርገው ችምችም ያለውን የሪዙን ጫፎች በጥርሱ ሲያኝክ ሁሉም ወለል ብሎ ታያቸው።

«ግን ከሞተ በኋላ አስከሬኑን ምን አድርገውት ይሆን? ፖሊሶቹ ባላቸውን ከገደሏቸው በኋላ ጥይቷ ግንባራቸው መሐል እንደተሰነቀረች አስከሬኑን እንደ ላኩላቸው ሁሉ የልጃቸውንም ሬሣ ቢልኩላቸው ምን ነበረበት!

«ድንገት የሰዎች ድምፅ ሰሙና ሃሳባቸው ተቋረጠ። ጀርመናውያኑ ወታደሮች ከመንደሯ መመለሳቸው ነበር። ደብዳቤውን በፍጥነት ቀሚሣቸው ኪስ ውስጥ ከተቱና ዕንባቸውን ከዓይኖቻቸው ላይ ከአባበሱ በኋላ በተረጋጋ መንፈስ ሠላምታ አቅርበው ተቀበሏቸው። ልክ እንደወትሮው።

«አራቱም ወጣቶች ደስ ብሏቸው ይሣሣቁ ነበር። አንድ ደህና ጥንቸል ይዘዋል። ምናልባት ከአንዱ ጋ የሰረቁት ሊሆን ይችላል። ጥሩ ምግብ እንደሚያበሏቸው ለአሮጊቷ በምልክት ገለፁላቸው።

«እናት ወደዚያው ምግባቸውን ለማዘጋጀት ተና ተና ማለት ጀመሩ። ጥንቸሉን መግደል ግን አቃታቸው። መቼም የመጀመሪያቸው እንደማይሆን ቢታወቅም ያን ዕለት ግን እምቢ አላቸው። ከወታደሮቹ አንደኛው ጆሮግንዱ ላይ በቡጢ ሲመታው ትንሹ አውሬ ጭጭ አለ።

«ቆዳውን ከቀዩ ሥጋ ላይ መግፈፉ ግን አላወካቸውም። ሆኖም የሚንካከት ደም፣ እጃቸው ላይ እየቀዘቀዘ የሚረጋው ትኩስ ደም እንዲንቀጠቀጡ አደረጋቸው። የጥንቸሉ ሥጋ እጆቻቸው ውስጥ እንደሚንቀጠቀጠው ሁሉ እሳቸውም ከእግር እስከ ራሳቸው ተንዘፈዘፉ።

«ምግቡ እንደደረሰ ከጀርመናውያኑ ጋር ማዕድ ቀረቡ። መብላት ግን አልሆነላቸውም። አንዲት ጉርሻ እንኳን ሳይቀምሱ ወታደሮቹ ለብቻቸው አጠናቀቁት። በአሮጊቷ አለመብላት እምብዛም አልተጨነቁም። እርሳቸውም በፀጥታ ተቀምጠው ወጣቶቹን ሰረቅ እያደረጉ ያስተውሏቸዋል። አዕምሮዋቸው ሃሣብ ይገምዳል። በገፃቸው ላይ ምንም የሚነበብ ስሜት ባለመታየቱ ወታደሮቹ ያስተዋሉት ነገር አልነበረም።

«ድንገት በፀጥታው መሃል 'እንግዲህ በአንድነት መኖር ከጀመርን ድፍን ወር ሊሆነን ነው። ግን እስከዛሬ ስማችሁን እንኳን አላወቅሁትም' አሉ አሮጊቷ።

«ወታደሮቹ የሴትዮዋን ፍላጎት ለመረዳት እምብዛም አልተቸገሩም።በየተራ ስማቸውን ተናገሩ።በቂ አልሆነም። በብጣሽ ወረቀት ላይ ስምና የየቤተሰቦቻቸውን አድራሻ እንዲጽፉላቸው አደረጉ። መነፅራቸውን አወጡና ትልቁ አፍንጫቸው ላይ በማስቀመጥ ወታደ

ሮቹ የሚጫጫሩትን ያልተለመደ ዓይነት ዕሉፍ በጥንቃቄና በትኩረት ተመለከቱት:: ሲበቃቸው አጣጠፉና ኪሳቸው ውስጥ አስቀመጡት - ከልጃቸው ደብዳቤ ጋር::

«ምግቡ እንደተገባደደ፣ 'አንዳንድ ነገር ላስነዳዳላችሁ መሄዴ ነው' ብለው ከገበታው ተነሱ::

«እናም የሣር ድርቆሽ እየተሸከሙ ሰዎቹ ወደ ማቲተኚበት ቆጥ ማጋዝ ጀመሩ::

«በሴትየዋ ያልተለመደ ዓይነት ሥራ ግራ የተጋቡት ወታደሮች ላቀረቡት ጥያቄ ቆጡን የበለጠ ሞቃት ለማድረግ አስበው መሆኑን ገለፁላቸው:: ይህኔ ልጆቹም ያግዟቸው ገቡ:: በደንብ የታሰሩትን የድርቆሽ ነዶዎች እስከጣሪያው ድረስ በመቆለል ግድግዳው ከከብት መና የተሰራ መልካም መዓዛ ያለው ሞቃት ክፍል ፈጠሩ-ሴሲቱን በመልካም እንቅልፍ ለማሣለፍ::

«ማታ ራት ሲቀርብ አሮጊቷ እህል የሚሉ ባለ መቅመሳቸው ከወታደሮቹ አንደኛው በጣም ተጨነቀ:: እርሳቸው ግን ሆዳቸውን እንዳመማቸውና ሻል ሲላቸው እንደሚበሉ ገለሁለት:: ገበታ ከፍ ካለ በኋላ በደንብ እንዲሞቃቸው በማለት አሮጊቷ የምድጃውን እሣት በደንብ አያይዘው ቁጭ አሉ:: አራቱ ጀርመናውያንም ዘወትር ማታ ማታ እንደሚያደርጉት በመስላላቸው ወጥተው ቆባቸው ላይ ሠፈሩ::

«ወታደሮቹ ወደሚተኙበት ቆጥ የሚያስገባውን በር እንደቀረቀሩ አሮጊቷ መሰላሉን አነሱት:: ከዚያ በኋላ ዋናውን የቤቱን በር በፀጥታ ከፍተው ወጥተው ተጨማሪ የሣር ድርቆሽ እያጋዙ ኩሽናው ውስጥ መከመር ጀመሩ:: አሮጊቷ በበረዶው ላይ የሚራመ

ዱት ጫማቸውን አውልቀው፣ በባዶ እግራቸው ስለ ነበር ሰዎቹ እንዳችም ኮሽታ አልሰሙም:: ሲትየዋ ግን እንቅልፍ ድብን ያደረጋቸው አራት ወታደሮች ኩርፊያ አሁንም አሁንም ጉላ ብሎ ይሰማቸዋል::

«ዝግጅታቸው እንደሚፈልጉት መሟላቱን ሲያረጋግጡ አንድ የድርቆሽ ነዶ አንስተው ምድጃው ላይ ወረወሩት:: በእሣቱ እንደተያያዘ አውጥተው ክፍሉ ውስጥ በተቆለለው ድርቆሽ ላይ በተኑት:: የእሣት ላንቃ እዚያም እዚያም መንጣጣት ሲጀምር የሚከተለውን ለማስተዋል አሮጊቷ ወደ ውጭ ወጡ::

«ከጥቂት ሴኮንዶች በኋላ ቤቱ በብርሃን ተሞላ:: ወዲያው የሚያስፈራ ምድጃ ሆነ:: ወደ ትልቅ እቶን ነት ተለወጠ::የሚንተገተገው ነበልባል ብርሃን በትንሿ መስኮት በኩል እየሾለከ ምድሩ ላይ ከተጋገረው በረዶ ጋር በመላተም ያንፀባርቅ ጀመር:: የብርሃን ዘንጉች ወደየአቅጣጫው ተወጠሩ::

«ከቤቱ ጣሪያ አካባቢ ኃይለኛ ጩኸት ተሰማ:: ልብ የሚቀረድድ የፍርሃትና የሥቃይ ዋይታ በማከታተል ማስተጋባት ቀጠለ::ጥቂት ቆይቶ ወታደሮቹ የተኙበት ቆጥ በር ተገርስሶ ሲወድቅ እንደ አውሎንፋስ የሚጥመለመል እሣት ቆጡን በአንዲት ቅፅበት ላስ አድርጎ ጣሪያውን በመበርቀስ ወደ ሰማይ መምዘግዘግ ጀመረ:: ከዚያ በኋላ ቤቱ ፍፁም ደመራ ሆነ::

«ከውስጥ በኩል የሚሰማ ድምፅ አልነበረም:: ከነበልባሉ መንጣጣት፣ ከግድግዳዎቹ መገርሰስና መፈረካከስ፣ ከጣሪያው ወራጅ እንጨቶች መሰባበር በስተቀር:: ድንገት ጣሪያው እንዳለ ተደረመሰና ወለሉ ላይ

ተዘረገፈ፡፡የሚግፈጠፈጥ ጢስና የትንታግ ፏፏቴ ከቤቱ ቅሪት ላይ ቱግ ብሎ ተነሣ፡፡

«በረዶ ለብሶ ዙሪያውን የተኮፈሰው ገጠር በነበ ልባሉ ወጋገን በርቶ ሲታይ ቀይ ቀለም በስሱ የተነ ከረ ሸማ ይመስላል፡፡

«ከሩቅ የደወል ድምፅ መሰማት ጀመረ፡፡

«አሮጊቷ ተቃጥሎ በማለቅ ላይ ባለው ቤታቸው ትይዩ ቆመዋል፡፡ ከሰዎቹ አንዳቸውም አምልጠው እን ዳይወጡ ለመከላከል የልጃቸውን አሮጌ ጠብመንጃ አጥ ብቀው ይዘዋል፡፡

«ሁሉም ነገር ባሰቡት ሁኔታ መፈፀሙን ሲያረጋ ግጡ ጠብመንጃውን ወደ እሣቱ ወረወሩት፡፡ ፍንዳታ ተከታትሎ ተሰማ፡፡

«ሰዎች ከየአቅጣጫው እየገሰገሱ መምጣት ጀመሩ፡፡ ገበሬዎችና የጀርመን ወታደሮች፡፡

«በፈፀሙት ተግባር የረኩት አዛውንት በወደቀ የዛፍ ግንድ ላይ በፀጥታና በርጋታ ተቀምጠው አገኟ ቸው፡፡

«ፈረንሣይኛ ልክ እንደ ፈረንሣዊ የሚናገር አንድ የጀርመን መኰንን፣ 'ወታደሮችሽ የታሉ?' ሲል ጠየቃ ቸው፡፡

«ቀጭን እጃቸውን በመሞት ላይ ወዳለው ቀይ የፍም ክምር ዘረጉና 'እዚያ ውስጥ ናቸው' ሲሉ መለ ሱለት- ጐልቶ በሚሰማ ድምፅ፡፡

«ከበቡዋቸው። 'ለመሆኑ እሣቱ እንዴት ሊነሣ ቻለ?' አለ ጀርመናዊው።

«'እኔ ነኝ' አለ አዛውንቷ።

«የተሰበሰቡት ሁሉ አላመኗቸውም። የሁሉም ግምት የእሣቱ አደጋ አሣብዷቸዋል የሚል ነበር። አሮጊቷ ግን በዙሪያቸው ለተገጠገጡት ሰዎች ጠቅላላ ታሪኩን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ነገሯቸው። የል ጃቸውን መርዶ ከያዘው ደብዳቤ መምጣት አንስቶ ከቤቱ ጋር የጋዩት አራት ሰዎች እስካሰሙት የመጨ ረሻ ጩኸት ድረስ ስለነበረው ሁኔታ ልቅም አድርገው አወጉቸው። ስለተሰማቸው ስሜትም ሆነ ስለፈፀሙት ድርጊት ያስቀሩት ቅንጣት ጉዳይ አልነበረም፤ ሁሉም ተዘረዘረ።

«ታሪኩ ተነግሮ ሲያበቃ ከቀሚሣቸው ኪስ ሁለት ብጣሽ ወረቀቶች አወጡ። ለመለየት እንዲረዳቸው መነፅራቸውን አውጥተው ዓይኖቻቸው ላይ ጣል አደ ረጉት። አንደኛውን ወረቀት አነሡና ዙሪያቸውን ለተ ኰለኰሉት ሰዎች እያሳዩ' ይኸኛው የቪክቶር ሞት ነው' አሉ።

«ቀጥሉ ደግሞ ሁለተኛውን ወረቀት ከፍ አድር ገው እያሳዩና ራሳቸውን ወደ እሣቱ አቅጣጫ እየነቀ ነቁ' ይህ ደግሞ የነርሱን ስሞች የያዘ ነው። ለቤተሰቦ ቻቸው ለመፃፍ እንድትችሉ ታስቦ የተዘጋጀ፣' አሉ።

«ረጋ ባለ ሁኔታ እጃቸውን ዘረጉና ትከሻቸውን ለቆመው ጀርመናዊ መኰንን ወረቀቱን ሰጡት። 'ስለተ ፈፀመው ድርጊት የሚገልፅ ደብዳቤ ለዘመዶቻቸው

መፃፍ አለብህ። ሁሉንም የፈፀምኩት እኔ መሆኔንም ግለፅላቸው። እኔ ቪክቶሪያ ሲሞን፣ ያልሠለጠንኩት ሴት! መሆኔን ፃፍላቸው። አደራ እንዳትረሣ።

«መኮንኑ በጀርመንኛ ቋንቋ አንዳች ትዕዛዝ ሰጠ። አሮጊቷ ከመቅዐበት ተያዙና ከቃጠሎ የተረፈውን የቤታቸውን ትኩስ ግድግዳ ተደግፈው እንዲቆሙ ተደረገ።



ወዲያው አሥራ ሁለት ወታደሮች ሃያ ሜትር ያህል
ራቅ ብለው ከፊት ለፊታቸው ተደረደሩ፡፡ አባቴው ግን
ፍንክች አላሉም፡፡ ነገሩ ምን እንደሆነ ገብቷቸዋል፡፡
በፀጥታ ቆመው የሚከተለውን መጠባበቅ ጀመሩ፡፡

«መኮንኑ አጠር ያለች ትዕዛዝ አሰማ፡፡ የእሩ
ምታ ተኩስ አስተጋባ፡፡እንዲት ነጠላ ተኩስ መጨረሻ
ላይ ለብቻዋ ለጠቀች፡፡

«እርግጥ በቁመታቸው ሙሉ አልወደቁም፡፡ሁለት
ቁንጃቸው የተቆረጠ ይመስል መሬቱ ላይ ዘፍ አሉ፡፡

«ጆርመናዊው መኮንን ወደርሣቸው ቀረበ፡፡ አካላ
ቸው ሁለት ቦታ ላይ ተቆርጧል፡፡ በአንደኛው እጃ
ቸው የልጃቸውን ደብዳቤ ጭምድድ አድርገው ይዘዋ
ታል፡፡ በደም ተለውሣለች፡፡»

ወዳጄ ሲርቫል ጨዋታውን ሲደመድም፣ «ጆርመ
ናቹ የወታደሮቻቸውን ደም የተበቀሉ መስሏቸው የኔ
ንም ህንፃ አቃጠሉት፣» አለና በዝምታ ተዋጠ፡፡

እኔ ግን በዚያ ቅፅበት የማስበው ስለነዚያ አዕሙ
ብቻ ተገትሮ በቀረው በዚያ የገጠር ቤት ውስጥ የዶግ
አመድ ስለሆኑት አራት ጨዋ ወጣቶች እናቶችና ግድ
ግዳውን ተደግፈው ስለተረሸኑት ሊላዋ እናት ጀግንነት
ነበር፡፡

ከዚህ ሃሣቢም ሳልመለስ ወደ መሬት ጉንበስ ብዬ
እንዲት ድንጋይ እንደዘበት አነሣሁ፡፡ በእሣቱ ተለብልባ
የጠቆረች ድንጋይ ነበረች፡፡

# አባጠራው

ሚኻኤል ሾሎኾቭ

ፀሐይዋ፣ አረንጓዴ ቀለሙ እየለቀቀ ግራጫ መምሰል በጀመረ ደስ የማያሰኝ ጫካ ውስጥ ተወሽቃለች። ወደ ዶን ወንዝ የሚዳፋውን ቁልቁለት ይዤ እንደረደራለሁ። እግሮቼ ከሚያርፉበት ርጥብ አሸዋ የሚተነው ጠረን፣ ውሃ ቋጥሮ መበስበስ ከጀመረ ግንድ ከሚወጣው ሽታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ቀጭኗ የእግር መንገድ በጫካው መሐል እየተሹለከለከች ትጠማዘዛለች። ፀሐይዋ ቀለሟን ወደ ሐምራዊ ለውጣ የመቃብሩን ስፍራ እየታከከች በጀርባው ስታዘቀዝቅ የምሽቱ ጥላዎች ከበስተኋላዩ መጠረቃቀም ጀመሩ።

ወንዙን ለመሻገር የምታገለግለው ጀልባ በፀጥታ ወደሚርመሰመሰው ውሃ ገባ ብሎ ከተሰራው ጉርድ ድልድይ ጋር በገመድ ተቆራኝታ ቆማለች። ውሃው ከግርጌዋ ሲወዛወዝ የመንቦራጨቅ ድምፅ ይሰጣል። በቀዳዳዎቻቸው ውስጥ ያሉትን መቅዘፊያዎቿን ደግሞ ወደላይ ወደታች፣ ወደፊት ወደኋላ እየናጠ ያጫውታቸዋል።

---

ሚኻኤል አሌክሣንድሮቪች ሾሎኾቭ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን የዓለም ታላላቅ ደራሲያን መካከል የሚመደብ የሶቪዬት ደራሲ ነው። የሰፊ የሥነ ጽሑፍ አዝመራ ባለቤት የሆነው ሾሎኾቭ በ1965 በሥነ ጽሑፍ የኖቤልን ሽልማት ያገኘ ሲሆን፣ ለዚህ ማዕረግ ካበቁት ሥራዎቹ መካከል «ኢንድ ኩዋየት ፍሊውስ ዘ ዶን» የተሰኘው ረጅም ልቦለድና «የአንድ ሰው ዕጣ» በሚል ርዕስ የሚታወቀው ኖቬላ ዋነኞቹ ናቸው። ሾሎኾቭ በ1905 ተወልዶ በ19 ? አረፈ።

የጀልባዋ ባለቤት በውስጧ የተጠራቀመውን ውሃ በባልዲ እየደነበቁ ወደወንዙ በማፍሰስ ሥራ ተጠምደዋል፡፡ አጠገባቸው ስደርስ ቀና አሉና ወደ ቢጫ በሚያደሉ ትንንሽ ዓይኖቻቸው ካስተዋሉኝ በኋላ «ለመሻገር ትፈልጋለህ መሰለኝ? አሁን እንነሳለን! በል ገመዱን ፍታ!»በማለት ጮኹ - በሻካራ ድምፅ፡፡

«ሁለታችን ብቻ ቀዘፋን የምንዘልቀው ይመስልዎታል?»

«የግድ ነዋ! ቀኑ እየመሸ ስለሆነ ከአሁን በኋላ የሚመጣ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡»

ሱሪያቸውን ወደላይ እየጠቀለሉ ለሁለተኛ ጊዜ ደህና አድርገው ተመለከቱኝ፡፡ «የዚህ አካባቢ ሰው አይደለህም. . . ጌታ ከወዴት ነው ዱብ ያረገህ ጃል?» ሲሉ ጠየቁኝ፡፡

«ሠራዊቱ ውስጥ ቆይቼ ወደ አገሬ መመለሴ ነው፡፡»

ባለጀልባው ኮፍያቸውን አውልቀው ብርማ ፀጉራቸውን በራሳቸው ንቅናቄ ወደ ኋላ መታ አደረጉና ከዓይናቸው ጥቅሻ ጋር መፈራረስ የጀመሩትን የበሰበሱ ጥርሶቻቸውን አሣዩኝ፡፡

«በፈቃድ ወይስ እንዲያው መሾለክህ ነው?»

«የለም፣ እንደያየን ተሰናብቼ ነው፡፡»

«እንግዲያስ ምንም የሚያሳስብህ ነገር የለም፡፡»

አንዳንድ መቅዘፊያ ያዝንና ጉዞ ጀመርን:: ዶን እያጫወተ በወዲያኛው ማዶ ዳርቻ ላይ ወደ ተኰ ፈሰው ጫካ ይዞን ነጐደ:: የወንዙ አነስተኛ ማዕበል በዕድሜ ብዛት ከከረከሰው የጀልባዋ ሆድና ደረት ጋር ይላተማል::ሰማያዊ የደም ስሮች ባፈጠጡባቸው የጀል ባዋ ባለቤት እግሮች ላይ ሰንበርማ ጡንቻቸው ተወጣ ጠሩ:: ቀለማቸው ሰማያዊ መሆን የጀመረው የውስጥ እግሮቻቸው የጀልባዋን የሚያድጥ ወለል ጨምድደው ረግጠዋል:: እጆቻቸው ረዣዥሞች ናቸው:: ከቆዳ በስተ ቀር ሥጋ የሚባል በላያቸው ያለ አይመስልም:: በመ ዳፎቻቸው አይብ ሉባ ላይ ያጉጠጉጡትን የጣት አጥ ንቶች የሸፈነው ቆዳ በአያሌ ዓመታት የከባድ ሥራ ጦስ ገብሯል:: ቁመታቸው ረጅም ሆኖ ትከሻቸው ግን ጠበብ ይላል:: ከወገባቸው ጉበጥ ብለው ሲቀዝፉ አያ ምርባቸውም:: ሆኖም መቅዘፊያው ሲታዘዛቸውና ጠልቆ እየገባ ውሃውን ሲገምሰው ለጉድ ነው::

ትንፋሻቸው ያለመቆራረጥ ሲውዘገዘግ ይሰማ ኛል:: ከለበሱት ሰደርያ መሳይ የሱፍ ሹራብ የሚወ ጣው ጠረን የላብና የትምባሆ ቅልቅል ነው:: ጥቂት እንደተጓዝን ወደኔ ዞር አሉና፣

«ጫካው መሃል ሊወሽቀን ነው መሰለኝ:: በርግጥ ደግ አይደለም:: ቢሆንም ምንም ማድረግ አንችልም ልጄ!» አሉ::

ወንዙ መሃል ላይ ያለው የውሃው አወራረድ ኃይል ዳርቻው ላይ ካለው ይበልጣል:: ጀልባችን ጋደድ - ዘንበል ብላ አቅጣጫዋን በመለወጧ ውሃውን ተከትለን መንሳፈፍ ጀመርን::

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ወገቡ ድረስ በውሃ ወደ ተዋጠ የቁጢማ ጫካ ተገፍተን ገባን:: ሁሉም መቅዘ

ፊያዎች በመሰበራቸው ዱሽቻቸው ብቻ በየቀዳዳዎቹ እንደተሰነቀሩ ቀርተዋል:: ጀልባው ጉን ላይ በተበረቀ ሰው ቀዳዳ በኩል ውሃ መግባት ሲጀምር እኛም ሌሊቱን ለማሳለፍ ዳርቻው ላይ ወደሚገኙት ዛፎች አመራን:: የጀልባዋ ባለቤት የዛፍ ቅርንጫፎች ዘነጣጥፈው መሬቱ ላይ ጉዝጉዙና አጠገቤ ተቀመጡ:: ከሸክላ የተሰራ ፒፓቸውን አውጥተው ትምባሆዋቸውን እየማገጡሱን ቡልቅ ያደርጉት ጀመር::ብዙም ሳይቆይ በአናታችን ያረበበውን ጨለማ እየሰነጠቁ የማያልፉት ዝይዎች በሚያራግቡዋቸው አክናፋት ከሚፈጠረው ድምፅ ልቆ ጉልህ ንግግራቸው መሰማት ጀመረ::

«እንግዲህ ወደቤትህ ነዋ፣ ወደዘመዶችህ...መቼም እናትህ ክፉኛ እንደናፈቁህ እገምታለሁ:: በስተርጅና ከልጃቸው ጋር ለመሆን መብቃት ለርሳቸው እንዴት ያለ ትልቅ መጽናኛ መሰለህ! አንተ ግን ይህንን አታውቀውም:: እናትህ የአንተን ዓይን ለማየት ቀን ቀን ስንቱን ታቦት ሲማጠኑ እንደሚውሉ፣ ሌሊቱን ደግሞ ምን ያህል ዕንባ ሲያዘንቡ እንደሚያድሩ አታውቀውም:: ልጆች ስትባሉ ሁላችሁም አንድ ናችሁ:: እናንተም በተራችሁ ባለልጅ እስክትሆኑ ድረስ ለቤተሰቦቻችሁ ስቃይና ጭንቀት ቁብ ይኖራችኋል ማለት ዘበት ነው:: ግን ወላጆች ለፍሬዎቻቸው ሲሉ የቱን ያህል ፍዳ እንደሚቆጥሩ፣ ስንቱን ችለው እንደሚኖሩ ትንሽ እንኳ ብታውቁላቸው ምንኛ ደግ በሆነ ነበር::

«አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሴቶች ዓሣ ሲበልቱ ድንገት የሃሞት ከረጢቱን ያፈርጡትና የሚዘጋጅልህ ሾርባ ሬት ሆኖ ይቀርባል:: የኔም ነገር እንደዚሁ ነው ልጄ:: ረጅም ዘመን በሕይወት ለመኖር ብታደልም ሕይወት ለኔ ምሬት እንጂ ሌላ ልትሆን አልቻለችም:: በርግጥ ዛሬም አለሁ::ሁሉንም ችየው እየኖርኩ ነው::

ሆኖም አልፎ አልፎ ሲበዛብኝ ትዕግስቱ ሁሉ ይሟጠ ጥና፣ 'ስሚኝ እስቲ ህይወት፣ ለመሆኑ መቼ ነው ማክ ተማያሽ?. . .' ለማለት እገደዳለሁ።

«አንተ ያካባቢያችን ሰው አይደለህም። እንግዳ ነህ። ስለዚህ የምነግርህን በደንብ አስብበት፣ አብላላ ውና በአንገቱ ዙሪያ ማበት የሚገባኝ ገመድ ምን መሣይ መሆን እንዳለበት ጠቁመኝ።

«አንዲት ልጅ አለችኝ፣ በመጪው ፀደይ አስራ ሰባት ዓመት ይሞላታል። እና ሥርከለት ምን እንደ ምትለኝ ታውቃለህ? 'አባባ፣ ካንተ ጋር በአንድ ማዕድ መቅረብ በጣም ነው የሚያስጠላኝ። በተለይ እጆችህን ሳስተውላቸው ወንድሞቼን መግደላቸው ትዝ ይለኝና ሊያስመልሰኝም ይቃጣዋል። ...'

«ግን ልጄ ያልገባት አንድ ቁምነገር አለ። ያሁሉ የጉድ ተግባር ለማን ተብሎ እንደተፈፀመ በጭራሽ ሊገባት አልቻለም። ግን ሁሉም ነገር የተደረገው ለነ ርሱ ነበር። ለርሷና ለሌሎቹ ህፃናት!

«አየህ ገና በወጣትነቴ ትዳር መሥረትሁ። ሚስቴ ሽለሙቅ ነበረችና ኩስማና ቢሆንም ስምንት ህፃናት በተከታታይ አስታቀፈችኝ። ዘጠነኛው ላይ ግን ነገር ተበላሸ። ዕንስት ደህና ከተገላገለች በኋላ ትኩሣት ጠና ባትና በአምስተኛው ቀን ይሂት ጥርግ አለ። እኔም ማቲዎቼን ታቅፌ ረግረግ መሃል እንደተጉለተ ጉቶ ብቻየን ቀረሁ። እግዜሩም ታልመሰለው ዳተኛ አይደል፣ ምን ብለምነው፣ ብወተውተው አንዳቸውን እንኳ በጨቅላነታቸው አልወሰደ ብሎ ሁሉም አደጉ። ታላቅየው ኢቫን ተባለ። ሀገሩ ቁርጥ እንደኔው ጥቁር ሐር ሲመስል፣ሲያዩት የደስ ደስ ያለው ሥራ ወዳድ

ነበር:: ብቻ ምናለፋህ፣ የወጣለት ኮዛክ[1] ነበር - በደፈናው:: ሌላው ልጄ የኢቫን የአራት ዓመት ታናሽ ልክ እናቱን መስሎ ወጣ:: ወፍራም ኩርምባዋ ቁመናው፣ ቡናማ ፀጉሩና ዓይኖቹ ዛሬም ወለል ብለው ይታዩኛል:: ከሌሎች ልጆቼ ሁሉ አብልጬ የምወደው እና ለልቤ ደስታን የሚያጎናፅፈው እሱ ነበር:: ዳኒላ አልነው ስም ስናወጣለት . . . ሌሎቹ ሰባቱ ግን ገና ትንንሽ ነበሩ:: ራስ በራስ የተወለዱ ወንድና ሴቶች::

ኢቫን ለአቅመ አዳም ሲደርስ ከመንደራችን ኮረዶች አንዷን መርጬ አጋባሁት:: ወዲያው ባለ ልጅ ሆኖ ቁጭ አለ:: ተረኛው ዳኒላ በመሆኑ የምትስማማውን ውሃ አጣጭ እያፈላለግሁት ሳለ የችግሩ ዘመን ከች አለ:: በኛ ክልል፣ ከተማ ውስጥ አዲስ የተመሰረተውን የሶቪየት ሥልጣን የሚቃወም እንቅስቃሴ በይፋ ተጀመረ:: በማግስቱ ኢቫን ሲበር መጣና 'አባየ፣ ይሄንን ቦታ ጥለን እንሂድ' አለኝ:: 'እንሂድና ከቀዮቹ ጋር እንቀላቀል:: እባክህ አባዬ በምታምነው ታቦት ልለምንህ! ትክክለኛውና ለዕውነት የቆመው መንግሥት የቀዮቹ ነውና ከነርሱ ጐን እንሰለፍ!'

«የታናሽየውም ሃሣብ ተመሳሳይ ነበር::ጧት ማታ ለሁለት እየተፈራረቁ ይነዘንዙኝ ገቡ:: አላስቆም አላስቀምጥ ቢሉኝ አንድ ቀን ዕቅጬን ነገርኳቸው::

---

[1] ኮዛክ በሶቪየት ኅብረት በተለይ በሩሲያ ሪፑብሊክ በዶን ወንዝ ዙሪያ የሚኖሩ ከጥንታዊዎቹ የሩሲያ ብሔረሰቦች የአንዱ መጠሪያ ነው:: ኮዛኮች በሃይማኖት አጥባቂነታቸውና በተዋጊነታቸው የሚታወቁበት የበለፀገ ታሪክ አላቸው::

«'ልጆቼ፣ ሁለታችሁም የመሰላችሁን መንገድ ስመ ከተል ትችላላችሁ:: እኔ ይህንን አድርጉ፣ ያንን ተዉ ብዬ አላስገድዳችሁም:: በበኩሌ ግን ይቺን ተወልጄ ያደኩባትን፣ ወልጄ የከበድኩባትን፣ ተከብሬ የኖርኩባ ትን ቀዬ ጥዬ ወዴትም ውልፍት አልልም:: ከናንተ ሌላ ሰባት አፎች በማዕዱ ዙሪያ መኖራቸውን አት ርሱ፤ እያንዳንዱ አፍ ደግሞ በየዕለቱ ጉርሻ ማግኘት ይፈልጋል!' አልኳቸው::

«ከዚህ በኋላ ብዙም አልቆዩ መንደራችንን ለቀው ሄዱ:: በከተማችን ያሉት የተቃውሞው መሪዎች የቻ ሉትን ያህል ነፍጥ አሰባስቡና ከሌሎች የመንደሩ ነዋ ሪዎች ጋር ወደ ጦርነቱ እንድንዘምት እኔንም ጠየ ቁኝ::

«በመንደራችን አደባባይ በተደረገው ስብሰባ ላይ ችግሬን በትሕትና አስረዳሁ:: 'የተከበራችሁ ያገር ሽማ ግሌዎች' አልኩ:: 'ባለቤቴ በመሞቷ ወንድም ሴትም ሆኜ ልጆቻችንን የማሣድገው እኔ መሆኔ ከናንተ የተሰ ወረ አይደለም:: ገና ከጅብ አፍ ያልዳኑ ሰባት ህፃናት አሉኝ:: ምንአልባት በውጊያው ውስጥ ብሞት እነዚህን ምስኪኖች ማን ዞር ብሎ ያያቸዋል?'

«በዚህም በዚያ ብዬ ለማስረዳት ሞከርኩ:: ግን አልሆነም! በዚያን ሰዓት ማን ሰምቶ ልጁ! ስለዚህ ወደጦር ግንባር መሄድ የማይቀር ሆነ::

«ደግነቱ በዚያን ወቅት ጦርነቱ የሚካሄደው ከመ ንደራችን ብዙም ርቆ አልነበረም:: ታዲያ ከፋሲካ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ምን ይሆናል መሰለህ... ዘጠኝ ምርኮኞች ወደመንደራችን ያመጣሉ:: ዳኒላም- የዓይኔ ብሌን ዳኒላ- ከምርኮኞቹ አንዱ ነበር... በሰ

ልፍ ሆነው አደባባዩን አቋረጡና ወደ አዛዣችን ዘንድ ቀረቡ:: የመንደሯ ኮዛኮች ግልብጥ ብለው በመውጣት 'ምርኮኞቹ ይውደሙ! ይወገሩ በከት ሁሉ! ምርመራ ችው እንዳለቀ ዋጋቸውን እንሰጣቸዋለን፤ 'እያሉ ይጮሁ ጀመር::

«ብርክ ያዘኝ:: ጉልበቶቼ እየተጋጩ ባለሁበት ደርቄ ቀረሁ:: ግን ለልጄ ለምወደው ዳኒላ ያዘንኩ መሆኔ እንዳይታወቅብኝ ለመደበቅ ታገልሁ:: ሆኖም በዓይኖቼ ሰረቅ እያደረግሁ ዙሪያየን የጉሪጥ ስመለከት ኮዛኮች ጭንቅላታቸውን ወደኔ አቅጣጫ እየነቀነቁ ሲን ሾካሹኩ አየሁዋቸው. . . ወዲያው የሻለቃ ባሻ አርካ ሽካ ወደኔ ቀረበና 'ታዲያ ሚኪሻራ፤ የተያዙትን ኮሚ ኒስቶች ለመግደል ዝግጁ ነህ?' በማለት ጠየቀኝ::

«'እንዴታ! አደባያቸው:: የተረገሙ ስብስብ አጋ ንንት ሁሉ!'

«'እንግዲያው ይህንን ሣንጃ ያዝና ወደ በረንዳው ሄደህ ቦታ ያዝ' አለና በሸር ከተሞላ ፈገግታ ጋር አት ኩሮ እያየኝ ሳንጃውን ሰጠኝ:: 'ግን እያንዳንዷን እንቅ ስቃሴህን በጥሞና እንከታተላለን ሚኪሻራ፤ ስለዚህ ጠንቀቅ እያልክ:: አለዚያ ደግ አይሆንም::' አለኝ::

«ወደበረንዳው የሚያስወጡትን ደረጃዎች ተጠጋ ሁና በአእምሮዬ ሃሣብ እያመነዠኩሁ ቆምኩ:: 'ቅድስት ድንግል ማርያም... እመብርሃን... ዕውነት አሁን ልጄን - የገዛ ልጄን በእጄ ልገድለው ነው?

«ድንገት አዛዣችን ድምፁን ከፍ አድርጐ ጮኸ:: እስረኞቹ እየተግተለተሉ ከቤቱ ውስጥ ወጡ:: የኔው

ዳኒላ ግንባር ቀደም ነበር። አንዴ ብቻ አየሁትና ዓይ ኖቼን ሰበርኩ። ብርድ እንደገባኝ ሁሉ ልቤ ተንቀ ጠቀጠ ... ጭንቅላቱ አብጦ ባልዲ አከሏል። ቆዳውም የተላጠ ይመስላል . . . በላዩ የረጋው ደም በመ ድረቁ ቅርፊት መስሏል። ሌጣ ራሱን ከዱላ ለመከ ላከል ራሱ ላይ ጣል ያደረጋቸው ሁለት ከሲና የተ ሰሩ የእጅ ጓንቲዎች በደሙ ርሰው ደርቀው ፀጉሩ ላይ ተጣብቀዋል... እስረኞቹን ወደመንደሯ ሲያመ ጧቸው በጣም እንደደበደቧቸው ያስታውቃል. . .ዳኒላ ከበረንዳው እየተንገዳገደ ሲወርድ አጠገቡ ቆሜ አየኝ ... እጆቹን ዘረጋ ... ፈገግ እንደማለትም ሞከረው። ሁለቱም ዓይኖቹ ዘገነዋል። አንደኛው ጭራሹን ደም አግቷል።

«በልጄ ላይ እጄን ካልሰነዘርኩ እኔም የመንደሬ ነዋሪዎች ሰለባ እንደምሆንና እምቦቀቅላዎቼም ያለ ሰብ ሳቢ ሜዳ ላይ ተበትነው እንደሚቀሩ የገባኝ ያን ጊዜ ነበር ... ዳኒላ ወደኔ ተጠጋና 'አባባ' አለኝ 'የምወድህ አባቴ ደህና ሁን'!

«ዕንባው ጉንጩ ላይ የተጋገረውን የደም ጭቅ ቅት እየጠረገ ቁልቁል ኩለል አለ። እጄን ማንሣት ተሳነኝ... ወደ እንጨትነት የተለወጠ መሰለኝ። ... ሣንጃውን ግን በመዳፌ አጥብቄ እንደያዝኩት ነው ... በእጄታው በኩል አንድ ጊዜ ጆሮ ግንዱ ላይ አጠነጋ ሁት ... አንጀት የሚበላ ጩኸት ተሰማ! እንዴት ዓይ ነት ጩኸት መሰለህ ... ልጄ ፊቱን በመዳፎቹ ሸፈ ነና ጅው ብሎ ደረጃዎቹ ላይ ባፍጢሙ ተደፋ... ኮዛኮቹ በሣቅ አወኩ። በል እንጂ ማኪሻራ፣ የያዝከ ውን ቀብቅብበት! ለልጅህ ያዘንክለት ትመስላለህ! ግደ ለው፣ አለያ ደምህን ነው የምንጠጣው!' እያሉ ጮኹ።

«አዛዦችን ሁሉንም በቁጣ እየተሳደበ ወደ በረ ንዳው ወጣ:: ዓይኖቹ ውስጥ ግን ሣቅና ፈገግታ ደምቆ ይታያል:: ወዲያው የመንደሬችን ሰዎች ምርኮ ኞቹ ላይ ተረባረበባቸው::በሳንጃ ያጥፏቸው ጀመር:: አንገሉ ዞረ:: እንደ ዕብድ አድርጌን ጎዳናውን ይዤ ቁልቁል መሮጥ ጀመርኩ:: በመሃሉ ወደ ኋላዬ ገል መጥ ስል ልጁን ዳኒላን ምን እያደረገት እንደሆን አየሁ::የሻለቃ ባሻው ሳንጃውን ጉሮሮው ላይ ሻጠበት:: ልጁ አንድ ጊዜ ብቻ እንቋረረ ...»

ሚኪቫራና እኔ ከተቀመጥንበት ትንሽ ዝቅ ብሎ ጀልባዋ የተሰራችበት ጣውላ እየተንቋቋ ሲሰባበር ተሰ ማኝ:: በተሸንቆረው ቀዳዳ ወደ ውስጥ የሚገባው ዓይ ነት የመንሳጠጥ ድምፅ በረጅሙ ይሰማል:: ሚኪቫራ በፒፓው ውስጥ የነበረውን አመድ እያራገፈ፣ «ጀልባ ችን እየሰመጠች ነው:: እስከ ነገ እኩለ ቀን ድረስ እዚህ መቆየታችን አልቀረም:: መልካም አጋጣሚ ነው!» አለ::

ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብሎ ከቆየ በኋላ በዚያው በሻ ካራ ድምፁ ንግግሩን ቀጠለ:: «እና ይኸውልህ በዚያ ቀን ለፈጸምኩት ጀብዱ የሃምሣ አለቃነት ማዕረግ ተሰ ጠኝ::

«ከዚያ ጊዜ አንስቶ በዶን ወንዝ ውስጥ ብዙ ውሃ ፈስሷል:: ግን ዛሬም አንዳንድ ምሽቶች አሉ:: አንድ ሰው ታንቆ ትንፋሽ ሲያጣ የሚያሰማውን ዓይነት የሣግና የነቅታ ድምፅ የምሰማባቸው ምሽቶች አሉ::በዚያን ዕለት ፊቴን አዞሬ ስሸመጥጥ ልጁ ዳኒላ ያሰማውን የመሰለ ድምፅ ማለት ነው . . .

«ከዚያ በኋላ እስከ ፀደይ ድረስ የኮምዩኒስቶችን ርምጃ በመግታት ግንባሩን ለብቻችን ገትረን ከረምን::

ወደኋላ ግድም ግን ከጄኔራል ሴክሬቴዩብ ጦር ጋር ተቀላቀልንና ከዶን ወንዝ ክልል በማስወጣት ወደ ሳራ ቶብ ክፍለ ሀገር እንዲገቡ አደረግናቸው:: የቤተሰብ ኃላፊነት እንዳለብኝ ቢያውቁም ከቦልሽ ጊች ጋር የተሰለፉ ልጆች ስላሉኝ ብቻ አዛገቹ አቤቱታየን ተቀብለው ከግዳጅ ሊያሰናብቱኝ አልፈቀዱም:: እና ይኸውልህ በለስ እየቀናችን እስከ ባላቦብ ከተማ ድረስ ገፋን:: ትልቁ ልጄ ኢቫን ግን ድራሹ ጠፋ:: ሆኖም የኛ ኬዛኮች አድራሻውን ማግኘት አልተሳናቸውም::

ለካስ ኢቫን ቀዮቹን ትቶ በ36ኛው የኬዛክ መድፈኛ ባትሪ ውስጥ ተሰልፎ በመዋጋት ላይ እንደሆነ ደርሰ ውበት ኖሯል::'ካገኘነው ሥጋውን ነው የምንዘለዝለው' በማለት የመንደራችን ሰዎች ሲዝቱ ሰማኋቸው::

«አንድ ቀን እነስ ወደምትል መንደር ሰተት ብለን ገባን::36ኛው የሰፈረባት ነበረች ... የኔውን ኢቫን ወዲያውኑ አገኙት:: እጆቹን የኋሊት ጠፍረው አዛዣችን ዘንድ አቀረቡት:: ባልተወለደ አንጀታቸው እየተቀባበሉ አበራዩት:: ይባስ ብለው እኔን ጠሩኝና 'ወደ ሬጂመንቱ ዋና መምሪያ ይዘኸው እንድትሄድ!' በማለት ትዕዛዝ ሰጡኝ::

«የሬጅመንታችን ዋና መምሪያ የሚገኝበት ሥፍራ ከመንደሯ አስራ ሁለት ኪሎ ሜትሮች ያህል ይርቃል:: አዛዣችን የይለፍ ፈቃዱንና ሌሎች ወረቀቶችን እያስረከበኝ፣ 'ልጅህን ወደ ዋናው መምሪያ አድርሰህ እንድትመለስ ሚኪቫራ::ለራሱም ደህንነት ቢሆን ካንተ ጋር መሄዱ ይሻለዋል:: ምንም ቢሆን ከአባቱ ለማምለጥ የሚሞክር አይመስለኝም!' አለኝ:: ወረቀቶቹንና ትዕዛዙን በሚሰጠኝ ጊዜ ሁሉ ዓይኖቼን በፍፁም አያያቸውም ነበር::



«ጌታ ግን ሁሉንም ለኔ ግልጽ አደረገልኝ፡፡ ለልጁ አኛቢ እንድሆን የመረጡኝ ያለምክንያት አልነበረም፡፡ አዝኜለት እንድለቀውና እሱን ዳግመኛ ሲይዙት እኔ ንም በሰበቡ ለመግደል ነበር ውጥናቸው፡፡

«ይኸውልህ ታዲያ የአለቃዬን ትዕዛዝ ተቀብዬ ሳበቃ በቀጥታ ኢቫን ወደታሰረበት ቤት አመራሁ፡፡ 'እስረኛውን አስረክቡኝ፡፡ ወደ ዋናው መምሪያ እንዳ ደርሰው ታዝዤአለሁ' አልኳቸው ዘቦቹን፡፡

«'ያንተው ነው፣ ውሰደው!' ሲሉ መለሱልኝ፡፡

«ኢቫን ካፖርቱን ትከሻው ላይ አስተካክለና መለ ዮውን ብድግ አድርጐ ለጥቂት ጊዜ በእጆቹ መሃል እያሻሸ ሲጠመዛዝዛት ከቆየ በኋላ መልሶ አግዳሚው ወንበር ላይ ወረወራት፡፡ ከመንደሯ ወጥተን ጉዞ ጀመርን - ሽቅብ ኮረብታዋን ይዘን፡፡ ንግግር የሚባል የለም፡፡ እኔ ብቻ የተከተለን ሰው እንዳለ ለማረጋገጥ ስል አሁንም አሁንም ገልመጥ እያልኩ ዙሪያዬን እቃ ኛለሁ፡፡ ግማሽ መንገድ በመጓዝ መሣለሚያውን አለ ፍን፡፡ የሚታይ፣ዝር የሚል- ነፍስ የለም፡፡ ያኔዬ ኢቫን ወደኔ ዞር አለና 'አባባ፣ ዋናው መምሪያ ስንደርስ ወዲያው ይገድሉኛል፡፡ የምትወስደኝ ወደሞቴ ነው፡፡ ለመሆኑ ኅሊናህ አሁንም በማንቀላፋት ላይ ነው?!' በማለት ጠየቀኝ፡፡

«'አይደለም ኢቫን'አልኩት፡፡'ኅሊናዬ አላንቀላፋም!'

«'ግን ለኔስ፣ አታዝንልኝም?'

«'በጣም እንጂ ልጄ፡፡ለያውም ነፍሴን የሚያደቅ ሃዘን ነዋ፡፡'

«'እንግዲያው ልቀቀኝና ልሂድ ... በዚች ምድር ሕይወትን ገና በደንብ አልኖርኩዋትም 'ክ!'

«መንገዱ መሃል ላይ ድንገት ተንበረከከና ሶስት ጊዜ በግንባሩ እየተደፋ ሠገደ:: በዚህ ጊዜ 'እንግዲያስ ፊፋው አካባቢ ስንደርስ መሮጥ ጀምር:: እኔም ለማ ስመሰል ያህል አንድ ሁለት ጥይቶች እተኩሣለሁ' አልኩት::

«የሚያስገርመው ግን ድሮ ትንሽ ልጅ እያለ እን ኳን አንድም ቀን የፍቅር ቃል ከአንደበቱ ሲወጣ ተሰ ምቶ የማያውቀው ኢቫን በዚያች ቅጽበት እጆቼን አጥ ብቆ ይዞ እየደጋገመ ሣማቸው ... ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ሁለት ኪሎ ሜትሮች ያህል ተጓዝን:: ሁለ ታችንም ፀጥ ብለን ነበር:: ፊፋው አቅራቢያ ስንደርስ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆመ:: 'እሺ እንግዲህ አባዬ፣ እንሰነባበት! ይህንን ቀውጢ ጊዜ አልፌን በሕይወት ለመገናኘት ከበቃን ቀሪውን ዕድሜህን በሙሉ ሳከብ ርህ እኖራለሁ:: የሚያስቀይምህ ቃል ከአንደበቴ አይወ ጣም' አለኝ::

«ከዚያ በኋላ በኃይል አቀፈኝ:: ልቤም በሃዘን ደማለት::

«'በል ልጄ አሁኑኑ ሂድ፣ ሩጥ!' አልኩት::

«ወደ ፊፋው አቅጣጫ ተንደረደረ:: ወደኋላ ገል መጥ እያለና እጁን ለሰላመታ እያወዛወዘ ወደ ፊፋው በረረ:: አርባ ርምጃዎች ያህል እስኪርቅ ድረስ ዝም ብዬ ተመለከትኩት:: ከዚህ በኋላ ጠብመንጃዬን ከትከ ሻዬ ላይ አወረድሁና እጄ እንዳይንቀጠቀጥ በጉልበቴ

በርከክ ብዬ በእጄ ላይ አንጣጠርኩ፡፡ተኮስኩ፡፡ ጀርባው ላይ መታሁት፡፡»

ማኪቫሬ የትምባሆ መያዣውን ከረጢት ፈልጐ ለማግኘትና እሳት ለኩሶ ፒፓውን ለመማግ ረጅም ጊዜ ወሰደበት፡፡ እሳት መለኮሻው መዳፎቹ መሃል ቦግ አለ፡፡ የጉንጬ ጡንቻዎች ይንቀጠቀጣሉ፣ ትንንሽ ዓይኖቹ ከአባበጡት ቆቦቻቸው ሥር በቀጣ ያስተውላሉ፡፡ ፀፀት ግን በጭራሽ አይታይባቸውም፡፡

«እና ... በመጀመሪያ እንደመዝለል አለና አስራ አምስት ርምጃዎች ያህል ሆዱን በእጁ ደግፎ ሮጠ፡፡ ከዚያ በኋላ ቆም ብሎ ፊቱን ወደኔ መለሰ፡፡'ግን ለምን አባባ? !' አለኝ፡፡ ድንገት መሬቱ ላይ ተዘረጋና ይንፈራገጥ ጀመር፡፡

«ወደ ወደቀበት ሮጬ አጠገቡ ተንበረከክሁ፡፡ ከግንባሩ ዝቅ ብሎ ዓይኖቹ ሰማዩ ላይ አፍጥጠዋል፡፡ ከንፈሮቹ በደም እንደረጠቡ ተመለከትሁ፡፡ ነፍሱ የወጣች መስሎኝ ነበር፡፡ ግን እንደምንም ብሎ ራሱን ቀና አደረገና እጄን ለመያዝ እየሩን በእጁ መዳበስ ጀመረ፡፡ 'አባባ ማስትና አንድ ልጅ አሉኝ...'

«ንግግሩን ግን አልጨረሰውም፡፡ ራሱን ወደ ጉን ዘንበል አድርጐ በጀርባው ጧ ብሎ ተዘረረ፡፡ የቁስሉን ቀዳዳ በጣቶቹ አንቆ ይዞታል፡፡ ፋይዳ ግን አልነበረውም!... ደሙ በጣቶቹ መሃል ይንፎለፎላል፡፡ ... አንድ ጊዜ ስርቅ አለውና ትክ ብሎ ያስተውለኝ ጀመር፡፡ ምላሱ ግን ሊታዘዝለት አልቻለም፡፡ ... አንዳች ነገር ለመናገር ይፈልጋል፡፡ ሆኖም 'አባ-ባ-አ-አ' ከማለት ፈደላት በስተቀር ሌላውን ለማውጣት አልቻለም፡፡ ዕንባዬ በዓይኖቼ ግጥም አለ፡፡ 'ለኔ ስትል

የስማዕትነትን ዘውድ በአናትህ መድፋት አለብህ ልጄ፡፡ በርግጥ አንተም ማስትና ልጅ አለህ፡ እኔ ግን ሰባት ምስኪን አፎችን መመገብ አለብኝ፡፡ ዝም ብዬ በለቅህ ክዛኩቹ አፍታም ሳያቆዩ እንደሚገድሉኝ ታውቃለህ፡፡ ከዚያ በኋላ ህፃናቱ የሚኖራችው ዕድል በየቦታው እየዞሩ በየሱስ ስም መለመን ይሆናል፡፡ ... አልኩት፡፡

«ለጥቂት ጊዜ እዚያው መሬቱ ላይ እንደ ተንጋለለ ቆየ፡፡ በመጨረሻ እጄን በእጁ አጥብቆ እንደጨበጠው ነፍሱ ከስጋው ተለየች፡፡ ካፖርቱንና ጫማዎቹን አውልቄ ያዝኩና ፊቱ ላይ መሃረብ ጣል አድርጌበት ወደ መንደሬ ተመለስኩ፡፡

«ስለዚህ አንተ መልካም ሰው ፍርድህን እንድትሰጥ እሻለሁ! ለልጆቼ ስል ሰንቱን ሃዘንና መከራ መስለህ የቻልኩት? መከራ ሀገሬን ባንዴ ጥጥ አስመስለው፡፡ ለልጆቼ ቁራሽ ዳቦ ለማግኘት ስል ከአቅሜ በላይ እሰራለሁ፡፡ ቀንም ሆነ ሌሊት ሰላም የሚሉ ነገር አላውቅም፡፡ እነሱ ታዲያ... በተለይ ሴቷ ልጄ ናታሻ፣ 'አባባ ካንተ ጋር ባንድ ማዕድ ስቀርብ እንጀራት መሰለህ የሚያመኝ ...' ትለኛለች፡፡

«ይህንን ታዲያ እንደምን አድርጌ ልቋቋመው የሚቻለኝ ይመስልሀል ልጄ?»

የጆልባዋ ባለቤት ማኪቫራ አትኩሮ ይመለከተኝ ጀመር፡፡ ከበስተጀርባው ቅዝዝ ያለ ጉህ መቅደድ እየጀመረ ነው፡፡ ከወንዙ የማዶ ዳርቻ ከሚመጣው የዳክዬዎች ማስካካት ጋር አንድ ሌላ ድምፅ ተቀላቅሎ ያስተጋባል፡፡ «ማኪቫራ! አንተ ዲያቢሎስ! ጆልባዋን ይዘህ ወዲህ ና!» የሚል ገና እንቅልፉን ያልጨረሰ ሰው ሻካራ ድምፅ ይሰማል፡፡



# አንድ በርሜል አሞንቲያዶ

ኤድጋር አለን ፖ*

ፎርቱናቶ በልዩ ልዩ መንገዶች ሲበድለኝ፣ ሲያስቀይመኝ፣ ሲያቆስለኝ ነበር የኖረው። እያሌ ዓመታት በትዕግስት አሳልፌአለሁ። በመጨረሻ ግን ከአቅሜ በላይ ሆነ። እንክፍ፣ ደካማ እያለ በይፋ መስደብ ሲጀምረኝና በምኩራብት የቤተሰቤ ስም ላይ ማላገጥ ሲጀምር አምርሬ ልበቀለው ቆረጥሁ። ለራሴ ቃል ኪዳን ገባሁ። ታዲያ ውሣኔና ዕቅዴን ሁሉ ለራሴ አምቄ ያዝኩት እንጂ ለአንድም ሌላ ነፍስ አልተነፈስኩም። ፀጥ እንዳልኩ ዋጋውን እከፍለዋለሁ። ግን በጥንቃቄ ነው። በጥንቃቄ እንደተወጠነ ሁሉ ሲፈፀምም በመጨ ረሻው ከፍተኛ ጥንቃቄ ይሆናል። በደሌን አበቀል ብዬ ሥቃይ እንዲደርስብኝ አልሻም። ጥፋት ደግሞ በዚህ ዓይነት ሊታረም አይችልም። ስለዚህ ፎርቱናቶ ዋጋ ውን የሚያገኘው ለየትኛው ጥፋቱ እንደሆነና በማን እጅ እንደሚከፈለው ጥሩ አድርጎ ማወቅ ይኖር በታል።

በኔ ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት የሚያነቃ አንዳ ችም ፍንጭ አልሰጠሁትም። ጥንቃቄዬ ፍፁም ነበር። የትም ቦታ ስንገናኝ ፈገግታዬን እለግሰዋለሁ። እርሱ

---

* ኤድጋር አለን ፖ በ1809- በአሜሪካ አገር በማሳቹስትስ ግዛት የተወለደ የብዕር ሰው ነበር። ፖ አሜሪካ በመጀሪ መያው ረድፍ ከምታሰልፋቸው ታላላቅ ባለቅኔዎች አንዱ ከመሆኑ ሌላ ድንቅ በሆኑት አጫጭር ልቦለዶቹ ለዚህ የሥነ ፅሑፍ ዘርፍ ዕድገት አስተዋፅኦ አበርክቷል። ፖ የሞተው በ1849 ነው።

ግን አይታየውም። ያ ሁሉ ፈገግታ የደገስኩለትን እያ ሰብሁ መሆኑ አይገባውም።

ፎርቱናቶ በአካባቢያችን በጣም የሚፈራ ኃይለኛ ሰው ቢሆንም ግልጽ ድክመቶችም ነበሩት። መቼም ስለወይን ጠጅ ከእርሱ በላይ የሚያውቅ ለአሣር ነው። እሱም በዚሁ ዕውቀቱ ይኩራበታል። በርግጥ በዚህ ጉዳይ እንመሣሣላለን ለማለት እደፍራለሁ። እኔም በቅምሻ ብቻ የወይን ጠጅን ዕድሜ የማወቅ ችሎታ አለኝ። አንዳንዴ ሲያመቸኝም ረጅም ዕድሜ ያላቸውን ውድ የወይን ጠጆች እገዛለሁ።

አንድ ቀን ደንገዝገዝ ሲል ፎርቱናቶን አገኘሁት። ከወትሮው ይበልጥ ሞቅ ባለ ሁኔታ አነጋገረኝ። ዓመትባል ስለነበር ብዙ ሲጠጣ መዋሉ ያስታው ቃል። ከላይ እስከታች በክት ልብስ ተሰትሯል። ራሱ ላይ ጣል ባደረገው ባርኔጣ ዙሪያ ትንንሽ ቃጭሎች ተንጠልጥለው በተንቀሳቀሰ ቁጥር ይቅጨለጨላሉ። በዚያን ወቅት ስላገኘሁት፣ በጣም ተደስቸ ስለነበር ለሰላምታ የጨበጥኩትን እጁን መነቅነቁን ማቆም ተሣነኝ።

«ወዳጄ ፎርቱናቶ በድንገት ስለተገናኘን በጣም ነው ደስ ያለኝ። ይኸውልህ ሰሞኑን አንድ በርሜል አሞቲንያዶ[1] አግኝቼ ነበር። ግን ዕውነተኛ ንፁህ አሞ ንቲያዶ መሆኑን ተጠራጥሬአለሁ» አልኩት።

---

[1] አሞንቲያዶ- ዋጋው በጣም ውድ የሆነ ምርጥ የስፖኝ ወይን ጠጅ ነው።

«ምን?» አለ። «አሞንቲያዶ?! ለያውም በርሜል ሙሉ? ሊሆን አይችልም። በዚያ ላይ ደግሞ በአውዳመት ሰሞን! አይመስለኝም!»

«የኔስ ጥርጣሬ በዚሁ አይደል» አልኩ። «በጣም የሚገርመው ግን አንተን ሳላማክር ሙሉውን ዋጋ መክፈሌ ነው። ለነገሩማ ስላልተሣካልኝ እንጂ አንተን ፍለጋ ያልገባሁበት ምን ቀዳዳ አለ።»

«አሞንቲያዶ!»

«ሆዴ ግን አሁንም በቅሬታ እየዋለለ ነው። የግድ ማረጋገጥ ይኖርብኛል።»

«አሞንቲያዶ!»

«አሁን እኮ የምሄደው ወደ ሉክሬዚ ነበር። ምናልባት አንተ በበዓሉ ምክንያት ካልተመቸህ እሱን ላማክረው ወስኜ ወደቤቱ እያመራሁ ነበር። መቼም ስለ ወይን ጠጅ ከሚያውቁት ጥቂት ሰዎች አንዱ እሱ ነውና...»

«ሉክሬዚኮ የወይን ጠጅ ከውሃ ለይቶ መናገር አይችልም።»

«እኔ ምናባቱን አውቃለሁ ብለህ!ብቻ አንዳንድ አጋሰሶች በወይን ጠጅ ቅምሻ ካንተ የሚስተካከል ችሎታ እንዳለው አስመስለው ያወራሉ።»

«በል ና እንሂድ!»
«ወዴት?»

«ወደቤትህ ነዋ»

«ተው አይሆንም ወዳጄ፣የዛሬው ቢቀር ይሻላል። በርግጥ ለጊዜው የምትሄድበት አጣዳፊ ጉዳይ ላይኖርህ ይችላል። ግን ኃይለኛ ጉንፋን እንደያዘህ ይታየኛል። የወይን ጠጅ የማከማችበት የምድር ቤቱ ክፍል ደግሞ በጣም ቀዝቃዛ ነው። ኋላ ለጤናህ ደግ አይሆንም።»

«ግድየለም እንሂድ። ጉንፋኑም ቢሆን እስተዚህ ለከፋ የሚሰጠኝ አይደለም። አሞንቲያዶ! አይ ወዳጄን እንድ አላቲ ሳይጫወትብህ አልቀረም። ሉዝሬዚን ግን እርሣው። አሞንቲያዶን ከሌላ የወይን ጠጅ መለየት አይችልም።»

ፎርቱናቶ የጀመረውን ንግግር ሣይጨርስ ክንዴን ጨምድዶ ያዘው። እኔም ፊቴ ላይ አንድ ጭምብል /ማስክ/ ጣል አድርጌ ካባየን ትክሻየ ላይ አስተካክልሁና ተከተልኩት። በቀጥታ ወደ ቤት አመራን።

ቤቱ ጭር ብሏል። ከሠራተኞቼ አንዱ እንኳን የለም፤ በሙሉ ሄደዋል። ቀን ከቤት ስወጣ፣ እስከማቀጥለው ማለዳ እንደማልመለስ በመግለፅ አንዳቸውም ቤቱን ጥለው ውልፍት እንዳይሉ ትዕዛዝ ሰጥቻቸው ነበር። ግን ገና እግሬ ወጣ ከማለቱ ሁሉም ቤቱን ጥለው ወደበዓሉ ሥፍራ እንዲሄዱ የሚያስገድድ ትዕዛዝ መሆኑን ልቦናዬ ያውቀዋል።

ግድግዳው ላይ ካለው ቀንዲል ሁለት ነበልባላቸው በደንብ የሚንተገተግ ፋናዎች አንሣሁና አንዱን ለፎርቱናቶ ሰጠሁት። እኔ እየመራሁ እሱ እየተከተለ ደርዘን ያህል ክፍሎች እያቋረጥን ከተጓዝን በኋላ ወደ ምድር ቤቱ እሚያስገባው በር

አጠገብ ደረስን። አሠራሩ በቅስት ቅርፅ ነው። እንዲ ጠነቀቅ ከመከርኩት በኋላ በኔ መሪነት በደረጃዎቹ ቁልቁል መውረድ ጀመርን። ደረጃዎቹ ግርጌ ስንደ ርስ በምድር ቤቱ የአፈር ወለል ላይ ጎን ለጎን ቆምን። ያ ሥፍራ የሞኑት ሬሳር ቤተሰብ አባላት የመጨረሻ ማረፊያ ነበር።

ጓደኛዬ ሲጋተው በዋለው የወይን ጠጅ ሰበብ የአ ካሉን ሚዛን መጠበቅ እንደሣነው ለመረዳት አላዳገ ተኝም። አጠገቤ ቆሞ ዘመም ዘመም ሲል ባርኔጣው ላይ የተንጠለጠሉት ቃጭሎች ለዘብ ያለ ድምፅ ያሰ ማሉ።

«በርሜሉስ?» አለ።

«ትንሽ ወደውስጥ ገባ ይላል» አልኩት። ዓይና ቹን አትኩሬ ሳስተውላቸው ብልቃጥ መስለው ታዩኝ። ቀኑን ሙሉ ሲጨልጥ የዋለው ሺና ውጤት ነው። «ለመሆኑ ጉንፋኑ ከመቼ ጀምሮ ነው የያዘህ? ጤንነትህን መጠበቅም አለብንኮ። ሀብታምና ተወ ዳጅ ሰው መሆንህን አትዘንጋ። በዚያ ላይ እኔ አንድ ወቅት እንደነበርኩት፣ ፍፁም ደስተኛ ነህ። ስለዚህ ወደኋላ ብንመለስ ይሻላል። ለቅምሻው እንደሆን ሉክሬዚም...»

«ግዴለም» አለ መቼም በጉንፋን አልሞት።»

«እሱስ ዕውነት ነው። ግን ጥንቃቄ ማድረግ አለ ብህ፣» አልኩና መሬቱ ላይ ከተደረደሩት ጠርሙሶች አንዱን አንስቼ አንገቱን ቀነጠስኩት።

«የወይን ጠጅ ስብርዱ ፍቱን መድሐኒት ነው። በጥቂቱም ቢሆን ያሟሙቀናል።»

መጠጡን ወደ ከናፍሩ እያስጠጋ የጉሬዋ ተመለከተኝ።

«በዙሪያችን ላሽለበት የሞንትሬሶር ሙታን ፅዋዩን አነሣለሁ፣» አለ።

«እኔ ደግሞ ረጅም ዕድሜ እመኝልሃለሁ።»

ክንዴን ያዘኝና ወደ ውስጥ ዘለቅን።

«ይህ የምድር ቤት እንዴት ትልቅ ነው ጃል!» አለ።

«የሞንትሬሶር ቤተሰብ ትልቅ፣ኃያልና ኩሩ ነበር» በማለት መለስኩለት።

የጠጣነው የወይን ጠጅ ሙቀት እየሞላብን መሄድ ጀመረ። በተለይ በወዳጄ ዓይኖች ውስጥ ሲን ፀባረቅ ቁልጭ ብሎ ይታየኛል። ቃጭሎቹ በሚፈጥሩት ድምፅ ውስጥ ጥርት ብሎ ይሰማኛል።

ወደ ምድር ቤቱ ውስጥ በጣም እየጠለቅን በሄድን መጠን በግራና ቀኝ ተቆልሎ የሚታየው የአፅም ክምር ይጨምር ጀመር። የሙታን አጥንት ባይነት ባይነቱ እየተነባበረ የአፅም ክምር ሠርቷል። በየጣልቃው ደግሞ የወይን ጠጅ በርሜሎች አለፍ አለፍ እያሉ ተገሽረዋል።

ድንገት ርምጃዩን ገታሁ። «አሁን የምንገኘው ከወንዙ ውሃ በታች ነው። ወንዙ የሚፈሰው ልክ

በአጥንቶቹ ከምር አናት ትይዩ ነው:: ስለዚህ ተመ ልሰን መውጣት ይኖርብናል:: ቀዝቃዛው ለጤናህ...»

«የለም፣ መቀጠል አለብን፣» በማለት አቋረጥኋ::

«በመጀመሪያ ግን ተጨማሪ የወይን ጠጅ መቅ መሱ አይከፋም::»

የሌላ ጠርሙስ አንገት ነመድኩና ሠጠሁት:: ጭልጥ አድርጎ ጠርሙሱን ካጋባ በኋላ ከት ብሎ ሣቀ::

እንደገና ቁልቁል መውረዳችንን ቀጠልን:: ዝቅ... ዝቅ... ዝቅ እያልን በመጨረሻ በጣም ጥልቅ ወደ ሆነው አካባቢ ደረስን:: በስፍራው ያለው አየር እየ ሣሣ በመሄዱ የፋናዎቻችን ነበልባል እየተስለመለመ መጥፋትም ይዳዳው ጀመር::

ከቆምንበት ራቅ ብሎ በክፍሉ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ አንዲት ትንሽ ክፍል ቢጤ ትታያለች:: የአፅም እንክልካይ እየታከካቸው በመቆለሉ ሦስቱ ግድግዳ ዎቿ አይታዩም:: በአራተኛው ግድግዳ ላይ ግን የአ ፅሙ ድርድር ተንዶ መሬቱ ላይ ተበትኗል:: በዚህ ኛው ግድግዳ ላይ አንድ ጠባብ ክፍተት አለ:: በክፍ ተቱ በኩል ሌላ ክፍል ከበስተጀርባ ይታያል:: ሥፍ ራው በጣም ጨለማ በመሆኑ የፋናዎቹ ፈዛዛ ነበል ባል ሊያሳየን የቻለው ጥቂቱን ብቻ ነው::

«ሂድ:: ወደፊት ሂድ በል፣»አልኩት:: «አሞንቲያ ዶው ያለው እዚያ ውስጥ ነው:: መቼም ሉክሬዚ...»

«ምነው እሱን ሰውዬ ብትረሣው። ምንም የማያውቅ ደደብ ነው አልኩህ» አለ ወዳጄ፣ እሱ እየመራ እኔ እየተከተልኩ ወደፊት ስንራመድ።

ግን ብዙም ሳንገፋ ከክፍሏ ግድግዳ አጠገብ ደረስ። ርቀቱ አጭር በመሆኑ ግራ ተጋብቶ ባለበት ተገተረ። ወዳያው ተከታትሎ በተፈፀመው ፈጣን ድርጊት በመደናገጡ ግብግብ ሊገጥመኝ አልቻለም። እኔስ ምኔ'ዋዛ ነው. . . ጊዜ ሳላባክን ከግድግዳው ጋር በተሰራ ካቴና ሁለት እጆቹን ከረቸምኩት። ተግባሬን ስፈፅም ወደ ኋላ ፈንጠር ብዬ በቅልጥፍና አፈገፈግሁ።

«እስቲ ግድግዳውን በእጅህ ዳብሰው፣» አልኩት። «የሚወረዛው ውሃ በላዩ ላይ እንዴት እንደሚያኘር ይሰማሃል።እና ወዳጄ ሆይ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተመልሰህ እንድትወጣ ልጠይቅህ። አይሆንም? እንግዲያው እኔ እዚሁ ጥየህ እወጣለሁ። ከዚያ በፊት ግን በኔአቅም ልፈፅምልህ የምችለውን ሁሉ ማድረግ አለብኝ።»

«አሞንቲያዶውን!» በማለት ጮኸ፣ ነገሩ ሁሉ ያልገባው ወዳጄ።

«ልክ ነህ» ስል መለስኩለት። «አሞንቲያዶውን ነው።»

እነዚህን ቃላት ከተናገርኩ በኋላ መሬት ላይ የተዝረከረኩትን አጥንቶች ወዲያና ወዲህ እየበታተንኩ ቀደም ሲል በቦታው ያስቀመጥኳቸውን ልዩ ልዩ መሣሪያዎች አመጣሁ።ጊዜ ሳላባክን ወዳጄ ፎርቱናቶ ወደታሰረበት አነስተኛ ክፍል የምታስገባውን ጠባብ

ከፍተት የመድፈን ሥራዬን ተያያዝኩት። የመጀመሪያውን ረድፍ ድንጋዮች በጥንቃቄ ደረደርኳቸው።

ጥቂት እንደሰራሁ ወዳጄ ከወይን ጠጅ የተቸረውን ድፍረትና ጉልበት ሁሉ እየከሰረ መሄድ መጀመሩን ተገነዘብኩ። ለዘብ ያለ ጩኸት አሰማ። ጩኸቱ ግን በደንብ የሰከረ ሰው ጩኸት አይመስልም። ረጅም ፀጥታ ተከተለ። ሥራዬን ቀጠልኩ። ኃይለኛ የሰንሰለት መንገጫገጭ ድምፁን ነረተው። በአንዴ ብቻ አልቆመም። ድምፁ ለብዙ ደቂቃዎች ቀጠለ። ሥራዬን አቋረጥኩና መሬቱን ባለበሱት አጥንቶች ላይ ቁጭ ብዬ በደስታ ማዳመጥ ጀመርኩ። ጥቂት ፋታ። እንደ ገና ፀጥታ አረበበ። እኔም ወደ ሥራዬ ተመለስኩ።አዲስ የማገነባው ግድግዳ ቁመት እያደገ ነው።

ውሃ ከማያገኘው ግድግዳ ጋር በሰንሰለት ከተቆየደው ሰው ልሣን ነርብ የሚቀረደድ ዋይታና እሪታ ይፈልቅ ጀመር። የድምፁ ኃያልነት ወደኋላ ገፍትሮ ከቆምኩበት የሚፈነግለኝ መሰለኝ።ለጥቂት ጊዜ የሥራ ጅስሚ ተብረከረክ። ሩህያዬ ተንሰፈሰፈች። ግን እንደ ምንም ጥንካሬዬን አሰባሰብሁና ወደ ሥራዬ ተመለስኩ። የሦስተኛውን ረድፍ ድንጋዮች መደርደር ይገፍሁ። ከወዳጄ ጩኸት አብልጬ በመጮኽ፣ ለጩኸቱ ምላሽ ሰጠሁት። ጩኸቱን በጩኸቴ ዋጥኩት። ፀጥ አለ።

አሁን እኩለ ሌሊት ሆኗል። ሥራዬ ወደ መገባደዱ እየተቃረበ ነው። የሚቀረኝ አንድ ከፍ ያለ ድንጋይ በተገቢ ቦታው ላይ ማስቀመጥ ብቻ ይሆናል። ግን ከጠደውስጥ የለበጣ ዓይነት ሣቅ በሰሆሣስ በመሰማቱ ፀጉሬ ቆሞ ብሎ ቆመ። በማከታተል ደግሞ

ከቶም የፎርቱናቶን የማይመስል ድምፅ መጣ። ድም
ፁም፣

«የወይን ጠጃችንን እየኰመኰምን፣ ስለዛሬው ሁኔታ እየተሣሣቅን እንደምንጨጪዋወት አምናለሁ» አለ።

«አሞንቲያዶው!» አልኩ።

ሣቁን መልሶ ደገመው። «አዎ፣ አሞንቲያዶው። እኔ የምልህ ግን ወዳጄ በጣም የመሸ አይመስልህም? ባለቤቴ እመቤት ሆዬ ፎርቱናቶና ሌሎችም ስለሚጠብቁኝ በጊዜ ብንሄድ አይሻልም?» አለ።

«አዎ፣ ይሻላል እንጂ። በጊዜ ብንሄድ ይሻላል፣» ስል መለስኩለት።

«ስለእግዚያብሔር ብለህ ሞንትሬሶር!»

ለነዚህ ቃላት ግን ምላሽ አላገኘሁም። ፍፁም ፀጥታ ሆነ። ድምጼን ከፍ አድርጌ ተጣራሁ።

«ፎርቱናቶ!»

ምንም መልስ የለም። እንደገና ተጣራሁ፣

«ፎርቱናቶ!»

አሁንም መልስ የለም። አንደኛውን ፋና ያዝኩና ወደመጨረሻዋ ቀዳዳ በማስጠጋት የነበልባሉን ፈዛዛ ብርሃን አዲስ ከተገነባው ግድግዳ ጀርባ የተጋገረውን

ድቅድቅ ጨለማ በመጠኑ እንዲገፈው አደረግሁ። የቃጭሉ'ቱ ድምፅ ብቻ ተሰማኝ። ሌላ ምላሽ የለም። ልቤ ከፋኛ ታመመ። ሥራዬን ለማጠናቀቅ መጣደፍ ጀመርኩ። የመጨረሻውን ድንጋይ እንደምንም ታግዬ ቦታው አስገባሁት። ልክክ አለ። ቀዳዳዋ ተደፈነች። መሬቱ ላይ የተዝረከረከውን የአጥንት ዘር እያነሳሁ ወደአዲሱ ግድግዳ በማስጠጋት እንደወትሮው መደር ደር ጀመርኩ። የጥንቱ የግድግዳ ሽፋን የቀድሞ ቦታ ውን ያዘ። ለግማሽ ምዕተ ዓመት እነዚያን አጥንቶች ማንም የረበሻቸው አልነበረም።

# ሣመሩና ብቻ . . .

ሄርናንዶ ቴሌዝ*

ሲገባ አንዳችም ቃል አልተነፈሰ። ከምላጮቼ መሃል ሻል ሻል ያሉትን በየተራ እያነሳሁ በስለት ማውጫው ቀበቶ ላይ ወሰድ መለስ በማድረግ በመሣል ላይ ነበርሁ። ብቻ የገባው ሰው ማን መሆኑን ስመለከት ሁለመናዬ በድንጋጤ ያረግድ ጀመር። እርሱ ግን ሁኔታየን ያጤነው አይመስልም። የሥራ አካሌን የሚንጠውን ውስጣዊ ስሜቱን ለመቆጣጠር ያመቸኝ ዘንድ ምላጮቼን እየሣልኩ፣ ስለታቸውን በአውራጣቴ ሥጋ ላይ መፈተሼን ቀጠልኩ። ይበልጥ ርግጠኛ ለመሆን ደግሞ ምላጮቹን ወደላይ ከፍ እያደረግሁ ስለቱ በሚገባ መውጣቱን በበሩ በኩል በሚገባው ብርሃን አማካይነት አረጋግጣለሁ። ሰውየው ጥይቶች የተሰገሰጉበትንና የሽጉጡ ማኅደር የተንጠለጠለበትን ቀበቶውን ፈታና ከግድግዳው ውስጥ ብቅ ብላ በምትታይ ሚስማር ላይ ሰቀለው። መለዮውን ከራሱ አንስቶ ቀበቶው ላይ ደረባት። ከዚያ በኋላ የከራቫቱን ሸምቀቆ እያላላ ወደኔ በመዞር «የዛሬው ሙቀት ደግሞ እንድያውን ገሀነም ሆኖ የለም እንዴ!እስቲ ፈጠን ብለህ ይህን ጺም አንሳልኝ» አለና ወንበሩ ላይ ተቀመጠ።

---

* ሄርናንዶ ቴሌዝ የኮሎምቢያ /ደቡብ አሜሪካ/ ተወላጅና ከዘመናችን ዝነኛ ደራስያን አንዱ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ሕይወቱ ያለፈው ይህ ብዕረኛ ይበልጥ የሚታወቀው በአጫጭር ልቦለዶቹና ወጎቹ ሲሆን በጋዜጠኝነት ሙያም ስመ - ጥር ነበር።

የጺ.ሙ ዕድሜ ከአራት ቀናት እንደማይበልጥ ገመትሁ:: የኛን አርበኞች ለመመንጠር ሲባል መሰን በቻውን የተካሄደውም ዘመቻ የወሰደው አራት ቀናት ነው:: በፀሐይ ሐሩር ሲጠበስ የከረመው ፊቱ ሳምባ መስሏል:: ጺ.ሙ ላይ የምቀባውን ሣሙና በጥንቃቄ ማዘጋጀት ጀመርኩ:: ከሣሙናው ላይ ጥቂት ቁር ጥራጮችን በሴንጢ እየቀረፍኩ ኩባያ ውስጥ ከጨ መርኩ በኋላ ከጥቂት ለብ ያለ ውኃ ጋር ስበጠብጥ አረፋው በአፍታ ተኩረፈረፈ:: «ሌሎችም የአሠሳው ቡድን አባላት ይሄኔ ጺ.ማቸው የዚሁን ያህል አድጎ ይሆናል» አልኩ አረፋውን እየመታሁ::

«የሚያረካ ተግባር ነው የፈፀምነው:: ቀንቶናል:: ቀንደኞቹ ተይዘዋል:: የሞቱትንም አስከሬን ይዘን መጥተናል:: በህይወት ያሉትም በአፋጣኝ ይረሸናሉ፣ ብዙም አይቆዩ::»

«የተያዙ ስንት ይሆናሉ?» ጠየቅሁት::

«አሥራ አራት:: ወደ ጫካው በጣም ዘልቀን ባን ገባ ኖሮ በጭራሽ አናገኛቸውም ነበር:: አሁን በደንብ እንበቀላቸዋለን:: አንዳቸውም አይተርፉ- ምንም::»

በአረፋ የተሸፈነውን ብሩሽ በእጄ ይዤ ቁልቁል ስመለከተው ወንበሩ ላይ ጋለል አለ:: ገና ጬርቁን ማልበስ አለብኝ:: ከፉኛ መደናገጤ ምንም አያጠያይ ቅም:: ከመሣቢያው ውስጥ አንድ ጬርቅ አውጥቼ ደረቱ ላይ ጣል አደረግሁና በአንገቱ ዙሪያ ቋጠር ኩት:: ወሬውን ሊያቆም አልቻለም::ምናልባት የእርሱ ፓርቲ ደጋፊ መስየው ይሆናል::

«በቀደምለት ከወሰድነው ርምጃ የከተማው ሕዝብ ጥሩ ትምህርት እንደቀሰመ ርግጠኛ ነኝ» አለ።

«አዎ» በሳብ በወረዛው ጥቁር አንገቱ ዙሪያ ቋጠሮውን እያጠበቅሁ መለስኩለት።

«ድንቅ ትርዒት ነበር። አይደለም?»

«በጣም ጥሩ እንጂ፣» አልኩ ብሩሹን ለማንሣት ፊቱን እያዞርኩ።ሰውየው እንደደከመው ከሚያመለክት እንቅስቃሴ ጋር ዓይኖቹን ከደንና ሣሙናው የሚሰጠውን ተሀድሶ መጠበቅ ጀመረ። እንደዚያ በጣም ቀርቦኝ አያውቅም። የአራቱን አብዮታዊያን ስቅላት ለመመልከት የከተማው ነዋሪዎች በትምህርት ቤቱ ቅጥር እንዲሰበሰቡ ባደረገበት ቀን ለጥቂት ደቂቃዎች ፊት ለፊት ግጥምጥም ብለን ነበር። ቢሆንም ልብ ብዬ አላስተዋልኩትም። የነዚያ አርበኞች የተዘነጣጠሉ በድን አካላት መላ ጥሞናየን ጨምድደው ስለያዙት አሁን በመዳፎቼ መሀል ላስገባው የተሰናዳሁትን ሰው ፊት በሚገባ ለማጤን አልቻልኩም። በርግጥ የሚያስጠላና ቀፋፊ ፊት አይደለም። ያለዕድሜው ጠና ያለ የሚያስመስለው ሪዙ እንኳ ተስማምቶታል። ቶሬስ ይባላል። የሻምበል ቶሬስ።

የመጀመሪያውን ዙር ሣሙና ጺሙ ላይ መለቅለቅ ጀመርኩ። ዓይኖቹን እንደከደነ ወንበሩ ላይ ተንጋሏል። «ዛሬ ከቀትር በኋላ ብዙ የማከናውነው ሥራ ባይኖርብኝ በቀላሉ እንቅልፍ ሊወስደኝ በቻለ ነበር፣» አለ።

ሣሙና መቀባቱን ቆም አደረግሁና ስለጉዳዩ ምንም ስሜት የሌለኝ በማስመሰል ዓይነት ጥያቄዬን ሠንዘር አደረግሁ።

«ዛሬም የሚረሸኑ አሉ?»

«እንግዲያማ ማን የዛሬው ግድያ ዝግ ባለ ሁኔታ ነው የሚፈፀመው::»

የማመናውን አረፋ ጺጦ ላይ መለሰኔን ቀጠልኩ::እጆቼም እንደገና መንቀጥቀጥ ጀመሩ:: ስውየው ግን ሊያስተውለው አይችልም:: ለኔ ጥሩ ነው:: ሲገባ ማየታቸው አያጠራጥርም::ጠላት ቤት ውስጥ እስከገባ ድግሞ አንዳንድ ሁኔታዎችን ማስከተሉ ስለማይቀር ጥንቃቄ ማድረጉ አይከፋም:: ጺጦን እንደማናቸውም ደንበኛ በጥንቃቄ የመላጨት ግዴታ አለብኝ - ረጋ ብዬ:: በቆዳው ላይ ካሉት ቀዳዳዎች አንዲ እንኳን ጠብታ ደም ማፍለቅ የለባትም:: የተቆጣጠሩ ፀጉሮች ምላጩን አደናቅፈውት ቆዳውን እንዳይጭር ወይም እንዳይቆርጠው መጠንቀቅ ያሻል::ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ ተላጭቶ ቆዳው ንፁህና ለሥላሣ መሆኑን በእይ በለብዬ ዳስሼ ማረጋገጥ ይኖርብኛል:: አዎ በህቡዕ አብዮተኛ ብሆንም ለሥራዬ አክብሮት ያለኝ፣ ኃላፊነት የሚሰማኝና በሥራዩ ጥራት የምኩራ ፀጉር አስተካካይ መሆኔንም ማስመስከር አለብኝ::እና ይህ የአራት ቀናት ዕድሜ ያለው ሪዝ ለኔ ብርቱ ፈተና ነው::

ምላጩን አነሣሁና በአንደኛው ጉንጩ በኩል ያለውን ጺም በመላጨት ሥራዬን ጀመርኩ:: ምላጩ ተግባሩን በጥሩ ሁኔታ ማከናወኑን ተያያዘው:: ፀጉሩ ጠንካራና ከርዳዳ ቢጤ ነው:: ረጅም ባይሆንም በአበቃቀሉ ጥቅጥቅ ብሏል:: ቀስ በቀስ ቆዳው መታየት ጀመረ:: መድረቅ የጀመረው የሣሙና አረፋ ከፀጉር ቁርጥራጮች ጋር እየተደባለቀ በምላጩ ስለታማ ጠርዝ ላይ መከማቸት ሲጀምር ምላጩ የተለመደውን ሻካራ ድምፅ እያሰማ ቁልቁል መቧጠጡን ቀጠለ::

ምላጩን ለማዕዳት ለአንድ አፍታ መላጩቱን ቆም አደረግሁ:: በዚያውም ስለት ለማውጣት ቆዳውን ማብ አደረግሁት:: እኔ ተግባራቸውን በትክክልና በአግባቡ ከማያከናውኑ ፀጉር አስተካካዮች ወገን ነኝ:: ሰውየው የተከደኑ ዓይኖቹን ገለጣቸው:: አንድ እጁን ከጨርቁ ሥር አውጥቶ የተላጨውን ጉንጩን ዳበስ ከአደረገ በኋላ «ዛሬ በአሥራ ሁለት ሰዓት ወደትምህርት ቤቱ ብቅ በል» አለ::

«ከበቀደምለቱ ጋር ተመሣሣይ ነገር ነው?» እየተ ሸበርሁ ጠየቅሁት::

«የተሻለም ሊሆን ይችላል::»

«ምን ለማድረግ ነው የታቀደው?»

«ገና በውል አላወቅሁትም:: ምንም ይሁን ምን፣ ብቻ ራሣችንን እናስደስታለን::»

እንደገና ወንበሩ ላይ ተንጋለለና ዓይኖቹን ከደ ናቸው:: ምላጬን አስተካክዬ ቀረብሁት:: ስፈራ ስቸር ጥያቄዬን ወረወርኩ::

«ሁሉንም ለመቅጣት ነው ያሰባችሁት?»

«በሙሉ!»

የሣሙናው አረፋ ፊቱ ላይ እየደረቀ ነው:: ፈጠን ማለት አለብኝ::

በመስታወቱ ውስጥ ጐዳናውን ተመለከትሁ:: ልክ እንደወትሮው ነው:: ግሮሰሪው ውስጥ ሁለት ሦስት

ሰዎች ይታያሉ። ዓይኖቼ ግድግዳ ላይ ወደተሰቀለው ሰዓት ተንጠራሩ።ስምንት ከሃያ ሆኗል፤ ከቀትር በኋላ። ምላጩ ቁልቁል መንፏቀቁን ቀጠለ። አሁን ግን በሌላው ጉንጩ ላይ ያለውን ጺም እየላጨ ነው። ጥቅጥቅ ያለ ሰማያዊ ሬዝ። አንዳንድ ባለቅኔዎችና ካህናት እን ደሚያደርጉት ወደታች ቢያንዠረግገው ይሻለው ነበር። ይበልጥ በተስማማውና ብዙ ሰዎችም ሊያውቁት ባል ቻሉ። ጥቅሙም ቢሆን ለራሱ ነው፤ እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ - የአንገቱን አካባቢ ከፀጉር እያፀዳሁ።

አንገቱ አካባቢ ሲደርስ ምላጩ በበለጠ ጥንቃቄ መያዝ አለበት። በዚያ ሥፍራ የበቀሉት ፀጉሮች ለስለሥ ያሉ ቢሆኑም እየተጠቀለሉ ትንንሽ ቀለበቶችን ስለ ፈጠሩ ምላጩ ልዩ ጥበብ ይፈልጋል። አለያ ከጥቃቅኖቹ የቆዳ ቀዳዳዎች አንዷ ድንገት ትበረገድና የደም ነጠብጣቦች ወጥተው ያፈጣሉ። እንደኔ ያለ ስመጥር ፀጉር አስተካካይ የሚኮራበት ነገር ቢኖር ይህን መሣይ ችግር በደንበኛው ላይ እንዳይደርስ ለመ ከላከል ብቁ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ በአንደኛ ደረጃ የሚመደብ ደንበኛ እንጂ እንዲያው በዋዛ የሚታይ አይደለም። ስንቶቻችንን ነው እንድንረሽን የወሰነብን? ስንቶቻችንን ነው እንድንበለት?. . . ያንን አለማሰቡ ይሻላል።

ቶሬስ ግን ጠላቱ መሆኔን አላወቀም። ለሱም ሆነ ለሌሎች ሥውር ነው። ጥቂቶች ብቻ የሚያውቁት ምሥጢር። ቶሬስ በከተማው ውስጥ ስለሚፈፅማቸው ድርጊቶችና ለአሠሣ በሚነሣ ጊዜ ስለሚያወጣቸው ዕቅዶች መረጃ እየቃረምኩ ለአብዮተኞቹ ለማስተላለፍ እንዲያመቸኝ ተብሎ በምስጢርነት የተያዘ ጉዳይ ነው። እንዲህ እጄ ውስጥ ገብቶ ሪዙን ብቻ ላጭቼ



በሰላም ለቀቅሁት ብዬ ለማስረዳት አዳጋች የሚሆንብ ኝም በዚሁ መንስኤ ነው::

አሁን ፊቱ ሙሉ በሙሉ ከጺም ፀድቷል:: ከበ ፊቱ ይልቅ ወጣት መሰለ:: በመጀመሪያ ሲገባ ተጭ ኖት የነበረው የዓመታት ሸክም ቀለል አለለት::ይህ

የፀጉር ማስተካከያ ሱቆችን በሚጉበኙ ሰዎች ላይ ሁሉ የሚደርስ ይመስለኛል:: ቶሬስ በምላጩ እየታደሰ ነበር:: የሚታደሰው ያለምክንያት አይደለም:: በከተማ ይቱ ካሉት ፀጉር አስተካካዮች መሃል አሪፍ የምባለው እኔ ስለሆንኩ ነው ለማለት እደፍራለሁ:: አሃ! እዚችጋ ትንሽ ተጨማሪ ጥሙና ያስፈልጋል:: አገጩ ሥር፣ በማንቁርቱ ዙሪያ፣ ትልቁ የደም ሥር ላይ:: ሙቀቱ ደግሞ እንዴት እየባሰበት ነው በሉ!

ቶሬስም የኔኑ ያህል እያላበው መሆን አለበት:: ፍርሃት የሚባል ግን ሲያልፍም አይነካው:: ረጋ- ፀጥ ያለሰው ነው:: ዛሬ አመሻሹ ላይ ምርኮኞቹን ምን እንደሚያደርጋቸው እንኳን አያስብም:: እኔ ግን ምላጩን በእጄ ጨብጬ፣ ቆዳውን አሥር ጊዜ መላልሼ እየቧጠጥኩ፣ እንዳላደማው እየተጠንቀቅሁ በደንብ ማሰብ ተስኖኛል::ባይመጣ ይሻለኝ ነበር- ምጣት ይምጣበትና:: ምክንያቱም እኔ አብዮተኛ እንጂ ነፍሰ ገዳይ አይደለሁም:: ደግሞ በዚያ ጊዜ እሱን መግደል እንዴት ቀላል ነበር:: መሞትም ይገባዋል:: አይገባ ውም? የለም! መጥፎ ዲያብሎስ!

አንዱ ነፍሰ ገዳይ ሊሆን ሌላውን ለሰማዕትነት ማብቃት የለበትም:: ይህንን በማድረግ ምን ይገኛል? ምን ጠብ ይላል? ምንም:: ሌሎች፣ ደግሞም ቀጥሎ ሌሎች ይመጣሉ:: የመጀመሪያዎቹ ሁለተኞቹን ይገድሏቸዋል:: እነርሱን ደግሞ ተከታዮች:: እና እንዲህ እያለ ሁሉም ነገር በደም ባህር እስኪጥለቀለቅ ድረስ ይቀጥላል:: አሁን እኔ ይህንን በመዳፌ ውስጥ ያለ ጉረሮ ላጥ! ላጥ! አድርጌ መቀንጠስ ምን ይሳነኛል:: ለመንፈራገጥም ሆነ ለጩኸት ጊዜ አይኖረውም:: ዓይኖቹም ስለተከደኑ ከምላጩና ከዓይኖቼ የሚፈነጠቀውን ነፀብራቅ እንኳን ለማየት አይበቃም:: እኔ ግን

እንደ ዕውነተኛው ነፍሰ ገዳይ እየተንዘፈዘፍኩ ነው። ...ከአንገቱ የደም ጉርፍ ይንፎለፎላል። ጨርቁን፣ ወንበሩን፣ እጆቼን፣ ወለሉን ይበክለዋል። እንዳይታይ በሩን መዝጋት ይኖርብኛል። ደሙ ግን በወለሉ ላይ ተንጣሎ መርመስመሱን ይቀጥላል። ሙቀቱ ሣይበርድ ልጥረግህ ብለው እምቢ፣ ልገድብህም ብለው አሻፈረኝ በማለት መሰስ ብሎ ወደ ጉዳናው ይወጣል። እንደ አነስተኛ ቀይ ኸረት ኩለል እያለ ይወርዳል። እርግጠኛ ነኝ ደህና አድርጌ በኃይል ከሰነዘርኩ ድጋሚ አያስፈልግም። ሥቃይም አይኖርበት።

ግን አስከሬኑንስ፣ ምን አደርገዋለሁ? የት አባቴን አደብቀዋለሁ። የሚኖረኝ አማራጭ ያለኝን ሁሉ ጥዬ ወደ ሩቅ ሥፍራ መሰደድ ብቻ ነው። ሩቅ፣ ሩቅ፣ በጣም ሩቅ ሥፍራ። ግን አይምሩኝም። እስኪይዙኝ ድረስ ያሳድዱኛል፣ ያድኑኛል። «የሻምበል ቶሬስ ገዳይ። ፊሪ - ጺሙን በሚላጨው ጊዜ እኮ ነው ያረደው። ልበ ቢስ! . . .» በሌላው ወገን ደግሞ «ደማችንን የተበቀለ ጀግና። ዘላለም ሲታወስ ሊኖር የሚገባው ስም (እና እዚህ ላይ የኔን ስም ይጠቅሣሉ) የከተማይቱ ታዋቂ ፀጉር አስተካካይ ነበር። ለዓላማችን መቆሙን፣ የትግላችን ደጋፊ መሆኑን የዚያን ጊዜ ማን አውቆ!»

ግን የዚህ ሁሉ ውጤት ምንድነው? ነፍሰ ገዳይነት ወይስ ጀግንነት? የኔ ዕጣ የሚወሰነው በጨበጥኩት ምላጭ ሥለት ነው። እጄን ትንሽ ዞር ማድረግ ጥቂት ኃይል ጨምሬ ምላጩን ጫን ማለት፣. . . ሥጋው ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማስመጥ፣ ቆዳው እንደ ሐር ይቀረደዳል፣ እንደ ጎማ ይሆነጠቃል፣ እንደ ከርታስ ይጠረመሣል። መቸም እንደ ሰው ቆዳ ለስላሳ የለም። ደሙ ደግሞ ቅርብ ስለሆነ ለመዘርገፍ ዝግጁ

ነው።ይህን መሣይ ምላጭ ደግሞ አያማናርም።እንዴ ከተሰነዘረ መች ይከሽፍና!እኔ ግን ነፍሰ ገዳይ መሆን አልሻም። የለም ጌታዩ፣ እኔ ዘንድ የመጣኸው ጺምህን ለመላጨት ነው። እኔም ተግባሬን በጨዋ ደንብ አከናውናለሁ።. . . እጄ ላይ ማመና ብቻ እንጂ ደም ማየት አልፈልግም። በቃ። አንተ የለየልህ አራጅ ነህ፣ እኔ ደግሞ የወጣልኝ ፀጉር አስተካካይ።በነገሮች አቀማመጥ ውስጥ እያንዳዱ ሰው የየራሱ ቦታ አለው። በትክክል የራሱ የሆነ ቦታ።

አሁን አገጩ በደንብ ተላጭቶ ንፁህና ለስላሳ ሆኗል። ሰውየው ከተንጋለለበት ቀና በማለት ተስተካ ክሎ ተቀመጠና ፊቱን መስተዋቱ ውስጥ ይመለከት ጀመር። ቆዳውን በጣቶቹ ሲዳስሰው አዲስ የተለወጠ ለት ያህል ሆኖ ተሰማው።

«አመሰግናለሁ» አለ። ቀበቶውን፣ ሽጉጥና መለ ዮውን ከተሰቀለበት እያወረደ። ፊቱ ግን በጣም ሳይገ ረጣ አልቀረም። ሸሚዜም ላብ ብቻ ሆኗል።

ቶሬስ ቀበቶውን በወገቡ ዙሪያ አበተና ሽጉጡን ማነደሩ ውስጥ እንዳለ አስተካከለው። ፀጉሩን በፊጣን እንቅስቃሴ ወደኋላ ከሞዠረጠ በኋላ መለዮውን አደ ረገ። ከሱሪ ኪሱ ውስጥ በርከት ያሉ ሣንቲሞች አው ጥቶ ያገልግሎቱን ዋጋ ከፈለኝና ወደ በሩ መራመድ ጀመረ። ደፉ ላይ ሲደርስ ርምጃውን ገታ አድርጎ ወደኔ ዞር በማለት፣

«ከዚህ ቤት በሕይወት እንደማልወጣ ነበር የተነ ገረኝ፣ እንደምትገድለኝ። የኔም አመጣጥ ወሬውን ለማረጋገጥ ነበር።መግደል ግን ቀላል አይደለም። እመ ነኝ፣ በፊለከው እምልልሃለሁ፣ መግደል ቀላል አይደ ለም»አለ።በዚያው ጉዳናውን ይዞ ቁልቁል ወረደ።

# ሽማግሌውና ባህሩ
/The old Man and the Sea/

በ
# ኧርነስት ሄሚንግዌይ

**"A man can be destroyed but not defeated"**
**_ Hemingway**

«ሰው ሊጠቃ ይችላል
ጨርሶ ግን አይረታም።»

- ሄሚንግዌይ

# ሽማግሌውና ባህሩ

ብቸኛ ሽማግሌ ናቸው:: ብቸኛ ዓሣ አጥማጅ:: ባህረ ሠላጤው ላይ ጀልባቸውን እየቀዘፉ ያላንዳች አጋዥ ዓሣ ያጠምዱ ነበር:: አሁን ግን አንድም ዓሣ ሳያጠምዱ ሰማኒያ አራት ቀን ሞላቸው:: የመጀመሪያ ዎቹን አርባ ቀናት ብቻቸውን አልነበሩም:: አንድ ልጅ አብሯቸው ነበር:: ከአርባኛው ቀን በኋላ ግን ተለያዩ:: ሽማግሌው የመጨረሻ ዕድለቢስ ስለሆኑ ከርሳቸው ጋር መሥራቱን እንዲያቆም ወላጆቹ ስላዘዙት ልጁ ሳይወድ በግድ ለሌሎች ዓሣ አሥጋሪዎች ተቀጠረ:: ለተን ኩሉ ደግሞ ቀናው:: በመጀመሪያው ሣምንት ብቻ ሦስት ማለፊያ ዓሣዎች ያዙ::ግን የሽማግሌው ሁኔታ ያሳዝነዋል:: ሠርክለት ባህር ለባህር ሲንገላቱ ውለው ባዶ እጃቸውን ሲመለሱ ባየ ቁጥር ሥቃይ ልቡናውን ይፈተፍተዋል:: በየዕለቱ ሽማግሌው ከባህር ውሎአቸው ሲመለሱ ወደቡ ላይ ይጠብቃቸውና የዓሣ ማጥመጃ ያዎቹን ገመዶች ወይም ባለዛቢያውን ሜንጦና* ሃርፑኑን** ተሸክሞ ወደቤት ያደርስላቸዋል:: አንዳንድ ቀን እንዲያውም የንፋሱ ሸራ*** የተጠመጠመበትን ተራዳ**** ተቀብሎ በማጓጓዝ ያግዛቸዋል:: እዚያም

---

* ባለዛቢያ ሜንጦ፣ የእንጨት ዛቢያ ያለው ሜንጦ ሲሆን ዓሣ አሥጋሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በገመድ የተያዙ ዓሣዎችን ወደ ጀልባቸው ጐትተው ለማውጣት ይጠቀሙባቸዋል::

** ሃርፑን፣ ዛቢያ የሌለው ፍላፃ:: አናቱ ላይ ግን ረጅም ገመድ ይታሰርበታል:: ዓሣ አጥማጆች በእጃቸው በመ ለጋት ወይም በተለይ ከተሰራ ጠብመንጃ በመተኰስ ዓሣ ነባሪና ሌሎች ግዙፍ ዓሣዎችን ይገድሉበታል::

*** የንፋስ ሸራ፣ ሞተር የሌላቸው መርከብና ጀልባዎች በንፋስ ኃይል እንዲጓዙ የሚረዳ በገመድ የሚወጠር ሸራ::

**** ተራዳ፣ ሸራው የሚወጠርበት ዋና ምሰሶ::

እዚያም በጆንያ የተጣጠፈው አሮጌ ሸራ ተራዳው ላይ ተጠምጥሞ ሲታይ የተሸናፊነት ቋሚ ዓርማ፣ዘወትር ድል ተመትተው የሚመለሱ ድኩማን ባንዲራ ይመስ ላል::

ሽማግሌው ቀጭን መጣጣ ናቸው:: የማጅራታ ቸው ቆዳ ተሸብሸቧል:: የፀሐይ ብርሃን ባህሩ ላይ ሲበተን በሚፈጠረው ነፀብራቅ ጦስ ያደረባቸው የቆዳ ካንሰር በጉንጫቸው ቁልቁል ተዛምቶ ማዲያት የወረ ራቸው አስመስሏቸዋል:: ግዙፍ ዓሣዎችን ከባህሩ ውስጥ በገመድ እየጎተቱ የሚያወጡባቸው መዳፎ ቻቸው ደድረው ሰንበር የመሣሰሉ ጠባሳዎች ፈጥረው ባቸው፣ የአያሌ ዓመታት የሙያ አሻራዎቻቸው ሆነ ዋል::አዎን፤ መዳፎቻቸው የዓሣ ዘር በሌለበት ምድረ በዳ የሚገኝ፣ አፈሩ ተጠርጐ ያለቀ አሮጌ መሬት ይመስላሉ::

ሁለመናቸው አሮጌ ነው:: መረታት ብሎ ነገር ከማይታይባቸውና ዘወትር ደስታ ከሚንፀባረቅባቸው ባህሩን ከሚመስሉ ዓይኖቻቸው በስተቀር ምናቸውም ምናቸውም አርጅቷል::

«ሳንቲያጐ፤»አለ ልጁ ጀልባዋ ከቆመችበት የባህሩ ዳርቻ ጀምሮ የሚያሻቅበውን ዳገት መውጣት እንደ ጀመሩ:: «አሁን እንደገና ከርሶ ጋር ለመሥራት እችላ ለሁ:: ሰሞኑን ደህና ስለሠራን ትንሽ ገንዘብ አግኝ ቻለሁ»

ልጁን ዓሣ ማስገር ያስተማሩት ሽማግሌው ስለ ነበሩ ከልብ ይወዳቸዋል::

«አሁን ገዳም ሰዎች አግኝተሀል:: ከነርሱ ጋር መቆየት አለብህ::»

«ግን ኮ እርስዎ ዓሣ ሳያሰግሩ ያሳለፏቸውን ሰማኒያ ሰባት ቀኖች ያስታውሱ፤ እኛ ግን ይኸው ሦስት ሣምንታችን፣በየቀኑ አንድ ትልቅ ዓሣ እናሰግራለን።»

«አስታውሳለሁ፣» አለ ሽማግሌው። «ጥለኸኝ የሄድከው የኔን ዕድል ሸሽተህ፣ እንደማይሣካልኝ ተጠራጥረህ እንዳልሆነ አውቃለሁ።»

«አባባ እኮ ነው ከርሶ ጋር እንዳልሠራ የከለከለኝ።ልጅ ስለሆንኩ ደግሞ የአባቴን ትዕዛዝ ለማክበር ተገደድሁ።»

«አውቃለሁ» አለ ሽማግሌው። «ይሄ ኮ ያለና የተለመደ ነው።»

«እሱ ብዙም ዕምነት ያለው ሰው አይደለም»

«እኛ ግን አለን። አይደል?» አለ ሽማግሌው።

«አዎ፣» አለ ልጁ። «ወደ ቡና ቤቱ ሄደን ቢራ ብጋብዝዎትስ? ዕቃውን ከዚያ በኋላ እናደርሰዋለን።»

«ምናለ፣ መልካም ነዋ፣»አለ ሽማግሌው።«ይህኮ በዓሣ አጥማጆች ዘንድ ያለና የተለመደ ነው።»

ቡና ቤቱ በረንዳ ላይ ቦታ ፈልገው ቁጭ አሉ። ሥፍራውን ካጣበቡት ዓሣ አጥማጆች መካከል ብዙዎቹ በሽማግሌው ላይ መቀለድ ጀመሩ። እሳቸው ግን ቅር አልተሰኙም፣ አልተቆጡም። በዕድሜ ጠና ያሉት ግን በፀጥታ ያስተውሏቸዋል። አፍ አውጥተው አልተናገሩም እንጂ እንዳዘኑላቸው ያስታውቃል። ስለወቅቱ አየርና ስለግል ገጠመኞቻቸው እያነሡ በለሆሣስ ያወጋሉ። ምድረ ዓሣ አጥማጅ ከየዋለበት ተመልሶዋል።

በለስ የቀናቸው ማርሲኖች ብልት በደንብ አውጥተው በሁለት ቀጫጭን ረጃጅም ጣውላዎች ላይ በመደርደር ለሁለት እየተሸከሙ ወደ ዓሣ መሸጫ ሱቆች ይርገደገ ዳሉ። የበረዶ ቤት በላያቸው የተገጠመላቸው ከባድ መኪኖች ምርቱን እየጫኑ ወደ ሀቫና ለማጓጓዝ በየ ሱቆች ደጃፍ ቆመው ይጠባበቃሉ። ሻርክ ያጠመዱት ደግሞ ግዳያቸውን ወደ ፋብሪካው ወስደዋል። እዚ ያም በትልልቅ ማንጠዎች ላይ ተንጠልጥለው የመበ ለቱ ሥራ ይከናወናል። ጉበታቸው ይወጣል... ክንፎቻ ቸው ይመለመላሉ . . . ቆዳቸው ይገፈፋል . . . ሥጋቸው እየተዘለዘለ በጨው ይለወሣል።

ዘወትር ንፋሱ ከወደ ምሥራቅ በኩል በሚነፍስ ጊዜ ከሻርክ ፋብሪካው የሚመጣ ሽታ አፍንጫ እያረ መደ ያልፋል። ዛሬ ግን ንፋሱ ወደ ሰሜን ተመልሶ ፀጥ ስላለ ብዙ ሽታ የለም። የቡና ቤቱ በረንዳ በም ሽት የፀሐይ ብርሃን ደምቆ እየሩም የደስ ደስ አለው።

«ሳንቲያጎ» አለ ልጁ።

«አቤት» አሉ ሽማግሌው፣ ብርጭቆአቸውን በእጃ ቸው እንደጨበጡ። ብዙ ዓመታት ወደ ኋላ ተመል ሰው በትዝታና በሀሳብ በመማሠን ላይ ነበሩ።

«አንዳፍታ ሮጥ ብዬ ለነገ የሚሆንዎትን ሠርዲን ላምጣልዎት?»

---

ማርሊን፣ በትልቅነቱ የታወቀ የዓሣ ዝርያ ነው።
ሻርክ፣ ሥጋ በል የሆነ አደገኛ የዓሣ ዝርያ ነው። ሰውን በመተናኮል የታወቀ።

«የለም አያስፈልግም:: ይልቅ ሂድና ቤዝቦል* ተጫወት:: አሁንምኮ ገና ነኝ:: በደንብ መቅዘፍ እችላ
ለሁ:: አስፈላጊ ከሆነ ሮጄሊዮ ያግዘኛል::»

«እኔ ግን አብሬዎት ብሄድ ነው ደስ የሚለኝ:: ዓሣ ባላጠምድም በሌላ መንገድ ልረዳዎት እፈል
ጋለሁ::»

«ተንግዲህማ ትልቅ ሰው ሆነሃል:: ስለዚህ ራስ
ህን መቻል አለብህ፣» አለ ሽማግሌው:: «ለኔ እንኳን ይኸው ቢራ እየገዛህልኝ አይደል?»

«ያኔ በጀልባዋ አሳፍረውኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ባህር ሲወስዱኝ ስንት ዓመቴ ነበር?»

«አምስት ዓመትህ ነበር:: ያን ጊዜ የያዝኩት ዓሣ ገና ጉልበቱ ሣይዝል ከባህሩ ጐትቼ ሳወጣው ጀልባ
ዋን ዘጠኝ ትንንሽ አድርጐ እንደበታተናት አንተም የሞትክ ያህል እንደነበርክ ትዝ ይልሀል?»

«በደንብ ነዋ:: እንዳንድ ነገር እየተወራጨ ጭራ
ውን እዚያና እዚህ እያማታ ከጀልባዋ ጋር ሲወቃው፣ የርሶን መቀመጫ አግዳሚ ጣውላ ሲያነካክተውና የዱላ መዓት ሲያወርዱበት ሁሉም በደንብ ይታወሰ
ኛል:: ርጥቡ ገመድ ተጠቅልሎ ወደተቀመጠበት የጀል
ባዋ አፍንጫ* አሽቀንጥረው ሲወረውሩኝ፣ ጀልባዋ እንደ

---

* ቤዝቦል፣ በአሜሪካ የተወደደ የስፖርት ዓይነት:: በቀድሞ ጊዜ ልጆች «የጅ ቦምብ» እያሉ የሚጠሩትን ጨዋታ ይመስላል::
* የጀልባ አፍንጫ፣ ይህ ቃል በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የሚያ
መለክተው የጀልባም ሆነ የመርከብ የፊት ለፊት ክፍል /ጉንናጉኖቹ የሚገናኙበትን/ አካባቢ ነው::

አንድ ነገር ስትርገፈገፍ፣ እርሶም ልክ ዛፍ እንደሚ. ቆርጥ ሰው እየተንጠራሩ ዓሣውን በዱላ ሲነርቱት፣ ምኑ ቅጡ ሁሉም ትዝ ይለኛል:: ሌላው ቀርቶ ሁለ መናዬን በከሎት የነበረው የዓሣው ደምና የሚጣፍጥ ሽታው አይረሳኝም::»

ሽማግሌው የፀሐይ ብርሃን ባደከማቸው ዓይኖች ልጁን አተኩረው ያስተውሉት ጀመር::

«የኔ ልጅ ብትሆን ኖሮ ምንም ላድርግ ምን ከአ ጠገቤ ባለየሁህ ነበር፤» አሉ ሽማግሌው:: «ግን ምን ያደርጋል፣ አንተ ያባትህና የናትህ ገንዘብ ነህ:: አሁን ደግሞ ገድ ካላቸው ሰዎች ጋር እንድትሠራ ታዞ ሀል::»

«ይበሉ ልሂድና ሠርዲኑን ላምጣልዎት:: አራት ዓሣዎችን ለማጥመድ የሚበቃ መደለያ የማገኝበት ቦታ አለ::»

«ምን አስቸገረህ ልጄ:: እኔም'ኮ ገና ያልተነኩ አሉኝ::ከዛሬ የተረፉትንም ከጨው ጋር አድርጌ ሳጥኑ ውስጥ አኑሬአቸዋለሁ::»

«ግዴለዎትም፣እኔ ደግሞ አራት ተጨማሪ ትኩስ ላምጣልዎት::»

«እንግዲያው አንድ:: አንድ ብቻ ይበቃል፤» አሉ ሽማግሌው::ዕምነታቸው በጭራሽ ተበግሮ አያውቅም:: ተስፋቸውም አላከተመም:: እንዲያውም ንፋሱ ማየል ሲጀምር እርሳቸውም እንደገና መታደስ ጀመሩ::

«እሺ. ሁለት ላርገው፤» አለ ልጁ::

«ደህና። እንዳልክ ይሁንልህ።» ሽማግሌው ስምምነታቸውን ገለጡ። «ግን አልሰረቅሃቸውም አይደል?»

«አስፈላጊ ከሆነ የማልሰርቅበት ምክንያት የለም፤» አለ ልጁ። «እነዚህ ግን በገንዘቤ የገዛሁዋቸው ናቸው።»

«አመሰግናለሁ» አሉ ሽማግሌው። «ከዚህ የአየር ጠባይ ጋር ነገ ደህና ማይሆን አይቀርም።»

«ወዴት ለመሄድ ነው ሃሳብዎ?» ልጁ ጠየቀ።

«ራቅ ለማለት ነው ያቀድኩት። ስለዚህ ጉህ ሳይቀድ መውጣት አለብኝ።»

«እኔም አሠሪዬ ራቅ ብሎ እንዲወጣ ለመገፋፋት እሞክራለሁ፤» አለ ልጁ። «ምናልባት ትልቅ ዓሣ ያጋጠመዎት እንደሆነ እናግዝዎታለን።»

« እሱ ደግሞ ካለ ነገሩ ሁሉ ርቆ ሄዶ መስራት አይወድም።»

«በጭራሽ!» አለ ልጁ። «ግን እርስዎ እንዴት ነዎት?»

«እኔኮ የተለየሁ ሽማግሌ ነኝ»

«ድንገት ትልቅ ዓሣ ቢያጋጥመዎት ጉልበትዎ የሚያስተማምን ነው?»

«ይመስለኛል። ደግሞ ጉልበት ብቻ አይደለም። ብዙ ዘዴዎችምኮ አሉ።»

«ይበሉ አሁን እንሂድና ዕቃውን ወደ ቤት እናድርስ» አለ ልጁ።

ሽማግሌው ተራዳውን አንስተው ትከሻቸው ላይ አጋደሙት።ልጁ ደግሞ በወፍራሙ የተሸረበት በናማ

ጠንካራ ገመዶች ከሚንጠው፣ ከሀርፑንና ከጦሩ ጋር የተቀመጠበትን የእንጨት ሣጥን አንጠለጠለ:: ለዓሣ መደለያ የሚሆኑ ሥጋዎችን የያዘው ሣጥን ከጀልባዋ ላይ አልወረደም:: ግዙፍ ዓሣዎች በሚያዙ ጊዜ ቶሎ አልሞት ብለው ሲያውኩ የሚወገሩበትና መንፈራገጣቸውን አቁመው ወደ ዘላለማዊ ፀጥታ እንዲተላለፉ የሚያስተናግዳቸው ቆመጥ እዚያው ተጋድሟል:: የሽማግሌውን ንብረት ለመስረቅ የሚደፍር ማንም የለም:: ግን ለከፋውም ለደጉ በተለይ ሸራውንና ገመዶቹን ወደ ቤት ማስገባቱ ይበጃል:: ጤዛውም ቢሆን ሊጎዳቸው ይችላል:: ነዋሪዎቹ ዕቃቸውን ለመንካት እንደማይደፍሩ ቢያውቁም ሚንጦና ሀርፑ በግላጭ ሲገኝ የማንንም ፍላጎት እንደማይፈታተን ሽማግሌው ማሰባቸው አልቀረም::

ተከታትለው ወደ ሽማግሌው ደሣሣ ጎጆ አመሩ:: ወደ ውስጥ እንደገቡ ሽማግሌው ሸራ የተጠመጠመበትን ተራዳ በዝግታ ግድግዳው ላይ አስደገፈው አቆሙት:: ልጁም ሣጥኑን አጠገቡ አስቀመጠው:: የተራዳው ቁመት ከጎጆው ቁመት ጋር እኩል ነው:: ከጉዋና* ቅጠልና ቅርንጫፎች በተሠራችው ድስቅስቅ ጎጆ ውስጥ ብዙም ቁሳቁስ የለም::አንድ አልጋ፣ አንድ ጠረጴዛና አንድ ወንበር ብቻ:: ተጠርጎ በማያውቀው ወለል ላይ የከሰል ምድጃ ተጎልቷል:: የጉዋናው ቅጠል እየተደራረበ በተሰራው ግድግዳ ላይ የክርስቶስን ቅዱስ ልብ የሚያሣይ በህብረ ቀለም የተሰራ ሥዕል ተንጠልጥሏል:: የድንግል ማርያም ምሥልም አለ:: ሁለቱም የሚስታቸው መታሰቢያዎች ናቸው:: በፊት ጊዜ የሚስታቸውን ፎቶግራፍ ግድግዳው ላይ ይሠቅሉ ነበር:: ኋላ ኋላ ግን ብቸኝነታቸው ጉልቶ

---

*ጉዋና፣ የዘምባባ ዝርያ የሆነ የዛፍ ዓይነት::

እንዲሰማቸው እያደረገ ስላስቸገራቸው አወረዱት። በአንደኛው ጥግ በሚገኘው መደርደሪያ ላይ ከንፁህ ሸማዛቸው ሥር አስቀመጡት።

«ለመሆኑ የሚበላ ነገር ምን አለዎት?» የልጁ ጥያቄ ነበር።

«ሩዝና ትንሽ ዓሣ አለ። ምነው የሚቀመስ ነገር ፈለግህ?»

«የለም። እኔ ቤት ሄጀ እበላለሁ። ምናልባት እርሶ የሚያስፈልግዎት ከሆኑ እሣት ላያይዝልዎት?»

«ግዴለም። ወደኋላ ግድም እኔው ራሴ አያይዘ ዋለሁ። ሩዙንማ ቀዝቃዛውንም ብበላው ይሆናል።»

«እንግዲያው ትልቁን የዓሣ ማጥመጃ መረብ ይገፍ ልሂድ?»

«እንዴታ፣ ትችላለህ!»

እንደዕውነቱ ከሆነ ግን በዚያ ቤት መረብ የሚ ባል ዘሩ አልነበረም። መቼ እንደተሸጠ ልጁ በሚገባ ያስታውሣል። ግን ይህንን ዓይነቱን ቀልድ በየቀኑ መደጋገሙን ሁለቱም ሥራዬ ብለው ይዘውታል። ውሸት ነው፤ በቤቱ ሩዝና ዓሣ የሚባል ሽታው እንኳ የለም። ሁለቱም ደህና አድርገው የሚያውቁት ዕው ነታ ነው። ግን ሁሉም ነገር እንዳለና እንደተሟላ እያ ስመሰሉ በቀልድ መልክ መጫዋወቱን ልማድ አድርገ ውታል።

ስለ ቤዝቦል፣ ሁለቱም ስለሚወዷቸው የአሜሪካ ቡድኖችና መሪዎቻቸው፣ የሎተሪ ቲኬት ገዝተው ዕድ ላቸውን መሞከር ያለባቸው ስለመሆኑ እያነሡ ሲያወጉ ቆዩ።

«ብቻ እንዳይበርድዎት ይጠንቀቁ። በምንም በም ንም መሟሟቅ ነው፣» አለ ልጁ በመጨረሻ። «ያለን በት ወር መስከረም መሆኑን አይርሱ።»

«መች አጣሁት። ትልቁ ዓሣ የሚመጣበት ወር አይደል? ዕውነተኛው አጥማጅም የሚለካበት ወቅት ነው» አሉ ሽማግሌው። «በግንቦት ማንም ተነስቶ ዓሣ አጥማጅ ሊሆን ይችላል።»

«አሁን ልሂድና ሠርዲኑን ላምጣልዎት፣» አለ ልጁ።

ከሄደበት ተመልሶ ሲመጣ ሽማግሌው ወንበራ ቸው ላይ እንደተቀመጡ እንቅልፍ ድብን አድርጐ ወስዷቸዋል። ፀሐይዋ ጨርሣ ጠልቃለች። ልጁ አል ጋው ላይ የነበረውን የወታደር የብርድ ልብስ አንሳና በወንበሩ ጀርባ አዙሮ ሽማግሌው ትከሻ ላይ ደረ በው። ልዩ ዓይነት ትከሻዎች ነበሩ። ምንም እርጅና ቢጫናቸው ገና በጥንካሬ እንደተሞሉ ናቸው። አንገ ታቸውም ገና ብርቱ መሆኑ ያስታውቃል። አሮጌ ሸሚዛቸው ተደጋግሞ የተጣጠፈ ነው። ከጀልባዋ ሸራ ጋር ይመሳሰላል። ሸሚዙ የተጣጣፉባቸው ጨርቆች የተለያዩ ቀለሞች በፀሐይ ብርሃን የተነሣ ተለውጠ ዋል። ዓይኖቻቸውን ሲከድኑ በአዛውንቱ ፊት ላይ አንዳችም ህይወት አይታይም። ሊያነቡ ጀምረውት የነበረው ጋዜጣ ጉልበታቸው ላይ እንደተዘረጋ ነው። ክንዳቸው ባይጫንበት ኖሮ የምሽቱ ንፋስ አውለብልቦ በወሰደው ነበር። ጫማ እንኳን የላቸውም። ባዶ እግ ራቸውን ናቸው።

«አበባ... አባባ፣» አለና ልጁ፣ እጁን አንደኛው ጉልበታቸው ላይ አሣረፈ።

ሽማግሌው ዓይኖቻቸውን ከፈቱ:: ተንዘውበት ከነ በረው ሩቅ ሥፍራ ለመመለስ ረጅም ጊዜ ወሰደባ ቸው:: በመጨረሻ ፈገግ አሉ::

«ምን ይዘህ መጣህ?» ሲሉ ልጁን ጠየቁት::

«ራት ቢጤ ነው» አላቸው::«ራታችንን በአንድነት እንድንበላ ብዬ ነው::»

«እኔ እንኳን ብዙም አልራብኝም::»

«አይ እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን አባባል ትተው ይልቅ ይያዙ:: ትንሽም ቢሆን ይቅመሱ:: ምግብ ሳይ በሉ ዓሣ ማጥመድ አይቻልም::»

«ይቻላል እንጂ ለምን አይቻልም:: እኔ በየቀኑ እያደረግሁት አይደል?» አሉ:: ሽማግሌው ከተቀመ ጡበት ተነስተው ጋዜጣውን ከአጣጠፉ በኋላ የብር ድልብሱን መቀለጣጠም ጀመሩ::

«የብርድልብሱን ቢለብሱት ይሻላል» አለ ልጁ:: «እኔ በህይወት እስካለሁ በባዶ ሆድዎ ዓሣ ሊያጠ ምዱ አይወጡም::»

«እንግዲያስ ረጅም ዕድሜ ይስጥህና ራስህን ለመ ጠበቅ ተጠቀምበት» አሉ ሽማግሌው:: «ለመሆኑ ምን ድነው ያመጣኸው?»

«ፋሶሊያና ሩዝ:: የተጠበሰ ሙዝና ጥቂት ሱጐ ነው::»

ልጁ ምግቡን ከቡና ቤቱ ያመጣው በስከ ሣህን ነበር:: ለሁለት ሰዎች እንዲሆኑ ብሎ ያመጣቸውን ማንኪያና ቢላዎች በአፍ መጥረጊያ ወረቀት ጠቅልሎ በኪሱ ይዟቸዋል::

«ይሄን ሁሉ ማን ሰጠህ?»
«ማርቲን ነው። የቡና ቤቱ ባለቤት።»
«ምስጋናየን መግለፅ አለብኝ።»

«አያስፈልግም። እኔ እንደ አመስግንዋለሁ።» አለ ልጁ። «የርሶ ድጋሚ ምስጋና አያሻም።»

«ትልቅ ዓሣ በምይዝ ጊዜ ደህና ብልት መርጬ አስጠዋለሁ» አለ ሽማግሌው፤ «ለመሆኑ እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም አድርጉ ያውቃል?»

«ይመስለኛል።»

«በጣም ያስብልናል ማለት ነው። ስለዚህ ስጦታው ከሆድ'ቃ ብልት ሻል ያለ መሆን ሊኖርበት ነው።»
«ሁለት ቢራም ልኳል።»

«በጣም የሚያስደስተኝ የጣሣ ቢራ ነው።»

«አውቃለሁ።ግን አሁን ያመጣሁት የጠርሙሱን ነው። ጠርሙሱ ይመለሣል ብሎኛል።»

«ደግነትህና ውለታህ እየከበደኝ ነው አንተ ልጅ»

አሉ ሽማግሌው።«ታዲያ ምን እንጠብቃለን፣እንበላም?»
«እኔማ ብዬ ነበር» አለ ልጁ በጨዋ አነጋገር።

«ሣህኑንም ያልከፈትኩት እስኪዘጋጁ ብዬ ነው።»

«አሁን ዝግጁ ነኝ» አሉ ሽማግሌው።

«መታጠብ ብቻ ነው የምፈልገው።»

ለመሆኑ የት ይሆን የሚታጠቡት? ልጁ በሀሳቡ ነበር ጥያቄውን ያነሣው። የመንደሬቸው የቦኖ ውሃ ትንሽ ራቅ እንደሚል ያውቃል።ውሃ፣ ሣሙናና ንፁህ ፎጣ አዘጋጅቼ እቤታቸው ውስጥ ማስቀመጥ ይገባኝ ነበር። ግን እስከዛሬ እንዴት አላሰብኩበትም? ቆይማ፣ ለክረምቱ የሚሆናቸውን ቅያሬ ሸሚዝና ጃኬት፣ አንድ ጫማና የብርድ ልብስ አመጣላቸዋለሁ።

«ድንቅ ሰው አይደለምንዴ ጃል?»አሉ ሽማግሌው።

«እስቲ ስለቢዝቦል ትንሽ ያውሩልኝ» አላቸው ልጁ።

«እሱማ እንግዲህ፣ያው ፊት እንዳልኩህ ከአሜሪካ ታላላቅ ቡድኖች መካከል በጣም ኃይለኞቹ ያንኪዎች ናቸው።» ሽማግሌው ሲናገሩ ደስታ እየተሰማቸው ነበር።

«ግን ታዲያ እነሱ ትናንት ተሸነፉ አይደል?» በማለት ልጁ ጠየቀ።

«ምንም አይደለም። ትልቁ ዲማጆዩ ወደ ቀድሞ ቦታው እየተመለሰ ነው።»

«ከሱ በስተቀር ቡድኑ ሌሎች ጉበዝ ተጨዋቾች የሉትም?»

«ሞልተውት፣ ግን የዲማጅዬ ልዩ ነው። የሱ መኖር አለመኖር ወሣኝነት አለው። ሌላው ትዝ የሚለኝ አሪፍ ተጨዋች ደግሞ ዲክ - ሲስለር ነው።»

«ዕውነትም። በተለይ ኳስ በመለጋት በሱ ልክ የሚሆን እስከዛሬ አይቼ አላውቅም።»

«ለመሆኑ ያኔ እዚህ መጥቶ ትልቁ ቡና ቤት ውስጥ አረቄውን ሲቀመቅም ትዝ ይልሀል? አብሮኝ ሂዶ ዓሣ እንዲያጠምድ ለማድረግ ስንቴ ነበር መሰለህ የተመኘሁት::ግን ምን ያደርጋል:: መጠየቁ እያሣፈረኝ ተውኩት:: አንተንም እንድትለምነው ብጠይቅህ መድፈር ተሣነህና በምኞት ብቻ ቀረ::»

«ሁሉንም በደንብ አስታውሣለሁ:: አለመጠየቃችን ግን ስህተት ነበር::እሺ ሊለንም ይችል ነበር:: ዕድሜ ያችንን ሙሉ የማንረሣው ቁም ነገር ይሆን ነበር::»

«ታላቁን ዲማጅዮን ዓሣ እንዲያጠምድ በጀልባዬ አሣፍሬው ወደ ባህሩ ብወጣ ደስ ብሎኝም አያበራ ነበር፣»አለ ሽማግሌው:: «አባቱም ዓሣ አጥማጅ ነበሩ ይባላል:: ምናልባት እንደኛ ድህነት ያደቀቃቸውም ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ ስሜታችንስ ሳይገባው ይቀር ነበር ብለህ?»

«የታላቁ ሲስለር አባት ግን ድሀ እንዳልነበሩ ሰምቻለሁ::ደግሞም በኔ ዕድሜ እያሉ በየትልልቆቹ ቡድኖች ውስጥ ይጫወቱ ነበር ይባላል::»

«እኔ ደግሞ አንተን በማህል ጊዜ በመርከብ ተሣፍሬ ወደ አፍሪካ ሄጄ ነበር:: ማታ ባህሩ ዳርቻ ላይ ተጉልቼ አንበሶችን ስመለከት ነበር የሚመሽው::»

«አዎ፣ አንድ ጊዜ ነግረውኛል::»

«ስለዚህ አሁን ስለማን እንጨዋወት? ስለ አፍሪካ ወይስ ስለቤዝቦል?»

«ቤዝቦል ይሻላል» አለ ልጁ:: «እስቲ ስለታላቁ ጆን ጄ ማክግሮው ደግሞ ያውሩኝ::»

«እሱም ድሮ ወደዚህ ይመጣጣ ነበር::በቃ ቁጡና ተሣዳቢ ስለሆነ በሚሰክር ጊዜ ትልቅ ችግር ይፈጥር ነበር::»

«ግን ትልቅ የቡድን መሪ ነበር ይባላል» አለ ልጁ። «እንዲያውም አባቴ ከሁሉም የሚበልጠው እሱ ነው እያለ ሲያወራ ሰምቼዋለሁ።»

«አዘውትሮ ወደዚህ ይመጣ ስለነበር ነው» አሉ ሽማግሌው። «ምናልባት ዱሮቸር ወዲህ መምጣቱን ቀጥሎ ቢሆን አባትህ ከሁሉም የሚያስበልጠው እሱን በሆነ ነበር።»

«ግን ያለምንም ማዳላት ዕውነተኛው ታላቅ የቡድን መሪ ማነው ይላሉ? ሉቃስ ወይስ ሚካኤል ጐንዛሎስ?»

«ሁለቱም እኩል ይመስሉኛል»

«ከዓሣ አጥማጆች ደግሞ አሪፉ እርሶ ነዎት።»

«አዬ! እሱን እንኳን ተወው። ከኔ የሚበላልጡ ሌሎች ስንትና ስንት አሉ።»

«ኬሻ* »አለ ልጁ። «በርግጥ ብዙ ጥሩ ዓሣ አጥማጆችና ጥቂት ደግሞ ታላቅ ሊባሉ የሚበቁ አሉ። የርሶ ግን ለብቻው ነው።»

«አመሰግናለሁ። እንዲህ ስትናገር ልቤን ደስ ይለዋል።ግን አንድ ቀን ግዙፍ ዓሣ አጋጥሞን ይህ ዕምነታችን የተሣሣተ መሆኑን አጋልጦ እንደሚያሣጣን አልጠራጠርም።»

«ይህን ሊያደርግ የሚችል ዓሣ እንኳን የለም። በተለይ ጥንካሬዎ ልክ እርስዎ እደሚሉት ከሆነ።»

---

* ኬሻ፣ የስፓኒሽ ቃል ሲሆን ትርጓሜው «ምንም አይደል» እንደማለት ነው።

«ብቻክ የማስበውን ያህል ጠንካራ ላልሆን እችላ ለሁ»አሉ ሽማግሌው። «ግን ብዙ ዘዴዎች አውቃለሁ። በዚያ ላይ ደግሞ ቆራጥ ነኝ።»

«ይበሉ አሁን በጊዜ ይተኙ። ጧት ንቁና ብርቱ እንዲሆኑ ይረዳዎታል። እኔም ዕቃዎቼን ሰብስቤ ወደ ቡና ቤቱ እሄዳለሁ።»

«እንዲያ ከሆነ መልካም። በሰላም ያሣድርህ። ማልጄ እነሣና አንተንም እቀሰቅስሃለሁ።»

«መቼም ቀስቃሽ ሰዓቴ እርስ ነዎት» አለ ልጁ።

«የኔ ቀስቃሽ ደግሞ ዕድሜዬ ነው» አሉ ሽማግ ሌው። «ግን የኔ ብጤ አሮጌዎች ማልደው የሚነቁት ለምን ይሆን? ምናልባት አንድ ተጨማሪ ረጅም ቀን ለመኖር በመፈለግ ይሆን?»

«እንጃ» አለ ልጁ። «እኔ የማውቀው ትንንሽ ልጆች ተኝተው የሚያረፍዱ መሆኑን ብቻ ነው።»

«አይዞህ አልረሣህም። በሰዓቱ እቀሰቅስሀለሁ» አሉ ሽማግሌው።

«አሰሪዬ እንዲቀሰቅሰኝ አልፈልግም። እሱ በቀሰ ቀሰኝ ቁጥር የዝቅተኝነት ስሜት ያሠቃየኛል። ከሱ ያነስኩ ይመስለኛል።»

«አውቃለሁ።»
«መልካም እንቅልፍ አባባ።»

ልጁ ውልቅ ብሎ ሄደ። ራታቸውን የበሉት በጨ ለማ ውስጥ ነበር። ጠረጴዛው ላይ መብራት የለም። ልጁ እንደሄደ ሽማግሌው ሱሪያቸውን አወለቁና በዳ በሣ ወደ አልጋቸው አመሩ። ከዚያ በኋላ የአሮጌ ጋዜ ጦች እንሶላ ለብሰው የሽቦ አልጋቸው ላይ ኩርምት ብለው ተኙ - ከላይ የብርድ ልብሳቸውን ጣል አድ ርገው።

ወዲያው በጥልቅ እንቅልፍ ተዋጡና በህልማቸው ወደ አፍሪካ ተመለሱ። በልጅነታቸው አይተዋቸው የነበሩ ወርቃማና ነጫጭ የባህር ዳርቻዎች እንዲሁም ቡናማ ቀለም ያላቸውን ተራሮች ማየት ጀመሩ።

ዘወትር የሚያልሙት ስለቦታዎች ብቻ ከሆነ ጊዜው ቆይቷል። ስለማዕበል፣ ስለቢቶች፣ ድንቅ ስለ ሆኑ አጋጣሚዎች፣ ስለትልልቅ ዓሣዎች ወይም ስለ ሚስታቸው ማለም ካቆሙ ብዙ ዓመታት አልፈዋል። አሁን አሁን በህልማቸው የሚያዩት የተለዩ ሥፍራዎችንና በአፍሪካ የባህር ዳርቻዎች ላይ ብላቴና ሳሉ አይተዋቸው የነበሩ አንበሶችን ብቻ ሆኗል። ምሽት ጥቁር በርኖሱን ለምድራቱ ማከናነብ ሲጀምር አናብስቱ እንደ ድመት ግልገሎች እየተላፉ መጫወቱን ይያያዙታል። አንበሶቹን የሚወዷቸው የልጁን ያህል ነው። ግን ልጁን አንድ ቀን እንኳን በህልማቸው አይተውት አያውቁም።

ሲነጋጋ ሲል ከእንቅልፋቸው ነቁ። ገርበብ ባለው በር በኩል ውጪውንና ጨረቃዋን አሾልቀው ተመለከቱና ተንተርሰውት ያደሩትን ሱሪ ከራስጌያቸው አንስተው አጠለቁት። ከጐጆዋቸው ወጥተው ሽንታቸውን ከከፈሉ በኋላ መንገዱን ይዘው ወደ ልጁ መኖሪያ አቀኑ። የማለዳው ብርድ ያንቀጠቅጣቸዋል። ብዙ እንደማይቆይ ግን ያውቁታል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጀልባቸው ላይ ጉብ ብለው ግዙፉን ባህር መቅዘፍ ሲጀምሩ የሠራ አካላቸው ይሟሟቃል።

ልጁ የሚኖርበት ቤት በር ስላልተቆለፈ ገፋ አድርገው፣ በባዶ እግራቸው መሬቱን ጠቀስ ጠቀስ እያደረጉ ያላንዳች ኮሽታ ወደ ውስጥ ገቡ።ልጁ በመጀመሪያው ክፍል ውስጥ ድንክ አልጋ ላይ ተኝቷል።

መከሰም በጀመረችው ጨረቃ ስልምልም ብርሃን ሸማ ግሌው በደንብ ያዩታል። ጠጋ አለና አንድ እግሩን ያዝ አደረጉት። ሲነቃ ሸማግሌው በራሳቸው ንቅናቄ ምልክት ሰጡት። ከመቅፅበት ቀና አለና ሱሪውን አጠ ገቡ ከሚገኝ ወንበር ላይ አንስቶ አጠለቀው - አል ጋው ላይ እንደተቀመጠ።

ሸማግሌው ቀድመው፣ ልጁ ተከትሎ ከቤቱ ወጡ። ሸማግሌው ገና እንቅልፉን ባልጨረሰው ልጅ ትከሻ ላይ እጃቸውን ጣል በማድረግ አቀፉትና፣ «ይቅርታ» አሉት።

«ኬሻ»አለ ልጁ «መሆን ያለበት ጉዳይ ነው።»

መንገዱን ይዘው ወደ ሸማግሌው ጉጆ አመሩ። በማለዳው ፈዛዛ ብርሃን ባልተሸነፈው አፈና ውስጥ ለእግራቸው ጫማ የሌላቸው በርካታ ሰዎች መንገዱን ሞልተው ይተላለፋሉ።ሁሉም የየጀልባዎቻቸውን ተራዳ ተሸክመዋል።

ወደ ጉጆዋ እንደደረሱ ልጁ ሚንጦውን፣ ሀርፑ ኑንና የተጠቀለለትን ገመዶች ከተቀመጡበት አንስቶ ያዘ። ሸማግሌው ደግሞ የጀልባዋን ተራዳና ሸራውን ተሸከሙ።

«ቡና ይሻዎታል?» የልጁ ጥያቄ ነበር።

«ዕቃዎቹን ጀልባዋ ውስጥ ካኖርን በኋላ እን ጠጣለን።»

በተለይ ለዓሣ አጥማጆች ሲባል በሌሊት ወደ ሚከፈት የሻይ ቤት ሄደው በወተት ጣሣ የተቀዳ ቡና ቀመሱ።

«ለመሆኑ ጥሩ እንቅልፍ ተኙ?»ልጁ ጠየቃቸው። አሁን እንቅልፉ እየለቀቀው በመሄድ ላይ ነበር።

«በደንብ ነው የተኛሁት ማኛሊን» አሉ ሽማግ ሌው። «ዛሬ በራስ የመተማመን ስሜት አጥብቆ ይሰማኛል።»

«እኔም» አለ ልጁ። «ይበሉ አሁን ለዓሣ መደለያ የሚሆኑትን ቅንጥብጣቢ ሥጋዎችና ሰርዲኖች ላምጣ ልዎ። የኛን መጫሪያዎች ወደ ጀልባው የሚወስደው ሰው ያው ራሱ ነው። ማንም እንዲያግዘው አይፈ ልግም።»

«እኔና እሱ ሁለት የተለያየን ሰዎች ነን።» አሉ ሽማግሌው።«ገና የአምስት ዓመት ልጅ እያለህ እንኳን አንዳንድ ዕቃዎች አሸክምህ እንደነበር ትገዝ ይልሀል?»

«በደንብ ነዋ» ሲል መለሰላቸው።«ይበሉ እኔ ሄጄ ልምጣ። እርሶ ቡናውን ይድገሙ። እዚህ ቤት ያምኑ ናል፣ ዱቤ መውሰድ እንችላለን።»

በባዶ እግሩ ነጠር እያለ ዓሣ መደለያ የሚሆኑ ሥጋዎችና ሰርዲኖች ወደሚሸጡበት ሱቅ ተፈተለከ።

ሽማግሌው ቡናቸውን በዝግታ ፉት ማለታቸውን ቀጠሉ። ቀኑን ሙሉ ሌላ ነገር ስለማያገኙ በደንብ መጠጣት እንዳለባቸው ያውቁታል።መብላት ብሎ ጣጣ በጣም አሰልች ከሆነባቸው ውሎ ስላደረ ምሣቸውን ይዘው መሄድ ካቆሙ ሰንብቷል። ጀልባቸው ውስጥ አንድ ጠርሙስ ውሃ አለ። ለዕለቱ የሚያስፈልጋቸው ያ ብቻ ነው።

ልጁ ለዓሣ መደለያ የሚሆኑትን ሠርዲኖችና የሥጋ ቅንጥብጣቢዎች በጋዜጣ ጠቅልሎ እንደ ተመ ለሰ ተያይዘው ወደ ጀልባዋ ወረዱ። የባህሩን ዳርቻ ያለበሰው አሸዋ ባዶግሮቻቸውን ይፈተፍታቸዋል። ሰሁ ለት እየተጋገዙ ጀልባዋን በአሸዋው ላይ እየገፉ አንሸራ ተቱና ወደውሃው አስገቧት።

«መልካም ዕድል አባባ!» አለ ልጁ::

«መልካም ዕድል ማኖሊን!» አሉ ሽማግሌው:: ወዲያው መቅዘፊያዎቻቸውን አስተካከሉና በዝግታ እየ ቀዘፉ ከወደቡ ወጡ:: ጨለማው ገና ሙሉ በሙሉ አልገለጠም:: ሆኖም ሌሎች ጀልባዎችም መሰማራት ጀምረዋል:: ጨረቃዋ ከተራሮች ጀርባ በመሰወሯ ሌሎቹ ጀልባዎች ባይታዩዋቸውም መቅዘፊያዎቻቸው ውሀውን እየቀረደዱ ወደ ውስጥ ሲጠልቁና በኃይል ሲገፉት የሚፈጠረው መንቦራጨቅ ይሰማቸዋል::

አልፎ አልፎ የአንዳንድ ሰዎች ንግግር ጨለማ ውን እየሰረሰረ ጆሮዋቸው ላይ ያስተጋባል:: አብዛኞቹ ግን የሚቀዝፉት በፀጥታ ነው::

ከወደቡ ከወጡ በኋላ ሁሉም ወደተለያዩ አቅጣ ጫዎች ተበታተኑ:: እያንዳንዱ ዓሣ አጥማጅ ይቀና ኛል ብሎ ወደሚያምንበት አካባቢ አመራ:: ሽማግሌው በጣም ርቀው ለመጓዝ ቆርጠዋል:: የመሬትን ጠረን ከኋላቸው ትተው ንፁህ ወደሆነው የውቅያኖሱ የማ ለዳ አየር ቀዘፉ::

ጨለማው እየገፈፈ ሄደ::በራሪ ዓሣዎች ከውሃው እየወጡ በአየሩ ላይ ሲምዘገዘጉ ግትር ያሉት ደረቅ ክንፎቻቸው አየሩን ሲሰነጥቁት የሚፈጠረው ድምፅ በውሀው መንቦራጨቅ ጣልቃ እየገባ ይሰማል:: ሽማግ ሌው እነዚህን ዓሣዎች በጣም ይወዷቸዋል::በባህር ላይ ብቸኛ በሚሆኑ ጊዜ በዙሪያቸው እየተዛለሉ ስለ ሚያጫውቷቸው ሲወዷቸው አይጣል ነው::

ሽማግሌው ባህርን የሚመስሉት በሴት ነው:: 'ላማር' ይሉታል:: ሰዎች ሴትን ሲያፈቅሯት የሚጠሩ በት የስፓኝ ቃል ነው:: አንዳንዶቹ፣ በተለይ ወጣት ዓሣ አጥማጆች ግን ባህሩን በወንድ ይመስሉታል:: እንደ ኃይለኛ ተፎካካሪ፣ አንዳንዴም እንደ ጠላት ነው

የሚያዩት:: ለሽማግሌው ግን ምንጊዜም እንስት ነው:: ያሏትን ድንቅ፣ ጣፋጭና አስደሳች ነገሮች ሁሉ ያላን ዳች ስስት እንደምትለግስ ወይም ያለ ርህራሄ እንደም ትነፍግ ሴት ይቆጥሩታል - ባህሩን:: ባህር አንዳንዴ አስከፊና የጭካኔ ድርጊት ብትፈፅምም ከአቅም በላይ እየሆነባት እንጂ ለተንኰል አይደለም የሚል ስሜት አላቸው::

ቀጥ ብለው ይቀዝፋሉ:: ውቅያኖሱ ፀጥ በማለቱ ብዙም ትግልና ድካም የሚጠይቅ አልነበረም:: የማለ ዳው ብርሃን ዙሪያ ገባውን እያበራው ሲሄድ በዚያ ሰዓት እደርስበታለሁ ብለው ከገመቱት በላይ ርቀው መጓዛቸውን ተገነዘቡ::

ሙሉ በሙሉ ብርሃን ከመስፈኑ በፊት ቀዘፋቸ ውን አቁመው የዓሣ ማጥመጃ ገመዶቻቸውን ወደ ውሃው ጣሏቸው:: ጀልባዋ በውሃው እንቅስቃሴ እየተ ገፋች በዝግታ ትንሣፈፋለች:: አንዱን ገመድ አርባ ፋቶም* ያህል ወደ ውሃው ውስጥ ለቀቁት:: ሁለተኛ ውን ሰባአምስት ፋቶም፣ ሦስተኛውን ደግሞ አንድ መቶና አንድ መቶ ሃያ አምስት ፋቶም ጥልቀት ድረስ ለቀቋቸው:: ለዓሣ መደለያ የሚያገለግሉት ሠርዲኖች በየመንጠቆዎቹ ቆልማማና ቀጥ ያለ አካል ላይ በደ ንብ ተሰግስገዋል:: መንጠቆዎቹ በያንዳንዱ ሠርዲን ዓይኖች ውስጥ እንዲያልፉ በመደረጋቸው ለየትኛውም ትልቅ ዓሣ ቢሆን ከሰርዲኖቹ ቀድሞ የመንጠቆዎቹ የማይጣፍጥ ብረታማ ጠረን ይሸተዋል ማለት ዘበት ነው:: ቅንጥብጣቢ ሥጋዎቹ ትንሽ የቆዩ በመሆናቸው

---

* ፋቶም፣ የውሃ ጥልቀት መለኪያ ነው:: አንድ ፋቶም ምን ዛሬው ስድስት ጫማ ወይም 1.8 ሜትር ይሆናል::

መስጠጥ የጀመረ ሽታቸውን ለመሸፈን ሲባል ከሰርዱ-
ኖቹ ጋር እየተሰባሰቡ ተሰግስገዋል።

እያንዳንዱ ገመድ የመፃፊያ እርሳስ ያህል ውፍ
ረት አለው። አልፎ አልፎ ኃይለኛ ዓሣ በሚያዝበት
ጊዜ መንጠቆውን አውልቆ ለማምለጥ ሲወራጭ ጀልባ
ዋን እንዳይገለብጣት ለመከላከል ሲባል የገመዶቹ
ቁመት ረጅም እንዲሆን ተደርጓል። ሌሎችም ለመጠባ
በቂያ የሚሆኑ ገመዶች እዚያው ጀልባዋ ላይ አሉ።
አንድ ዓሣ እስከ ሦስት መቶ ፋቶም ድረስ እየተ
ጉተተ ይዞት ሊወርድ የሚችለው ገመድ ተዘጋጅቷል።

ሀሣዩዋ በዝግታ ከባህሩ በስተጀርባ በኩል አስ
ገገች። በተንጣለለው ባህር ላይ የተበተኑት ሌሎች ጀል
ባዎች ይታዩዋቸው ጀመር። አብዛኞቹ ከዳርቻው
ብዙም አልራቁም። ሽማግሌው በጀልባዋ ጎኖች በኩል
ቁልቁል የወረዱትን ገመዶች አጉንብሰው ተመለከቱና
እያንዳንዱ ገመድ በሚፈለገው ጥልቀት ላይ ተጠብቆ
እንዲቆይ ለማድረግ ሲሉ በዝግታ መቅዘፍ ጀመሩ።
እየደመቀ የሄደው የሀሐይዋ ብርሃን በሀጥታ በተለ
ሸለሸው ውሃ ላይ ነፀብራቁን ያጣቅሣል። ሽማግሌው
ዓይኖቻቸው በነፀብራቁ እንዳይጎዱ በማለት ወደ
ውሃው በርቀት አሻግረው ከመመልከት ታቅበው መቅዘ
ፋቸውን ቀጠሉ። እንደገና ጉንበስ ብለው ወደ ውሃው
ውስጥ ተመለከቱ። ገመዶቻቸው ቀጥ ብለው ጨለማ
ወደዋጠው የባህሩ ማህፀን ሠርገዋል። ማንም እንዲያ
ተሣክቶለት አያውቅም። እንደ ዘንግ ተቀስተው ወርደ
ውላቸዋል። ዓይን ቢጎጉጥ እንኳን በማይታይበት
በዚያ ፀሊም የውሃ ዓለም ውስጥ ከየትም ሲገሰግስ
መጥቶ የሚመሰግባቸውን ዓሣ በትዕግስት የሚጠባበቁ
መንጠቆዎቻቸው በሠርዲንና በሥጋ ቅንጥብጣቢዎች
ከብደው በተለያዩ ጥልቀቶች ላይ ተንጠልጥለዋል።
አንዳንድ ዓሣ አጥማጆች ገመዶቻቸውን ወደ ውሃው

ውስጥ ሲለቁ እምብዛም ስለማይጠነቀቁ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ገመዶቹ ወደላይ ይንሣፈፋሉ።

እኔ ግን ገመዶቹን የጣልኳቸው በጥንቃቄ ነው እሱ ሽማግሌው በሀሳባቸው። እኔን የሚጐድለኝ ዕድል ብቻ ነው። አሁንማ እንደያውን የተሟጠጠ ይመስለኛል። ግን ማን ያውቃል? ምናልባት ዛሬ ይሣካልኝ ይሆናል። እያንዳንዱ ቀን አዲስ ቀን ነው። በሆነም ዕድለኛነትን የመሰለ ነገር የለም። ለማንኛውም በኔ በኩል ሥራዬን በትክክል ለማከናወን መታከት የለብኝም። ከዚያ በኋላ ዕድል ከች ብትልም እንኳን ዝግጁ ነኝ ማለት ነው።

ፀሐይዋ ከወጣች ሁለት ሰዓት ያህል አልፏል። በሰማዩ ላይ እየመጠቀች በመሄዷ ሽማግሌው ዓይናቻቸውን ወደ ምሥራቅ ቢወረውሩም ምንም ችግር አይገጥማቸውም።

አሁን በአቅራቢያቸው የሚታዩት ሦስት ጀልባዎች ብቻ ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ ወደ ባህሩ ዳርቻ ጠጋ በማለታቸውና ሽማግሌው በጣም በመራቃቸው የሚታዩት ወደታች ዝቅ ብለው በከፊል ነው።

ዕድሜዬን በሙሉ ዓይኖቼ የማለዳ ፀሐይ መቋቋም እንደተሣናቸው ነው የኖርኩት አሉ በሀሳባቸው። ያም ሆኖ ግን እስተዛሬ አሣፍረውኝ አያውቁም። ማታ ማታ እንኳን አይተው ሲለዩ ከጉረምሣ ዓይኖች ያስንቃሉ። ዳፍንት የሚባል ነገር አያውቃቸውም። እንዲያውም በምሽት ነው የሚበረቱት።ሲነጋ ግን ተመልሰው ያው ናቸው። ይታመማሉ። ያሰቃዩኛል።

ይሄን እያውጠነጠኑ አሻግረው ሲማትሩ ከፊት ለፊታቸው አንድ አሞራ ተመለከቱ። ክንፎቹን ወደ ኋላው አጠፍ አድርጎ እንደ ፍላፃ ወደ ባህሩ ተሽቆ ነጠረ። ብዙም አልቆየ፤ ፍጥነቱን እንደጠበቀ ወደላይ

ተቀልብሶ ሽቅብ በመሣጠቅ ያንን ክብ መስመሩን እያደራ በአየሩ ላይ መንሣፈፍ ቀጠለ::

«እጅሬ አንድ ነገር አግኝቷል ማለት ነው» አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን ጉላ አድርገው:: «እየቆኝ ብቻ አይደለም::»

አሞራው ወደሚያንገበብበት አካባቢ በዝግታ መቅዘፍ ጀመሩ:: ውሃው ውስጥ የጣሏቸውን ገመዶች ወደላይ ሣብ፣ ወደታች ለቀቅ እያደረጉ አወራረዳቸው እንዳይናጋ ያስተካክላሉ::

አሞራው ወደ ላይ እየመጠቀ፣ ክፍታውን እየጨመረ ዑደት ማድረጉን ቀጠለ:: የተዘረጉት ክናፎቹ አይላወሱም:: ድንገት የመጀመሪያውን እንቅስቃሴ ደገመው:: አፈፍ አለና ቁልቁል ወደ ባህሩ ተስፈነጠረ:: ወዲያው አንድ በራሪ ዓሣ ከውሃው እመር ብሎ በመውጣት ላይ ላዩን በጭንቀት መዋኘት ጀመረ::

«ዶልፊን!» አሉ ሽማግሌው በጩኸት:: «ትልቅ ዶልፊን!» መቅዘፊያዎቻቸውን ለቀቁና ከጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ አንድ አነስተኛ ጥቅል ገመድ አነሡ:: ጫፉ ላይ አነስተኛ መንጠቆ ተንጠልጥሏል:: ከሠርዲኖቹ አንዱን ብድግ አድርገው መንጠቆው ላይ ሻጡት:: ዝግጅቱን ሲጨርሱ ገመዱን ወደ ውሃው ለቀቁት:: መንጠቆው እስከሚፈልጉት ርቀት ድረስ መውረዱን ሲያረጋግጡ ጀልባዋ ጉን ላይ በሚገኝ ዘለበት ላይ ገመዱን ሽብ አደረጉት:: ቀጥለው ሌላ ገመድ አነሡና መንጠቆው ላይ ሠርዲኖች ከሰገሰጉበት በኋላ እንደተጠቀለለ መልሰው ጀልባዋ ወለል ላይ አስቀመጡና ወደ መቅዘፋቸው ተመለሱ:: እየቀዘፉ ደግሞ ወደ ባሕሩ ዝቅ ብሎ የሚንሣፈፈውን አሞራ ቷኪ... [illegible]

በመሀሉ አሞራው ክንፉን ወደ ኋላው ሸምጥጥ አደረገና ቁልቁል ተምዘገዘገ:: መሀል ላይ ሲደርስ ክን ፎቹን መልሶ ዘረጋና በኃይል እያራገበ በፍጥነት የሚ ዋኘውን በራሪ ዓሣ መከተል ጀመረ:: ከበራሪው ዓሣ በስተጀርባ በኩል ያለው የባህሩ ውሀ በመጠኑ ወደላይ አበጥ ማለቱን ሽማግሌው አስተዋለ:: ትንሹን ዓሣ የሚያሣድደው ከላይ አሞራው ብቻ ሳይሆን ከሥር ዶልፊን መኖሩንም አረጋገጠ::አሣ! እዚህ አካባቢ የዶ ልፊን መንጋ አለ ማለት ነው አለ በሀሳቡ:: በዚህ ዓይነት ትንሹ ዓሣ ለማምለጥ የሚኖረው ዕድል የመ ነመነ ነው:: አሞራውም ቢሆን እንዲያው ድክም ቢለው እንጂ አይሣካለትም:: በራሪ አሣዎችን በመጠን ብቻ ሣይሆን በፍጥነትም አይስተካከላቸውም::

በራሪው ዓሣ አሁንም ከውሀው ብቅ እያለ ተመ ልሶ ጥልቅ ሲል አሞራው ደግሞ ልቡ እስኪፈርስ ክን ፎቹን እያራገበ ያለምንም ውጤት በከንቱ ሲከንፍ ሽማግሌው በጥሞና ይመለከታሉ:: አሁንስ ዶልፊኖቹ በጣም እየራቁ ሄዱ አሉ በሀሳባቸው:: ፍጥነትም ጨምረዋል:: ግን ምን ይታወቃል አንድ የባዘነ ዓሣ ያጋጥመኝ ይሆናል::

በርቀት በሚታየው መሬት ላይ ሲያንገዋብቡ የነበ ሩት ደመናዎች እንደ ተራራ እየተቆለሉ፣ እየገዘፉ መሄድ ጀመሩ:: የባህሩ ዳርቻም ቅርፁ እየጠፋ አንድ ረጅም አረንጓዴ መስመር ብቻ ሆነ:: ከበስተጀርባው ጭጋግ እንደነጠላ የተከናነቡ ሰማያዊ ተራሮች ይታ ያሉ:: ሽማግሌው ቁልቁል ሲያስተውሉ ፀሐይዋ በጨ ለማው ውሃ ውስጥ የፈጠረችውን ልዩ ዓይነት ብርሃን ተመለከቱ:: ለዓሣ ምግብ በመሆን የሚያገለግሉ ዕፅዋ ትም በብዛት ይታያሉ:: ገመዶቻቸው ቀጥ ብለው መዘለቃቸውንም እግረመንገዳቸውን መቃኘታቸው አል ቀረም:: የዕፅዋቱን መብዛት ሲያዩ ደስታ ተሰማቸው::

በአካባቢው በርካታ ዓሦች ለመኖራቸው ምልክት ነው። ፀሐይዋ በእናት ትይዩ ልትሆን ምንም ያህል አልቀ ራት። ባሻገር መሬቱ ላይ አርብበው የሚታዩት ደመና ዎች ቅርፅና የፀሐይዋ ብርሃን አየሩ ሰላማዊ ሆኖ እን ደሚውል የሚጠቁሙ ዓይነት ናቸው። አሞራው ግን ድራሹ ጠፍቷል። በየትኛውም አቅጣጫ አይታይም። ባህሩ ላይ ከሚንሣፈፈው የሣር ጋስ አረም በስተቀር የሚታይ ነገር የለም።

ጥቂት ቆይተው ሽማግሌው ቀና ሲሉ አሞራው ተመልሷል። እንደገና ክብ መስመሩን ተከትሎ ይን ሣፈፋል።

«አሁን ዓሣ አገኘ» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድር ገው።ግን አንድም በራሪ ዓሣ ባህሩን በርቅሶ ወደ ላይ ሲፈናጠር አልታየም። በአካባቢው የተሠራጩ ሚጢጢ ዓሦችም አይታዩም።ብዙም ሳይቆይ አንድ ትንሽ ቶና* ከውሃው ወጥቶ ወደላይ ከተምዘገዘገ በኋላ ተመልሶ ውሃው ውስጥ ተሰወረ። የቶናው ገላ ብርማ ቀለም ከፀሐይዋ ብርሃን ጋር ይጣቀሳል . . . ያንፀባርቃል። ሰጠቁና ሌሎች በርከት ያሉ ቶናዎች ብቅ ጥልቅ ማለት ጀመሩ። ሁሉም ወደ አየር ከዘለሉ በኋላ ተመ ልሰው ውሃውን ቀርድደው ይሰጥማሉ። እንዲህ አድር ገው ውሃውን ማመሣቸውና ወደ ሰማይ እመር ማለታቸው በአካባቢው ያሉትን ሚጢጢ ዓሣዎች ከበው ለማሣደድ ነው።

ፍጥነታቸውን ካልጨመሩ በስተቀር አያመልጡ ኝም። እደርስባቸዋለሁ፣ አሉ ሽማግሌው በሀሳባቸው። እያሰቡ ደግሞ ከፊት ለፊታቸው የሚካሄደውን ትር

---

* ቶና፦ በባህር የሚገኝ ያዓሣ ዝርያ ነው።

ዓት በጥንቃቄ ያስተውላሉ። ቶናዎቹ በዝላያቸው ትር ምስ ባህሩን አረሩ አስደፍቀውታል። አሞራው ደግሞ በቶናዎቹ ቱማታ በርግገው ወደ ላይ ብቅ የሚሉትን ሚጢጢ ዓሣዎች ለመጥለፍ ደጋግሞ ይሞክራል። አሁንም አሁንም ቁልቁል ይወረወርና ውሃውን ጨልፎ ወደላይ ይመልሳል።

«አሞራው ትልቅ ረዳት ነው...ለሱ ሽማግሌው። ልክ የዚያን ሰዓት በጀልባዋ ጭራ በኩል ወደ ውሃው ውስጥ የተለቀቀው ገመድ በኃይል ተስቦ ሲወጠር እግ ራቸው ስር ተሰማቸው። ገመዱ እግራቸው ላይ አንድ ዙር ጠምጠም ተደርጎ ነበር። ቀልጠፍ ብለው መቅ ዘፊያዎቹን ጣሉና በእግራቸው ላይ ተጠምጥሞ ያለ ፊውን ገመድ አፈፍ አድርገው ወደ ላይ መጎተት ጀመሩ።የተያዘው አነስተኛ ቶና ከመንጠቆው ለመላቀቅ ሲፍጨረጨር ወደ ውሃው ይስባቸዋል። እርሳቸው ግን ገመዱን አጥብቀው ወደላይ መጎተታቸውን ቀጠሉ። ኃይል እየጨመሩ ገመዱን ወደጀልባቸው ባስ ገቡት ቁጥር የዓሣው መንቀጥቀጥና መርበትበት እየ ጨመረ ከመሄዱ ሌላ ሰማያዊ ቀለም ያለው ጀርባ ውና ወርቅማ ጎኖቹ ይታዩቸው ጀመር። ትግሉ ለጥቂት ጊዜ ከተካሄደ በኋላ በሽማግሌው አሸናፊነት አበቃ። ትንሹን ቶና ከውሃው መንጭቀው አውጥተው ጀልባው ወለል ላይ ዘረሩት።

የጥይት ቅርፅ ያለው ዓሣ በዚያ ጠራራ ፀሐይ ትልልቅ ዓይኖቹን አፍጥጦ በጉጉት እንደተጋደመ ጅራ ቱን ከጀልባዋ ጎኖች ጋር በእልህ ማላተሙን ተያያ

---

የጀልባ ጭራ፦ ይህ ቃል በዚህ ዕሑፍ ውስጥ "stern" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይተካል። የጀልባን ሆነ የመርከብ ኋለኛ ክፍል የሚያመለክት ነው።

ዘው። ሽማግሌው ቀመጣቸውን አነሱና ጭንቅላቱን አንድ ጊዜ መቱት። ፀጥ አለ። ሥጋው ግን ለጥቂት ጊዜ እየተንቀጠቀጠ ቆየ።

«አልባኩሬ» አሉ ሽማግሌው በሹክሹክታ።«ሥጋው በደንብ ከተበለተ ከሠርዲኖቹ ጋር ጥሩ መደለያ ይወጣዋል።ክብደቱም ደህና ነው። መቼም ከአምስት ኪሎ በታች አይሆንም።»

ለብቻቸው የማውራት ልምድ የተጠናወታቸው መቼ እንደሆነ በጭራሽ ትዝ አይላቸውም። በርግጥ ድሮ ብቻቸውን በሚሆኑ ጊዜ ይዘፍኑ ነበር። በተለይ በምሽት ጀልባቸው ውስጥ አድፍጠው ብቸኝነቱ ሲጠናባቸው የማያውቁትን ዜማ ማንጐራጐር ይጀምራሉ። ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለራሳቸው ማውራት የጀመሩት ምናልባት ልጁ ከተለያቸው በኋላ ሊሆን ይችላል። ብቻ በውል የሚያስታውሱት ነገር የለም።ልጁ አብሯቸው በነበረበትም ጊዜ ውይይታቸው የተቆጠበ ነበር። አስፈላጊ ሆኖ እስካላገኙት ድረስ አይነጋገሩም። ሁለቱም ወደ ዝምታ ያፈገፍጋሉ።በሌሊው የሚያወሩት ማታ ማታ ወይም ማዕበል ሲይዛቸው ብቻ ነበር። በባህር ላይ ሣሉ ያለምክንያት መለፍለፍ በአካባቢው ልማድ እንደ ነውር ይቆጠራል። ሽማግሌው ደግሞ በዚህ አጥብቀው ስለሚያምኑ በባህር ላይ በሚቆዩ ጊዜ ዝምታ ያበዛሉ። አሁን ግን ያገር ልማድ በማፍረሳቸው የሚያወግዛቸውም ሆነ የሚታዘባቸው ሰው በአጠገባቸው ስለሌለ ሀሳባቸውን የሚተነፍሱት ድምፃቸውን ጉላ እያደረጉ ነው።

---

አልባኩሬ፣ዓሣው በስፓኝ ቋንቋ የሚጠራበት ስም ነው።

ስመሆኑ እንዲህ ብቻየን ስለፈልና ሰዎች በሰ
ሙኝ ምን ይሉ ይሆን? መቼም ያበደኩ ነው የሚመ
ስላቸው፡፡ አሉ እንደገና ድምፃቸውን ከፍ አድርገው፡፡
"ግን ምንግዶ! ዕብድ እንዳልሆንኩ አውቀዋለሁ፡፡ ሀብ
ታሞቹማ በየጀልባቸው ውስጥ ቁጭ ብለው የሚያጫ
ውቷቸውን ሬዲዮኖች ይዘው አይደል የሚጠብቱ-
ያውም ስለቢዝቦል ጨዋታ ሳይቀር የሚያወሯት
ውን፡፡ አሁን ግን ስለቢዝቦል ጨዋታ የሚያስቡበት
ጊዜ አይደለም አሉ በሀሳባቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ማሰብ
የሚገባኝ ስለአንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ስለተፈጠርኩለት
ነገር ብቻ፡፡ እዚያ ማዶ ከሚበርቁት ዓሣዎች አካባቢ
አንድ ትልቅ ግዙፍ ዓሣ ማይኖር አይቀርም አሉ፤
አያይዘውም ይሄ የያዝኩት ከጓደኞቹ ተነጥሎ የሚባ
ዝን መሆን አለበት፡፡

ባሸገር የሚታየው አረንጓዴ ቀለም የመሬቱ
ጠርዝ ቀስ በቀስ ከዓይን እየጠፋ ሄደ፡፡ ሰማያዊ ቀለም
ያላቸው ኮረብቶች ግን ጫፋቸው ገና እየታየ ነው፡፡
ከአናታቸው ያረበበት ነጭ ደመናዎች የበረዶ ቆብ
ጭነው የተከሉ አስመስሏቸዋል፡፡ ፀሐይዋ እየገረረች
በመሄዷ ሙቀቱ የሸማግሌውን ጀርባ ይጠብሳቸው
ጀመር፡፡ በዚያ ላይ ጀልባቸውን ይቀዝፋሉ፡፡ ላባቸው
አከርካሪያቸውን ተከትሎ ቁልቁል ሲንቆረቆር ይሰማ
ቸዋል፡፡

መቅዘፋን አቁሜ ጀልባዋ የውሀውን እንቅስቃሴ
ተከትላ እንድትንሣፈፍ ማድረግና እኔም ትንሽ ማሸ
ለብ እችል ነበር አሉ በሀሳባቸው፡፡ ባይሆን ከእንቅልፌ
እንዲቀሰቅሰኝ ገመዱን ሸምቅቆ ሰርቼለት አውራጣቴ
ላይ አስረዋለሁ፡፡ ግን ምን ያደርጋል ዓሣ የሚሉ ከያ
ዝኩ ሰማኒያ አምስተኛ ቀኔ ነውና መዘናጋት አያስፈ
ልግም፡፡ ዕለቱን በደንብ ልጠቀምበት ይገባል፡፡ እንደ
ማንም ብዬ ደህና ዓሣ መያዝ አለብኝ አሉ በሀሳባ
ቸው፡፡

እያሰቡ ደግሞ ዓይኖቻቸውን ውሀው ውስጥ ወደ ለቀቋቸው ገመዶች ሲያንጣጥሩ አንደኛው ገመድ ላይ አለፍ አለፍ እያሉ አግድም ከታሰሩት ቀጫጭን ገመዶች አንደኛው ወደ ውስጥ ሲጠልቅ ተመለከቱት።

«እሽ! » አሉ። «እም!» ፈጠን ብለው መቅዘፊያዎቻቸውን በመልቀቅ ገመዱን ለቀም አድርገው በቀኝ እጃቸው አውራጣትና አመልካችጣት መሀል ፈጥርቀው ያዙት። ግን እንደገመቱት ገመዱ አልተወጠረም ወይም ወደታች አልተሳበም። እያያዛቸውን ላላ አደረጉት። ጥቂት ቆይቶ ገመዱ ወደ ታች ሲጐተት ተሰማቸው። እንደገና ጐተተ። ነገሩ የሙከራ፣ የፍተሻ ዓይነት እንጂ የመፈታተንና ኃይል የተሞላበት አይደለም። ምን እንደሆን ለማወቅ አልተሣናቸውም። ማርሊን ሆዬ አንድ መቶ ፋቶም ጥልቀት ውስጥ ሆኖ መንጠቆው ላይ የተሰገሰጉትን ሠርዲኖች እየኰመኰመ መሆኑን ወዲያው ተረዱ።

ገመዱን ወደ ግራ እጃቸው በጥንቃቄ አዛወሩና ላላ አድርገው ያዙት። አሁን ገመዱ በጣቶቻቸው መሀል እየተንሸራተተ ነው። ዓሣው የተያዘ መሆኑን ሳይረዳ እስካሻው ጥልቀት ድረስ እንዲስበው ለማድረግ ያመቻቸዋል።

በል እንጂ ጌታው ዓሣ የቀረቡልህን ሠርዲኖች ችላ አትበላቸው።አይዞህ ከስክስ።ኧረ እባክህ ሞክር። ነውር አይደለም እንዴ! ላንተ ነው'ኮ የቀረበት። ደሞ እንዴት ትኩስ መሰሉህ? ሙቼም ቀኑን ሙሉ እዚያ ቅዝቃዜና ዳፍንት ውስጥ ሣይሞረሙርህ አይቀርም። እና እኮ በል ግብግቡን ሣትንቅ ትንሽ ቀማምስ፣ አሉ ሽማግሌው በሃሳባቸው።

የያዙት ገመድ በመጠኑ ሣብ ሲደረግ ተሰማ ቸው:: ወዲያው አከታትሎ አንድ ጊዜ በኃይል ተጐ ተተ:: ከሰርዲኖቹ አንደኛው ከመንጠቆው ላይ በቀላሉ አልላቀቅ ስላለው በጉልበት ሲመነጭቀው መሆን አለ በት:: ከዚህ በኋላ ግን ሁሉም ነገር ፀጥ አለ::

«አይዞህ» አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን ከፍ አድ ርገው:: «ብልኅ እንደገና ተመለስና መዓዛቸውን አሽት ተው:: እንዲህ እንዳይመስሉህ- ድንቅ ናቸው:: ሠርዲ ኖቹን አጣጥመህ ስታበቃ የቶኖው ከትፎ ደግሞ አለ ልህ:: ቅዝቅዝ ብሎ ሲጣፍጥ አይጣል ነው:: ጣት ያስ ቆረጥማል:: እኮበል:: አይዞህ አትፍራ:: ወገኛ፣ ደሞ የምን መሽኮርምም ነው? ኧረ ሰው እንዳይሰማህ:: ለምኑ ብለህ ነው?የሚያይህ የለ! ይልቅ ሞኝ አትሁን:: በግላጭ ሲገኝ እንከት አድርገህ መብላት ነው::»

ገመዱን በአውራ ጣታቸውና በአመልካች ጣታ ቸው መሀል እንቀው እንደያዙ እንቅስቃሴውን ያዳም ጣሉ::አልፎ አልፎ ደግሞ በጀልባዋ አፍንጫና ጭራ፣ እንዲሁም በጐንና በጐኗ በኩል ወደውሃው የተለቀቁ ትን ገመዶች ይማትራሉ - ምናልባት ዓሣው የጀመ ረውን ትቶ ወደነሱ ካመራ በሚል ጥርጣሬ:: ትንሽ እንደቆዩ የመጀመሪያውን የመሰለ ለዘብ ያለ ጐተታ ተሰማቸው::

«አሁን ወደአፉ ሊያስገባው ነው» አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን አጉልተው::

«አምላኬ እባክህ መንጠቆውን ደህና አድርጐ እን ዲጉርሰው እርዳው::»

ዓሣው ግን የተመኙትን አልፈፀመም:: ከናካቴው ከአካባቢው ሄደ:: የሚሰማ ነገር ጠፋ:: ፀጥታ ብቻ::

«አይደረግማ . . . አይደረግም፡፡ ጨኪና ትቶ አይሄድም» አለ ሽማግሌው፡፡ «ክርስቶስ ምስክሬ ነው፤ ታላበደ በቀር ይህን መሣይ ማሰድ ጥሎ አይሄድም፡፡ እንዲያው ትንሽ ዞር ዞር ብሎ ሊመለስ ይሆናል፡፡ ማን ያውቃል፧ምናልባት ቴህ ቀደም ተደዞ ያመለጠም ሊሆን ይችላል፡፡ እና ያቺ ትዝ አያለችው ይሆናል ዳር ዳር የሚለው፡፡»

ወዲያው እንደበሬቱ ለዘብ ያለ ስበት ተሰማቻቸው፡፡ የሽማግሌው ስጋት በደስታ ተተካ፡፡

«መች አጣሁት፤ አውቄዋለሁ፡፡ ትንሽ ተዘዋዙር ሊመለስ ብሎ ነው፡፡አሁን በደንብ ይጎርሆዋል» አለ፡፡

ገመዱን በመጠኑ ጉተት ሲያደርገው ተሰማቸው፡፡ ልባቸው ጮቤ መምታት ከጀለው፡፡ በማከታተልም እጅግ ከፍተኛ ኃይልና ከቶም የማይታመን ዓይነት ክብደት ወደታች መዘናቸው፡፡ የዓሣው ክብደት ነው፡፡ እንደ ተመኙት ሆነ ማለት ነው፡፡ መንጠቆውን ሙሉ በሙሉ ጉረሰው፡፡ ሽማግሌው ከመቅዐበት ገመዱን ወደውሃው ውስጥ መልቀቅ ጀመሩ፡፡ ቁልቁል. . . ቁልቁል. . . አሁንም ቁልቁል፡፡ ገመዱ እንዳይወጠር ከሁለቱ የመጠባበቂያ ጥቅሎች አንደኛውን እየተረተሩ ቁልቁል ለቀቁት፡፡ ገመዱ በጣቶቻቸው መሃል እየተጥመለመለና ቆዳቸውን እየሞገዞቀ ሲንሸራተት ከውሃው በታች ያለው ክብደት ቁልቁል ሲመዝናቸው ይሰማቸዋል፡፡

«ምን ዓይነት ዓሣ ቢሆን ነው ጃል!» አለ፡፡ «ይህኔ መንጠቆው አፉ ውስጥ የተሰነቀረው አግድም ይሆናል፡፡»

አሁን እንግዲህ ወዲያና ወዲህ እሂሂራለሁ ሲል አንጀያውን በደንብ ይቀረቅርበትና ያርፈዋል፡፡ አለ·

በሀሳባቸው። ያሀኛውን ሀሳባቸውን ድምፃቸውን አጉልተው በመናገር ፋንታ ለራሳቸው ብቻ በሆዳቸው የተነፈሱት ያለምክንያት አልነበረም። አንድን ጥሩ ነገር ያሀናል በማለት አስቀድሞ ከተናገሩት ሣይሳካ ይቀራል የሚል ዕምነት ነበራቸው። ወጥመዳቸው ውስጥ የገባው ዓሣ የቱን ያህል ግዙፍና ትልቅ እንደሆነ ገምተዋል።የቶኖ ሥጋ የተደረደረበት መንጠቆ አፉ ውስጥ አግድም ተቀርቅሮበት ሲወራጭ ወለል ብሎ በዓይን ህሊናቸው ታያቸው። ግን የተማከሩ ይመስል ልክ በዚያው ቅፅበት ዓሣው ማናቸውን እንቅስቃሴውን እቆመና ፀጥ- ፀጥ አለ። ክብደቱ ግን አሁንም ይሰማቸዋል። በእጃቸው ከያዙት ገመድ ጫፍ ቁልቁል ይመዝናቸዋል። እንዲያውም ከበፊቱ ትንሽ የጨመረ መስላቸው። ቀልጠፍ ብለው ገመዱን ለቀቅ በማድረግ አያያዛቸውን አጠበቁት። የዓሣው ክብደት እየጨመረ ከመሄድ በላይ ቁልቁል እየጠለቀ፣ እየራቀ ሲሄድም ይሰማቸዋል።

ዓሣው ገመዱን እየሣበ እመቀመቅት በወረደ መጠን ገመዱ አልቆ እንዳይወጠር ባንድ ፊት በቀኝ እጃቸው የያዙትን ገመድ ለቀቅ ለቀቅ እያደረጉ በሌላ በኩል ደግሞ የኋሊት ለጠጥ በማለት የሁለቱን የመጠባበቂያ ጥቅል ገመዶች ጫፍና ጫፍ በግራ እጃቸው ስበው በሌሎች ሁለት ጥቅል የመጠባበቂያ ገመዶች ሽምቅቆ ውስጥ አስገብተው ቋጠሩት። ይህም ሆኖ በቀኝ እጃቸው ከያዙት ዓሣው የተጠመደበት ገመድ ሌላ እያንዳንዳቸው አርባ ፋቶም ጥልቀት ድረስ ሊወርዱ የሚችሉ ሦስት ጥቅል ተጨማሪ የመጠባበቂያ ገመዶች ነበሯቸው።

«በል'ኮ ደህና አድርገህ አስገባው» አሉ።

በል አትሰስትለት።ሁሉም ላንተው የተዘጋጀ ነው። አየህ የመንጠቆው ጫፍ በቀጥታ ልብህ ላይ ይሻግና

በቀላሉ ይገላግልሃል አሉ በሀሳባቸው። ደግሞ ቀስ እያ ልክ ወደላይ ብቅ ብትልልኝ ሀርፑኔን ደህና አርጌ እቀበቅብብሃለሁ። ማዕድ ላይ መቀመጡ ግን ይብቃህ። እሺ።

«አሁን ነው እንግዲህ!» አሉና ሽማግሌው በሁለ ቱ እጆቻቸውን በፍጥነት እያፈራረቁ ገመዱን ባለ ኃይላቸው ወደ ላይ መሳብ ጀመሩ።

ምንም ብቅ ያለ ነገር የለም። ዓሣው ቀስ በቀስ ከጀልባዋ እየራቀ መሄዱን በመጀመሩ ሽማግሌው እንዳ ሰቡት አንዲት ጋት እንኳን ከውሃው ሊያወጡት አል ተሳካላቸውም። ለትልልቅ ዓሣዎች ማጥመጃ እንዲ ሆን ታስቦ የተዘጋጀውን ጠንካራ ገመድ ወጥረው ለመ ያዝ እንዲረዳቸው በማለት ጀርባቸው ላይ አጋደሙት። ዓሣው እየራቀ በሄደ መጠን ገመዱ በጣም ተወጠረ። በተወጠረ ቁጥር ደግሞ በላዩ ላይ እንደጤዛ ጉች ጉች ያሉ የውሃ ጠብታዎች ይፈናጠሩ ጀመር። ጥቂት የመ ንሣጠጥ ድምፅ ተከተለ። ሽማግሌው በደንብ ለመወ ጠር እንዲረዳቸው ወደኋላ ለጠጥ ብለው ገመዱን አጥብቀው ይዘዋል። አንድ አንድ እያለች ጀልባዋ መንቀሣቀስ ጀመረችና ወደሰሜን ምዕራብ ጉዞዋን ተያያዘችው።

ዓሣው ቀጥ ብሎ መዋኙን ቀጠለ። ጀልባዋና ሽማግሌውም በረጋው ውሃ ላይ ተከትለውት ይንሣፈ ፉሉ። ሌሎቹ ገመዶች በዓሣ መደለያዎች ከብደው ውሃው ውስጥ እንደተጣሉ ናቸው። በዝምታ ከመ ጉተት በስተቀር ሊደረግ የሚቻል ነገር አልነበረም።

«ልጁ አብሮኝ ቢኖር እንዴት ጥሩ ነበር» አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።«እንዲህ በዓሣ እየተጉተትኩ ደስፍላጉቱ የትም አልወሰድም ነበር።

ገመዱን በኃይል ወጥሬም እንቅስቃሴውን መግታት ባልተሣነኝ ነበር:: ግን በዚህ ጉልበቱ ባንዳፍታ ነው በጣጥሶ የሚጥለው:: ስለዚህ የሚያስፈልገውን ያህል ገመድ ከመጠባበቂያው ጥቅል እየለቀቅሁለት ይዤው እቆያለሁ እንጂ መላቀቅ መቸም ዘበት ነው:: ለየ ውም ወደ ውስጥ ለመውረድ አለመፈለጉ ራሱ ተመስ ገን ነው::»

እንዲያው ግን ወደፊት በመጓዝ ፋንታ ቁልቁል ወደውሃው ውስጥ መውረድ ቢመርጥ ኖሮ ምናባቴን ነበር የማደርገው? እኔ እንጃ! ደግሞስ ውሃው ውስጥ እንዳለ ቢሞት? ያም ቢሆን በበኩሌ የማውቀው ነገር የለም:: በርግጥ መቼም ዝም ብዬ አላየውም:: ካሉኝ ብዙ አማራጮች መሃል አንዱን መፈፀሜ አይቀርም::

ሽማግሌው አንድጊዜ በጀርባቸው ላይ ተጋድሞ በማለፍ ጋደድ ብሎ ወደውሃው ውስጥ የሚሰወረውን ገመድ፤ ሌላጊዜ ደግሞ ያለፍላጐታቸው ወደ ሰሜን ምዕራብ የምትነጉደውን ጀልባ በየተራ ይመለከታሉ::

ይህ ድርጊት በራሱ ይገድለዋል ሲሉ አሰቡ ሽማ ግሌው::መቼም ይህንን ዝንተ-ዓለም ሲፈፅመው ሊኖር አይችልም:: ዓሣው ግን የዋዛ አይደለም:: ሽማግሌው ይህን ሀሳባቸውን ካብላሉት ከአራት ሰዓት በኋላ ዓሣ ውም ጀልባዋን እየጐተተ ወደታላቁ ባህር እምብርት በጥንካሬ መዋኘቱን እንደቀጠለ ነበር:: ሽማግሌውም ፍንክች አላሉ፤ ገመዱን ጀርባቸው ላይ እንዳጋደሙ በቁርጠኝነት ጀልባዋ ላይ ተገትረዋል::

«የያዝኩት ልክ እኩለ ቀን ላይ ነው» አሉ:: «ግን እስካሁን ድረስ ዓይኑን አላየሁትም::»

ዓሣውን ከመያዛቸው ቀደም ብሎ የሰሌን ባርኔ ጣቸውን ወደታች ሣብ አድርገው ጆሮግንዳቸው ድረስ

አውርደውት ስለነበር ግንባራቸውን እየቢጠጠ ያስቸግ
ራቸው ጀመር:: በዚያ ላይ የውሃ ጥም መጣ:: ገመ
ዱን ላለማንቃንቅ በጣም እየተጠነቀቁ በዝግታ ወለሉ
ላይ ተንበረከኩና የተቻላቸውን ያህል ወደ ጀልባዋ አፍ
ንጫ በመጠጋት የውሃ ጠርሙሳቸውን በአንድ እጃ
ቸው አነሡት:: ቡሹን ከፍተው እንዴ ተጉነጩና እዚ
ያው ደገፍ ብለው ዕረፍት አደረጉ:: እንቅስቃሴ ሳያ
በዙ በዝግታ ሸተት እያሉ ወደጀልባዋ መሀል ተሸጋ
ገሩና በተጋደመው ተራዳ ላይ ተቀመጡ:: እስከ መጨ
ረሻው ሳይበገሩ ለመቋቋም እንጂ በሀሳብ ላለመጠመድ
መታገል ያዙ::

ብዙም ሳይቆዩ ወደኋላ ገልመጥ ብለው ተመ
ለከቱ:: መሬት የሚባል ነገር አይታይም:: መሬት ታየ
አልታየ ምንም ለውጥ አያመጣም አሉ በሀሳባቸው::
ቢመሽም ከሀሻና ከተማ የሚፈካውን የብርሃን ወጋገን
እየተከተልኩ ወደ ወደቡ ማምራት እችላለሁ:: ጊዜ
ውም ገና ነው:: ፀሐይዋም ገና ሁለት ሰዓት ያህል
ይቀራታል:: እስከዚያ እሱም ብቅ ይል ይሆናል::
ከዘገየም ጨረቃዋ ስትወጣ አብሮ ይወጣ ይሆናል::

ግፋ ቢል ደግሞ ነገ ጠዋት ተመልሳ ከምትመ
ጣው ፀሐይ ጋር አብሮ መከሰቱ አይቀርም:: ደግነቱ
እኔም እስካሁን ደህና ነኝ:: ጉልበቴም እንዳለ ነው::
ደህና የሚያወላዳ ይመስለኛል:: እሱ እንጂ በመንጠቆ
ተሰቅ፤ የሚቃትት፤ እኔማ ምን አለብኝ! ግን እንዲ
ያው ለነገሩ ምን ዓይነት ዓሣ ቢሆን ነው እንዲህ
ከነጀልባዬ አንጠልጥሎኝ ሊከንፍ የቻለ? የጉድ ነው::
ወጥቶ አይቼው ብቻ:: ይህኔ አፉን መንጠቆው ላይ
ግጥም አድርጐ ዘግቶ መሆን አለበት:: ግን ባየው
እንዴት ደስ ይለኝ ነበር:: ተፋላሚዬ ምን መሣይ
እንደሆነ ላንዳፍታ እንኳን ባየው ምንኛ ጥሩ ነበር::

ሽማግሌው የከዋክብቱን አቀማመጥና አቅጣጫ በማየት ዓሣው ቀን የያዘውን መስመር አለመለወጡን ተገነዘቡ። ሌሊቱን በሙሉ በዚያው ቀጠለ። ፀሐይዋ ከጠለቀች በኋላ አየሩ በመቀዝቀዙ ቀን ሽማግሌውን ሲያጠምቃቸው የዋለው ላብ ጀርባቸው፣ ክንዶቻቸውና እግሮቻቸው ላይ ተጋገረ። ለዓሣ መደለያነት የሚያውሏቸውን ሠርዲኖችና ቁርጥራጭ ሥጋ የሚያስቀምጡበትን ማጥን የሚሸፍኑበትን ኬሻ ቀኑን ሙሉ አስጥተውት ውለው ደርቆላቸው ስለነበር አንገታቸው ላይ ጠመጠሙና ወደ ኋላ አሣልፈው ጀርባቸው ላይ ጣል አደረጉት። ቀስ ብለውም በትከሻቸው አቋርጦ በተጋደመው ገመድ ሥር ጉዘጉዙት። ገመዱ በአካላቸው ላይ ማስከተል የጀመረው የህመም ስሜት ቀነስ በማለቱ መጠነኛ ምቾት ተሰማቸው።

በዚህ ዓይነት እስከቀጠለ ድረስ እኔም እሱም ምንም የምንደራረገው ነገር እንደማይኖር ግልፅ ነው አሉ ለራሳቸው።

በሌሊቱ ጉዟቸው ወቅት አንድ ጊዜ ከተቀመጡበት ተነስተው በጀልባዋ ጎን በኩል ሽንታቸውን ከሸኑ በኋላ የሚሄዱበትን አቅጣጫ ለመለየት እንዲረዳቸው ከዋክብቱን ቀና ብለው ተመለከቷቸው። ፍጥነታቸው ቀንሶ ጉዟቸው በዝግታ ሆኗል። የሀቫና ከተማ የብርሃን ወጋገን እምብዛም ደምቆ አይታይም።ጥቁሩ ሰማይ ወደምሥራቅ አቅጣጫ እየመሩ መሆኑን ጠቆማቸው። አሃ! የሀቫና ብርሃን እየተሰወረ እኛም ወደ ምሥራቅ በመጓዝ ላይ ነን ማለት ነው አሉ በሀሳባቸው። ሌሎች ሀሳቦች ተከታትለው ተረባረቡባቸው። ስለ ቤዝቦል ጨዋታ፣ ስለ ዓሣ ማስገር ሙያ . . .

ትንሽ ቆይተው ደግሞ «ወይ ነዶ! ልጁ አብሮኝ ቢኖር እንዴት ጥሩ ነበር» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።

«እያገዘኝ ይህንንም ጉድ ያየ ነበር።»

ማንም ሰው ቢሆን በሽምግልና ዕድሜው ብቻውን መሆን የለበትም። ግን ምን ላድርግ? ልጄን ማስቀረት ከአቅሜ በላይ ሆነብኝ። ለማንኛውም በዚህ ትግል እንዳሸንፍ ጉልበቱን በደንብ መጠበቅ አለብኝ። . . . ፍላጐትህ ይነስም ይብዛ ባት ተኛውን ልትበላ እንደሚገባ ማስታወስ አለብህ። እንዳትረሣ፤ አሉ ራሳቸው ለራሳቸው።

ስንት እንደሆን ለይተው በማያውቁት ሰዓት ላይ ሁለት ፖርፖይዞች[1] ጀልባዋን ተጠግተው ሲዋኙ ሰሟቸው። የወንዱንና የሴቷን ትንፋሽ ለይተው ያውቁታል።

«ግሩም ፍጥረታት»አሉ ሽማግሌው። «ሲጫወቱ፣ ሲቃለዱና ሲፋቀሩ ለጉድ'ኮ ነው። እንደ በራሪዎቹ ዓሣዎች እነርሱም ወንድሞቻችን ናቸው።»

በመንጠቆዋቸው ተሰንጉ ስለተያዘው ትልቅ ዓሣ ሀዘን ይሰማቸው ጀመር። ለየት ያለ ግሩም ዓሣ ነው። በዚያ ላይ ዕድሜው ስንት እንደሆን ማንም አያውቅም። ሀሳብ በሀሳብ ሆኑ። እኔ መቼም በዕድሜዬ ሙሉ እንዲህ ያለ ጠንካራና ነገረ- ሥራው ሁሉ ልዩ የሆነ ዓሣ አጋጥሞኝ አያውቅም። ምናልባት ወደላይ ዘሎ ብቅ አለማለቱ የብልህነት ሳይሆን ይቀራል? ግን ዝላይ ቢጀምር ወይም በኃይል ልሽምጥጥ ቢል በቀላሉ ድራሹን ባጠፋው ነበር። ግን ከአሁን ቀደም ምናልባት በሌሎች ዓሣ አጥማጆች መንጠቆ እየተያዘ በማምለጥ ሰፊ ልምድ ያዳበረም ሊሆን ይችላል።

[1] ፖርፖይዝ፡- ከዓሣ ነባሪና ከዶልፊን ጋር ተመሳሳይነት ያለው የዓሣ ዝርያ ነው።

እናም ከኔ ጋር የሚያደርገውን ትግል በዚህ መልክ
ማካሄዱን የመረጠው ከዚሁ ልምዱ በመነሣት ይሆ
ናል፡፡ ግን እስከ መጨረሻው ሊቋቋመው ቆርጦ የተነ
ሣው የዛሬው አጥማጄ አንድ ብቻ መሆኑን አያው
ቅም፡፡ ሰውየው ሽማግሌ መሆኑንማ በጭራሽ አይጠ
ረጥርም፡፡ ግን ትልቅ ዓሣ መሆን አለበት፡፡ በዚህ
ግዙፍነቱ ላይ ሥጋውም ጥሩ ዓይነት ከሆነ በቃ፣
በአንድ ቀን አሻረኝ ማለት ነው፡፡ መንጠቆው ላይ ተደ
ርድሮ የቀረበለትን ምግብ እንደ ወንድ ተጋብሆ፣ ጀልባ
ዋንም የሚጐትታት ልክ እንደ ወንድ ነው፡፡ ሽብርና
ድንጋጤ ብሎ ነገር ሲያልፍም የማይነካው ልቡ ሙሉ
ይመስላል፡፡

አንድ ጊዜ ሁለት ማርሊኖች አግኝተው አንዱን
አጥምደው ሣለ የገጠማቸው ሁሉ ትዝ አላቸው፡፡ ወን
ድና ሴት ነበሩ፡፡ ምግብ ሲያገኙ ሴቷ ቀድማ እንድ
ትበላ ማድረግ የወንዱ የተፈጥሮ ባህርይ በመሆኑ ያን
ለትም ቅድሚያው ይሰጣታል፡፡ ሴቷ ማረሊ በመብቷ
ተጠቅማ ለመመገብ አፏን ስትከፍት የሽማግሌው መን
ጠቆ ይሰነቀርባታል፡፡

በድንጋጤና በብስጭት እየተወራጨች በኃይል
መታገል ትጀምራለች፡፡ ማሸነፍ ግን አልሆነላትም፡፡
የሚበቃትንና የምትችለውን ያህል ስትወራጭና ስት
ንፈራገጥ ከቆየች በኋላ እየደከመች ትሄዳለች፡፡ ሆኖም
በዚያ የፈተናና የዛዕሯ ወቅት ወንዱ ማርሊን ለአን
ዲት ቅፅበት እንኳን ከአጠገቧ አልተለየም፡፡ የተያዘ
ችበትን ገመድ አንዴ በላይ፣ አንዴ በታች እያቋረጠ
በጭንቀት ይዞራታል፡፡ ወደላይ ስትንሣፈፍ እሱም አብ
ሯት ብቅ በማለት ይቁነጠነጣል፡፡ በጣም ቅርቧ ስለ
ነበር በመጠኑም ሆነ በቅርፁ ትልቁን የፈረንጅ
ማጭድ በሚመስለው ጭራው ገመዱን ይቆርጠዋል

በማለት ሽማግሌው ከፉኛ ሰግተው ነበር:: በመጨረሻ በሀርፑን ከወጓትና ቆዳዋ የመስተዋት ጀርባ የሚቀባውን ቀለም እስኪመስል ድረስ በዱላቸው አናቷን በመቀጥቀጥ ከአዝለፈለፏት በኋላ፣ ያኔ ከልጁ ጋር ተጋግዘው ጀልባዋ ላይ እስካጋደሟት ድረስ ወንዱ ማርሊን ከአጠገቧ ልውስ አላለም ነበር:: ወዳጁ ከውሃው ከወጣችም በኋላ ተስፋ አልቆረጠም:: የጀልባዋን ጥግ ይዞ እዚያው ሲልከሰከስ ቆየ:: በኋላ ግን ገመዳቸውን እየሰበሰቡ እቃዎቻቸውን መከቶችም ሲጀምሩ አንድ ጊዜ አመር ብሎ ከውሃው በመውጣት ወደላይ አሻቀበና ወዳጁ ያለችበትን ለአፍታ አየት አድርጎ ተመልሶ ወደ ባህሩ ጠለቀ:: እስከዛሬ ከሽማግሌው አይነ-ህሊና ያልጠፋ በጣም ቆንጆ ማርሊን ነበር::

ብቻ አጠቃላይ ሁኔታው በጣም የሚያሳዝን ነበር አሉ ሽማግሌው በሀሳባቸው:: ልጁ እንኳ የቱን ያህል ነበር ያዘነው? ግን ምን ያደርጋል፣ ጀልባዋ ላይ የተዘረጋችውን ሴት ማርሊን ስለፈፀምነው ሁሉ ይቅርታ ከጠየቅናት በኋላ አጣድፈን በለትናት::

«ልጁ አሁንም አብሮኝ ቢኖር ምንኛ መልካም ነበር!»አሉና ጐላ ባለ ድምፅ የጀልባዋን አፍንጫ ደገፍ ብለው ተቀመጡ:: ወደ መረጠው አቅጣጫ ይዟቸው የሚነጉደው ዓሣ ትንግርታዊ ጥንካሬ ትከሻቸው ላይ በተጋደመው ገመድ ውስጥ ያለማቋረጥ ይሰማቸዋል::

የእሱ ምርጫ ከማናቸውም አደጋና ወጥመድ ርቆ በጨለማው ከርሠ-ማይ በሠላም መኖር ነበር አሉ ሽማግሌው በሀሳባቸው:: የኔ ምርጫ ደግሞ ከሰዎች ሁሉ ርቄ ተጉዤ፣ አደፈጠበት ድረስ ሄጄ እርሱን መያዝ ነበር:: ይኸው አሁን ሁለታችንም ተገናኘን:: ተግናኝቱንም ተጣመርን:: ጵንሆም ከእኩለ ቀን አንስቶ

እንደተቆራኘን አለን። ደግሞ ብቸኞችንን ነን። ሁለታች ንም ረዳት ወይም አጋዥ የለንም።

ምናልባት ዓሣ አጥማጅ መሆን አልነበረብኝ ይሆን? አሉ፣ አሁንም በሀሳባቸው። ግን ያለጥርጥር የተፈጠርኩት ለዚሁ ነው። ጧት ጀምበር እንደሠረቀች ቱናውን መብላት እንዳለብኝ ማስታወስ ይኖርብኛል።

ውድቅት ላይ ከበስተጀርባቸው በኩል ውሃው ውስጥ ከተለቀቁት ገመዶች በአንደኛው መንጠቆ ላይ የተሰገሠጉትን የመደለያ ምግቦች የሆነ ነገር መንትፎ ወሰዳቸው። ገመዱ ላይ አግድም የተቋጠረው ቀጭን እንጨት ተሰበረና ገመዱ በጀልባዋ ጠርዝ እየተንሸራ ተተ ቁልቁል መውረድ ጀመረ። ሽማግሌው ቀልጠፍ አሉና ትከሻቸው ላይ የተጋደመውን ገመድ በአንድ እጃቸው አጥብቀው ይዘው ወደውሀው እየተግተለተለ በመግባት ላይ ያለውን ገመድ ከጀልባዋ እንጨት ጋር አጣብቀው ያዙት። እንደገና ቀረብ የሚላቸውን አንድ ሌላ ገመድ ቆረጡና የሁለቱን ጫፎች በአንድነት ቋጠ ራቸው። ይህንን ሁሉ በአንድ እጃቸው ብቻ ሲያከና ውኑ ችሎታና ቅልጥፍናቸው ለጉድ የሚታይ ነው። አንድ እግራቸውን እገመዶቹ ጥቅል ላይ አሳርፈው ወጠሩና ቋጠሮውን አጠበቁት። አሁን ስድስት ጥቅል የመጣበቂያ ገመድ ቀራቸው። መንጠቀው ላይ የነበ ሩትን ሥጋዎች የወሰደው ማን እንደሆነ ለማወቅ ግን አልቻሉም። ግራ ገባቸው። ምናልባት ሌላ ማርሊን፣ አለያም ሻርክ ሊሆን ይችላል።ግን እንዴት ሳልሰማው ቀረሁ?

«ልጁ አብሮኝ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር?...» አሉ ድምፃቸውን ዘለግ አድርገው።

በጨለማው ውስጥ ገመዶቻቸውን በማስተካከል ላይ እንዳሉ ዓሣው ድንገት ኃይለኛ እንቅስቃሴ አደረ ገና ወደቀኝ ጕተታቸው:: በዚሁ ጦስ ገመዱ ከዓይና ቸው ትንሽ ዝቅ ብሎ ቆረጣቸው:: ደማቸው በጉንጫ ቸው አቋርጦ ቁልቁል ወርዶ አገጫቸው ላይ ከመድ ረሱ በፊት ረግቶ ቆመ:: እንደምንም የሚያስተካከሉ ትን አስተካከለው ሲያበቁ ወደ ጀልባዋ አፍንጫ ተመ ልሰው እንጨቱን ተደግፈው አረፍ አሉ:: ጀርባቸው ላይ ባል ያደረጉትን ጆንያ አስተካከሉና ገመዱን ወደ ሌላው ትከሻቸው በጥንቃቄ አዛወሩት::ዓሣው ወደፊት እየሣበ ሲወዘገዘግ ይሰማቸዋል:: አንዱን እጃቸውን ወደውሃው ሰደድ አድርገው የጀልባዋን እንቅስቃሴ ለማዳመጥ ሞከሩ::

ግን ቅድም እንዲያ በኃይል የጐተተኝ ለምን ይሆን? ራሳቸውን ጠየቁ:: ምናልባት ገመዱ ከሩብታ በማያክለው ትከሻቸው ላይ ተንሸራትቶ ይሆናል:: መቼም እኔን ጀርባዬን የሚያመኝን ያህል የሱን ጀርባ የሚያመው አይመስለኝም:: ግን የቱንም ያህል ግዙፍ ቢሆን ይቺን ጀልባ መቼም ለዘለዓለሙ ሲጐትታት አይኖርም::

«ዓሣ!» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በለሰለሰ አነጋገር:: «ነፍሴ እስክምትወጣ ድረስ እንደማልለቅህ እንድታውቀው::»

ምን እኔ ብቻ እሱም የሚለቀኝ አይመስለኝም አሉ ሽማግሌው እንደገና በሀሳባቸው::እንቅልፍ የሚሉ ባይናቸው ሳይዞር ቁጭ እንዳሉ ንጋትን መጠባበቅ ጀመሩ:: አየሩ በጣም እየቀዘቀዘ በመሄዱ ምናልባት ትንሽ ቢሞቀኝ ብለው ወደጀልባዋ ግድግዳ በጣም ተጠ ግተው ተቀመጡ:: የሱን ያህል መቋቋም አይሣነኝም

አለ፡ አሁንም በአዕምሮዋቸው። ጆሊባዋ ቀጥ ብላ መንሿን ቀጥላለች። የሀሊደዋ ጫፍ በሽማግሌው የቆነ ትከሻ ትይዩ ብቅ አለ።

«አሣ፣ አጅሬ አቅጣጫውን ለውጦ ወደሰሜን አቅንቷል ማለት ነው» አለ። «የንፋሱና የባህሩ እንቅስቃሴ ግን ወደምሥራቅ ነበር የሚወስደን። ለኔ የሚበጀው ያንን ቢከተል ነበር።ለማናቸውም እየተዳከመ በመሄድ ላይ መሆኑን ያመለክታል።»

የሀሊደዋ በደንብ እየወጣች ስትሄድ ዓሣው እንደ ገመቱት እየደከመ አለመሆኑን ተገነዘቡ። ግን ሌላ አንድ ነገር ደግሞ አስተዋሉ። የገመዱ አቀማመጥ ዓሣው ወደላይ ከፍ እያለ መምጣቱን የሚያመለክት ዓይነት ነበር። ይህ ሁኔታ ግን ከውሃው ወጥቶ ይዘላል ማለት ሊሆን አይችልም። መቼም ስለዚህ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ መሆን ቢያዳግትም ያደርገዋል ብሎ መጠርጠርም ይገባል።

«እባክህ አምላኬ እንዳይዘል አድርገው፣» አለ ሽማግሌው። «ልቆጣጠረው የምችልበት ለርሱ የማይሆን በቂ ገመድ እንደሆን አለኝ።»

ምናልባት ገመዱን በይበልጥ ብወጥረው የህመም ስሜት ቢጤ ይፈጥርበትና እንዲዘል ያደርገው ይሆናል የሚል ሀሳብ ተሀነሠባቸው። ገመዱን ሣብ በማድረግ ውጥረቱን ለመጨመር ሞከሩ። ግን ገመዱ እስከ መጨረሻው ተወጥሮ ስለነበር ምንም ሊጨምሩ አልቻሉም። ከዚያ በላይ መሞከር ደግሞ የገመዱን መበጠስ ሊያስከትል ይችላል። ገመዱን ማወዛወዝ የለብኝም ሲሉ አሰቡ። በየንዳንዱ የገመዱ ውዝዋዜ ሣቢያ መንጠቆው ባፀደቀው ትክክል ላይ የፈጠረው ቀዳዳ እየሰፋ

ሊሄድና ኋላ በሚዘል ጊዜ መንጠቆው አፈትልኮ እንዲ ወጣ ሊያደርግ ይችላል።

ቢጫ የባህር አረም ገመዱ ላይ መከማቸቱን ሽማ ግሌው ተመልክተው ደስ አላቸው።በገመዱ ላይ ተጨል ማሪ ክብደት ስለሚፈጥር አሣውን ለማዳከም መልካም አጋዥ ይሆናቸዋል።

«ዓሣ!» አሉ። «በጣም እወድሃለሁ፣ አከብርሃለሁ። ግን ይቺ ጀምበር ከመጥለቋ በፊት እገድልሃለሁ» ባይ ሆን ተስፋ እንኳ እናድርግ እስቲ። ለጥቀው አሰቡ።

ከወደሰሜን በኩል አንድ ትንሽ ወፍ ወደ ጀል ባው መጣ። ወደባህሩ በጣም ቀረብ ብሎ ስለሚበር ድካም ያዛለው መሆኑን ሽማግሌው ወዲያው አወቁ።

ጀልባው ጭራ ላይ አረፈ። እንደገና ተር ብሎ በሽማግሌው አናት ላይ አንዴ ከዞረ በኋላ ትልቁ ዓሣ ተወጥሮ በተያዘበት ገመድ ላይ ተመቻችቶ ተቀመጠ።

«ዕድሜህ ስንት ነው?»ሽማግሌው ለወፉ ያቀረቡት የመጀመሪያው ጥያቄ ነበር። «ይህ የጀመሪያ ጉዞህ ነው?»

ሽማግሌው ሲለፈልፉ ወፉ ትክ ብሎ ያስተውላ ቸዋል። በጣም ተዳክሞ ስለነበር ቁጢጥ ያለበትን ገመድ እንኳን በደንብ ለመፈተሽ አልቻለም። ቀጫጭን ጣቶቹ ገመዱን ቁንጥጥ አድርገው ቢይዙም ሚዛኑን መጠበቅ ተስኖት መርገድገድና መዋዠቁ ግን አል ቀረም።

«አይዞህ ገመዱ በደንብ ተወጥሯል» አሉ ሽማግ ሌው።«ሊሊቱን ደግሞ ምንም ንፋስ ስላልነበረ እስተ

ዚ.ህም ሊ.ደክምህ አይገባም። ለመሆኑ ግን ወሮች ለም ንድነው ወደ ባህሩ የምትመጡት?

«አይዞህ አትፍራ ዲምቢጥየዋ። ዘና ብለህ ዕረፍት ማድረግ ትችላለህ።» አሉ። «ትንፋሽህን ተሰበሰብክ በኋላ ልክ እንደማናቸውም ሰው፣ ወፍ ወይም ዓሣ ተነስተህ ዕድልክን መሞከር ነው።»

ከወፉ ጋር መወያየታቸው ትንሽ ብርታት ሰጣቸው። ሊሊቱን ጀርባቸው ድርቅ ብሎ ስላደረ መጠነኛ ሥቃይ ሊሰማቸው ጀምሮዋል።

«ታዲያ ወፉ! ምናለ ደስ ካለህ ከ እዚሁ ተኔው ጋር መቆየትም ትችላለህ» አሉ። «ግን የጀልባየን ሸራ ስላልወጠርኩት አዝናለሁ። ደሞ ብቻየን እንዳልመስ ልህ። ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ነው ያለሁት።»

ልክ ይህን እንደተናገሩ ዓሣው ድንገት በከፍተኛ ኃይል ወደፊት በመወርወሩ ሽማግሌውን ሳያስበት ጉተታቸው። ቀልጠፍ ብለው እግሮቻቸውን በማንፈራ ጠጥ ማዛናቸውን ጠብቀው ባይቆሙና ገመዱን በጥ ቂቱ ለቀቅ አድርገው ባያረግቡት ኖሮ ከጀልባዋ ላይ መንጥቆ ባህሩ ውስጥ ባፍጢማቸው ይደፍቃቸው ነበር።

በተፈጠረው ያልታሰበ እንቅስቃሴ ማቢያ ወፉ ተነስቶ በረረ። ሽማግሌው ግን መሄዱን ልብ አላሉ ትም።ቀስ ብለው ገመዱን በቀኝ እጃቸው ሲጨብጡት መዳፋቸው ተሞሽልቆ እየደማ መሆኑን አስተዋሉ።

ወደ ኋላቸው ተገላምጠው ቢያዩ ወፉ የለም። ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ጓደኝነቱን ወደውት ነበር። ግን ምን ያደርጋል ድራሹ ጠፍቷል። ከንፈሬ አውጪኝ ብሏል።


አዬ፣ ትንሽ እንኳን ብትቆይ አሉ ሽማግሌው በሀሳባቸው:: ቶሎ ወደዳርቻው ካልተመለስክ የምትሄድበት የባሰውኑ የከፋ ነው:: ይሄ ጉደኛ ዓሣ ግን አንዴ በመመንጨቁ ብቻ እንዴት እጄን ሊቆርጠው ቻለ በሉ? እኔም በጣም ሳልደድብ አልቀረሁም:: ምናልባት ያንን ትንሽ ወፍ እያየሁ ስለርሱ በማሰብ ተዘናግቼለት ይሆናል:: አሁን ግን ጥሞናዬን በሙሉ ወደሥራዬ መመለስ ይኖርብኛል:: ጉልበቴም እየደከመ እንዳያሳጣኝ ትናንት የያዝኩትን ቱና መመገብ አለብኝ::

«ሁሉም ግን ልጁ አብሮኝ ቢኖር ጥሩ ነበር:: ለሥጋው የሚሆን ትንሽ ጨው ባገኝ ደግሞ በቃ፣ ሁሉም የተሟላ ነበር::»

ገመዱን ከቀኝ ወደ ግራ ትከሻቸው አዛወሩና በዝግታ ሽብረክ ብለው በመንበርከክ ቀኝ እጃቸውን ባህሩ ውስጥ ከከቱት:: ቶሎ አላወጡትም:: ወደ ባህሩ እንዳቀረቀሩ ከአንድ ደቂቃ ለሚበልጥ ጊዜ ዘፍዝፈው አቆዩት:: መዳፋቸውን የበከለው ደም እየለቀቀ በውሃው ላይ የሚነድፈውን ውልቅምቅም መስመርና ወደፊት በምትጓዘው ጀልባ የሚገመሰው ውሃ በእጃቸው ዙሪያ የሚፈጥረውን እንቅስቃሴ በዝዝ ብለው ሲመለከቱ ቆዩ::

«አጅሬ ፍጥነቱን እየቀነሰ ነው» አሉ::

የቆሰለ እጃቸውን በጨውማው ባህር ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሊያቆዩት በወደዱ ነበር:: ግን ዓሣው ቀደም ሲል እንዳደረገው ድንገት ወደፊት ይፈናጠር ይሆናል ብለው ስለሰጉ ከእንብርክካቸው ተነስተው እግሮቻቸውን አንፈራጠው በመቆም እጃቸውን ወደ ፀሐይዋ ዘረጉት:: ብዙ የሚሰራውና ለትግሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ቀኝ እጃቸው በዚያ የትግል ወቅት መቁሰሉ ቅር አሰኛቸው::



«አሁን እንግዲህ»አሉ እጃቸው እንደደረቀ፣«ቶናየን መብላት አለብኝ። ካለሁበት ሳልንቀሳቀስ በሚንጦው ወግቼ ወደኔ ልስበውና ተዝናንቼ ልመገበው እችላለሁ።»

በርከክ አሉና ጀልባዋ ጭራ አካባቢ የተጋደመውን ቶና በባለዛቢያው ሚንጦ ወግተው እየሣቡ አስጠጉት። ግራ ትከሻቸው ላይ ያጋደሙትን ገመድ ግራ ክንዳቸው ላይ ወጠሩና ቶናውን ከሚንጦው ከአስለቀቁ በኋላ አንካሴውን ወደቦታው ወረወሩት። በአንደኛው ጉልበታቸው ዓሣውን ከጀልባዋ ወለል ጋር ሰፍተው ያዙና ከአናቱ እስከጅራቱ ሥጋውን እየገሸለጡ ከአጥንቱ ላይ በማላቀቅ የሽብልቅ ቅርፅ ያላቸው ዝልዝሎች አወጡ። ስድስት ዝልዝል እንዳወጡ ጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ እንጨቱ ላይ በማስጣት መደዳውን ደረደሯቸው።ካራቸውን ከአፎቱ መዘው ሱሪያቸው ላይ ጠራረጉና ዓሣውን በጭራው በማንጠልጠል ወደባህሩ ወረወሩት።

«መቼም ሁሉንም በልቼ መጨረስ የምችል አይመስለኝም» አሉና ከዝልዝሎቹ አንደኛውን ሁለት ላይ ቆረጡት።ትከሻቸው ላይ የተጋደመው ገመድ ወደ ፊት በኃይል ሲጐተት ይሰማቸዋል። የግራ እጃቸው መዳፍ ደግሞ ተሸምቅቋል። ከባዱን ገመድ እንቅ አድርጐ የያዘውን መዳፋቸውን በጥላቻ አስተዋሉት።

«መሆኑን ግን ምን አይነት እጅ ነው?» አሉ። «ከፈለግህ መሸማቀቅ መብትህ ነው። ካሻህም ደግሞ ወደ ጉጠትነት መለወጥ ትችላለህ።»

ወደጉን፣አግድም ሽፋፍ ብሉ በተወጠረው ገመድ ላይ አሺጋግረው ጨለማ ወደ ዋጠው ባህር አፈጠጡ። አሁን እንግዲህ የቶናውን ቁርጥ አጎዛባው፣ ፡ እጅህም

ጥንከሬ ይበጅሃል። አቶ እጅም በሆንክ ጥፋተኛ አይደለም።ከዓሣው ጋር ስትታገል ብዙ ሰዓቶች ማሳለፍህን አትዘንጋ። እስከወዲያኛው እንደተቀራኘኸው ልትቀይም ትችላለህ። በል ለማንኛውም ቶናህን ክምኩም።

አንዱን የሥጋ ጉማጅ አንስተው ወዳፋቸው አስገ ቡና በዝግታ ያላምጡት ጀመር። ጣዕሙ ለክፉ አይሰጥም።

ደህና አድርገህ አድቅቀው አሉ በሀሳባቸው። ያን ጊዜ ነው በውስጡ ያለውን ፈሳሽ ሙሉ በሙሉ ለመጣጣመቅ የምትችለው። ትንሽ ሎሚ ወይም ጨው ቢገኝማ ኖሮ እንዴት አድርጎ በጣፈጠ ነበር።

«ታዲያስ እጅ፣ አሁን እንዴት ነህ? ምን ይሰማ ሃል?» ጥያቄያቸውን ያቀረቡት ለተሸመቀቀ እጃቸው ነበር። «ቶሎ እንድትፈታ ከሥጋው ጥቂት መጨመር አለብኝ።»

ሌላ ጉማጅ አንስተው ጉረሱና በጥንቃቄ ካላመጡ በኋላ ቆዳውን ለይተው ተፉት።

«እህ- አቶ እጅ፣ እንዴት ነህ? ወይስ ውጤቱን ለማወቅ ገና ነው?»

አንዱን ዝልዝል አንስተው እንዳለ ጉረሱና ማመ ንገክ ጀመሩ።

«ለነገሩ ፍርጥም ያለና ደማም ዓሣ ኖሯል ጻል» አሉ በሀሳባቸው።

«ከዶልፊን ይልቅ እሱን ማግኘቴ ዕድለኛ ነኝ። ዶልፊን ትንሽ ጣፋጭነት አለው። ይህኛው ጥርስ ያዝ ማድረጉም ሆነ ጣዕሙ ጥሩ ዓይነት ነው።»

ትንሽ ጨው በ.ኖር ደሞ የበለጠ በሆነ ነበር- ፀሐዩ ሲያደርቀው ወይም ብዙ ሲቆይ ሊበላሽ ስለ ማችል፡፡ ቢሆንም ቁንጣን ቢይዘኝም ይያዘኝ እንጂ ሁሉንም መብላት አለብኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ለማናቸውም ነገር ዝግጁ እሆናለሁ፡፡

«እጅ፣ ትዕግሥት!» አለ፡፡ «ይህንን ሁሉ የማደ ርገው ላንተ ብዬ ነው፡፡ ይገባሀል?»

ዓሣው ግን ምነው አደፈጠ? እንቅስቃሴውን ብሰማ ምንኛ ደስ ባለኝ አሉ በሀሳባቸው፡፡ ወንድሜ ነው፡፡ ሆኖም እገድለዋለሁ፡፡ ይህንን ለመፈፀም ደግሞ ጥንካ ሬየን መጠበቅ አለብኝ፡፡ ዝግ ብለው ዝልዝሎቹን በሙሉ አንድባንድ በልተው ጨረሱ፡፡

ቀጥ ብለው ተቀመጡና እጃቸውን ሱሪያቸው ላይ ጠራረጉት፡፡

«አሁን ገመዱን መልቀቅ ትችላለህ እጅ» አሉ፡፡ «ከዚያ በኋላ እስኪሻልህ ድረስ በቀኝ እጄ እይዘዋለሁ፡፡»

«አምላኬ ሆይ፣ የተሸመቀቀው እጄ እንዲፍታታ መልካም ፈቃድህ ይሁን» አሉ፡፡«ምክንያቱም እዚያታች ያደፈጠው ዓሣ ምን እንደሚያደርግ አላውቅምና፡፡»

አጅሬ ፀጥ- ረጋ ብሎ ዕቅዱን በመፈፀም ላይ ያለ ይመስላል አሉ በሀሳባቸው፡፡ ግን ምን ይሆን ዕቅዱ? የኔስ? እኔማ ዕቅድ ማውጣትም ላያስፈልገኝ ይችላል፡፡ እርሱ ግዙፍና ጠንካራ ስለሆነ የኔውን በርሱ ዕቅድ ላይ መስርቼ እዘጋጅዋለሁ፡፡ ምናልባት ከውሃው ዘልሎ ከወጣም ሲጥ ላደርገው እችላለሁ፡፡ ካያያዙ ግን ይህ ንን የሚያደርግ አይመስልም፡፡ እዚያታች ለዘለዓለሙ

ይቆያታል እንጂ ወደላይ ብቅ አይላትም:: እኔም አል ለቅ:: እስከዘላለሙ ሙጥኝ እላታለሁ እንጂ::

የተሸመቀቀ እጃቸውን ሱሪያቸው ላይ አባበሱና ጣቶቻቸውን ዘና ለማድረግ ሞከሩ::ግን አልተዘረጉም:: ምናልባት ፀሐይዋ በደንብ ስትሞቅ ይዘረጉ ይሆናል:: ወይም የበላሁት ጥሬ ቶሎ ሲሠራ ልክ ይገባሉ:: እስፈ ላጊ ሆኖ ከተገኘ ግን የመጣው ይምጣ እንጂ እዘረጋቸ ዋለሁ:: ለጊዜው ግን በጉልበት አላስገድዳቸውም::

ወደባህሩ አሽጋግረው ተመለከቱ::የቱን ያህልብቸኛ እንደሆኑ ተሰማቸው:: ከዓሣው ጋር የተቆራኙበት ገመድ ከፊት ለፊታቸው ገደድ ብሎ እንደተወጠረ ይታያቸዋል:: ሰማዩ ላይ ደመና እየተሰባሰበ ነው:: ወዲያ ማዶ ዳክየዎች እጅብ ብለው ይንሣፈፋሉ:: ማንም ቢሆን በባህር ላይ ፍፁም ብቸኛ እንደማይሆን አሰቡ::

ሰዎች በትንሽ ጀልባ ላይ ሆነው በባህር ሲንሣፈፉ መሬት ከእይታቸው በሚሰወር ጊዜ ስለሚሰማቸው ፍርሃት ማሰላሰል ያዙ:: ግን ኑ መጥፎ የአየር ጠባይ ሳይታሰብ በሚከሰትባቸው ጊዜያት ሰዎች ፍራት - ፍራት ቢላቸውም ዕውነት አላቸው አሉ በሀሳባቸው:: ይሄ ወር ደግሞ አውሎ ንፋስ የሚበዛበት ነው:: አውሎ ንፋስ ከሌለ ግን እንደዚህ ወቅት ጥሩ አየር የሚነፍስበት ከቶም በዓመቱ ውስጥ የለም::

አውሎ ንፋስ ቢመጣም ባህር የሚያዘወትር ሰው ከብዙ ቀናት አስቀድሞ ምልክቶቹን በሰማዩ ላይ ለማ የት ይችላል:: የመሬት ሰዎች ግን ምልክቱን አያውቁ ትም፣አያዩትምም:: አሁን ግን አውሎ ንፋስ የሚመጣ [illegible]

ወደላይ አንጋጠው ተመለከቱ::በመለከረሙ ሰማይ ላይ ነጭ ደመና እንደጆላቲ አንዱ ባንዱ ላይ እየተነ ባበረ መከመር ይዟል::

«ወዳጄ ዓሣ፣ አየሩ ካንተ ይልቅ ለኔ ተስማሚ እየሆነ ነው::»

የግራ እጃቸው እንደተሸማቀቀ ቢሆንም ቀስ በቀስ መፍታታት መጀመሩ ይሰማቸዋል:: በዓለም ላይ ከሚያስጠሉኝ ነገሮች አንዱ የእጅ መሸምቀቅ ነው አሉ በሀሳባቸው:: በራስ ላይ ከህደት እንደመፈፀም ይቆጠራል::

ልጁ አብሮኝ ቢኖር እንኳን ቀስ እያለ ያሽልኝ ነበር፣አሉ አሁንም በሀሳባቸው:: ቢሆንም ግድ የለም:: አንድ አንድ እያለ መፍታተቱ አይቀርም::

በዚህ ጊዜ የዓሣው አጉታተት ለወጥ እያለ መሆኑ ገመዱን በያዙበት ቀኝ እጃቸው ላይ ተሰማቸው:: ትንሽ ቆይቶ የተሸመቀቀ እጃቸውን ጭናቸው ላይ መታ መታ በማድረግ ላይ እንዳሉ ገመዱ ከፍ እያለ ከውሃው ሲወጣ ታያቸው::

«አሃ! አጅሬ ወደላይ እየመጣ ነው»አሉ:: «አይዞህ እጅ፣በርታ::እባክህ ጓዴ ና::ወደላይ ብቅ በልናልይሁ::»

ከርር ብሎ የተቋጠረው ገመድ በዝግታ ወደ ውሃው አናት መውጣቱን ቀጠለ:: ወዲያው ከጀልባዋ ፊት ለፊት ያለው የባህሩ ውሃ አበጠና ዓሣው ብቅ አለ:: ውሃው በጉንና ጉኑ ላይ እየፈሰሰ ወጥቶ ወጥቶ የሚያልቅ በሚመስል ሁኔታ ወደላይ መዝለቁን ቀጠለ:: የጭንቅላቱና የጀርባው ደማቅ የወይን ጠጅ ቀለም ፀሐይዋ ብርሃን ፈካ:: ብሩህ የወይን ጠጅ ቀለም

ያላቸው መስመሮች በጉኖቹ ላይ ተጋደመዋል።
በመጨረሻ መላ ቁመናው እስኪታይ ከውሃው ወጣ።
ግን ብዙም ሳይቆይ ተመልሶ ጠለቀ።ትልቁን የፌረንጅ
ማጭድ የሚመስለው ጅራቱ ከአየር እስኪሰወር ድረስ
ሽማግሌው ፈዘው ተመለከቱት። ጀልባዋን እንደነበረው
መጐተቱን ቀጠለ። ገመዱም እርሱን ተከትሎ የባህሩን
ውሃ ይሰነጥቀዋል።

«የኔ ያለህ! ቁመቱኮ ከጀልባዋ በሁለት ጫማ
ይበልጣል» አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው።

በጣም ትልቅ ዓሣ ስለሆነ በሙሉ ጉልበቱ እንዳ
ይጠቀም መግታት አለብኝ አሉ በሀሳባቸው። የበሉ
የጠጡትን ያህል ገመዱን ወጥረው ወደ ራሳቸው በመ
ሣብ ካልተቋቋሙት በስተቀር ኃይልና ፍጥነቱን እየ
ጨመረ ወደፊት በመሣብ ገመዱን በጥሶ ሊጥለው እን
ደሚችል ግልፅ ሆነላቸው።ባንድ ፊት ግን የኛን ያህል
ብልጥ አለመሆናቸው ተመስገን ነው አሉ በሀሳባቸው።
ምንም እንኳን በጨዋነትና በጉልበት ቢበልጡንም
በማሰብ ችሎታ ግን አጠገባችንም አይደርሱ።

ሽማግሌው ከዚያ በፊት ብዙ ግዙፍ ዓሣዎች አይ
ተዋል። አንዳንዶቹ ከአምስት መቶ ኪሎ በላይ የሚመ
ዝኑ ነበሩ። ማየት ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም ያን ያህል
ክብደት ያላቸውን ከአንድም ሁለት ይዘዋል። ግን እን
ዲህ እንደዛሬው ለብቻቸው ሆነው አልነበረም። አሁን
አንድም አጋዥ ሳይኖራቸው ነው ይህ ጉድ የገጠ
ማቸው። በዚያ ላይ ከወደቡ በጣም ርቀዋል። በዓይ
ናቸው ካዩዋቸውም ሆነ ዝናቸውን በወሬ ከሰሙላቸው
ግዙፋን ዓሦች ሁሉ ከሚበልጠው ጋር በገመድ ተቆራ
ኝተው ብቻቸውን ተፋጠዋል። በዚያ ላይ ደግሞ ግራ

አጃቸው ሶምን እንደ ጨመደደ እንደ ጆሬ አሞራ ጣቶች ተጨብጦ አሻፈረኝ ብሏል።

በሆንም ቀስ ብሎ መፍታታት አይቀርም። አመ ሁን ትቶ ጓደኛውን እንደሚያግዘው አምናለሁ።ዓማውና ሁለቱ እጆቹ ወንድማማች ናቸው። እንደ ምንም ብሎ መዘርጋት አለበት።እንዲህ ያለ ሀኬተኛነት ከርሱ የሚ ጠበቅ አይደለም። ዓማው ዝግ እያለ በመጀመሪያው ፍጥነቱ መጓዝ ጀመረ።

ለምን ብቅ እንዳለ ግን በጭራሽ ሊገባኝ አልቻለም አሉ - ሽማግሌው በሀሳባቸው። ደሞኮ አወጣጡ ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ ሊያሳየኝ የፈለገ ዓይነት ሆኖ ነው። ወይ ነዶ! እኔም ምን ዓይነት ሰው እንደ ሆንኩ ላሳየው ብችል ምንኛ ጥሩ ነበር። ግን ደሞ ይሄን የተሸመቀቀ እጄን ያይብኝና ነገር ይበላሻል። ስለዚህ ልክ እንደጀመረው ከሆንኩት በላይ አድርጐ መገመቱን ይቀጥልበት። እኔም እንደዚያው እያስመሰልኩ እቆያ ለሁ።ግን ምን ነበረበት እኔ እሱን ብሆን። የቱን ያህል ደስ ባለኝ ነበር። የኔ ከሆኑት ባህርያት መካከል ሁሉ ቱን፣ ፍላጐቱንና ዕውቀቱን ብቻ እንደያዝኩ ምነው እሱን በሆንኩ።

ዓማው ቀጥ ብሎ ወደፊት መንገዱን ቀጠለ። ጀል ባዋም ጨለማ የሰፈነበትን ባህር እየሰነጠቀች ትከተ ላለች።ሽማግሌው በዝግታ የጀልባዋን ጐን ደገፍ አሉና ተመቻችተው ተቀመጡ። ቀትር ላይ ከወደ ምሥራቅ በኩል በሚመጣ ንፋስ ሳቢያ ባህሩ በመጠኑ ወደላይ ከፍ ማለት ጀመረ።የሽማግሌውም የግራእጅ ተፍታታና ተዘረጋ።

«አዝናለሁ ዓማ። ይሄ ላንተ መጥፎ ዜና ነው» አሉና ገመዱን ጀርባቸውን በሸፈነው ጆንያ ላይ አስተ ካከለው አጋደሙት።

ከበፊቱ ይልቅ አሁን ትንሽ ቢመቻቸውም ስቃዩ ግን ያው ነበር።

«አማኝ እንኳን አይደለሁም» አለ። «ብቻ እንዲያው ይህንን ዓሣ ይገፍ ቤቴ እንድገባ አባታችን ሆይ ንና ሰላምለኪን አሥር አሥር ጊዜ ደጋግሜ እፀልያለሁ። መጨረሻውን ካሳመረልኝ ከበር ማርያም ድረስ በእግሬ እሄዳለሁ።»

በዘልማድ የሚያውቁትን ፀሎት ማነብነብ ጀመሩ። ከድካማቸው የተነሣ አንዳንዴ ፀሎቱን ያቋርጡና ዝም- ጭጭ ይላሉ። ደግሞ እንደገና በፍጥነት ያነበንባሉ። ሰላም ለኪ ቀለል ስለሚል እሱን ብደግም ይሻላል አሉ በሀሳባቸው።

«ሰላም ለኪ እንዘንሰግድ ንብለኪ ማርያም እምነ ናስተበቁዐኪ። እምአርዌ ነዓዊ ተማኅፀነ ብኪ። በእንተ ሐና እምኪ ወኢያቄም አቡኪ ማህበረነዩም ድንግል ባርኪ።አሜን» አሉ። ቀጠሉናም «የተቀደስሽ ንፅህት ድንግል ሆይ ይህ ዓሣ እንዲሞት ያንቺም ፈቃድ ይሁን።ውብና ድንቅ ፍጡር ቢሆንም ምንም ልናደርግ አንችልም» ሲሉ አከሉበት።

ፀሎታቸውን ሲያበቁ ትንሽ ቀለል አላቸው። ስቃያቸው ግን አልቀነሰም። እንዲያውም ጥቂት ጠንከር ያለ ይመስላል። የጀልባቸውን አፍንጫ ደገፍ ብለው የግራእጃቸውን ጣቶች ማነቃነቅ፣ማጣጠፍ፣ መዘርጋት ጀመሩ።

ንፋሱ እየጨመረ ቢሄድም የፀሐይዋ ሙቀት እንዳየለ ነበር።

«በዛች በትንሿ ገመድ መንጠቆ ላይ ጥቂት ሠርዲኖች ወተፍ ወተፍ አድርጌ እንደገና ማጥመዱ አይ

ከፋም» አለ። «አጅሬ አንድ ሌላ ተጨማሪ ሌሊት በህ ይወት ለመቆየት ከወሰነ እኔም ምግብ ሊያስፈልገኝ ነው። የጠርሙሱም ውሃ መገርገድ ጀምሯል። እዚህ አካባቢ ግን ከዶልፊን ሌላ ምንም የማገኝ አይመስለ ኝም።ግን ዶልፊንም'ኮ በትክክሉ ከተበላ ከፉ አይደለም። አቤት፣በራሪ አሣዎች ባገኝ!እንዴት ደስ ይለኝ ነበር። ግን ምን ያደርጋል እነሱን የሚስብልኝ መብራት የለ ኝም። በተለይ ለጥሬ ከነሱ የሚስተካከል ምን ይገ ኛል። በዚያ ላይ ብልት በማውጣት አያስቸግሩ፣ ዘል ዝለኝ- ምተሩኝ አይሉ። ብቻ በተቻለ መጠን ጉልበቱን መቆጠብ አለብኝ። ጌታዬ ሆይ፣ የያዝኩት ዓሣ ይህንን ያህል ትልቅ መሆኑን አላወቅሁም ነበር።

«ግን ምንም ይሁን ምን አገድለዋለሁ» አለ። «ታላቅነቱንና ክብሩን እንደያዘ እገድለዋለሁ።»

በርግጥ ትክክልና ተገቢም እንዳልሆነ ይሰማኛል። ግን አሳየዋለሁ። የሰው ልጅ ሊያደርግና ሊቋቋም የሚ ችለውን ሁሉ አሣየዋለሁ አለ በሀሳባቸው።

«ለየት ያልኩ ሽማግሌ መሆኔን ለልጁ ነግሬው ነበር» አለ።

«ይህንን የማረጋግጥበት ጊዜውም፣ አጋጣሚውም አሁን ነው።»

ግን ይህንን ጉዳይ ከዚያ በፊት አንዴ ሳይሆን አንድ ሺህ ጊዜ አረጋግጠዋል። ሆኖም ከአሁኑ ጋር ሲነፃፀር የቀድሞው በሙሉ ከምንም የሚቆጠር አል ነበረም።እያንዳንዱ ጊዜ በራሱ አዲስ ነው። ሽማግሌው ዘወትር አንዳች ነገር መስራት ሲጀምሩ ስላለፉ ጊዜ ያት ማሰብ አይወዱም።

አሁን እንቅልፍ በወሰደውና እኔም ትንሽ አሽልቤ ስለአንበሶቹ ባልም ምንኛ ደቤ ባለኝ አሉ በሀሳባቸው:: ለመሆኑ ግን ከሁሉም ከሁሉም የአንበሶቹ ጉዳይ ብቻ ከኔ ጋር መቅረቱ በምን የተነሣ ይሆን?በቃ ተወው ሽሜ፣ ስለሱ አታስብ አሉ ለራሳቸው:: አሁን ረጋ ብለህ የጀልባዋን እንጨት ተደገፍና ትንሽ ዕረፍት አድርግ:: ስለምንም ነገር አታስብ:: እሱ በከባድ ሥራ ተጠምዷል:: አንተ ግን በተቻለ መጠን ጥቂት ለመሥራት ሞክር::

ቀትር አልፎ ጊዜው ወደምሽት መገስገስ ጀመረ:: ጀልባዋ በዝግታ መንሳፈፏን ቀጥላለች:: ጀርባቸው ላይ የተጋደመውም ገመድ ሽማግሌውን እያሰቃያቸው ነው::

በመሃሉ ገመዱ እንደገና ወደ ላይ ከፍ ማለት ጀመረ:: ዓሣው ግን ከውሃው አልወጣም:: ብቻ በጥቂቱ ከፍ ብሎ መቀኘቱን ቀጠለ:: የፀሐይዋ ብርሃን በሽማግሌው የግራ እጅ፣ ትከሻና ጀርባ ላይ በማረፉ ዓሣው አቅጣጫውን ወደምሥራቅ ማዞሩን ተገነዘቡ::

ከበፊቱ ይልቅ አሁን ዓሣው ምን እንደሚመስልና ምን እንደሚያደርግ ወለል ብሎ በዓይነ - ህሊናቸው ይታያቸዋል:: አንድ ጊዜ ብቅ ብሎ ስላዩት የወይንጠጅ ቀለም ያላቸው ክንፎቹን በሰፊው ዘርግቶ፣ ቀጥ ብሎ በተገተረው ትልቅ ጭራው ጨለማ የሰፈነበትን ውሃ እየሰነጠቀ ሲዋኝ ሥዕሉ ቁልጭ ብሎ ይታያቸዋል:: በዚያ የእንጦርጦስ ጥልቀት ውስጥ ሆኖ በደንብ እያየ መጓዙ የሚያስደንቅ እኮ ነው አሉ በሀሳባቸው:: እኔስ በአንድ ወቅት እንዲሁ አልነበርኩ:: የፈለገውን ያህል ጨለማ ቢሆን ድመት በምሽት ለማየት የምትችለውን ያህል ወለል ብሎ ነበር የሚታየኝ::

ጣቶቻቸውን ያለማቋረጥ በማንቀሣቀሣቸውና የሀ ሐይዋም ሙቀት ታከሉበት ግራ እጃቸው ሙሉ በሙሉ ተፍታቶ እንደወትሮው ደህና ሆነላቸው። ተራ እየገባ የቀኝ እጃቸውን ሸከም መጋራት ጀመረ። ከዓ ሣው ጋር ያቆራኛቸው ገመድ ጀርባቸው ላይ የሚፈ ጥረውን የህመም ስሜት ለማርገብ እንዲረዳቸው አልፎ አልፎ የትከሻቸውን ጡንቻዎች ያንቋንቋቸዋል።

«ሙቼም በአሁኑ ወቅት ድካም ካልተሰማህ ዕውነ ተኛው ጉድ ፍጡር ነህ ለማለት ደፍራለሁ፣» አሉ ሽማግሌው።

እርሳቸው ግን በጣም እየደከማቸው ነው። ምሽቱ ደግሞ በጣም ተቃርቧል። ተስፋቸውን አይዞህ ለማለት ያህል ስለሌሎች ጉዳዮች ማሰብ ጀመሩ።ስለታላላቆቹ የቤዝቦል ቡድኖች ማውጠንጠን ያዙ።ለርሳቸው ትልቁ ቡድን ግራን ሊጋስ የሚባለው ነው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የኒውዮርክ ያንኪዎችና የዲ ትሮይት ነብሮች ግጥሚያ እንደሚያደርጉ አሣምረው ያውቃሉ።

ዛሬ እንግዲህ ሁለተኛ ቀኔ መሆኑ ነው። ሁዌንስ ምን ውጤት አግኝቶ ይሆን? አሉ በሀሳባቸው። እኔ ግን በራሴ ላይ ዕምነት ሊኖረኝ ይገባል። በዚያ ላይ እንደ አውራ ዶሮ በተረከዙ ላይ ያፈነገጠ አጥንት እያ ሰቃየው እንኳን ማናቸውንም ነገር በፍፁምነት ደረጃ ከማከናወን እንደማይታቀበው እንደ ዲማጂዮ መሆን አለብኝ።ለመሆኑ ግን በተረከዝ ላይ ያጥንት ማፈንገጥ ምን ይሆን?ጥያቄውን ያቀረቡት ለራሳቸው ነበር። የት ርፍ አጥንት መኖር ነዋ። እኛ ግን የለንም። በበኩሌ ግን እንዷ፣አንዱ ወይም ሁለቱም ዓይኖቼ ከጠፉ በኋላ እንደ አውራ ዶሮ የጀመርኩትን ትግል ለመቀጠል

የምችል አይመስለኝም። ሰውኮ በትልልቆቹ አሰዋኖና አራዊት አኳያ ሲታይ እስከዚህም አይደለም። እኔም ብሆን በአሁኗ ቅፅበት እዚያ ታች ዕልመት በዋጠው የባህር ማህፀን ውስጥ ያለውን አውሬ ብሆን እመ ኛለሁ።

«እሱም ቢሆን ሻርኮች እስካልመጡ ድረስ ነው» አሉ ድምፃቸውን አጉልተው። «ሻርኮች ከመጡ ግን ወዮ ለሱም ለኔም። ለሁለታችንም እግዜር ይሁነን ማለት ብቻ ነው።»

ለመሆኑ እኔ ከዚህ ዓሣ ጋር ተቆራኝቼ የቆየሁ ትን ያህል ዲማጂዮ ከዓሣ ጋር ሊቆይ ይቻለው ይሆን? አሉ በሀሳባቸው። ለምንሣ አይችልም? ወጣትና ጠንካራ ነውና ለበለጠም ጊዜ ቆይቶ ሊቋቋመው እንደ ሚችል አምናለሁ።የሱስ አባት ዓሣ አሥጋሪ አልነበሩ? እንዲያው ግን ያ ተረከዙ ላይ ያፈነገጠ አጥንት ብርቱ ህመም እየፈጠረ ያሰቃየው ይሆን?

«እንጃ! ምናባቱንስ አውቃለሁ» አሉ በጩኸት። «እኔ እንደሆንኩ በህይወቴ ሙሉ የተረከዜ አጥንት አፈንግጦ አያውቅ።»

ፀሐይዋ ስትጠልቅ ራሳቸውን ለማበረታታትና ለማደፋፈር ሲሉ በሀሳብ ወደኋላ በማዘገም ከትዝታ ቻው ጋር መቆዘም ያዙ። አንድ ቀን ካዛብላንካ ውስጥ በሚገኝ ቡና ቤት ያደረጉት ውድድር ፊታቸው ላይ ድቅን አለባቸው። ከሲየንፉዌጎ አካባቢ ከመጣ ጥቁር ሰው ጋር የገጠሙት የክንድ ጥንካሬ መገመቻ ፉክክር ነበር። ሰውየው በወደቡ አካባቢ ለጉልበተኛነቱ አቻ አልነበረውም።

አንድ ጠረጴዛ ላይ ክብ መስመር በጠመኔ ከተነ
ደፈ. በኋላ ሁለቱ ሰዎች መዳፎቻቸውን አጨባብጠው
ክርኖቻቸውን ቀለበቱ መሃል ጠረጴዛው ላይ በመትከል
መፋለማቸውንና የማ.ያሸንፍ ጠፍቶ እንደተፋጠጡ
አንድ ቀንና አንድ ሌሊት ማሳለፋቸውን ያሰላስሉ
ጀመር:: ከፍሉ ከበላያቸው በተንጠለጠለው የማሾ ብር
ሃን ደምቆ፣ ዙሪያቸውን ያሰፈሰፋት ተመልካቾች እያ
ወኩ ውርርዱን ሲያቀልጡት እርሳቸው የተፎካካሪያቸ
ውን ጥቁር እጅና ጥቁር ፊት ትክ ብለው ያስተው
ላሉ::ከመጀመሪያዎቹ ስምንት ሰዓቶች በኋላ ዳኞቻቸው
በየአራቱ ሰዓት ይለዋወጡ ነበር - ለመተኛትና ለማ
ረፍ እንዲችሉ::ከሁለቱ ተጋጣሚዎች ጥፍሮች ውስጥ
ደም ማዝነት ጀመረ:: ግን ማን ፍንክች ሊል:: ጥቁሩ
ሰው የእርሳቸውን ዓይኖች፣ ክንዶችና መዳፎች ያስተ
ውላል:: እርሳቸውም የጥቁሩን ሰው ዓይኖችና ክንዶች
ይቃኛሉ:: በነርሱ የትንቅንቅ ውጤት ላይ የሚወራረ
ዱት ተመልካቾች ደግሞ እርፎ መቀመጥ አልሆንላ
ቸው ያለ ይመስል ይቁነጠነጣሉ:: አሥር ጊዜ ወጣ
ገባ ይላሉ::ደግሞ ረጃጅም ወንበሮች ላይ ይቀመጡና
ግድግዳውን በመደገፍ ውድድሩን ይከታተላሉ:: ሰማ
ያዊ ቀለም በተቀቡት የእንጨት ግድግዳዎች ላይ የሁ
ለቱ ሰዎች ጥላ ገዝፎ ይታያል::

ሌሊቱን በሙሉ የድሉ ሚዛን አንዴ ወዳንዱ፣
አንዴ ደግሞ ወደሌላው ሰው እያፈራረቀ ሲያጋድል
እንዲሁ እንደተቋለፉ አደሩ:: የጥቁሩ ሰው ደጋፊዎች
በየመሀሉ ራም[*] ያጠጡታል:: ከንፈሮቹ መሃል ሲጋራ
ይሰኩና በእሣት ያቀጣጥሉለታል:: እሱም መጠጡን
በቀመሰ ቁጥር ያለ ኃይሉን ሁሉ ያሰባስብና አሸናፊ

[*] ራም:- የአልኮል ይዘቱ ከፍተኛ የሆነ አረቂ መሣይ
መጠጥ ነው::

ነትን ለመቀዳጀት ይፍጨረጨራል። ዕውነትም አንድ ወቅት ላይ የሽማግሌውን ሚዛን ስስት ኢንች ያህል አናግቶት ነበር። እርሳቸው ግን ያን ጊዜ እንዳሁኑ ሽማግሌ አልነበሩም- ሳንቲያጎ ሻምፒዮናው እንጂ። ስለዚህ ለተፋላሚያቸው ማየል አልተበገሩም። በጥቁሩ ሰው ክንድ ተዕዕኖ ወደጠረጴዛው ዘመም ማለት ጀምሮ የነበረ ክንዳቸውን ቀስ በቀስ ወደላይ በመመለስ እንደገና ቀጥ ብሎ በእኩልነት እንዲቆም አደረጉት።

ጠባየ ሺጋና የተዋጣለት ስፖርተኛ በመባል የሚታወቀውን ጥቁር ሰው በመጨረሻ እንደሚፈቱት በልባቸው ርግጠኛ የሆኑት በዚያን ጊዜ ነበር። ዕው ነትም ንጋት ላይ፣ የፀሐይ የማለዳ ጨረር የማሾውን ብርሃን መደምሰስ ሲጀምርና ተስፋ የቆረጡ ተወራ ራጆች ውድድሩ ያለአሸናፊ በአቻ ውጤት እንዲያበቃ በጥያቄ ሲወተውቱ፣ዳኛውም ራሱን በመስማማት ዓይ ነት በመነቅነቅ ላይ እንዳለ ሽማግሌው መላ ኃይላቸ ውን አጠረቃቅመው እንደሰንደቅ የተገተረውን የጥቁ ሩን ሰው ክንድ ወደጠረጴዛው መገርሰስ ጀመሩ። ወደ ታች፣ ወደታች፣ አሁንም ወደታች. . . ጠረጴዛው ላይ እስኪጋደም ድረስ ያንን ጥቁር ክንድ ወደታች መጫና ቸውን ቀጠሉ። ዕሁድ ጠዋት የተጀመረው ውድድር ሰኞ ማለዳ አበቃ። የውርርድ ገንዘብ ካሲያዙት መካ ከል አብዛኞቹ መርከብ ላይ ስኳር ወደ መጫን ሥራ ቸው ወይም ተቀጥረው ወደሚያገለግሉበት የሀቫና የከሰል ኩባንያ በሰዓቱ ለመሄድ እንዲችሉ ውድድሩ በአቻ ውጤት እንዲፈፀም የዳኛውን ውሣኔ እየጠየቁ ሣሉ ሽማግሌው ገላገሏቸው። አንድም ሰው ከሥፍ ራው ልውሽ ሣይል ውድድሩ በሽማግሌው አሸናፊነት አበቃ።

ከዚያ በኋላ ለብዙ ጊዜያት ሰው ሁሉ ሲጠራ ቸው ሻምፒዮናው እያለ ነበር።እንደገና በፀደይ ግድም

ሁለቱ ሰዎች የመልስ ግጥሚያ አደረጉ። ይህኛው ውድ ድር ግን እንደመጀመሪያው ሞቅ ያለና የጦፈ ፉክክር የታየበት አልነበረም። ሽማግሌው የሲየንፉ ዌጉውን ጥቁር ሰው ወኔና በራስ መተማመን በመጀመሪያው ግጥሚያ አንኮታኩተውት ስለነበር በሁለተኛው ግጥ ሚያ በቀላሉ አሸነፉት። እሳቸውም ከዚያ በኋላ ብዙም ውድድር አላደረጉም። ከጥቂት ግጥሚያዎች በኋላ እር ግፍ አድርገው ተውት። ውድድሩን ማዘውተር ቀኝ እጃቸውን ከጉዳት ላይ እንደሚጥለውና በሥራቸው ላይ እክል ሊፈጥር እንደሚችል በመገመት ፉክክሩን እርም አሉ።

ወደሚያሚ የሚበር አይሮፕላን በፊታቸው ትይዩ አለፈ። የአይሮፕላኑ ጥላ በአካባቢው የነበሩ በራሪ ዓሣ ዎችን አስበረገጋቸው።

«ይህን የሚያህል የበራሪ ዓሣ መንጋ ካለ እዚህ ቦታ ዶልፊን አይጠፋም ማለት ነው» አሉ። ጀልባዋ በዝግታ ወደፊት መጓዟን እንደቀጠለች ነው። አይሮ ፕላኑ ከዓይናቸው እስኪሰወር ድረስ ሲመለከቱት ቆዩ።

መቼም አይሮፕላን ሲባል ውስጡ የተለየ መሆን አለበት፣አሉ በሀሳባቸው። ለመሆኑ እዚያ ላይ ተሰቅሎ ቁልቁል ሲያዩት ባህሩ ምን ይመስል ይሆን? ርግጠኛ ነኝ በጣም ርቀት ታልመጠቁ የኔን ዓሣ በደንብ ሊያ ዩት ይችላሉ። በሁለት መቶ ፋቶም ርቀት ላይ ሆኜ በዝግታ እየበረርኩ ዓሣውን ቁልቁል ብመለከተው እን ዴት ደስ ይለኝ ነበር።

ምሽቱ ተጫጭኖ ለዓይን ከመያዙ በፊት እንደ ደሴት በተኰየሰ የሳርጋሶ አረም ቁልል አጠገብ አለፉ። የተቆለለው አረም በባህሩ ላይ ከፍ- ዝቅ፣ ወደፊት ወደኋላ እያለ ሲወዛወዝ ውቅያኖሱ ቢጫ የብርድልብስ

ተከናንቦ ከአንድ ነገር ጋር የማብሪ ሥጋ ግንኙነት
በመፈፀም ላይ ያለ ይመስላል:: ልክ በዚያን ሰዓት
ትንሷ ገመድ አንድ ዶልፊን ያዘች::

መጀመሪያ ያዩት ከውሀው ወጥቶ ወደ ላይ
ሲዘል ነበር:: ጉብጥ- ቀጥ -ጉብጥ እያለና ክንፉን
እያራገበ በንዴቱና በቁጣ ሲወራጭ በመጥለቅ ላይ ባለ
ችው ፀሐይ የመጨረሻ ብርሃን ተመለከቱት:: ሽማግ
ሌው ትልቁን ገመድ በቀኝ እጃቸው መዳፍና ክንድ
ላይ ጠምጥመው ያዙና በግራ እጃቸው ደግሞ ትንሿን
ገመድ ይዘው ዶልፊኑን ወደጀልባዋ መሣብ ጀመሩ::
ወደውስጥ የማስቡትን ገመድ ጀልባዋ ወለል ላይ ያሣ
ርፉና በሲባው የግራ እግራቸው ይቆሙበታል:: ዶል
ፊኑ የሞት ሞቱን እየተወራጨና ከወዲያ ወዲህ እየ
ተላጋ ወደጀልባዋ ጭራ ሲጠጋላቸው ሽማግሌው ቁል
ቁል ተጎንብሰው ወርቃማውን ዓሣ በመያዝ ወደላይ
ጎትተው አወጡት:: ሙቼም እልሁ ይህ ነው አይባ
ልም:: አፉ ውስጥ የተሰነቀረውን መንጠቆ እየደጋገመ
ይነክሰዋል::በረጅም አካሉ፣ በጭራውና በጭንቅላቱ የጀ
ልባዋን ወለል ይቀጠቅጠዋል:: ሽማግሌው ዱላቸውን
አንሱና አናቱን መነረት ጀመሩ:: በመጨረሻ አንድ ጊዜ
በኃይል ተንቀጠቀጠና ለዘለቄታው ፀጥ አለ::

ሽማግሌው መንጠቆውን ከዓሣው አላቀቁና ሌሎች
ሰርዲኖችን በላዩ ሰግስገው መልሰው ወደ ባህሩ ወረወ
ሩት::ከዚያ በኋላ በጥንቃቄ ወደ ቦታቸው ተመለሱ::
ግራ እጃቸውን በውሃ ታጥበው ሱሪያቸው ላይ አደራረ
ቁት:: ቀጠሉና ትልቁን ገመድ ወደ ግራ እጃቸው በማ
ዛወር ቀኙንም በባህሩ ውሃ አጠቡት:: እየታጠበ
ደግሞ ወደውቅያኖሱ በመጥለቅ ላይ ያለችውን ፀሐ
ይና ከጀልባዋ ፊት ለፊት ጋደድ ብሎ የተወጠረውን
ገመድ ይመለከቱ ጀመር::

በጭራሽ አልተለወጠም። ያው ነው። አለ።

ዶልፊኑን ትንሽ ቆይቶ መብላት ይሻላል፤ ደሙ ከረጋ በኋላ። አለያ በነንቱ ተፋሶ ያልቃል አለ በሀሳባቸው። ዓሣውንም ቢሆን በፀሐይ መጥለቂያ ሰዓት መረበሽ ተገቢ አይደለም። የፀሐይ መጥለቂያ ለዓሶች ሁሉ አስቸጋሪ ወቅት ነው።

ግን ኮ እስታሁን ምንም አልቀመሰም።መንጠቆው ላይ የነበሩትን ሰርዲኖች ከበላ በኋላ ምግብ የሚባል ነገር በአፉ አልዞረም።ደሞ ግዙፍ ስለሆነ ብዙ ምግብ ሳያስፈልገው ይቀራል?እኔ እንኳን ምንም አልል፤እንደ ሙሉ ቶና ከምኩማያለሁ። ለነገ ደግሞ ዶልፊኑ አለኝ።

«ታዲያስ ዓሣ እንዴት ነህ?ምን ይሰማሃል?» ጥያቄያቸው ያቀረቡት ጉላ ባለ ድምፅ ነበር። «እኔ ደህና ነኝ ግራ እጄንም ተሸሎኛል። ለአንድ ቀንና ሌሊት የሚሆን ምግብም አለኝ። በል አንተም ጀልባዋን በመጎተቱ በርታበት።»

እንደዕውነቱ ከሆነ ግን ያባባላቸውን ያህል ደህና አልነበሩም። በርግጥ በገመዱ የተነሣ ጀርባቸው ላይ ተፈጥሮ የነበረው የህመም ስሜት ድራሹ ጠፍቶ ቦታው ደንዝዟል። ግን ሁኔታውን አላመኑትም። ለነገሩማ ቱህ ቀደም ብዙ የባሱ ነገሮች እያጋጠሙኝ ሁሉንም አልፌያቸው የለ? አሉ በሀሳባቸው። አንደኛው እጄ ቢቆስልም እስከዚህም ለከፋ የሚሰጥ አይደለም። ተሸምቅቆ የነበረውም ተፍታቷል።ይመስገነው። እግሮቼ ደህና ናቸው። ዋናው ደግሞ የምግብ ጥያቄ ቢሆንም ከዓሣው ይልቅ እኔ እሻላለሁ። ለቀረበልኝ የምግብ ጥያቄ በቅርቡ ምላሽ ሰጥቻለሁ።

አሁን ምሽቱ በደንብ ጨልሟል:: ወትሮም በመስከረም ወር ይኸው ነው::ሀሐይዋ እንደጠለቀች ፈጥኖ ይጨላልማል::የጀልባዋ አፍንጫ የተሠራበትን በሰድሜ ብዛት ድቅቅ ያለና የተበላ እንጨት ደገፍ ብለው የሚችሉትን ያህል ሰረፍት አደረጉ:: የመጀመሪያዎቹ ከዋከብት ብቅ ብቅ ብለዋል:: ብዙም ሳይቆይ ሁሉም ይወጡና ሰማዩን ያንቆጠቁጡታል:: የሽማግሌው የሩቅ ወዳጆች ናቸው:: ለመሰባሰብ ረጅም ጊዜ እንደማይወስድባቸው እሳቸውም በደንብ ያውቁታል::

«ዓሣውም ኮ ጓደኛዬ ነው»አሉ ድምፃቸውን ጉላ አድርገው::«ግን እንዲህ ዓይነት ዓሣ ከተፈጠርኩ አይቼም አላውቅ:: በወሬ እንኳን አልሰማሁም:: ታዲያ ምን ያደርጋል እገድለዋለሁ:: ከዋክብቱን ለመግደል መሞከር የማያስፈልገን መሆኑ ግን በጣም ነው የሚያስደስተኝ::»

ለነገሩ ግን የሰው ልጅ ጨረቃን በየዕለቱ ለመግደል ቢሞክር ኖሮ ሁኔታው ምን ይመስል ነበር?አሉ በሀሳባቸው::ጨረቃዋ በርራ ትጠፋለች:: እሺ፣ ደግሞስ አንድ ሰው በየዕለቱ ፀሐይን ለመግደል ይሞክራል ብለን ብንገምት? ብቻ ዋናው ቁም ነገር ስንወለድ ዕድለኛ ሆነን መወለዳችን ነው አሉ በሀሳባቸው::

ከተያዘባት ቅዕበት አንስቶ አንዳችም ምግብ ላልቀመሰው ዓሣ ድንገት ሀዘን ተሰማቸው:: ግን ምንም ያህል ቢያዝኑለት እንደሚገድሉት ቁርጥ ነው:: ለመሆኑ ለስንት ሰው ይበቃ ይሆን?ደግሞስ እነማን ናቸው የሚመገቡት? እሱን ለመብላት ብቃት ይኖራቸው ይሆን? እንጃ:: ከጨዋነቱና ከብሩን የሚጠብቅ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ እሱን ለመብላት ብቁ የሚሆን አንድም ሰው የሚገኝ አይመስለኝም::

ለኔ ግን እነዚህ ነገሮች እምብዛም ግልፅ አይደ ሉም። ብቻ ሀሐይንም ሆነ ጨረቃዋንና ከዋክብቱን ለመግደል መቃጣት ተገቢ አለመሆኑ መልካም ነው። ባህሩ ላይ እየኖርን ዕውነተኛ ወንድሞቻችንን መግደሉ ብቻ ይበቃል።

ለማንኛውም አሁን ትንሽ ምግብ መቅመስ አለ ብኝ። ዶልፊኑ እንዳይበላሽ ልበልተውና ትንሽ ልቀ ማምስለት። ጉልበቱን ለማደስም ይበጀኛል። ከዚያ በኋላ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ጥሩ ዕረፍት ማድረግ።

በርግተው ግምት ሁለት ሰዓት ለሚሆን ጊዜ ደህና ዕረፍት አደረጉ። ወቅቱ ጨረቃዋ በጊዜ የም ትወጣበት አይደለም። ቃመሻለች።ስለዚህ ሰዓቱን የሚ ያሰሉበት ምንም መንገድ አልነበራቸውም። ዕረፍቱም ከቀድሞው ትግልና ድካማቸው ጋር ሲነፃፀር ካልሆነ በስተቀር ዕረፍት ሊባል የሚገባው ዓይነት አይደለም። ዓሣው የተያዘበት ገመድ ትከሻቸው ላይ እንደተጋደመ ነው።

በርግጥ ገመዱን በጣም ብወጥረው ሊቀለኝ በቻለ ነበር አሉ በሀሳባቸው። ግን አንድ ጊዜ በኃይል ከመነ ጨቀኝ ወዲያውኑ ይበጥሰዋል።

«ግን ኮ እስካሁን እንቅልፍ የሚሉ ባይንህ አልዞ ረም ሽሜ» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው። «ግማሽ ቀንና አንድ ሌሊት አልፈዋል። አሁን ደግሞ አንድ ሙሉ ቀን ተደገመ።አንተ ግን እንዳፈጠጥህ ነህ። ይል ቁንም አጅሬ በፀጥታ በመንዝ ላይ እስከሆነ ድረስ አንተ ጥቂት የምታሸልብበትን ሁኔታ መሻት ይኖር ብሀል።አለያ አዕምሮህም በደንብ አይሠራም። እንቅልፍ ከፉ ነው። አይምሮን ያደበዝዛል።»

አይምሮዬ እንኳ በደንብ እየሠራ ነው፣ አሉ በሀሳባቸው:: እንዲያውም ብሩህነቱ ልክ እንደወንድሞቼ እንደከዋክብቱ ነው:: ቢሆንም ዕንቅልፍ ያስፈልጋል:: ዕንቅልፍ ከፉ አይደለም:: እነሱስ ይተኙ የለ? ጨረቃና ፀሐይም ይተኛሉ:: ውቅያኖሱ ሳይቀር ይተኛል:: አንዳንዴ ማዕበል በማይናርባቸውና ሁሉም ነገር ፀጥ በሚልባቸው ቀናት ውቅያኖሱም ያንቀላፋል::

በርግጥ እንቅልፍ ባላገኝም የጀመርኩትን መቀጠል እንደማይሣነኝ አምናለሁ አሉ ለራሳቸው:: ግን አደገኛ ሊሆን ይችላል::

ዓሣውን ላለማነቃነቅ በጣም ተጠንቅቀው በእጆቻቸውና በጉልበቶቻቸው እየዳሁ ወደጀልባዋ ጅራት መራመድ ጀመሩ:: እሱንም ይሄኔ እንቅልፍ እያንገላጀጀው ይሆናል አሉ በሀሳባቸው:: በምንም ዓይነት እንቅልፍ ማግኘት የለበትም:: ነፍሱ እስክትወጣ ድረስ መጐተቱን መቀጠል አለበት::

ጀልባዋ ጭራ አካባቢ ሲደርሱ ወደኋላ በመጠምዘዝ ትከሻቸው ላይ የተጋደመውን ገመድ በግራ እጃቸው አጥብቀው ከያዙ በኋላ በቀኝ እጃቸው ጩቤያቸውን ከአፎቱ መዘዙት:: የከዋክብቱ ብርሀን ከመድመቁ ጀልባዋ ወለል ላይ የተዘረጋው ዶልፊን ቁልጭ ብሎ ታያቸው:: ጭንቅላቱን በጩቤያቸው ወጉና ሣብ አድርገው ወደርሳቸው አስጠጉት:: በአንድ እግራቸው ረግጠው ከወለሉ ጋር በማጣበቅ እታችኛው መንጋጋው ድረስ አንዴ አወራረዱት:: ጩቤያቸውን አስቀመጡና ሆድቃውን በቀኝ እጃቸው ማውጣት ጀመሩ:: ሁለት በራሪ አሣዎች ሆዱ ውስጥ ተጋድመዋል:: ደህና ስለነበሩ ሁለቱንም አውጥተው ዳር አስቀመጧቸው:: ሆድቃውን ወደ ባህሩ ወረወሩት:: ውሃው ላይ የቅባት ፊለግ ትቶ ወደታች ዘቀጠ:: በከዋክብቱ ብርሀን ወለል

ብሎ የሚታየውን የዶልፊኑን ቀዝቃዛ ጭንቅላት በአንድ እግራቸው ረግጠው ከአንደኛው ወገን ቆዳውን ገፈፉት:: ያን ሲጨርሱ ወደሌላው ገለበጡት:: ገፈው እንደጨረሱ ከአናት እስከ ጅራቱ በመሰንጠቅ ሁለት ቦታ ላይ ከፈሉት::

የሚፈልጓቸውን ብልቶች ከአወጡ በኋላ ቀሪውን ወደባህሩ ወረወሩት::በስሱ ያወጡትን ፊሌቶና ሁለቱን በራሪ ዓሣዎች በአንድነት ጠቀለሏቸው:: ጨቤያቸውን ወደ ሰገባው ከትተው በዝግታ ወደጀልባዋ አፍንጫ መመለስ ጀመሩ:: ትከሻቸው ላይ የተጋደመው ገመድ ጀርባቸውን በመጠኑ አጉብጦታል::

የዶልፊኑን ሥጋና ሁለቱን በራሪ ዓሣዎች እንጨቱ ላይ አንጠፉዋቸው - ጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ:: ገመዱን ትከሻቸው ላይ አስተካከሉና እንደገና በግራ እጃቸው አጥብቀው ያዙት:: ጉንበስ ብለው የጀልባዋን ጐን በመደገፍ በራሪ ዓሣዎቹን ውሃው ውስጥ አለቀለቋቸው::

«እየተዳከመ ይሆን ወይስ እረፍት እያደረገነው?» አሉ ሽማግሌው::«ለማንኛውም ሥጋዩን ልቀማምስና ትንሽ ዕረፍት ላድርግ:: ጥቂት ማሸለቡም ከፋ አይደለ::»

ከዋክብቱ ቁልቁል አፍጥጠው እያዩዋቸውና የምሽቱ ብርድ እንደለበቅ እየሸነቆጣቸው ከዶልፊኑ ፊሌቶዎች የአንዱን ግማሽ፣ከበራሪ ዓሣዎቹ ደግሞ አንደኛውን ተመገቡ::

«ዶልፊን የሚጣፍጠው ተጠብሶ ሲበላ ነውና ጿል» አሉ:: «ጥሬውን ግን ብላሽ አይደለምንዴ? ለወደፊቱ ግን ጨውና ሎሚ ሳልይዝ መውጣት አይለመደኝም::»

አንተል ቢኖረኝማ ቀኑን ሙሉ ከባህሩ ውሃ እየ ደነበቀሁ ጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ በማፍሰስ ሲደርቅ ጨዉ ለማግኘት በቻልኩ ነበር አሉ በሀሳባቸው፡፡ በር ግጥ ዶልፊኑን ያጠመድኩት ለኀይን ተያዘ በኋላ ነው፡፡ ቢሆንም ግን የዝግጅት ጉድለት መኖሩ አያጠያ ይቅም፡፡

በስተምስራቅ በኩል ሰማዩ ደመና እያሰበሰበ በመ ሄዱ የሚያውቋቸው ከዋክብት በሙሉ አንዳንድ እያሉ ከእይታቸው ተሰወሩ፡፡ ወደትልቅ የደመና ሸለቆ የሚያመሩ መሰላቸው፡፡ ንፋሱም ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሄደ፡፡

«በሶስትና አራት ቀናት ውስጥ መጥፎ አየር መምጣቱ አይቀርም» አሉ፡፡ «ዛሬ ሲሊትና ገገን ምንም አይልም፡፡ ስለዚህ አሁን ነው ትንሽ ማሸለብ ሽሜ፡፡ ዓሣው ፀጥ ብሎ በሚጓዝበት ሰዓት ነው እንድ-ሁለት ማውጣት»

ገመዱን በቀኝ እጃቸው ወጥረው ያዙና ጭናቸ ውን ወደዚያ በማስጠጋት ሙሉ ክብደታቸውን ጀልባዋ ጉን ላይ አሳረፉት፡፡ ቀጥለው ገመዱን በትከሻቸው ላይ በመጠኑም ወደታች ሸተት በማድረግ ግራ እጃቸ ውን ላዩ ላይ ጣል አድርገው አስደገፉት፡፡

እስከተወጠረ ድረስ ቀኝ እጄ ይይዘዋል አሉ በሀሳ ባቸው፡፡ እንቅልፍ ወስዶኝ ሣለ ቀኙ ዘና የሚል ከሆነ ደግሞ ገመዱ እየተፈተለከ ከቁጥጥሬ ማምለጥ ሲጀ ምር ግራው ሊቀሰቅሰኝ ይችላል፡፡ በርግጥ ለቀኝ እጄ ይከብደው ይሆናል፡፡ ግን ቅጣት የለመደ በመሆኑ ምንም አይልም፡፡ ሀያ ደቂቃ ወይም ግማሽ ሰዓት እን ኳን ብተኛ ይበቃኛል፡፡

ክብደታቸውን እንዳለ ቀኝ እጃቸው ላይ አሣር ፈው ወደፊት ዘመም በማለት ከርምት ብለው ተኙ:: ወዲያው እንቅልፍ ወሰዳቸው:: የተለያየ ህልም እያፈ ራረቁ ማየት ጀመሩ:: አንድ ጊዜ የዓሣ መንጋ፣ አንዴ የአፍሪካ አናብስት ይታዩዋቸዋል::ወዲያው ደግሞ ቤታ ቸው ውስጥ አልጋቸው ላይ ተጋድመው ራሳቸውን ያልማሉ:: ከሁሉም ከሁሉም በጣም ያስደሰቷቸው ግን በቢጫው የባህር ዳር አሸዋ ላይ ያዩዋቸው አንበሶች ነበሩ::

ጨረቃዋ ከወጣች ቆይታለች:: እሳቸው ግን እንቅ ልፋቸውን እየለጠጡ ነው:: ዓሣውም ቀጥ ብሎ ወደ ፊት መሣቡን ቀጥሏል:: ጀልባዋም ወደ ደመናው ዋሻ ስተት ብላ እየገባች ነው::

ድንገት የቀኝ መዳፋቸው ከፊታቸው ጋር ሲጋ ጭና ገመዱ ቀኝ እጃቸውን እንደ እሣት እየለበለበ ሲጐተት ተሰማቸውና ከእንቅልፋቸው ነቁ:: የግራ እጃ ቸው የት እንዳለ ፈጥነው ለማወቅ አልቻሉም:: በከፍ ተኛ ፍጥነት እየተፈተለከ ወደባህሩ በመንጐድ ላይ ያለውን ገመድ ጨምድደው ለመግታት ቢሞክሩም አልተሣካም::በመጨረሻ በግራ እጃቸው እንቅ አድርገው ያዙት:: ኃይል ለመጨመር እንዲረዳቸው የኋሊት ተለ ጠጡና ገመዱ ላይ ተጋደሙበት:: ትከሻቸውን ሞሽላ ልቆ ግራ እጃቸውን ክፉኛ ቆረጠው:: ዞር ብለው የተ ጠቀለሉትን ገመዶች ተመለከቷቸው:: እየተተረተሩ ናቸው::

ልክ በዚያን ሰዓት ዓሣው የባህሩን ውሃ ግራና ቀኝ ገመሰና ወደላይ ዘሎ ወጣ:: ብዙም ሳይቆይ ተመ ልሶ ውሃው ላይ በኃይል ወደቀ:: ግን በዚያው አልቀ ረም:: ደጋግሞ ወደላይ ዘለለ:: ጀልባዋ በፍጥነት እየተ ጓዘች ነው:: ገመዱም ከተጠቀለለበት እየተተረተረ ወደ

ውሃው መውዘግዘጉን ቀጥሏል።ሽማግሌው ደግሞ ወደ ርሣቸው ጉትተው ለመመለስ ይታገላሉ። የሚበጠስ እስኪመስል ድረስ ገመዱ ተወጥሯል።ሽማግሌው ሚዛ ናቸውን ለመጠበቅና ገመዱን ወደውሃው በሙሣብ ላይ ያለውን ብርቱ ኃይል ለመቋቋም እንዲረዳቸው ወደ ፊት ዘመም ብለው ጀልባዋ አፍንጫ ላይ ተደፍተ ዋል። ፊታቸው የዶልፊኑን ፌሌቶ ተንተርሷል።

እስካሁን ስንጠብቅ የቆየነው ይህንኑ አልነበር? እን ግዲህ መቻል ነው።

ዓሣው ከባህሩ እመር እያለ ሲወጣ አይታያቸ ውም። ብቻ ውሀውን በርግዶ ወደላይ ከዘለለ በኋላ ተመልሶ በኃይል ሲፈጠፈጥ የሚፈጠረው መንቦራጨቅ ይሰማቸዋል። በእጆቻቸው መሀል እየተንሸራተተ ወደ ባህሩ የሚውዘገዘገው ገመድ መዳፎቻቸውን እየገሸለ ጠው ነው። ግን ይህን መሣዩ ነገር እንደሚደርስባ ቸው አስቀድመው ስለሚያውቁት ጉዳቱ ከገበሩት የመ ዳፎቻቸው ክፍሎች አልፎ ለጣቶቻቸውም እንዳይተርፍ መከላከል ያዙ።

ወይ ነዶ፣ ይህኔ ልጁ አብሮኝ ቢሆን ኖሮ የተጠ ቀለለውን ገመድ በውሃ ያርስልኝ ነበር አሉ በሀሳባ ቸው። ልጁ አብሮኝ በነበረ . . .

ገመዱ ወደባህሩ መፈትለኩን ቀጥሏል። መው ጣት፣መውጣት፣ አሁንም መውጣት። ፍጥነቱ ግን እየ ቀነሰ ነው።እሣቸውም ዓሣው የፈለገውን ያህል ገመድ እንዲያገኝ ለቀቅ እያደረጉለት ነው።ራሳቸውን ከጀልባዋ እንጨትና በጉንጫቸው ከጨፈለቁት ፊሌቶ ላይ በመ ጠኑ ቀና አደረጉት። ቀጥለውም በጉልበታቸው በርከክ አሉና ቀስ ብለው በሁለቱ እግሮቻቸው ቆሙ። አንድ አንድ እያሉ ገመዱን በዝግታ ለቀቅ ያደርጉታል። ረጋ

ብለው ከጥንቃቄ ጋር ወደ ኋላቸው በመመለስ የማይ ታዩዋቸውን ጥቅል ገመዶች በእግራቸው መዳበስ ጀመሩ:: ገና ብዙ ገመድ ይቀራቸዋል::

አዎ፣አሉ ሽማግሌው በሀሳባቸው::አጅሬ ከአሥር ጊዜ በላይ ከውሀው ወጥቶ በመዝለሉ በጀርባው በኩል ያሉት ከረጢቶቹ በአየር ስለሚሞሉ ከእንግዲህ በኋላ ወደ ውስጥ በጣም ጠልቆ ሊገባ አይችልም:: ቢሞትም እንኳ ጉትቼ ለማውጣት አዳጋች ወደሚሆንብኝ ጥል ቀት ሊወርድ አይቻለውም:: እንዲያውም ብዙ ሳይቆይ ዑደት ማድረግ ይጀምራል:: እኔም የምሠራለት ያኔ ነው:: መሆኑን ግን እንዲያ ድንገት አስደንብሮ ያስዘለ ሰው ነገር ምን ይሆን?እንዲያው እንዲያ የተወራጨው ምን ቢገጥመው ይሆን?ምናልባት ረሀብ? ወይስ አንዳች አስደንጋጭ ነገር?ምን ይታወቃል:: በምሽቱ ድቅድቅ ጨለማ ፍርሀት ተሰምቶትም ይሆናል:: እስካሁን እንደ ታዘብኩት ግን ረጋ ያለና ጠንካራ ዓሣ ይመስላል:: ፍርሀት ብሎ ነገር የማያውቅ፣ በራሱ የሚተማመን ቢጤ ነው:: ያሁኑ ታዲያ ለየት ያለ ነው::

«የሱን ትተህ የራስክን ድፍረትና እምነት ብታ ጠንክር ይሻልሀል ሽሜ» አሉ ራሳቸው:: «ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዑደት ማድረግ ይጀምራል::»

ሽማግሌው ገመዱን በግራ እጃቸውና በትከሻዎቻ ቸው ውጥር አድርገው ያዙና ጉንበስ ብለው በቀኝ እጃቸው የባሀሩን ውሀ በመጭለፍ ፊታቸው ላይ የተ መረገውን የተጨፈላለቀ የዶልፊን ሥጋ አጠቡት:: አቅለሽልሾ እንዳያስታውካቸውና ጉልበታቸው እንዳይ ቀንስ ሥጋት አድሮባቸው ነበር:: ፊታቸውን ካፀዱ በኋላ ቀኝ እጃቸውን በጀልባዋ ጐን በኩል ወደባሀሩ ሰደው አጠቡት:: ቶሎ ግን አላወጡትም:: እዚያው ጨውማው ውሀ ውስጥ ዘፍዝፈው አቆዩት:: ቀና

ብለው ሲመለከቱ ከሀሊዩዋ ቀድሞ የሚወጣውን የቅድመ ጉሕ ፊዛዛ ብርሀን ተመለከቱ። አጅሬ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ እየደላው ነው አሉ በሀሳባቸው። ይህ የሚያመለክተው እንደደከመውና ባህሩ በንፋስ ግፊት የሚንቀሳቀስበትን አቅጣጫ ተከትሎ በመንዝ ላይ መሆኑን ነው። ስለዚህ በቅርቡ ዑደት ማድረጉን መጀመር ይኖርበታል። ያን ጊዜ እውነተኛው ሥራችን ይጀምራል።

ቀኝ እጃቸው የሚበቃውን ያህል በውሃው ውስጥ ተዘፍዝፎ መቆየቱን ከገመቱ በኋላ አውጥተው እያገላበጡ አስተዋሉት።

«ለከፋ አይሰጥም» አሉ። «ለወንድ ልጅ ደግሞ ሥቃይ ምንድነው?»

ገመዱን በጥንቃቄ ወደቀኝ እጃቸው አዛወሩና በተራው ግራ እጃቸውን ውሃው ውስጥ ነከሩት።

«ምንም እንኳን ጉዳዩ እስተዚህም ርባና ያለው ባይሆንም የፈፀምከው ተግባር መልካም ነው»አሉ ግራ እጃቸውን።«ግን ተቸግሬ ሳለሁ ልትጠቅመኝ ያልቻልክ በትም ጊዜ ነበር።»

ግን ለምንድነው ከሁለት ጥሩ ጥሩ እጆች ጋር ያልተወለድሁት? አሉ በሀሳባቸው።ምናልባት ግራዬን በሚገባ አለማሠልጠኔ ጥፋቱ የኔው ሊሆን ይችላል። ግን እሱም ራሱ ለመማር ብቁና ዝግጁ መሆኑን የሚያውቀው እግዜር ብቻ ነው።ቢሆንም ሌሊት የፈፀመው ተግባር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የተሸመቀቀውም አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከአሁን በኋላ ድጋሚ እሸመቀቃለሁ ካለ ግን የራሱ ጉዳይ!ገመዱ ጉምዶ ይጣለው። ቁብ የለኝም።

አዘጋጅተው ያስቀመጡትን በራሪ ዓሣ በግራ እጃ
ቸው እነሡና መብላት ጀመሩ፡፡ አጥንቱን ሣይቀር
በጥንቃቄ እያላመጡ እስከጭራው ድረስ ሙልጭ አድ
ርገው በሉት፡፡

በምግብነት የሚሰጠው ጥቅም ከየትኛውም ዓሣ
ይበልጣል አሉ በሀሳባቸው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ለዚህ
ቀውጢ ጊዜ የሚያስፈልገኝን ብርታትና ጥንካሬ ይሰ
ጠኛል፡፡

ወደባህር ከወጡ ጀምሮ ለሶስተኛ ጊዜ ፀሐይዋ
ብቅ አለች፡፡ ዓሣውም በጀልባዋ ዙሪያ ዑደት ማድረግ
ጀመረ፡፡

ተወጥሮ የቆየው ገመድ በመጠኑ ረገብ ሲል ተሰ
ማቸው፡፡ በቀኝ እጃቸው ዝግ ብለው ሲስቡት እንደገና
መወጠር ጀመረ፡፡ ከርር ብሎ ከተወጠረ በኋላ ተመ
ልሶ መርገብ ሲጀምር ትከሻቸውንና ራሳቸውን ከገመዱ
አላቀቁና ወደርሣቸው መሣብ ቀጠሉ፡፡ ባለጉልበታ
ቸው በመጠቀም በሁለት እጆቻቸው እያፈራረቁ ሣብ-
ጐተት፣ ሣብ- ጐተት ማድረግ ያዙ፡፡

ትንሽ እንደሣቡ ገመዱ ወደውስጥ መምጣቱን
አቆመ፡፡ደጋግመው ሞከሩ፡፡ንቅንቅ የለም፡፡ እንደ በፊቱ
ከርር ብሎ በመወጠሩ ወደጀልባዋ በሣቡት ቁጥር ጤዛ
የመሣሰሉ የውሃ ጠብታዎች ከላዩ ሲፈናጠቁ በፀሐይዋ
ብርሀን ታያቸው፡፡ ትንሽ ቆይቶ ገመዱ እንደገና ወደ
ውሃው መጐተት ጀመረ፡፡ ሽማግሌውም ጥቂት በጥ
ቂት ለቀቅ ለማድረግ እንዲያመቻቸው ጀልባዋ ወለል
ላይ በርከክ አሉ፡፡

«እህ የሚዞርበትን ክብ መስመር እያሰፋው ነው»
አሉ፡፡ ስለዚህ የምችለውን ያህል ወጥሬ መያዝ ይኖር

ብኛል ሲሉ አሰቡ። ወጥሬ በያዝኩት መጠን የማዞርበትን መስመር ስፋት እያጠበበው ይሄዳል። ምናልባትም በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ዓይን ለዓይን እንተያይ ይሆናል። ከዚያ በኋላ በህይወቱ ላይ እጨክንበታለሁ።

ዓሣው ግን በዝግታ ዑደት ማድረጉን እንደቀጠለ የሁለት ሰዓት ጊዜ አለፈ። ሽማግሌው በላብ ተዘፍቀውና እስካጥንታቸው ዘልቆ በሚሰማ ድካም ተብረከርከው ገመዱን ወጥረው እንደያዙ ጅብራ መስለው ተገትረዋል። ዓሣው ዑደት የሚያደርግበት መስመር ግን ልክ እንደገመቱት እየጠበበ መሄዱ አልቀረም። ከዚያም ሌላ ወደ ላይ ከፍ እያለ በመምጣት ላይ መሆኑንም ከገመዱ አቀማመጥ ማጤን አልተሣናቸውም። ከሽማግሌው ግንባር የሚፈልቀው ላብ ቁልቁል እየተንገርቀገርቀ ወደ ዓይናቸውና ከዓይናቸው ከፍ ብሎ ወዳለው ቁስል እየገባ ይቆጠቁጣቸው ጀመር። አንድ ሁለቴ ያህል እንደማዞር ከጅሎዋቸው ስለነበር ትንሽ ሳያሰጋቸው አልቀረም። ከድካም የተነሣ ጥቋቁር ነጥቦች ዓይኖቻቸው ላይ ይታዩዋቸው ጀመር።

«የመጣው ይምጣ ይህን መሣይ ዓሣ ከያዝኩ በኋላ ተረትቼ መሞት የለብኝም»አሉ ጎላ ባለ ድምፅ። «ያውም አሁን እንዲህ እያማረበት፣ ወደላይ እየመጣልኝማ ይሙት እጄን ልስጥ? ብቻ አንተ ሁሉ የማይሣንህ ጌታ ብርታቱን ስጠኝ። ባይሆን እንኳን አባታችን ሆይን አንድ መቶ ጊዜ፣ ሠላም ለኪን መቶ ጊዜ እደግማለሁ። አሁን ግን ሁለቱንም ለማለት አልችልም።»

ስለዚህ አምላኬ አንተ ልክ እንዳልኳቸው ቆጥረህ እርዳኝ አሉ በሀሳባቸው። በኋላ ግን፣ እመነኝ፣ በደንብ እነበንባቸዋለሁ።

ልክ ይህንን እንዳሉ በሁለት እጃቸው ጥርቅም አድርገረው የያዙት ገመድ በድንገት ሲናጋና ሲነቃነቅ ተሰማቸው:: ንቅናቄው ያስከተለው ንዝረት ከባድና ጠንካራ ዓይነት ነበር::

በገመዱና በመንጠቆው መካከል ያለውን ሽቦ አፉ ላይ በተገተረው መንቆር ሲደበድበው መሆን አለበት አሉ በሀሳባቸው:: ምናልባት ወደላይ ዘሎ ለመውጣት ይረዳው ይሆናል:: እኔ ግን ባለበት ሆኖ ዑደቱን ቢቀጥል ነው የምመርጠው:: አየር ለማግኘት ሲል እየዘለለ በወጣ ቁጥር መንጠቆው የተሰነቀረበትን ቀዳዳ እያሰፋው ይሄድና በመጨረሻ መንጠቆው አፈትልኮ ሊወጣለት ይችላል:: ይህ ከሆነ ደሞ አመሰጠ ማለት ነው::

«ዓሣ! ይህንን መዝለልህን ተወኝ» አሉ:: «አትዝለል ብየሀለሁ::»

ዓሣው ግን በገመዱና በመንጠቆው መካከል ያለውን ካቦ መደብደቡን ቀጠለ:: እሱ ይህንን ባደረገ መጠን ሽማግሌው ደግሞ ከገመዱ ጥቂት ለቀቅ፣ ጥቂት ለቀቅ ያደርጉለታል::

ሥቃዩ እንዳይጠናበት ባለበት ባቆየው ይሻላል አሉ በሀሳባቸው:: የኔውን መቼም እንደምንም እችለዋለሁ:: የእርሱ ግን እያየለበት በሄደ መጠን አንድያውን ዕብድ መሆኑ ነው::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዓሣው ሽቦውን መደብደቡን አቆመና እንደገና ዝግ እያለ ዑደት ማድረጉን ጀመረ:: ሽማግሌውም ቀስ በቀስ ገመዱን ወደውስጥ መሣብ ጀመሩ:: አካላቸው በጣም በመድከሙ ራሳቸውን የመሣት ስሜት አልፎ አልፎ ሲፈታተናቸው ይሰማቸ

ዋል:: በግራ እጃቸው የባህሩን ውሃ ዘገኑና ጭንቅላታቸው ላይ አፈሰሱት:: ትንሽ ቀዝቀዝ ሲሉ ማጅራታቸውን አባበሱና አደራረቁት::

«አሁን ሁለቱም እጆቼ ደህና ናቸው:: አንዳቸውም አልተሸመቀቁ» አሉ ድምፃቸውን ጐላ አድርገው:: «አጅሬም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ብቅ ማለቱ አይቀርም:: እስተዚያው እኔም ላለመረታት እታገላለሁ:: ሽሚ እንግዲህ በርትተህ መቋቋም ነው:: በቀላሉ እንዳትፈታ» አሉ::

ተንበርክከው የጀልባዋን አፍንጫ በመደገፍ ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ገመዱን ጀርባቸው ላይ አጋደሙት:: አሁን እንግዲህ አሉ በሀሳባቸው፣ ከብ መስመሩን ይዞ ዑደት ሲያደርግ እኔ ትንሽ ማረፍ ይኖርብኛል:: ኋላ ብቅ ሲል እኔም በትኩስ ጉልበት እሠራለታለሁ በማለት ወሰኑ::

በርግጥም በዚያን ሰዓት ጀልባዋን ደገፍ ብሎ ዕረፍት ማድረግ በጣም የሚያጓጓ ነበር:: ግን ሽማግሌው እንዳሉት ሊሆንላቸው አልቻለም:: ተወጥሮ የነበረው ገመድ በመርገቡ ዓሣው ተመልሶ እየመጣ መሆኑን በመረዳት ከቅምጣቸው ብድግ ብለው ገመዱን ወደ ውስጥ መሣብ ጀመሩ::

እንዲህ ዓይነት ድካም ደርሶብኝም አያውቅ አሉ በሀሳባቸው:: ደግነቱ ግን ከደቡብና ከሰሜን ምሥራቅ የሚነፍሰው ንፋስ እየመጣ ነው:: አጅሬን ወደ ጀልባዋ ጉትቼ ለማስጠጋት ይረዳኛል::

የሰሌን ባርኔጣቸው ወደማጅራታቸው ዝቅ ብሎ ጭንቅላታቸው ጀርባ ላይ ቂብ ብሏል:: ለሰስ ብሎ በሚነፍሰው ንፋስ ምክንያት የባህሩ ውሀ ወደ ላይ ከፍ እያለ ነው:: ለመልስ ጉዞ ይመቻል::

«ጀልባዋ በቀጥታ ወደደቡብ ምዕራብ እንድታመራ አደርጋታለሁ» አለ:: «ምንም ቢሆን የሰው ልጅ ባህር ላይ እያለ አቅጣጫውን ስቶ ይጠፋል ማለት ዘበት ነው:: ደሴታችን ደግሞ በጣም ረጅም ስለሆነች ችግር አይኖርም::»

ዓሣው ዑደቱን ቀጥሏል:: ሶስት ዙር እንዳገባደደ ሽማግሌው ዓሣውን አዩት::

መጀመሪያ በጀልባዋ ሥር እየተጉተተ የሚያልፍ የአንዳች ነገር ጥላ መስሏቸው ነበር:: በውሃው ውስጥ እየተውዘገዘገ ለማለፍ ረጅም ጊዜ የፈጀው ያ ግዙፍ ጥላ የዓሣው ነው ብለው በጭራሽ አልገመቱም::

«አይደረግም» አሉ በሀሳባቸው:: «ምንም ቢሆን ይህንን ያህል ሊተልቅ አይችልም::»

ዓሣው ግን የጥላውን ያህል ትልቅ ነበር:: ሶስተኛ ዙር ዑደቱን እንደፈፀመ ከጀልባዋ ሠላሣ ያርድ[1] ያህል ራቅ ብሎ ከውሃው ብቅ አለ::ጅራቱን ከውሀው ወጥቶ ሲያዩት ሽማግሌው ዓይናቸውን ማመን አልቻሉም:: የጅራቱ ቁመት ከትልቁ የፈረንጅ ማጭድ ይበልጣል:: ዓይናቸውንም አዩዋቸው::

ሽማግሊው ላብ በላብ ሆኑ:: ሰበቡ ግን የፀሐዩሙቀት ብቻ አልነበረም:: ዓሣው ረጋ ብሎ አንድ ዙር ባጠናቀቀ ቁጥር ሽማግሌው ይበልጥ ወደ ውስጥ ይስቡታል:: በዚህ ዓይነት ከቀጠለ ከአንድና ሁለት ዙር በኋላ ሀርፑኑን ሊስቡበት ይችላሉ::

---

[1] ያርድ:-የርዝመት መለኪያ ነው አንድ ሜትር 1.094 ያርድ ይሆናል:: በዚህ መሠረት 30 ያርድ ሲባል 27.4 ሜትር ይሆናል ማለት ነው::

በመጀመሪያ ግን በደንብ መቅረብ፣መቅረብ፣ መቅረብ አለበት አለ በሀሳባቸው። ዲላማየም ልቡ እንጂ ጭንቅላቱ አይሆንም።

«ለማንኛውም ረጋ በል ሽሜ። አደብ ገዝተህ ጉል በትህን ተንከባከብ» አለ።

ተከታዩን ዑደት እንደጀመረ የዓሣው ጀርባ ሙሉ በሙሉ ከውሃው ወጣ። አሁን ግን ከጀልባዋ ጥቂት ራቅ ብሏል። ሌላ ዑደት ቀጠለ።ይህኔ ከበፊቱ ይበልጥ ከፍ ብሎ መታየት ጀመረ። ርቀቱ ግን ጨምሯል። ሽማግሌውም ገመዱን በመጠኑ ሣብ በማድረግ ብቻ ወደጀልባዋ ሊያስጠጉት እንደሚችሉ ርግጠኛ እየሆኑ ነው።

ሀርፑናቸውን ካዘጋጁት ቆይተዋል። ከእጀታው ጋር ተያይዞ ቅርጫት ውስጥ የተቀመጠው ጥቅል ገመድ ጫፍ ጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ ባለ ማበቻ ላይ ታስሯል።

ዓሣው ክብ መስመሩን ይዞ እየዋኘ ወደጀልባዋ መጠጋት ጀምሯል። ፀጥ ያለና ውብ ነው። ትልቁ ጅራቱ ያለማቋረጥ ይወዛወዛል። ሽማግሌው ገመዱን ወደርሣቸው ሣብ አደረጉት። ትልቁ ዓሣ ላንዳፍታ ወዳንድ ጐኑ በመጠኑ ዘንበል አለና እንደገና አቋሙን በማስተካከል ዑደቱን ቀጠለ።

«አንቀሣቀስኩትኮ» አሉ ሽማግሌው። «አንቀሣቀስኩት»

እንደቀድሞው ራሳቸውን የመሣት ዓይነት ስሜት ዳር ዳር ይበላቸው እንጂ ዓሣቸውን ግን ወጥረው እንደያዙ ናቸው። ምንም ቢሆን እንደ. እነቃንቁዋለሁ

አሉ በሀሳባቸው። ምናልባትም ጉትቼ ላስጠጋው ይሳካ ልኝ ይሆናል። እጆች በርቱ እንግዲህ በርቱ፣ ጉትቱ፣ ሣቡ አሉ በሀሳባቸው። እግሮች፣ እናንተም አይዟችሁ፣ ያዙ። አንጉል!ዋ ዛሬ ትረታና። ዳር ሳትደርስ እንዳት በገር አደራ።አልቆለታል። አሁን አስጠጋዋለሁ። ጉትቼ አመጣዋለሁ።

አቅማቸው በፈቀደ መጠን መሣብ ጀመሩ።ዓሣው ግን ቅም ያለውም አልመሠለ። መስመሩን ይዞ በፀጥታ ይዋኛል።

«ዓሣ» አሉ ሽማግሌው «ምንም ይሁን ምን መሞትህ እንደማይቀር እንድታውቀው። ወይስ እኔም አብሬህ መሞት ይኖርብኛል»

በድጋሚ ሞከሩ። ሊሣካላቸው ሲል ለጥቂት ከሸፈ ባቸው። ዓሣው እንደገና መስመሩን ይዞ እየዋኘ ሄደ።

እየገደልከኝኮ ነው ዓሣ አሉ ሽማግሌው በሀሳባ ቸው።ግን ይገባሀል። መብትህም ነው። እውነቱን ልን ገርህና እስከዛሬ ከአንተ የበለጠ ግዙፍና ጨዋ፣ ካንተ በላይ ረጋ ያለና ውብ ፍጡር አይቼ አላውቅም ወንድ ምየ። ከፈለግህ ናና ግደለኝ። ማንም ማንን ቢገድል እኔ እንደሁ ቁብ የለኝም።

ሁለተኛ አከታትለው ሞከሩ። ውጤቱ ግን እንደ በፊቱ ነበር።

ምንድነው ነገሩ? አሉ በሀሳባቸው። ሞከረው በከሸ ፈባቸው ቁጥር ትተው የመሄድ ፍላጎት ይተናነቃቸ ዋል።ግን ወዲያው መለስ ይላሉ። ነገሩ ሊገባኝ አልቻ ለም። ቢሆንም እንደገና እሞክራለሁ።

ድጋሚ ሞከሩ:: አልተሣካም:: አየር ውስጥ እንደ አምድ የተገተረ ጅራቱን እያማታ በዝግታ ዋኝቶ ሄደ::

እንደገና እሞክራለሁ ሲሉ ለራሳቸው ቃል ገቡ-ሽማግሌው::

ሞከሩ:: ግን ውጤቱ ያው ነበር:: እንደገና አንድ ጊዜ እሞክራለሁ አሉ አሁንም::

ቀረኝ የሚሉትን ኃይልና ጉልበት እንዲሁም ከብዙ ጊዜ በፊት ትተውት የሄደ ኩራታቸውን አንድ ላይ አሰባሰቡና ዓሣውን መጕተት ጀመሩ:: ዓሣው የጐድን መዋኘት ጀመረ:: ወደጀልባዋም እየተጠጋ መጣ:: አፉ የጀልባዋን እንጨት የሚነካ እስኪመስል ድረስ ቀረብ ብሎ መዋኘት ጀመረ:: ረጅምና ሰፊ ነው:: ቀለሙ ደሞ የብርና የሀምራዊ ህብር:: ሄዶ ሄዶ የማያልቅ በሚመስል ሁኔታ በውሀው ውስጥ ይርመሠመሣል::

ሽማግሌው ገመዱን ወለሉ ላይ ወረወሩና በእግራቸው ረግጠው ያዙት:: ወዲያው ሀርፑናቸውን አንስተው የሚቻላቸውን ያህል ከአናታቸው በላይ ከፍ አድርገው ሰቀሉት:: እንዲያ ሆነው ብዙም አልቆዩ:: የበሉ የጠጡትን ያህል ቁልቁል እንደዘነዘና በማውረድ ዓሣው ጐን ላይ ቀበቀቡት:: አልበቃቸውም:: ፋታ ሳይሰጡት ደገሙት:: ሀርፑኑ ስተት ብሎ መግባቱ ሲሰማቸው ይበልጥ ዘልቆ እንዲሰምጥ እጀታውን ተደግፈው ቁልቁል ተጫኑት:: ስምጥ ብሎ ገባ::

ይህኔ ገና ነፍሱ ያልወጣችው ዓሣ ሞቱን በጐኑና በጀርባው እንደተሸከመ ከውሃው ብቅ አለ:: የቁመቱን ርዝማኔና የአካሉን ግዝፈት፣ልክ የሌለው ጉልበቱንና ወደር የለሽ ውበቱን እያስመረቀ ወደ ሰማይ እመር

አለ:: ጀልባዋ ውስጥ ባሉት ሽማግሌ አናት ላይ እንዳ ረበበ አየሩ ውስጥ ተንጠልጥሎ የሚቆይ ነበር የሚመ ስለው::ግን ወዲያው ተዘለፈለፈና ውሃው ውስጥ ዘፍ ብሎ ወደቀ::የፈነጠቀው ውሃ ሽማግሌውንና ጀልባዋን አለበሳቸው::

· ሽማግሌውን የህመም ስሜት ተጠናወታቸው:: ልባቸው ፍስስ ብሎ እንደማዞርም አላቸው:: ዓይናቸ ውም አጥርቶ ለማየት ተሳነው:: ግን እንደምንም ብለው ከጦሩ ጋር የተያያዘውን ገመድ ከተበተበበት ጉጥ ነገር ላይ ፈትተው በማስረዘም በእጆቻቸው መሀል ቀስ እያለ እየተንሸራተተ ዓሣውንና ጦሩን ተከ ትሎ ወደውሃው እንዲወርድ ለቀቁት:: ዓሣው በጀር ባው ተገልብጦ ብርማ ቀለም ያለው ሆዱ ወደ ሰማይ ተሰጥቶ አዩት:: ሀርፑኑ በትከሻው በኩል ወደ ላይ ተካትሯል:: የባህሩ ውሀ ከዓሣው ልብ በሚፈልቀው ቀይ ደም እየቀለመ ነው:: መጀመሪያ ጠቁሮ ሲታይ አንድ ማይል ጥልቀት ባለው ሰማያዊ ውሀ ውስጥ እጅብ ብለው የሚዋኙ ትንንሽ ዓሣዎች ይመስል ነበር:: እየቆየ ግን እንደደመና ተበታተነ:: ብርማው ዓሣ ፀጥ ብሎ ከማዕበሉ ጋር እየተወዛወዘ ይንሣፈ ፉል::

«አንጉል፣ አደራህን:: በደንብ ሥራ» አሉ የጀል ባዋ አፍንጫ የተሠራበትን እንጨት ደገፍ እያሉ:: «ደካማ ሽማግሌ ነኝ::ግን እኮ ወንድሜን ገድየዋለሁ:: አሁን እንግዲህ ቀሪውን የገባር ሥራ እናከናውናለን::»

በመጀመሪያ ዓሣውን ከጀልባዋ ጋር ጥፍር አድ ርጌ የማሥርበት ገመድ ማዘጋጀት አለብኝ አሉ በሀሳባቸው:: ከዚህ ሌላ ይህንን የገደል ቅራፊ የሚያ ህል ጉድ ወደ ደሴቷ የማደርስበት ምንም ብልሀት አይኖርም:: ጀልባዋ ትችለዋለች ማለት መቼም ዘበት

ነው።ያለው አማራጭ ከጉኗ ጋር መጠፈር ብቻ ነው። ከያ በኋላ ተራዳውን አቁምና የንፋስ ሽራዬን ወጥሬ ወደቤቱ መሽምጠጥ ነው።

የዓሣውን ራሣ ወደጀልባዋ መሣብ ጀመሩ። የሚፈልጉትን ያህል ካስጠጉ በኋላ በሚተነፍስበት ስንጥብ በኩል ገመድ አስገብተው በአፉ አሾልከው በማውጣት ጭንቅላቱን ከጀልባዋ አፍንጫ ጋር ግጥም አድርገው ማሠር ይችላሉ። ባየው ግን ምንኛ ደስ ባለኝ አሉ በሀሳባቸው።እንዲያውም ልዳስሰውና ልነካካው ብችል እን ደምን ጥሩ ነበር። ፎርቱናየኮ ነው። ገጹ ነው። ግን ያኔ የገደልኩት ጊዜ የዳሰስኩት ይመስለኛል። እንዲያ ውም የነካሁት ልቡን ነበር። የሀርፑኑን እጀታ ቁል ቁል ተጭኜ ገላውን በሃይል ስጠረምሰው ያንየ ልቡን የነካሁት ይመስለኛል። ለማንኛውም እንደ የሆነው ሆኗል። አሁን የሚቀረው በደንብ ሲጠጋ አንዱን ሽም ቀቆ ወገቡ ላይ፣ ሌላውን ደግሞ በጭራው ዙሪያ አስ ገብቶ ከጀልባዋ ጋር ጥፍንግ አድርጎ ማሠር ብቻ ነው።

«በል እንግዲህ ስራህን ቀጥል ሽሜ» አሉ ለራሳቸው። ጥግ አስቀምጠውት ከነበረው ውሀ በጥቂቱ ተጉነጩ። «ፍልሚያው ካለቀ ዘንዳ የጉልበቱ ሥራ መቀጠል ይኖርበታል።»

ቀና ብለው ሰማዩን ተመለከቱና ዓይኖቻቸውን ወደ ዓሣው መለሷቸው። ፀሐይዋን በጥንቃቄ አስተዋሉዋት። ግፋ ቢል ቀትር ቢሆን ነው አሉ በሀሳባቸው። ከደቡብና ሰሜን ምሥራቅ ወደ ምድር ወገብ የሚጋልበው ሃይለኛ ንፋስ እየመጣ ነው። ገመዶቹም ከጥቅም ውጪ ሆነዋል። ምናባቱ በሰላም ወደቤቴ ይመልሰኝ እንጂ ከልጁ ጋር እንደገና እንገምዳቸዋለን።

«በል እንግዲህ ዓሣ፣ ወዲህ ጠጋ በል» አለ። ዓሣው ግን ጥሪውን የተቀበለ አይመስልም። ባህሩ ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይንከባለላል። ሽማግሌው ጀልባ ዋን ወደሱ አስጠጋት።

የጀልባዋን አፍንጫ ወደጭንቅላቱ በማስጠጋት ላይ እያሉ እንኳን ግዙፍነቱን ለማመን አልቻሉም። ከሀርፑኑ ጋር ተያይዞ የነበረውን ገመድ ከታሰረበት ላይ ፈቱና ጫፉን በአንደኛው የዓሣ ጉን በማገኘው ስንጥብ በኩል አስገብተው በጥርሶቹ መሀል በማሾለክ እንደሠይፍ በተገተረው አፉ ላይ ሁለቱ አዙረው ጠመ ጠሙት። ቀጥለውም በሌላው ጉኑ ባለው ስንጥብ በኩል ገመዱን በማስገባት መንቁሩ ላይ ደግመው ከጠ መጠሙት በኋላ አጥብቀው ቋጠሩት። መለሱና የገመ ዱን ጫፍ ጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ ባለው ጉጥ ላይ እንደገና አሰሩት።ተራፊውን ገመድ ቆርጠው ጭራውን ለማሠር ወደጀልባዋ የኋላ ክፍል አመሩ። ዓሣው የሀምራዊና የብር ሀብር የሆነ ቱባ ቀለሙን እየቀየረ ሙሉ በሙሉ ብርማ መሆን ጀምሯል። ጅራቱ አካባቢ ያሉት ሸንትሮች ግን የወትሮ ቀለማቸውን እንደያዙ ናቸው - ሀምራዊ የወይን ጠጅ። እያንዳንዱ ሸንትር በደንብ ከተዘረጋ የሰው መዳፍ ይሰፋል።አይኖቹ እንደ መነጽር ቂዛዛ ፈጠዋል።

«እሱን ለመግደል የሚቻልበት መንገድ ይኸው ብቻ ነው»አሉ ሽማግሌው ውሀውን ከተጎነጩ በኋላ። ትንሽ ሻል ብሏቸዋል። አዕምሮዋቸውም በደንብ እያሰበ ነው። አሁን ባለበት ሁኔታ ቢመዘን ርግጠኛ ነኝ 1500 ፓውንድ ይሆናል አሉ በሀሳባቸው። እረ እንዲያውም ይበልጣል። ሶስት እጅ የሚሆነው እንኳን በደንብ ተበልቶ አንዷ ፓውንድ በሰላሣ ሣንቲም ብትቸበቸብ የትና የት!

«በትክክል ለማስላት ግን እርሳስ ያስፈልገኛል» አለ፡፡ «አዕምሮዬ ለብቻው ይህንን ያህል ሂሣብ ለማስላት ገና ነው፡፡ ብዙም አጥርቶ አያስብ፡፡ ለማንኛውም ዛሬ ትልቁ ዲማጂዮ እንደሚኮራብኝ አያጠራጥርም፡፡»

ዓሣውን ከጀልባዋ አፍንጫና ጀርባት እንዲሁም መካከል ላይ ከተጋደመው የመቀመጫ ሣንቃ ጋር ግጥም አድርገው በገመድ ቀየዱት፡፡ ከግዙፍነቱ የተነሳ ጀልባዋ ጐን ላይ አንድ ሌላ ትልቅ ጀልባ የማሠር ያህል ነበር ሁኔታው፡፡ የአሣው አፍ ገርበብ ብሎ በመንገዳቸው ላይ እንቅፋት እንዳይሆን በማለት ሽማግሌው አንድ ገመድ ቆረጡና ሁለቱን መንጋጋዎቹን በሀይል አጋጥመው አሰሯቸው፡፡ ከዚያ ተራዳውን ተከሉና የተጣጣፈውን ሸራ ወጠሩት፡፡ ጀልባዋ መለስ እያለች ወደፊት መጓዝ ጀመረች፡፡ ሽማግሌው ጀልባዋ ጭራ አካባቢ ጋደም አሉ፡፡አቅጣጫቸው ወደ ደቡብ ምዕራብ ነበር፡፡

ደቡብ ምዕራብ በየት በኩል እንደሆን ለመለየት አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ አያስፈልጋቸውም፡፡ ከሰሜን ምሥራቅ ወደ ምድር ሠቅ የሚጋልበው ሃያል ነፋስና የሸራቸው በደንብ መወጠር ብቻ ይበቃቸዋል፡፡ ሽምጥ የያዙትውን ጀልባ የእንጨት መሪ በክንዳቸው ደገፍ ብለው፣ ወዲያውም መስመሯን እንዳትስት ይቆጣጠራሉ፡፡ ዓሣው የጀልባዋን ጐን የሙጥኝ ብሎ ሲጓዝ ይታያቸዋል፡፡ ግን ሁሉም ነገር እውነት አይመስላቸውም፡፡ ያጋጠማቸውን ሁሉ መለስ ብለው ሲያስቡት በህልማቸው የሆነ ነው የሚመስላቸው፡፡ እጆቻቸውን ሲያዩና የጀልባዋን እንጨት የተደገፈ ጀርባቸው ህመም ሲሰማቸው ብቻ ነው ሁሉም ነገር በዕውን ስለመፈፀሙ ርግጠኛ የሚሆኑት፡፡

እጆቼ ቶሎ ይድናሉ አሉ በሀሳባቸው:: የባህሩ ውሀ ያድናቸዋል:: ጨውማውን የባህር ውሀ የመሰለ ፈውስ የለም:: በኔ በኩል ማድረግ ያለብኝ አዕምሮዬ እንዳይደነዝዝ መጠንቀቅ ብቻ ነው:: እጆቼ እንደሆኑ ግዴታቸውን በሚገባ ተወጥተዋል:: መንገዳችንም ቀና እየሆነ ነው:: እሱም አፋን ተሸብቦና ጅራቱን እንደ ሰንደቅ ገትሮ ልክ እንደወንድም አብሮኝ እየተጓዘ ነው::

ድንገት አንድ ነገር በአዕምሮዋቸው ብቅ አለና ተምታታባቸው:: አሁን ለመሆኑ ማነው አሸናፊው? እሱ ወይስ እኔ? በሀሳባቸው ጠየቁ:: አካሄዳችን ከኋላየ አስከትየው፣ እየጐተትኩት ቢሆን ኖሮ ምንም ባላጠራጠረ ነበር:: ወይም ኩራቱ ሁሉ ከላዩ ተራግፎ ሬሳውን ጀልባዬ ውስጥ አጋድሜው ቢሆን እንዳችም ጥያቄ ባላስነሣ ነበር::አሁን ግን የምንጓዘው ጐን ለጐን ሆነን ነው::ግን ቢሆንስ፣ ምንተዳዬ:: ተመስለው ድል ያድርገኝ:: እኔም ከሱ የምሻለው በማታለል ችሎታዬ ብቻ ነው:: እሱ እንደሁ እኔን ለመጉዳት አንዳችም ሙከራ አላደረገም::

ጉዟቸውን በሠላም ቀጠሉ::ሽማግሌው እጆቻቸውን እየመላለሱ ውሃ ውስጥ በመንከር አ'ዕምሮዋቸው እን ዳይቦዝዝ ይከላከላሉ:: ሰማዩ ላይ አልፎ አልፎ የተኮፈሱትን የጥጥ ባዘቶ የመሣሠሉ ደመናዎች ሲመለከቱ ንፋሱ እንደሚያነጋ ርግጠኛ ሆኑ:: ዓሣው ገሀድ እንጂ ህልም አለመሆኑን ለማረጋገጥ አስር ጊዜ ቀና እያሉ ይመለከቱታል:: በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያው ሻርክ ከመምጣቱ በፊት አንድ ሰዓት አለፈ::

የሻርኩ አመጣጥ ድንገተኛ አልነበረም:: ደም ነው የጠራው:: የዓሣው ደም ልክ እንደ ጥቁር ደመና እየ ተገፈጠፈጠ የአንድ ማይል ጥልቀት ወዳለው የባህሩ

ውሀ አሽቀልቅሎ ሲበተን ነበር ሻርክ ሆዬ ሽታው አስ ክሮት እየጋለበ የመጣው:: ፍጥነቱ ከቁጥጥር ውጭ ስለነበር ሰማያዊውን ውሀ በርቅሶ ወደላይ ሲወጣና ለፀሐይዋ ሲጋለጥ አልታወቀውም:: ወዲያው ተመልሶ ውሀው ላይ ተፈጠፈጠና የትልቁ ዓሣ ጠረን የሚመጣ በትን አቅጣጫ ከያዘ በኋላ ጀልባዋ የምትጓዝበትን መስመር ተከትሎ መዋኘቱን ቀጠለ::

አንዳንድ ጊዜ የጠረኑ ፈለግ ይጠፋበትና ብዙም ሳይቆይ መልሶ ያገኘዋል:: ፍጥነቱን ይጨምራል:: «ማኮ» የሚባል የሻርክ ዝርያ ነው:: አካለ ግዙፍ፣ ከየትኛውም ዓይነት ዓሣ ይበልጥ ፈጠኖ መጓዝ የሚ ችል፣ከጥርሶቹ በስተቀር ሁለመናው የሚያምር ፍጡር ነው:: ጆርባው ሰማያዊ፣ ሆዱ አካባቢ ብርማ ሆኖ ቆዳው ለሥላሣና ቆንጆ ነው:: የጥርሶቹም ቅርፅ ከአብ ዛኞቹ ሻርኮች ለየት ይላል:: እንዳሞራ ጥፍር ከወደ ጫፋቸው ይቆለመማሉ:: የያንዳንዱ ጥርስ ርዝመት ከሽማግሌው ጣቶች ደካሞቹን፣ ፈጣንና ጠንካራ የሚባ ሉትንም የባህር አራዊት ሳይቀር ለመብላት የተፈጠረ ነው:: የትልቁ ዓሣ ጠረን እየቀረበው ሲሄድ ፍጥነቱን በመጨመርና ወደላይ ከፍ በማለት ትከሻው ላይ በጉን ቆለው ክንፍ ውሀውን እየቀረደደ ወደፊት መሽቀ ንጠሩን ቀጠለ::

ሽማግሌው ልክ እንዳዩት አወቁት::ፍርሀት የሚሉ ነገር የሌለበት፣ ያሻውን ከመፈፀም ወደኋላ የማይል የሻርክ ዓይነት ነው:: ዓይናቸውን ከላዩ ሳይነቅሉ ሀርፑናቸውን አሰናዱና እጀታው ላይ ገመድ አስ ሩበት:: ዓሣውን ከጀልባዋ ላይ ለመወደር ሲሉ ቆርጠ ውለት ትንሽ አጠር ብሏል - ገመዱ::

የሽማግሌው አዕምሮ ነቃ-ነቃ እያለ ነው:: ብቻ ተስፋቸው ወደመሟጠጡ ያለ ይመስላል:: ወኔያቸው

ግን አልተነካም:: ሻርኩ በጣም ሲቃረብ ወደ ትልቁ ዓሣ ዞር ብለው ላንዳፍታ አስተዋሉት:: ግን'ኮ ህል ምም ሊሆን ይችላል አሉ በሀሳባቸው:: መቼም አደጋ ከማድረስ ልገታው አልችልም፣ ግን ደህና አድርጌ አገ ኘው ይሆናል:: ዴንቱሶ[1] አሉ በሀሳባቸው:: ወዮ ዛሬ! ለዚያች ለናትህ ይብላኝላት::

ሻርኩ በፍጥነት ወደጀልባዋ ጭራ ተቃረበ:: ትል ቁን ዓሣ አንድ ጊዜ ሲገጨው ሽማግሌው የተከፈተ አፉንና ለየት ያሉ ዓይኖቹን ተመለከቷቸው:: ወደፊት ተስፈነጠረና ከዓሣው ጅራት ከፍ ብሎ ባለው ሥጋ ውስጥ እኒያን መጋዝ ጥርሶቹን ሲሰገሥጋቸው አዩት:: ጭንቅላቱ ከውሀው በላይ ብቅ ብሏል:: ጀርባውም ወደ ላይ እየወጣ ነው:: የትልቁ ዓሣ ሥጋ ከአጥንቱ ላይ ሲገሸለጥ ሽማግሌው ሰሙ:: ስቅጥጥ እንዳላቸው ተወ ራጩና በተጠንቀቅ ይዘውት የነበረውን ሀርፑን ወደ ሻርኩ ጭንቅላት ለጉት:: ከአፍንጫው ተነስቶ ወደማ ጅራቱ የሚወጣ መስመርና በዓይኖቹ መሀል የተዘረጋ ሌላ መስመር በሚገናኙበት ነጥብ ላይ ሀርፑኑ ተቀ ረቀረ:: የአንጎሉ አካባቢ መሆኑ ነው:: ደም በጉረሱ ቁስለኛ እጆቻቸው የሰነዘሩትን ሀርፑን ባለ ሀይላቸው ቁልቁል ተጫኑት:: የመግደል ፍላጐትና ቁርጠኝነት እንጂ የማሸነፍ ተስፋ አልነበራቸውም::

ሻርኩ እንደመንፈራገጥ ብሎ ሲገለበጥ ዓይኖቹን አስተዋሉ:: ህይወት እየራቀው ሄዷል:: በድጋሚ ተገለ በጠ:: ይህን ጊዜ ከሀርፑኑ ጋር የተያያዘውን ገመድ ሁለት ጊዜ አካሉ ላይ ጠመጠመው:: ሽማግሌው

---

[1] ጥርስ እንደማለት ነው:: ሻርክ የሚታወቀው አንድም በመጋዝ ጥርሶቹ ነውና በአሸሙር ዓይነት መንካታቸው ነው::

መሞቱን አረጋገጠ። ሻርኩ ግን አሜን ብሎ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም። በጀርባው ተንጋሎ መንጋጋውን እያንገጫገጨና ጅራቱን እያወናጨፈ እንደ ባለሞተር ጀልባ ውሀውን ሁለት ላይ ይገምሰው ገባ። ጅራቱን ባሳረፈበት ቁጥር ባህሩ አረፋ ይደፍቃል። ሶስት እጅ የሚሆነው አካሉ ከውሀው ወጥቶ በመወራጨት ላይ እንዳለ ከሀርፑኑ ጋር የተያያዘው ገመድ በሀይል ተወ ጠረና ላንዳፍታ ተንቀጠቀጠ። በሚቀጥለው ቅፅበት ጧ ብሎ ተበጠሰ። ሻርኩ ለጥቂት ጊዜ ፀጥ ብሎ እንደ ተንጋለለ ሲንሣፈፍ ቆየ። ሽማግሌው አትኩረው ተመ ለከቱት።ወዲያው ዝግ እያለ ቁልቁል ወረደ። ሰመጠ።

«የወሰደው ሥጋ አርባ ፖውንድ ይሆናል»አሉ ሽማግሌው ድምፃቸውን ጮኻ አድርገው። «ይባስ ብሎ ደሞ ሀርፑኑን ከነገመዱ ይዞት መሄዱ» አሉ አያይ ዘው። ዓሣው እንደገና እየደማ ስለሆነ ሌሎችም መም ጣታቸው የማይቀር ነው።

ከዚህ በኋላ ዓሣው ስለተዘነጣጠለ ሊያዩት አል ፈለጉም። ሻርኩ እንደ ደረሰ በሀይል በገጨው ጊዜ እሳቸውኑ እንደመታቸው ያህል ሆኖ ነበር የተሰ ማቸው።

ግን ምንም አይደለም። እኔን ደፍሮ፣ ዓሣዬን ዘን ጥሎ አልቀረም። ዋጋውን ሰጥቼዋለሁ። ደሞ ምን ያህ ላል በሉ። እስከዛሬ ካየኋቸው መሀል ይህንን የሚስተ ካከል የለም።

እንደነበረ ሆኖ ቢዘልቅ ምንኛ መልካም ነበር። አሁን ግን ሁሉም ነገር ህልም ቢሆን ቅር አይለኝም። በዚች ወቅት ጋዜጦች በተነጠፉባት አልጋዬ ላይ ለብ ቻዬ ተጋድሜ ቢሆን ነበር - ምኞቴ አሉ በሀሳባቸው ሲያስተነትኑ።

«ግንኮ ሰው የተፈጠረው ለሽንፈት አይደለም» አለ:: «በርግጥ ሰው ይጠቃ ይሆናል:: ይረታል ማለት ግን ዘበት ነው::» ይሁንና ታላቁን ዓሣ ስለገደልኩት አዝናለሁ አሉ በሀሳባቸው:: ተንግዲህ የሚጠብቀኝ መጥፎ ጊዜ ነው:: በዚያ ላይ ባዶ እጄን ነኝ:: ሀርፑን እንኳን የለኝ:: ያ መናጢ ሻርክ ጭካኔ ብቻ ሣይሆን ብልጠትና ጥንካሬም አያጣ:: ለብልጠቱማ እኔስ መች እሰንፋለሁ:: ብቻ ምን ይታወቃል፣ አሉ እንደገና በሀሳ ባቸው:: ምናልባት የምበልጠው የተሻለ መሣሪያ በመ ታጠቄ ብቻ ሊሆን ይችላል::

«በቃ እንግዲህ ሽሜ፣ ብዙ አታስብ» አሉ ድምፃ ቸውን ከፍ አድርገው:: «ዝም ብለህ ጉዞህን ቀጥል:: ከዚያ ሌላ የሚመጣውን እንደየአመጣጡ መቀበል ነው::»

ግን እኮ ማሰብ ይገባኛል አሉ:: ምክንያቱም የቀ ረኝ እሱ ብቻ ነው:: ሀሳብና ቤዝቦል ብቻ ናቸው የቀ ሩኝ:: ለመሆኑ ማጂዬ የሻርኩን አንጎል እንዴት እንደ በጠረቀሁት ቢያይ የቱን ያህል ይደሰት ይሆን? ግንኮ ያም ቢሆን እስተዚህም ፍሬ ያለው ጉዳይ አይደለም:: ማንም ሰው የሚፈፅመው ነው አሉ አሁንም በሀሳ ባቸው::

ወደፊት ምን እንደሚያጋጥማቸው በደንብ ያውቁ ታል:: ግን አንዳችም ሊያደርጉት የሚቻላቸው ነገር አልነበረም::

«እም! እንደዚያ ማድረግ ይቻላል» አሉ ድንገት በሃይል ጮኸው:: «ጩቤዬን በአንደኛው መቅዘፊያ እጄታ ላይ አስሬ እንደ ጦር ልጠቀምበት እችላለሁ::»

ወዲያው እንዳሉት አደረጉ::

«አሁንም ያው እንደ ቅድሙ ያለሁ ሽማግሌ ነኝ» አሉ።«አሁን ግን ትጥቅ አልባ አይደለሁም።»

ሽው የሚለው ንፋስ ደስ ያሰኛል። ጀልባዋ ወደ ፊት መሰስ እያለች ነው። ሽማግሌው የሚያዩት የዓሣ ውን ጭንቅላት እንጂ ወደማጅራቱ አካባቢ ሥረቅ እን ኳን አያደርጉም። ተመናምኖ የነበረ ተስፋቸውም ማን ሠራራት ጀመረ።

ተስፋ አለማድረግ ጅልነት ነው አሉ በሀሳባቸው። ሃጢአትም እንደሆነ አምናለሁ። እባክህ ሽሜ ስለኃጢ አት አታስብ አሉ። በአሁኑ ወቅት እንኳንስ ኃጢአት ተጨምሮበት እንዲሁም የችግሩ ዓይነትና ብዛት የማይ ቻል ሆኗል አሉ። በዚያ ላይ ኃጢአት ብሎ ነገር በጭ ራሽ አይገባኝም።

ስለኃጢአት የሚገባኝም ሆነ የማውቀው ነገር የለም። የማምንበት ስለመሆኑም እጠራጠራለሁ። ምና ልባት ትልቁን ዓሣ መግደል ከኃጢአት ሊቆጠር ይች ላል። ምንም እንኳን ህይወቴን ለማቆየትና ብዙ ሰዎ ችን ለመመገብ ስል የፈፀምኩት ቢሆንም ከኃጢአት ተራ ሊመደብ እንደሚችል እኔም እገምታለሁ። እንዲህ ከተባለ ደግሞ ሁሉም ነገር ኃጢአት ከመሆን ላይድን ነው። ለማንኛውም አሁን ስለኃጢአት አታስብ ሽሜ። እሱን ለማድረግ ጊዜው አልፏል። ዘግይቷል። በዚያ ላይ ስለኃጢአት እንዲያስቡ ሆን ተብሎ የሚከፈላቸው ሰዎች አሉ።ስለ ኃጢአት እነርሱ ይጨነቁበት። እነርሱ ያስቡበት። አየህ ዓሣው ዓሣ ለመሆን እንደተፈጠረ ሁሉ አንተም የተሠራኸው ዓሣ አጥማጅ ለመሆን ነው።የትልቁ ዲማጂዮ አባት ዓሣ ሲያጠምድ እንደኖረ ሁሉ ቅዱስ ጴጥሮስም ዓሣ አስጋሪ እንደነበር አት ዘንጋ።

ቢሆንም ማሰቡን አልጠሉትም:: የሚያዳምጡት ሬዲዮ ወይም የሚያነቡት ነገር ስላልነበራቸው ስለ ትናንት ህይወታቸውና ስለገጠመኞቻቸው ማውጠን ጠኑን አልጠሉትም:: ብዙ ጉዳዮችን አንስተው ጣሉ:: አሰቡ::ብዙ አሰቡ:: በዚያውም ስለኃጢአት የጀመሩትን ማስተንተን ቀጠሉበት:: ዓሣውን የገደልከው በህይወት ለመቆየትና ለዚህም የሚያስፈልግህን ምግብ ለመግዛት የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ብቻ አይደለም:: ለክብርህና ለሙያህም ጭምር ስትል ነው:: በህይወቱ ሣለ ወደ ድኸው:: ከዚያም በኋላ ፍቅርህ አልተቀነሰም:: እየ ወደድከው መግደልህ ደግሞ ከቶም ከኃጢአት አይቆ ጠርብህም::

«ምነዋ ሀሳብ ብቻ ሆንክ ሽሜ?»አሉ ድምፃቸውን ጉላ አድርገው::

ሻርኩን መግደልህ ግን አስደስቶሃል አሉ የጀመ ሩትን በመቀጠል:: ግንኮ እሱም እንዳንተው ዓሣ አድኖ ነው የሚኖረው::ነፍሱን የሚያሳድር፣ ህይወቱን የሚጠብቃት ዓሣ አሣዶ ነው:: ደሞም ይህኛው ኩሩ ቢጤ ነው:: እንደ ጥንብ አንሣ ሻርክ አሰስ ገሠሡን ሲቃርም የሚውል ልክስክስ አይደለም:: በዚያ ላይ ቆንጆ፣ ጨዋ፣ ልበ- ሙሉ ነው::

«የገደልኩት ራሴን ለመከላከል ስል ነው» አሉ ሽማግሌው ጮክ ብለው:: «በደንብ ነው የሰራሁለት::»

በዚያ ላይ አሉ ወደ ሀሳባቸው ተመልሰው:: የአ ንዱ ሌላውን በተለያዩ ዘዴዎች መግደል በፍጥረታት ዘንድ ሁሉ ያለ ነው:: ዓሣ ማስገር ህይወቴን የሚጠ ብቃትን ያህል እየገደላትም ነው:: ምንም አይደል ልጁ አለልኝ፣ አሉና ብቻ ራሴን ብዙ ማታለል አይገባኝም ሲሉ አከሉበት::

በጀልባዋ ጎን በኩል ተጎንበሱና ሻርኩ ሲዘነጥል ተንዘላዝሎ ከቀረው የዓሣው ሥጋ ላይ ጥቂት ቀንበብ አድርገው ጎረሱ። እያላመጡ፥ እያጣጣሙ አደነቁት- ጣፋጭነቱን። ገበያ ላይ ሲቀርብ የሚያወጣው ዋጋ ታያቸው። ግን ምን ያደርጋል ጠረኑን ከአካባቢው ለማጥፋት የሚቻልበት ዘዴ የለም። ጣጣ እየጎተተ ነው። ከፊታቸው የሚጠብቃቸው ጊዜ እጅግ የከፋ እንደሚሆን ታውቋቸዋል።

ንፋሱ እንደነበረ ነው። ትንሽም አልተለወጠ። ሽማግሌው አሻግረው ተመለከቱ። የሌላ ጀልባ የንፋስ ሸራ ወይም የትልቅ መርከብ አካልና ጢስ አይታይም። በራሪ ዓሣዎች ብቻ በግራ በቀኝ ውርውር ይላሉ። በተቀረ የወፍ ዘር እንኳን የለም። ለሁለት ሰዓት ያህል በሰላም ተጓዙ። ሽማግሌው ጀልባዋ ጭራ አካባቢ አረፍ ብለዋል።አንዳንዴ ከዓሣው ሥጋ ነጨት ያደርጉና ይጎርሟሉ። እንዲህ እንዲህ እያሉ የደከመ አካላቸውን ለማሳረፍና ጉልበታቸውን ለማደስ እየሞከሩ ሳለ ከሁለቱ ሻርኮች የመጀመሪያውን ድንገት አዩት።

«አይ» አሉ ድምፃቸውን ጎላ አድርገው። የቃሉን መልዕክትና ስሜት በትክክል ለመተርጎም ያዳግታል። ብቻ አንድ ሰው እጁ ከእንጨት ጋር ተጣብቆ በምሥማር ሲቸነከር ሊያሰማ የሚችለው ዓይነት ድምፅ ነው቉ቢባል ይቀል ይሆናል።

«ጋላኖስ» አሉ እንደገና በጩኸት። በደንብ ከሚታየው የመጀመሪያው ሻርክ የጀርባ ክንፍ በስተኋላ ሌላ ክንፍ ከውሀው ብቅ ሲልና እንደ ጅራት በፍጥነት ሲወናጨፍ ተመለከቱ። የዓሣው ጠረን ያቀረበላቸውን ግብዣ ተቀብለው መምጣታቸው ነበር።

ሽማግሌው ጫፉ ላይ ጩቤያቸው የተዋደደበትን
መቅዘፊያ አነሱ። የእጃቸው ህመም ስላስቸገራቸው
መቅዘፊያውን ሲያነሱ በጥንቃቄ ነበር። ጣቶቻቸውን
ለማፍታታት ዘርጋ ጨበጥ አደረጓቸው። በመጨረሻ
አጥብቀው ጨበጧቸው። እንዲህ ሲያደርጉ ሥቃዩን
ለመቋቋም ይረዳቸዋል። የማይበገሩም ይሆናል። ሻር
ኮቹ በጣም መቃረባቸውን ተመለከቱ። የአካፋ ቅርፅ
ያለው ሰፊና ጠፍጣፋ ጭንቅላታቸው በደንብ ይታያ
ቸው ጀመር። ወዲያው ለዩዋቸው። አደገኛና ተንኰለኛ
የሚባሉት የሻርክ ዓይነት ናቸው። በተለይ በሚራቡ
ጊዜ ለምንም ነገር አይመለሱም። ጥምብ - አንሣ የሚ
ባሉት ለዚህ ነው። እንኳንስ ህይወት ያለው ፍጡር
የጀልባ መቅዘፊያም አይምሩ።

«እህ» አሉ ሽማግሌው። «ጋላናስ፣ ወዲህ ኑ።
ቀረብ በሉ።»

ሻርኮቹ ተጠጉ። የፊተኛው ሻርክ ቀርቦ የነበረ
ውን ያህል ለመጠጋት ግን አልደፈሩም። አንደኛው
ወደኋላ ተመለሰና ጀልባዋ ሥር ገብቶ ተሰወረ። የዓሣ
ውን ጉያ ሲቦጠቡጥ ጀልባዋ መወዛወዝ ጀመረች።
ሁለተኛው ደግሞ መቅዘፊያውን ከራሳቸው በላይ ከፍ
አድርገው እንደያዙ የቆሙትን ሽማግሌ በትንንሽ ቢጫ
ዓይኖቹ ትክ ብሎ ሲመለከታቸው ከቆየ በኋላ ጥር
ሶቹን አግጥጦ ወደ ዓሣው ጅራት ተምዘገዘገ። በአን
ገቱና በአከርካሪው መጋጠሚያ አካባቢ ያለው መስ
መር ጭንቅላቱ ላይ በግልፅ ይታያል። ሽማግሌው
የሚፈልጉትን ያህል እንደተጠጋ ከመቅዘፊያው ጋር
የተዋደደ ጩቤያቸውን መስመሩ ላይ ተከሉት። ፋታ
ሳይሰጡ ነቅለው እንደገና በመሰንዘር የድመት በሚመ
ስሉት ቢጫ ዓይኖቹ ውስጥ ሻጡት። አፍታም አል
ቆየ፤ አካሉ ዛለና የነከሰውን ዓሣ ለቆ ሽተት እያለ

ቁልቁል ጠረደ:: እንደ. የቦጨቀውን በአፉ እንደያዘ ሰመጠ:: የጉረሰውን እየዋጠ ዘቀጠ::

ጆልባዋ ግን ሊ.ላው ሻርክ በዓሣው ላይ በማ.ያደ ርሰው አደ.ጋ ሳቢ.ያ መርገፍገፏን እንደቀጠለች ነው:: ሽማግሌ.ው አንድ ዘዴ ብልጭ አለባቸው:: ጆልባዋን ወደጐን ገለል በማድረግ ሻርኩን ማጋለጥ:: የንፋሱ ሽራ ከታሰረባቸው ገመዶች አንዱን ፈ.ቱት:: ሽራው ሲ.ረግብ ጆልባዋ ወዳንድ ወገን ዘንበል አለች:: ሻርኩን አዩት:: በጆልባዋ ጐን በኩል ተጉንብሰው መቅዘፊ ያቸውን ሰነዘሩ:: እንዳሰቡት አልሆነም:: ጩቢ.ያቸው የሻርኩን ጠንካራ ቆዳ ሊ.ዘልቅ አልቻለም:: ይልቁን ንዝረቱ የእጃቸውንና የትከሻቸውን ስቃይ እጥፍ አደ ረገው:: ግን ጨዳ.ያው ሌላ ጥሩ ዕድል አጋጠማቸው:: ሻርኩ በፍጥነት እየተስለከለከ ጭንቅላቱን ከውሃው አውጥቶ መጥቶ ጥርሶቹን ዓሣው ሥጋ ላይ ሲ.ሠካ ሽማግሌውም የሰላ ሾተላቸውን አናቱ ላይ ቀበቀቡት:: አልበቃቸውም:: ከመቅፀበት ነቀሉና እንደገና በኃይል በመሰንዘር እዚ.ያው ቦታ ላይ ወጉት:: ሻርከ ሆዬ ጥር ሶቹን ሥጋው ላይ እንደሰገሠገ ሙጭጭ ብሉ ቀረ:: ሽማግሌው በእድሉ ለመጠቀም ጩቤያቸውን ነቅለው ግራ ዓይኑ ላይ ሸነቀሩት:: ሻርኩ ግን ሥጋው ላይ እንደተንጠለጠለ ቀረ::

«አይደረግማ»ብለው ሽማግሌው እንደገና ሰነዘሩ:: የጩቤው ስለት በአንጐሉና በአከርካሪው መሀል አረፈ:: አሰነዛዘራቸው ጠንካራ ስለነበር ለስላሣው የአከ ርካሪ አጥንት ሲ.በጠስ ታወቃቸው:: አፉን ለማላቀቅ መቅዘፊያውን ወደጐን ገደድ አድርገው የጩቤውን ስለት መንጋጋዎቹ መሀል በማስገባት ጠመዘዙት:: ትልቁ ዓሣ ላይ ተከርችሞ የነበረ አፉ ተላቀቀ:: ከዚ. ያም እየተዝለፈ.ለፈ. በዝግታ ቁልቁል መውረድ ጀመረ::

«ደህና ሁን ጋሻና፣ በቸር አገርህ ግባ። ከጓደኛህ ተቀላቀል። ምን ይታወቃል እናትህም ልትሆን ትችላለች። እሱ የራስህ ጉዳይ ነው» አሉ ሽማግሌው።

የጨቤውን ስለት ጠራረጉና መቅዘፊያውን አስቀመጡት። አላልተውት የነበረውን የሽራውን ገመድ መልሰው አጠበቁት። በንፋስ ጢቅ ብሎ ተወጠረ። ጆልባዋንም ወደ ቀድሞው የጉዞ መስመሯ ቀለሷት።

«ሲሶ የማይሆነውን ሣይወስዱ አልቀሩም። ለዚያውም ደህናውን ሥጋ ነው» አሉ ድምፃቸውን ጉላ አድርገው። «ነገሩ ሁሉ ህልም ቢሆንና እኔም ባልያዝኩት እንደምን መልካም ነበር። ለማንኛውም ግን ስለፈፀምኩት ሁሉ በጣም አዝናለሁ ዓሣ፣» አሉ። አሁን በጭራሽ ሊያዩት አይፈልጉም። ደሙ በመሚጠጡና አካሉ በባህሩ ውሃ በመታጠቡ ሁለመናው የመስተዋት ጆርባ የሚቀባውን ቀለም መስሏል። ጆርባው ላይ የተጋደሙት መስመሮች ግን ቁልጭ ብለው ይታያሉ።

«ወትሮውንም ይህንን ያህል ርቄ መንዝ አያስፈልገኝም ነበር ዓሣ» አሉ። «ላንተም ሆነ ለኔ ላይበጅ እንዲያ መድከም አልነበረብኝም። አዝናለሁ ዓሣ። አዝናለሁ።»

አሁን ይልቅ አሉ ለራሳቸው ምክር ሲለግሡ። ጨባጩና መቅዘፊያው የተቀደዱበት ገመድ ተቆርጦ እንደሆን ፈትሸው። ከዚያ በኋላ እጆችህ ለሌላ ትግል እንዲዘጋጁ ትንሽ አሣርፈህ አስታማቸው። ገና የሚመጡ እንግዶች እንዳሉብህ አትዘንጋ።

«ድንጋይ ቢኖረኝ እንደምን ጥሩ ነበር» አሉ ሽማግሌው፣ጨቤው ከመቅዘፊያው ጋር የታሰረበትን ገመድ

ከፊቱሽ በኋላ። ለማንኛውም ድንጋይ ይገዤ መምጣት ነበረብኝ። አይ አንተ እሱማ ብዙ ነገር ማምጣት ነበረብህ አሉ ወዲያው በሀሳባቸው፤ ግን ምን ያደርጋል አንዱንም አላመጣህም ሽሜ። አሁን ባለው ልትሰራ ስለምትችለው የምታስብበት እንጂ በሌለህ ነገር የምታውጠነጥንበት ጊዜ አይደለም።

«ብዙ ጥሩ ጥሩ ምክሮች ትሰጠኛለህ» አሉ በጩኸት።«አሁን ግን በቃኝ።ተወኝ።በጣም ነው የሰለቸኝ።»

ወደፊት የምትንሣፈፈውን ጀልባ መሪ ለክንዳቸው ትራስ አድርገው ወዲያውም እየተቆጣጠሩ መዳፎቻቸውን ውሀው ውስጥ ነከሯቸው።

«ያ የመጨረሻው ምን ያህል ይዞ እንደሄደ እንድዬ ብቻ ነው የሚያውቀው» አሉ። «ጀልባዋ ግን በጣም ቀለል ብሏታል።» ስለተዘነጣጠለው የዓሣ ሆድ በጭራሽ ማሰብ አልፈለጉም። ጀልባዋ በተርገፈገፈች ቁጥር አንዳንድ ጉርሻ እየመነደበ ሲወስድ እንደነበር አውቀውታል። ስለዚህ ይህን ጊዜ ሆድቃው ውሀው ውስጥ በመዘርገፍ ርቀው የሚገኙትን ሻርኮች ሳይቀር ግብር የሚጠራ ፈርስና ሞራ በሰፊው ተንጣሏል ማለት ነው።

ለአንድ ሰው መቼም ለሙሉ ክረምት መውጫ ይበቃ ነበር አሉ በሀሳባቸው። በቃ ስለሱ አታስብ። ዝም ብለህ ዕረፍት በማድረግ እጆችህን ለተከታዩ ፍልሚያ አዘጋጃቸው።

ቀጥሎ የመጣው ሻርክ ባልደረባ አልነበረውም። አፉን ብርግድ አድርጎ እንደከፈተ ወደ ዓሣው ገሠ ገሠ። ሽማግሌው ዓሣውን እስከሚገጨው ጠበቁና

መቅዘፊያቸውን በሀይል ሠነዘሩ፡፡ ቀናቸው፡፡ አንጉሉን በጥርቀው ጣሉት፡፡ ሻርኩ የኋሊት በኃይል ተመንጭቶ እያፈገፈገ ሲገለባበጥ የጨበጡው ስለት ሁለት ላይ ተሰበረ፡፡

ሽማግሌው ወደ ጀልባዋ ጭራ ተመልሰው መሪያ ቸውን ያዙ፡፡ ትልቁ ሻርክ በዝግታ ወደ መቃብሩ ሲወ ርድ፣ ከግዙፍ ቅርፅ ወደ ነቁጥ እየሟሸሸ ሲጠፋ ለመ መልከት ቅንጣት ታህል ደንታ አልነበራቸውም፡፡

«አሁን የቀረኝ እንግዲህ ባለዛቢያው ሚንጦ ብቻ መሆኑ ነው» አሉ ሽማግሌው፡፡ «እሱ ደግሞ ለምንም አይረባ፡፡ መቅዘፊያዎቼና ቆመጡ ይሻላሉ፡፡»

አሁን ገና አሸነፉኝ አሉ በሀሳባቸው፡፡ሻርክን ያህል ዓሣ በቆመጥ፣ ለያውም በኔ አቅም፣ ቀጥቅጦ መግደል ዘበት ነው፡፡ ለዚያ ዓይነት ትግል በጣም አርጅቻለሁ፡፡ ግን ምን ቢያደርግ እጄን አልሰጥም፤ መቅዘፊያዎቼና ቆመጡ እስካሉኝ ድረስ የምችለውን ያህል እከላ ከላለሁ፡፡

መዳፎቻቸውን መልሰው ባህሩ ውስጥ ነከሯቸው፡፡ ሰዓቱ ወደምሽት እየተቃረበ ነው፡፡ ከባህሩና ከሰማዩ በስተቀር አንድም የሚታያቸው ነገር የለም፡፡ነፋሱ ግን ጨምሯል፡፡ ብዙም ሣይቆይ መሬት እንደሚያዩ ተስፋ አደረጉ፡፡

«ደክሞሀል ሽሜ» አሉ፡፡ «ውስጥህ ከፉኛ ተዳከ ሚል፡፡»

ሌሎች ሻርኮች ፀሐይ እስከጠለቀች ድረስ ዝር አላሉም፡፡ ሲመጡ ግን አስቀድመው ያዩት በሩቁ የጀ ርባ ክንፎቻቸውን ነበር፡፡ እነሆሞቹ የዓሣውን ጠረን

ማንፍንፍ ያስፈለጋቸውም አይመስለም:: ጉን ለጉን ሆነው በርግጠኛነት ወደጀልባዋ ይዋኛሉ::

የጀልባዋን መሪ እንዳይወዛወዝ አሰሩና የንፋስ ሸራውን ገመድ ውል አጠባብቀው ቆመጣቸውን አነሱ:: የተሰበረ መቅዘፊያ እጀታ ነው:: ቁመቱ ሁለት ጫማ ተኩል ይሆናል:: በቀኝ እጃቸው አጥብቀው ይዘው ሻርኮቹን ይመለከቱ ጀመር:: ሁለቱም ጋላኖ ናቸው::

የመጀመሪያው በደንብ ተጠግቶ ሥጋውን እስ ኪነክስ መጠበቅ አለብኝ:: ያኔ አስተካክዬ እወቃዋለሁ አሉ በሀሳባቸው::

ቀደም ያለው ሻርክ አፉን ከፍቶ ብርማ ቀለም ባለው የዓሣው ጉን ውስጥ ጥርሶቹን ጭፍቅ ሲያደ ርጋቸው ሽማግሌው የሚችሉትን ያህል ተንጠራርተው ጠፍጣፋ አናቱን መቱት:: ሥጋውን ለቆ ቁልቁል ሲን ሸራተት ሆርኑ ላይ ደገሙት::መለስ ቀለስ እያለ ከሥ ጋው ነሞጥ ያደርግ የነበረው ሁለተኛው ሻርክ አፉን በሰፊው ከፍቶ ለሌላ ጉርሻ ተጠጋ:: ሽማግሌው ቆመ ጣቸውን ሠነዘሩ:: ሻርኩ አንደ አየት አደረጋቸውና አፍ የሚሞላ ሥጋ ቦትሮፍ አደረገ:: የጉረሰውን ለመ ዋጥ ወደ ውሀው እሰርጋለሁ ሲል ቆመጡ አናቱ ላይ አረፈ::

«ናማ ጋላኖ:: ና»አሉ ሽማግሌው:: «ደግመህ ብቅ በል::»

ሻርኩ በፈጣን እንቅስቃሴ ብቅ አለ:: የተከፈተ አፉን በሚቹ ሥጋ ላይ ሲገጥመውና ሽማግሌው ተን ጠራርተው ሲነርቱት አንድ ሆነ:: የእንጉሉን አጥንት በደንብ እንዳገኙት ታወቃቸው:: አልሞት ባይ ተጋዳዩ ሻርክ ግን በደመነፍስ እየተንዘላዘለ ከሥጋው ለመቋደስ

እንደገና አፉን ሲከፍት መጀመሪያው ቦታ ላይ ደህና አድርገው አደባዩት::ማማረጊያ ሆነው:: አሉም በቃው:: ከዓሣው በድን ላይ በዝግታ እየተንሸራተተ ወረደ::

ተመልሶ ይመጣል በሚል ጥርጣሬ ሽማግሌው ተዘጋጅተው ጠበቁት:: ግን ሁለቱም ብቃያቸው ጠፋ:: ብዙ ቆይቶ አንደኛውን አዩት:: ወደላይ ዘልቆ በክብ መስመር ይዋኛል:: የሌላው ግን ደብዛው የለም::

ልገድላቸው እንደማልችል ወትሮውንም አውቄ ዋለሁ አሉ በሀሳባቸው:: ግን ተጉድተዋል:: ቆመጡን የያዝኩት በሁለት እጆቼ ቢሆን ግን የመጀመሪያውን እገለው ነበር::

ከዚያ በኋላ የሻርክ ቀለብ የሆነውን ዓሣ ማየት አስጠላቸው:: ግማሽ ያህሉ እንደወደመ አውቀውታል:: ከሻርኮቹ ጋር ግብ ግብ ይዘው ሣለ ፀሐይ ጨርሳ ጠልቃ ነበር::

«ትንሽ ቆይቶ በደንብ ይጨልማል» አሉ:: «ያን ጊዜ የሀቫና ውጋገን ይታየኛል:: ያለሁት በስተምሥራቅ በኩል ከሆን ከአዳዲሶቹ አሸዋማ ዳርቻዎች የአንደ ኛውን መብራቶች ለማየት እችላለሁ::»

በአሁኑ ጊዜ ብዙም ሩቅ ልሆን አልችልም አሉ በሀሳባቸው:: በመጥፋቴ እምብዛም የሚጨነቅልኝ እንደ ማይኖር ርግጠኛ ነኝ:: ልጁ ግን በስጋትና በጭንቀት ሲሞት ይታየኛል:: ብቻ በኔ ላይ ፅኑ እምነት ስላለው ምንም ሳይነካኝ እንደምመለስ ልቦናው ያውቀዋል:: ከሱ ሌላ ምናልባት በእድሜ ጠና ካሉት ዓሣ አጥማ ጆች ብዙዎቹ ይጨነቁ ይሆናል- ሌሎችም፣ ሲሉ አሰቡ:: የምኖረው ጥሩ ከተማ ውስጥ ነው::

ትልቁ ዓሣ ከፉኛ በመዘንጣጠሉ አሁን እንደ በፊቱ ሊያዋዩት አይችሉም። ድንገት አንዳች ነገር አእ ምሮዎቻቸው ውስጥ ብልጭ አለባቸው።

«አንተ ግማሽ ዓሣ. . .» አሉ። «ያሁኑን አያር ገውና ከልብህ ዓሣ ነበርክ። ግን ያንን ያህል ርቄ መጓዝ እንደምን እየቆጨኝ መሰለህ። አንዳችንንም አል ጠቀምኩ። ሁለታችንንም ነው የጐዳሁት። ቢሆንም ብዙ ሻርኮች ገድለናል። ለመሆኑ ግን አንተ በህይወት በነበርክ ጊዜ ስንት ሻርኮች ገድለሀል? መቼም ያንን ዘገር የመሰለ መንቁር አፍህ ላይ የተሸከምከው ያለ ነገር አይደል።»

ትልቁ ዓሣ ነፃ ሆኖ በመዋኘት ላይ እንዳለ ሻርኮ ቹን ቢያገኛቸው ምን ያደርጋቸው እንደነበር ማሠላ ሠል ያዙ። ሀሳቡን በጣም ወደዱት። ወይ ነዶ ምሣር ወይም ጨቤ ቢኖረኝ መንቁሩን ቆርጬ ሻርኮቹን እዋ ጋበት ነበር አሉ በሀሳባቸው። ከመቅዘፊያው ጋር አስ ረውና ድንቅ መሣሪያ ይወጣው ነበር። ያን ጊዜ ሻር ኮቹን የምንታገለው ሁለታችንም እንሆን ነበር። ለመ ሆኑ ሌሊት ላይ መጥተው ጥቃት ካደረሱ ምንድነው የምታደርገው? ምን ልታደርግ ትችላለህ?

«ያው መፋለም ነዋ» አሉ። «እስከሞት ድረስ እፋለማችዋለሁ።»

ግን በዚያች ቅዕበት ድቅድቅ ባለው ጨለማ ውስጥ ሆነው፣ የህቫና ውጋገን በማይታይበትና የን ፋሱ ሽውታ ብቻ በሚሰማበት ጨለማ ተውጠው ሣለ በውስጣቸው የገነነው ስሜት ሌላ ነበር። ሞት። የመ ሞት ስሜት። የሞቱ ሆኖ ተሰማቸው። መዳፎቻቸውን አንዱን በሌላው ዳሰሱዋቸው። ገና በድን አልሆኑም።

ወደኋላ ለጠጥ ብለው የጀልባዋን ጭራ አካባቢ ደገፍ ሲሉ አለመሞታቸው ታወቃቸው። ትከሻዎቻቸውም ነገሩቸው።

ስለት አለብኝ ለካ። ዓሣውን ከያዝኩት ፀሎት አደርግለሁ ብዬ ተስዬ ነበርና አሉ በሀሳባቸው። አሁን ግን አልችልም። ክፉኛ ደክሞኛል። ይልቅ ያንን ኬሻ ትከሻዬ ላይ ጣል ባደርገው ይሻለኛል።

የጀልባዋን እንጨት ደገፍ ብለው ተንጋለው መሪ ውን እየተቆጣጠሩ የከተማይቱ ወጋገን ሰማዩ ላይ ሲፈካ ለማየት በጉጉት ይጠባበቃሉ። መቼም ሌላውን ቢያበላሹት ግማሹን ይገባሉ አሉ በሀሳባቸው። ለዚያ ውም እድል ካለኝ ነው። መቼም ትንሽ መጣጭ እድል ሳይኖረኝ ይቀራል? እንጃ፣ አይመስለኝም አሉ። ርቀህ ስትንዝ ያኔ ዕድልህን አበላሽተሀታል።

«ሞኝ አትሁን» አሉ ድምፃቸውን ከፍ አድር ገው።«ይልቅ ነቅተህ ጀልባህን ተቆጣጠር። ገና የበለጠ እድል ሊገጥምህ ይችላል።»

«ዕድል የምትሸጥበት ቦታ ቢኖርማ ትንሽ በገዛሁ ነበር» አሉ።

ግን ልገዛስ ብል በምኔ ነው? ራሳቸውን ጠየቁ። በጠፋ ፍላፃ፣ በተሰበረ ጩቤና በሁለት ቁስለኛ እጆች መግዛት ይቻለኝ ይሆን?

«ምናልባት» አሉ። «ሰማኒያ ሰባት ቀናት ባህር ላይ በመቆየት ልትገዛው ሞክረህስ የለ።»

ኢድያ! ዝምብዬ እንቶ ፈንቶውን ሁሉ ማሰብ የለ ብኝም አሉ። ዕድል እንደየሆነች አመጣጧ በብዙ ዓይ

ነት ቅርፅ ነው። ስለዚህ ማን ሊለየት ይችላል? እኔ ግን የትኛውንም ዓይነት ቅርፅ ይዛ ትምጣ ጥቂት ቆን ጠር አድርጌም ቢሆን የጠየቁኝን በሙሉ በከፈልኩ ነበር። አሁን የመብራቶቹ ውጋጋን ቢታየኝ ምንኛ በተ ደሰትሁ አሉ በሀሳባቸው። አቤት የምኞት ብዛት። ስን ቱን እመኝዋለሁ አሉ። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ግን በአ ሁኗ ቅፅበት የምመኘው ነገር ቢኖር የከተማዋን ብር ሀን ማየት ብቻ ነው። በደንብ ተመቻችተው ለመተ ኛት ሞከሩ። እዚያም እዚያም የሚሰማቸው ህመም እለመሞታቸውን አረጋገጠላቸው።

ከምሽቱ አራት ሰዓት ግድም የከተማይቱ ብርሀን ሰማዩን እየላሰ ፏ ብሎ ሲያንፀባርቅ ታያቸው። መሪ ውን በማስተካከል ጀልባቸው የውጋገኑን አቅጣጫ እንድትይዝ አደረጓት። ቀስ በቀስ ኃይል በመጨመር ላይ ባለው ነፋስ ማቢያ ውቅያኖሱ መቆጣት እየጀመረ ነው።

ተፈፀመ አሉ በሀሳባቸው። እነዚያ አርከሶች ግን እንደገና ይመጡ ይሆናል። ግን አንድ ብቸኛ ሰው ምንም መሣሪያ ሳይኖረው፣ ለዚያውም በጨለማ ምን ሊያደርጋቸው ይችላል።

የደካከመው ሰውታቸው ከሙንገሉ ሌላ እንደ እን ጨት ድርቅ ብሏል።ቁስላቸው ብርዱ በነካቸው ቁጥር ይጠዘጥዛቸዋል። ከሻርክ ጋር ዳግመኛ ውጊያ እንደማ ልገጥም ተስፋ አደርጋለሁ አሉ በሀሳባቸው። ተመልሼ ፍልሚያ ውስጥ እንደማልገባ አምናለሁ።

ግን እንደተስፋና ዕምነታቸው አልሆነም። መን ፈቀ ሌሊት ላይ ተስፋ ያላደረጉት ደረሰ። ከሻርክ ጋር ትንቅንቅ ያዙ።ፍሬቢስ ትግል መሆኑን ግን ልቦናቸው

ያወቀዋል:: የወረራቸው የሻርክ መንጋ በጨለማው ውስጥ አይታያቸውም:: የሚታያቸው ነገር በናር ዓሣው ላይ ለመረባረብ ሲሽቀዳደሙ የጀርባ ክንፎቻ ቸው ውሀው ላይ የሚፈጥሩት መስመር ብቻ ነው:: ያገኙትን ባገኙ ብለው ቆመጣቸውን በነሲብ መሰንዘር ጀመሩ:: እንዲያ በዱበሏ በሰነዘሩ ቁጥር የሻርክ እናት መምታታቸው ይታወቃቸዋል::ሻርኮቹ የዓሣውን ሥጋ ሲዘነጥሉት የሚፈጠረውም ድምፅ ይሰማቸዋል:: ጀል ባዋ በምትንቃነቅ ጊዜ ደግሞ ጉያው ውስጥ ገብተው እየፈተፈቱት መሆኑን ይረዳሉ:: እንዲሁ በመላ እየሠ ነዘሩ ያገኙትን ሲቀጠቅጡ አንድ ነገር ቆመጣቸውን ድንገት አፈፍ አድርጉ ከጃቸው መንተፈው- ነጥቆ ወሰደው::

ቀልጥፈው የመሪውን እጀታ ነቀሉና በሁለት እጆ ቻቸው ይዘው ድብደባቸውን ቀጠሉ:: የሻርኮቹ ጥቃት በጀልባዋ አፍንጫ አካባቢ ተወሰነ:: ሲያጠቁ ደግሞ አንዴ በየተራ በቅደም ተከተል፣ አንዴ ደግሞ ግር ብለው በጋራ ነበር::

በመጨረሻ አንድ ሻርክ ለብቻው ተጠግቶ የዓሣ ውን ጭንቅላት ተያያዘው:: ሽማግሌው ነገሩ እንዳ ከተመ ተገነዘቡ:: ምሬታቸው ባሰባሰበላቸው ከፍተኛ ኃይል ተጠቅመው የመሪውን እንጨት ብቸኛው ሻርክ እናት ላይ አሣረፉት:: የሻርኩ ጥርሶች ዓሣው ጭንቅ ላት ውስጥ በመቀርቀራቸው ለማስለቀቅ በመተናነቅ ላይ እንዳለ እየደጋገሙ ያበራዩት ገቡ:: ሲበዛበት የመ ሪው እጀታ ተሰበረ:: ሽማግሌው ግን እጅ አልሰጡም:: ጫፉ በተሰነጣጠረው ጉማጅ ሻርኩን ይጓጉጡት ጀመር:: ጥርሶቹን እንዳስለቀቀ ሻርኩም ፊቱን አዙሮ ሄደ:: ከመንጋው ውስጥ የመጨረሻው ነበር:: ከዚያ በኋላ ቢመለሱም ምንም የሚያገኙት ነገር አልነበረም::

ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ የሚለው ሽማግሌ አንድ ልዩና እንግዳ የሆነ ጣዕም አፋቸው ውስጥ ተሰማቸው::

ምራቃቸውን ወደባህሩ ጢቅ አደረጉና «ጋላኖ፣ ያውላችሁ ይሄንንም ብሉት» አሉ በጩኸት::

በመጨረሻ መረታታቸውን አረጋገጡ:: ለሽንፈታቸው ምንም መድህን የለውም:: ወደ ጀልባዋ ጭራ አምርተው ጉራጁን የመሪ እጀታ ቦታው ላይ ሰኩት:: ሰባራም ቢሆን ለጊዜው ያገለግላል:: ኪሻውን አነሱና ትከሻቸው ላይ ጣል በማድረግ ጀልባቸውን መምራት ቀጠሉ:: አሁን ስለምንም ነገር አያስቡም:: ስለምንም ነገር ስሜት የላቸውም:: ብቻ ፀጥ ብለው ወደ ወደባቸው ለመድረስ ባላቸው ችሎታና ዕውቀት እየተጠቀሙ ጀልባቸውን በደንብ ይመሯታል:: ውድቅት አካባቢ ጥቂት ሻርኮች መጥተው ዓሣውን ይጉነታትሉት ጀመር:: ሁኔታው ምግብ ከተበላበት ጠረጴዛ ላይ ፍርፋሪ እንደሚለቅም ሰው ዓይነት ነበር:: ሽማግሌው ግን ከቁም ነገርም አልጣፉት:: ጀልባቸውን በፀጥታ ይመራሉ:: አንድ ነገር ብቻ ልብ ብለዋል:: ከብደቱ ስለቀለላት የጀልባዋ ፍጥነት መጨመሩን::

ወደር የላትም አሉ በሀሳባቸው:: ከመሪዋ በስተቀር ምንም ጉዳት አልደረሰባትም:: እሱም ቢሆን በቀላሉ ይተካል::

ወደ ወደቡ መቅረብ ጀመሩ::

ለማንኛውም ንፋሱ ትልቅ ጓደኛችን ነው አሉ በሀሳባቸው:: ግን አልፎ አልፎ ነው በማለት አከሉበት:: ታላቁ ባህር ደሞ ወዳጆቻችንንም ጠላቶቻችንንም አን

ድነት ይዟል:: አልጋም ወዳጁ ነው:: አዎ አልጋ::ለካን መሸነፍ ቀላል ነውና አሉ አሁንም ሀሳባቸውን በመቀ ጠል:: መረታት የቱን ያህል ቀላል እንደሆነ እስከዛሬ አላውቅም ነበር:: ግን ምንድነው ያሸነፈህ ሽሜ?

«ምንም» አሉ ሎክ ብለው::«ያሸነፈኝ ርቄ መጓዜ ብቻ ነው::»

ወደ ትንሿ ወደብ ሲገቡ የቡና ቤቱ መብራቶች በሙሉ መጥፋታቸውን አስተዋሉ:: ሰው ሁሉ እንቅ ልፉን እየለጠጠ መሆኑ ገባቸው:: አሁን ንፋሱም ጉል በቱን ጨምሮ በኃይል መውዘግዘግ ይዟል:: የወደቡ አካባቢ ፀጥ፣ጭር፣ ዝም ብሏል:: ጀልባዋን ቋጥኞቹ ግርጌ ወዳለ ጠጠራማ ሥፍራ አስጠጓት:: የሚያግ ዛቸው ሰው ባለመኖሩ ጀልባዋን ለብቻቸው እየሳቡ ከውሀው ማውጣት ጀመሩ:: የሚችሉትን ያህል ወደ ዳር ካወጧት በኋላ ከአንድ ቋጥኝ ጋር አቆራኟት::

ተራዳውን ነቅለው ሸራውን በዙሪያው ከጠመ ጠሙ በኋላ በገመድ ጠፈሩት:: ተራዳውን ትከሻቸው ላይ አጋድመው አቀበቱን መውጣት ጀመሩ:: ድካማ ቸው የቱን ያህል የበዛ እንደሆነ የተገነዘቡት ያኔ ነበር:: ለአንድ አፍታ ቆም አሉና ወደኋላ ገልመጥ ብለው ወደሰማይ የተገተረውን የዓሣውን ትልቅ ጅራት ከመንገድ መብራቶች በሚፈነጠቀው ብርሀን አማካይ ነት ተመለከቱት:: ነጭ የጀርባ አጥንቱ፣ ጥቁር ጭንቅ ላቱና ርቃኑን የተጋደመው አፅሙ ታዩዋቸው::

መንገዳቸውን እንደገና ቀጥለው አፋፉ ላይ ሲደ ርሱ በአፍጢማቸው ተደፉ:: ቶሎ አልተነሡም:: ተራ ዳው ትከሻቸው ላይ እንደተጋደመ ለጥቂት ጊዜ መሬቱ ላይ ተደፍተው ቆዩ:: ለመነሳት ቢሞክሩም

አልቻሉም። ቀስ ብለው ተራዳውን ከትከሻቸው ሳያነሱ ቁጭ በማለት ወደ መንገዱ ማማተር ጀመሩ። አንድ ድመት ራቅ ብሎ ወደጉዳዩ ሲያዘግም አዩት። መል ሰው መንገድ መንገዱን ማስተዋል ቀጠሉ።

በመጨረሻ ተራዳውን መሬት ላይ አኖሩና በዝ ግታ ተነስተው ቆሙ። ተራዳውን ተሸክመው መንገዳ ቸው ገቡ። ጐጆዋቸው ከመድረሳቸው በፊት አምስት ጊዜ ያህል ቁጭ እያሉ፣ እያረፉ ነበር።

ጐጆዋቸው እንደገቡ ተራዳውን ግድግዳ አስደግ ፈው አቆሙት። ጨለማ ቢሆንም እንደምንም እየዳበሱ ውሀ የያዘ ጠርሙስ አገኙና ምላሳቸውን አረጠቡ። ከዚያ አልጋቸው ላይ በቁማቸው ወደቁ። የብርድ ልብ ሣቸውን ሣብ ሣብ እያደረጉ በማስተካከል ጀርባቸ ውንና እግሮቻቸውን ከሸፈኑ በኋላ አልጋውን ባለበሱት ጋዜጦች ላይ በልባቸው ተደፍተው እጆቻቸውን ግራና ቀኝ ዘርግተው ለጥ አሉ።

ማለዳ ልጁ ወደውስጥ አሾልቆ ሲመለከት ሽማግ ሌው ነፍሳቸውን አያውቁም። ንፋሱ እጅግ በርትቶ ስለነበር ወደባህር የሚወጣ አንድም ዓሣ አጥማጅ አል ነበረም። ልጁም ሥራ ስለሌለው እስከ ረፋዱ ተኝቶ ከቆየ በኋላ መከረሚያውን ማልዶ እየተነሣ ሲያደርግ እንደስነበተው ሽማግሌው መመለሳቸውን ለማየት መምጣቱ ነበር። መጀመሪያ ትንፋሽ እንዳላቸው አረጋ ገጠ። ቀጠሉና የቆሳሰሉ እጆቻቸውን ሲያይ ማልቀስ ጀመረ። ትንሽ ቆይቶ ምንም ኰሽታ ሳያሰማ ትኩስ ቡና ለማምጣት ወጣ። ቁልቁል ሲንደረደር ሁሉ እየተ ነፋረቀ ነበር።

ብዙ ዓሣ አጥማጆች ጀልባዋን ከበው ጐኗ ላይ የተወደረውን ጉድ ያስተውላሉ። አንደኛው ዓሣ አሥ

ጋሪ ሱሪውን እስከጉልበቱ ሰቅስቆ ውሃው ውስጥ በመ ቆም የዓሣውን አፅም በገመድ ይለካል::

ልጁ ወደዚያ አልሄደም:: ወደ ጉጆዋ ከማም ራቱ በፊት ሄዶ አይቶቷል:: ከዓሣ አጥማጆቹ አንዱን ጆልባዋን እንዲጠብቅለት አድርጎ ነው የተመለሰው::

«ሰመሆኑ እንዴት ናቸው?» አለ አንዱ ዓሣ አሥ ጋሪ በጩኸት::

«ተኝተዋል»ልጁ መለሰ::ሲያለቅስ ቢያዩትም ጉዳዩ አልነበረም::«አደራ ማንም እንዳይረብሻቸው::»

«አሥራ ስምንት ጫማ ነበር ቁመቱ ጓል፤» አለ አፅሙን ሲለካ የነበረው ዓሣ አጥማጅ::

«አምናለሁ» አለ ልጁ::

ወደቡና ቤቱ በመሄድ ቡና አዘዘ::

«ትኩስ ይሁን:: ስኳርና ወተት ደሞ በደንብ ይግባበት::»

«ሌላስ?»

«ምንም አያስፈልግ::ሌላው በኋላ ይደርሣል:: ምን እንደሚያሻቸው ከጠየቅሁዋቸው በኋላ ይሻላል::»

«እንዴት ያለ ዓሣ ነበር ግን» አለ ባለቡና ቤቱ:: «እንዲህ ያለ ዓሣ ታይቶም አያቅ:: እናንተ ትናንት ያጠመዳችሁዋቸው ሁለቱም ጥሩ ጥሩ ዓሣዎች ነበሩ::»

«ገደል ይግቡ» አለና ልጁ እንደገና ማልቀስ ጀመረ::

«መጠጥ ነገር ትፈልጋለህ?»የቡና ቤቱ ባለቤት ጠየቀ።

«የለም» አለ ልጁ።«ይልቅ ሳንቲሞችን እንዳይረብሿቸው ለሰዎቹ ንገራቸው።እኔ ተመልሼ እመጣለሁ።»

«በጣም ደዟንኩ መሆኑን ንገርልኝ እባክህ።»

«አመሰግናለሁ» አለ ልጁ።

ትኩሱን ቡና በዕቃ ይዞ ወደ ሽማግሌው ጎጆ በረረ። እስኪነቁ ድረስ ባጠገባቸው ቁጭ ብሎ መጠባበቅ ጀመረ። አንድ ጊዜ እንደመንቃት አሉና ተመልሰው ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ወደቁ። ልጁም ቡናውን የሚያሞቅበት እንጨት ተበድሮ ለማምጣት ወደ ጐረቤት ወጣ።

በመጨረሻ ሽማግሌው ነቁ።

«ቁጭ እንዳይሉ» አለ ልጁ። «ቀና ብለው ይቺን ይቅመሱ።» ከቡናው ጥቂት በብርጭቆ ቀዳላቸው።

ሽማግሌው ተቀብለው በሙሉ ጠጡት።

«ድል አደረጉኝ ማኖሊን፤» አሉ። «በዕውነት አሸነፉኝ።»

«እሱ ግን አላሸነፈዎትም።ድል ያደረግዎት ዓሣው አይደለም።»

«በፍፁም። በጭራሽ። በኋላ ነው ጉድየሆንኩት።»

«ፔድሪኮ ጀልባዋንና መሣሪያዎቹን እንዲጠብቅ ነግሬዋለሁ። ጭንቅላቱ ምን እንዲደረግ ይፈልጋሉ?»

«ፔድራኮ ይቆራርጠውና ለዓሣ ማጥመጃ ይጠቀምበት::»

«መንቆሩንስ?»

«ከፈለግህ አንተ ውሰደው::»

«አልፈልገዋለሁ» አለ ልጁ:: «አሁን እንግዲህ ስለ ሌሎቹ ነገሮች ዕቅድ ማውጣት አለብን::»

«ለመሆኑ ፈለጉኝ?»

«እንዴታ:: ያውም ባይሮፕላኖቹና በጠረፍ ዘበኞች ጭምር ነዋ!»

«ውቅያኖሱ ግዙፍ ነው:: ጀልባዋ ደሞ እርምታህል ነገር ስለሆነች መች ትታያለች መሰለህ» አሉ ሽማግሌው::ከባህሩና ከራሳቸው ጋር ከማውራት ይልቅ ከሌላ ሰብአዊ ፍጡር ጋር መነጋገር ምን ያህል እንደ ማያስደስት ተገነዘቡ:: «በጣም ነው የናፈቅኸኝ» አሉ:: «ለመሆኑ ምንም አልቀናችሁ?»

«በመጀመሪያው ቀን አንድ:: በሁለተኛውም እንዲሁ:: በሦስተኛው ደሞ ሦስት::»

«መልካም ነው::»

«ከአሁን በኋላ እንደወትሮአችን በአንድነት ማጥመድ እንቀጥላለን»

«አይሆንም:: እኔ ዕድለ ቢስ ሰው ነኝ:: ከእንግዲህ በኋላም ዕድል አይኖረኝም::»

«ዕድል ጀሀነም ይግባ» አለ ልጁ:: «ዕድሉን እኔ ይገኘው አመጣለሁ::»

«ቤተሰቦችህስ፣ ምንም አይሉህ?»

«ምንም ቢሉ ጉዳዬ አይደለም:: ትናንት ሁለት አጥምጃለሁ:: ግን ከአሁን በኋላ ከርሶ ጋር ነው የማጠምደው:: ገና ብዙ የምማረው አለኝ::»

«ማለፊያ ሀርፑን ማዘጋጀት ይኖርብናል:: ከአሮጌዋ ፎርድ መኪና ባሌስትራ አንተው ራስህ ቀጥቅጠህ ልትሰራው ትችላለህ:: ከዚያ ጉዋናባኩአ ወስደን

እናስሞርደዋለን:: በጣም ስል መሆን አለበት:: በዚያ ላይ ልምጥ ልምጥ የሚል እንጂ ድርቅ ያለ መሆን የለበትም:: በነገርህ ላይ ጩቤዬን ተሠበረ::»

«ምንም አይደለም:: እኔ ሌላ ጩቤ አመጣለሁ:: ባሌስትራውንም አስሞርዳለሁ:: ሁሉንም እኔ አዘጋጃ ለሁ:: እስከዚያ እርሶ እጆችዎን ያስታሙ::»

«አይቦህ፣ እንዴት ልንከባከባቸው እንደሚገባ አው ቃለሁ:: ይገርምሀል ሌሊት ላይ ጣዕሙ ለየት ያለ አን ዳች ነገር ተፋሁ:: ደረቴ ውስጥ ደግሞ አንድ ነገር የተሰበረ መስሎ ተሰማኝ::»

«እሱንም ያስታሙት» አለ ልጁ:: «አሁን ትንሽ ጋደም ይበሉ:: እኔ ሄጄ የታጠበ ሸሚዝዎንና ትንሽ የሚቀምሱት ነገር ላምጣልዎት::»

«እዚህ ባልነበርኩባቸው ቀናት ከወጡት ጋዜጦ ችም ውስጥ ያገኘኸውን ይዘህልኝ ና»አሉ ሽማግሌው::

«ቶሎ መዳን አለብዎት:: ምክንያቱም ገና ከርሶ የምማረው ብዙ ነገር አለ:: ለእጆችዎ የሚሆን መድ ኃኒትም ከፋርማሲ አመጣልዎታለሁ::»

«ጭንቅላቱ የሱ መሆኑን ለፔድራኩ እንድት ነግረው:: እንዳትረሣ::»

«አልረሣም::»

ልጁ ከጐጆዋ ወጥቶ ወደተውለቀለቀው መንገድ ሲገባ እንደገና ማልቀሱን ጀመረ::

በዚያን ዕለት ከቀትር በኋላ ብዙ ቱሪስቶች ቡና ቤቱ ውስጥ ተሰብስበው ነበር:: ከመካከላቸው አንድ ሴት ቁልቁል ወደባህሩ አሽጋግራ ስትቃኝ ትልቅ የእከርካሬ አጥንት በተባለ ባዶ የቢራ ጣሣዎች መሀል ተጋድሞ አየች:: የባህሩ ውሀ በንፋስ አማካይነት ከፍ ዝቅ ባለ ቁጥር አብሮ የሚጫወት ግዙፍ ጭራ ጫፉ ላይ አለ::

«ምንድነው ያ?» እንዱን አሣላፊ ጠየቀችው፤ አሁን እንደማንኛውም ቆሻሻ ነገር ወደሆነው የትልቁ ዓሣ የጀርባ አጥንት እየጠቆመች::

«ቴቤሮን» ሲል መለሰላት የቡና ቤቱ* አሣላፊ:: «ሼሻርክ::» በሱ ቤት ስለሁኔታው መግለፁ ነበር::

«በዕውነቱ ሻርኮች እንደዚህ ያለ ውብ ጭራ ያላቸው አይመስለኝም ነበር» አለች::

«እኔም» አለ አብሯት የነበረው ወዳጅዋ::

እነርሱ ካሉበት ጥቂት ከፍ ብሎ ሽማግሌው ጐጆዋቸው ውስጥ እንደገና እንቅልፋቸውን መለጠጥ ጀምረው ነበር:: የአሁኑ አስተኛኘታቸውም ልክ እንደ በፊቱ በልባቸው ተደፍተው ነው:: ልጁ አጠገባቸው ቁጭ ብሎ ያስተውላቸዋል:: እሳቸው ደግሞ ስለ አንበሶች ህልም እያዩ ነበር::

---

*ቴቡሮን:- ሻርክ በስፓኝ ቋንቋ የሚጠራበት ስም ነው::

## ሄሚንግዌይ እና «ሽማግሌውና ባህሩ»

*ብቸኛ ሽማግሌ ናቸው፡፡ብቸኛ አሳ አጥማጅ ሽማግሌ፡፡*

«ሽማግሌውና ባህሩ» የሚለው የኧርነስት ሄሚንግዌይ መፅሀፍ የሚጀምረው በነዚህ ሁለት አረፍተ ነገሮች ነው፡፡ . . .

«ሽማግሌውና ባህሩ» ከአጭር ልቦለድ ከፍ፣ ከረ ጅም ልቦለድ ደግሞ አነስ ይላል፡፡ አጭር ረጅም ልቦለድ ነው፡፡

ይህ መፅሀፍ በዚህ በሀያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተ ፃፉት ጥቂት ውብና ድንቅ ልቦለዶች አንዱ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ስለመፅሀፉ ብዙ ተብሏል፣ አያሌ ሂሶችና ሂሳዊ ሀተታዎች ተፅፈዋል፡፡ ፊልም ተቀርጾም ተደንቋል፡፡ ዛሬ ሽማግሌውና ባህሩ ዘመን ሳይሸራቸው በይዘትም በቅር ፅም ተሟልተው፣የጥሩ ፅሑፍ ማንፀሪያ ሆነው ከሚገኙ ጥቂት ወጥ ስራዎች አንዱ እን ደሚሆን ይገመታል፡፡

ሄሚንግዌይ ታዋቂ ከሆኑት የአሜሪካ ደራሲያን አንዱ ነው፡፡ ረጅም ልቦለዶችን ፅፏል፡፡ በርካታ አጫ ጭር ልቦለዶችንም አበርክቷል፡፡ ኢልቦለድ የሆኑ ድርሰ ቶችም አሉት፡፡ "Across the River and into the Trees" የሚለውን ልቦለድ ድርሰቱን እስከፃፈበት ጊዜ ድረስም - ምንም እንኳ ሀያሲያን አንዳንድ ጉድለት ያጠጡለት እንደነበር ግልፅ ቢሆን- ሄሚንግዌይ በአንባቢዎቹ ዘንድ የተደነቀ- የተወደደ ደራሲ ነበር፡፡

"Across the Reiver ..."ን ፃፈ:: ታትሞ ወጣ:: ... ደከም ያለ ነበር:: እናም ሀያሲያን በሄሚንግዌይ ላይ ተነሱበት:: . . .

. . . አለቀለት አሉት:: ሄሚንግዌይ ነጠፈ ተባለ:: . . . "Across the River" በከተ:: ሄሚንግዌይ ምን አለ? ተስፋ ቆረጠ? . . .

*መጀመሪያ ምን እንደተሰማው አላውቅም:: ግን እንደተባለው አልሆነም:: አላለቀለትም፣ አልነጠፈም...*

ከሁለት አመት በኋላ፣ በኮሪያ የወታደራዊ አገል ግሎቱን በመወጣት ላይ ለነበረው ጀምስ ኤ. ሚችነር አንድ መልእክት ደረሰው:: ሚችነር ዛሬ ባልቆ፣ በስሙ እንደ«ሀዋይ»፣«ዘ ሶርስ» የመሳሰሉት መፃህፍት ደራሲ ነው::መልእክቱ ወደ ጀምስ ሚችነር የተላከው በጃፓን አገር ከሚገኘው የ«ላይፍ» መፅሄት ወኪል ቢሮ ነበር:: የ«ላይፍ» መፅሄት ዋና መስሪያ ቤት በኒውዮርክ የሚ ገኝ ሲሆን የጃፓኑ ወኪል ያመጣው መልእክትም ከዚህ ከዋናው መስሪያ ቤት ነበር::

የመልእክቱ ፍሬ ነገር ባጭሩ:-

የላይፍ መፅሄት በቅርቡ አንድ ከዚያ በፊት ያል ተለመደ ነገር ለመሞከር እቅድ እንዳለው ይገልፃል:: ይህ እቅድ ምን እንደሆነ ሲገልፅም - መልእክተኛው እንዲህ ይለዋል - (ለሚችነር)-

«በአመት ከምናወጣቸው በርካታ ቅጾች አንዱ ሙሉ በሙሉ አንድ ወጥ ስራ ይዞ እንዲወጣ ታቅ ዷል»

ሚችነር እዚያ ውስጥ እሱ የተፈለገበትን ምክን ያት ሲጠይቅ የመፅሄቱ የበላይ ሹማምንት ያን የሚወ ጣውን ስራ አንድ አዋቂ ሰው አንብቦ አስተያየቱን እን ዲሰጣቸው ወስነው፣ ሰውየውንም (ገምጋሚውን) እንደ

መረጡ - ይነገረዋል፡፡ ማለት የተመረጠው ገምጋሚ እራሱ ሚችነር - እንደሆነ ይሰማል፡፡

ሚችነር ተስማማ፡፡ በመፅሄቱ ላይ አንዱን ቅፅ ሙሉ በሙሉ አስፍቶ የሚይዘውን ጽሁፍ ቅጂ ሰጠው፣ መልክተኛው፡፡ ተቀበለ፡፡ ማንበብ ቀጠለ፡፡

«ጀመርኩት፡፡ ገና ስጀምረው ደነቀኝ፡፡ ከዚያ በኋላ ለማሰብም - ለማቆምም የማያመዛዝን አእምሮ አልነበ ረኝም» ይላል ጀምስ ሚችነር፡፡ አነበበው፡፡ አደነቀው፡፡ አድናቆቱንም ኒውዮርክ ለሚገኘው የ'ላይፍ' መፅሄት ዝግጅት ቢሮ ላከ - በፅሁፍ፡፡

ከጃፓኑ ወኪል ፅህፈት ቤት የተላከው ሰው ከኒውዮርክ ውጭ ያለች ኮፒ ይህች አንተ ዘንድ ያለችው ብቻ ናት ብሎት ነበርና - ሚችነር ሚስጥሩን አላወጣም፡፡

በሴፕቴምበር ወር 1952 መጀመሪያ ሳምንት ላይ የወጣው የ«ላይፍ» መፅሄት ሌላ ጽሁፍ ሳይደባልቅ፣ ያንን ሚችነር አድንቆ የገመገመውን ድርሰት ይዞ ወጣ፡፡ ይህ ድርሰት የኧርነስት ሄሚንግዌይ «ሽማግሌው ና ባህሩ» (The Old Man and The Sea) ነበር፡፡ ያንን ድርሰት ብቻ ይዞ የወጣው የ«ላይፍ» መጽሄት ልዩ እትም ከአምስት ሚሊዮን ኮፒ በላይ ተሸጠ፡፡ . . .

የ'ላይፍ'መጽሄት መልእክተኛ ከኒውዮርክ ውጭ ያለች ኮፒ ባንተ እጅ ያለችዋ ብቻ ነች፤ ይበል እንጂ በአሜሪካ በአውሮፓና በሌላም ክፍላተ አለም ለሚገኙ መልካም ዳኝነት ይሰጣሉ ለተባሉ ሌሎች ስድስት መቶ ሰዎች ያቺ ኮፒ ደርሳ እንደነበር ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ለጀምስ ሚችነር ተነግሮታል፡፡

ወድያው የሄሚንግዌይ ወዳጅና መፃህፍቱን ያሳት ምለት የነበረው ቻርልስ ስክሪብነር ታሪኩ በመፅሐፍ

ታትሞ እንዲወጣ አደረገ። «ሽማግሌውና ባህሩ»ን ያነበበ ሁሉ አደነቀው።

ሄሚንግዌይ እንሰራሬ። . . .

በዛሬ ዘመንና መፅሀፉ እንደታተመ ጊዜም «ሽማግሌውና ባህሩ» የሄሚንግዌይ የራሱ ታሪክ ነው፤ ማለትም ሽማግሌው ዓሣ አጥማጅ ሄሚንግዌይ ራሱ ነው፤አሳው ድርሰቱ ነው፤ ከአሳው ጋር ያለው ትግል ድርሰቱን ለማፍለቅ ያደረገው ጥረት ነው፤ አሳውን ያዘው፤ ትልቅ አሳ ነበር፤ይህም መጽሀፉ ትልቅ እንደ ነበር ያሳያል፤ ሻርኮች በሚጨቁት፤ ሻርኮቹ ሀያስያኑ ናቸው፤ ስለዚህም ወደሰው የደረሰው አጽሙ ወይም ሀያስያኑ ገነጣጥለው ባዶ ያደረጉት ነው፤- ያሉ ተንታኞች ነበሩ። ይህም ብቻ ሳይሆን ለሄሚንግዌይ «ሽማግሌውና ባህሩ» ብዙ ፍች ተሰጥቶታል። ይህ መፅሀፍ በብዙ መንገድ ተተርጉሟል። የቱ ነው ልክ? ይህን እኔ አላውቅም።. . .

. . . ለእኔ የሚሰማኝ «ሽማግሌውና ባህሩ» ትልቅ ስራ መሆኑ ነው።እኔ የሚሰማኝ- «ሽማግሌውና ባህሩ» በጠባቡ ቢተረጉም፤ማለትም የደራሲና የጨካኝ ሀያሲ ታሪክ ብቻ ሆኖ ቢወሰን፣ ዋጋው ዝቅ ይልብኛል። የሌላም ቢሆን ከጠበበ ያው ነው። ዋጋው ይቀንሳል።

. . . «ሽማግሌውና ባህሩ» የሰው ልጆች አጠቃላይ ታሪክ ነው።የ«ብላዕ በሀፊ ገዕክ» ርግማን በግልፅ የሚታይበት ታላቅ ድርሰት ነው። ... ለኔ የሚሰማኝ ይኸ ነው። ለኔ የሚታየኝ ይህን ያህል ሰፍቶ ነው።

ባሴ ሀብቱ
ነሀሴ፤ 1982
አዲስ አበባ

105193 107 /2000
የዞን 4 ሕዝብ ቤተ መጻሕፍት
Zone 4 Public Library

“ሽማግሌውና ባህሩ” በብዕር ሀገሩ በመሬቱት አብጆዷ ላይ በሚንቀሳቀሱ የሚያሳዩት ፊልም ያሙም ዶማ ታላቅ ቀንደኛ ጠብር ባለው ሁኔታ ፊስጡበት ፊልም ይመስላል።

ኧርነስት ሄሚንግዌይ ታላቅ ዋጋ ያለው ደራሲ ነው። ቅላት ሲቀጥብ አያጣል አዚህ ላይ ሞገሩን አለማየሁ ጠ ቢሞልስ የሄሚንግዌይን መንገድ በሚገባ ተከ ተርጉሞ የስችሏል

ባሉ ፀብቱ

ሜጋ ማሳተሚያ ድርጅት

ዋጋ ብር 11.50